ነፃነትና
እኩልነት
ፓርቲ

የምርጫ ማኒፌስቶ

6ኛው ጠቅላላ ምርጫ

ብዕርነ ፀምረሽ

‹‹እኩልነት በተግባር!››

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

"እኩልነት በተግባር"

ብዕርን ይምረጡ!

የካቲት 2013
አዲስ አበባ

ማውጫ

የሊቀ-መንበሩ መልዕክት 6

ክፍል አንድ
አጠቃላይ 8

1. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፡ ራዕይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች 9
2. የእቅዱ ማጠንጠኛ፡ ትምህርት ተኮር የልማት ስትራቴጂ 10
3. ዓለም ዓቀፍ ዳራ 11
4. የልማት ፍልስፍናችን፡- “የሀገር ልማት የዜጎች ነጻነት ነው” 11
5. ሀገራዊ መራር ሀቆች: የሁኔታዎች ትንታኔ 12
5.1. ያልተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር 12
5.2. ግጭት፣ መፈናቀል፣ ስደት እና ሞት በኢትዮጵያ 13
5.3. የድህነት አዙሪት 15
5.4. የኑሮ ውድነት 16
5.5. ስራ አጥነት 18
5.6. ብልሹ የመንግስት አሰራር፣ ደካማ ቢሮክራሲ እና የፍትህ እጦት 18

ክፍል ሁለት
የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ
የአምስት አመት የትኩረት አቅጣጫ 20

ምዕራፍ አንድ፡ ሥነ-መንግስት 21
1. አካታች ብሄረ መንግስት መገንባት 21
2. ህገ-መንግስት ማሻሻያ 22
3. ብሄራዊ እርቅ እና መግባባት 24
4. የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት 25
5. እውነተኛ ፌዴራሊዝም 27
6. ፓርቲ እና መንግስትን መለየት 30
7. የዜጎች ሰብአዊ መብት 30
8. የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ 31
9.መልካም አስተዳደር 34
10.ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ 35
11. የህግ የበላይነት 38
12. የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች 39
13. ብዙሀን መገናኛ (ሚዲያ) 40
14. የአዲስ አበባ ጉዳይ 42
15. የውጭ ግንኙነት እና ሀገራዊ ደህንነት 45
ምዕራፍ ሁለት፡ ጠንካራ እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ 47
1. አካታች የኢኮኖሚ እድገት እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል 47
2. የመሬት አስተዳደር 48
3. ግብርና፣ ገጠር ልማት እና የምግብ ዋስትና 52
4. አርብቶ አደር ልማት፡ የተረሱ ዜጎች 53
5. ቱሪዝም እና ቅርስ ጥበቃ 55
6. ማክሮ ኢኮኖሚ 56
7. የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲ 57
8. የፋይናንስ ተቋማት 57
9. ኢንደስትሪ 59
10. ንግድና ኢንቨስትመንት 61
11. ዲጂታል ኢኮኖሚ 62
12. ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር 66

ምዕራፍ ሶስት፡ መሰረተ ልማት 68
1. መንገድ 68
2. ትራንስፖርት 70
3. የማዕድን ሀብት ልማት 71
4. የኢነርጂ ሀብት ልማትና አጠቃቀም 73
ምዕራፍ አራት፡ ጤናማ እና ደስተኛ ማህበረሰብ 76
1. ትምህርት 76
2. ጤና 77
3. የአካል ጉዳተኞች፡ እኩልነትና አካታችነት 79
4. የውሀ ሀብት ልማት 81
5. ለመኖሪያ እና ለስራ ምቹ አካባቢ፡ ቤቶች እና ከተማ ልማት 83

ክፍል ሶስት 85
ጠቅላላ ጉዳዮች (CROSS CUTTING ISSUES)
1. አካባቢ ጥበቃ 86
2. ስርአተ-ጾታ 87

ክፍል አራት 90
የአቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶች እና መለኪያዎች
1 የማስፈጸሚያ ስልቶች እና መሳሪያዎች 91
2 የስኬት መለኪያዎች 92

አብዱልቃድር አደም (ዶ/ር)
ሊቀ-መንበር

የሊቀ - መንበሩ መልዕክት

ውድ ኢትዮጵያውያን፣
ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ፈታኝ እና አስጨናቂ በሆነ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በማለፍ ላይ ትገኛለች። ያልተቋጨው የሀገር ግንባታ ፕሮጀክት የወለዳቸው ታላላቅ ተቃርኖዎች፣ ለግማሽ ምዕተ-አመት በሀገራችን የናኘው የግራ ፖለቲካ፣ በስርአት ያልተመራው የሪፎርም ሂደት ስር ከሰደደው ድህነት ጋር ተደርቦ የህዝባችንን ህይወት በሰቆቃ እና በስጋት የተሞላ አድርጎታል።

ሀገራችን በዘርፈ ብዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ችግሮች ውስጥ ተዘፍቃ በርካታ ዘመን አልፏል። የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጨፍለቅ፣ ሙስና እና አድልዎ፣ የፍትህ መዛባት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች መጓደል፣ ሥራ-አጥነት፣ የግጭቶች መበራከት፣ የሰላምና መረጋጋት መጥፋት የሀገራችን መለያ ምልክቶች ሆነዋል። በታሪክ የወረስናቸው ዜጎችን "አንደኛ እና ሁለተኛ" አድርገው የከፈሉ ግልጽ እና ስውር መንግስታዊ አሰራሮች እና ልማዶች ነጻነት፣ እኩልነት እና ፍትህ የሰፈነበት የመንግስት ስርአት የመመስረት ሀገራዊ ትልማችን እውን እንዳይሆን እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል።
ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የእለት ጉርስ የአመት ልብስ ማግኘት የቀን ህልም ነው። የንጹህ የመጠጥ ውሀ፣ ዳቦ፣ መብራት እና ትራንስፖርት የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች ለአብዛኛው የሀገራችን ህዝብ እንደ ሰማይ የራቁ ናቸው። ህዝባችን ይህ ሳያንሰው ከቤት በሰላም ወጥቶ መመለስ እጅግ አሳሳቢ ሆኖበታል። በሀገራችን ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ሆኖ የቆየ ሲሆን፣ ሰፊው የማህበረሰብ ክፍል ሀሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብቱ ተገፎ በርካታ ትውልድ አልፏል።

መላ የሀገራችን ህዝቦች ሰላም እና መረጋጋትን የሚያረጋግጥ የፖለቲካ ስርአት፣ የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚያስከብር ህገ-መንግስታዊ ዋስትና፣ ከአስከፊ ድህነት እና የኑሮ ውድነት የሚያላቅቅ፣ ለዜጎች በተለይም ለወጣቶች በቂ የስራ እድል የሚያስገኝ የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ ዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን በተግባር የሚያረጋግጥ ጠንካራ እና እውነተኛ የፌደራል ስርአት፣ ከጎረቤት ሀገራት እና ከመላው የዓለም ህዝቦች ጋር ሰላም እና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ይሻሉ። ዘርፈ ብዙ ታሪካዊ እና ወቅታዊ ችግሮቻችንን አስወግደን ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ልማት ለማረጋገጥ እና ህብረ-ብሄራዊ አንድነታችንን ለማጠናከር በህዝብ የተመረጠ፣ ህዝብን የሚያገለግል እና ለህዝብ ተጠያቂ የሆነ መንግስት ያስፈልጋል።

የተከበራችሁ የሀገሬ ህዝቦች!!
በሀገራችን ታሪክ ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ ተካሂዶ አያውቅም - በፍጹም። ባለፉት 25 አመታት የተካሄዱት ምርጫዎች ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው። የምርጫ ሂደት እና ውጤት ኢዴሞክራሲያዊ የነበሩ፣ የዜጎችን ነጻነት እና የስልጣን ባለቤትነት በግልጽ የካዱና ያዋረዱ፣ አማራጭ ሀሳቦች እንዳይሰሙ የታፈኑበት፣ በግጭት የተሞሉና በርካታ ንጹሀን ዜጎችን ለሞት እና ለአካል ጉዳት የዳረጉ ነበሩ። ጠንካራ እና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳይፈጠሩ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ መሰናክሎችን በመፍጠር እውነተኛ የመድብለ-ፓርቲ ስርአት እንዳይፈጠር ተደርጓል። በሀገራችን የተካሄዱ ምርጫዎች በሙሉ አንድ ፓርቲ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ የሚያሸንፍበት፣ ከውጭ ኃይላት ድጋፍ ለማግኘት ሲባል የሚካሄድ ትርኢት ነበር። 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ የሚካሄደው በዚህ መራር ታሪካዊ ሀቅ ውስጥ ሆነን ነው።

የመምረጥ እና መመረጥ መብት ከዴሞክራሲያዊ መብቶች አንዱ እና ዋነኛው ነው። ቀደምት ኢትዮጵያውያን ይህንን መብት ለማግኘት ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል። ከህዝባችን የዴሞክራሲ ፍላጎት በተቃራኒ የቆሙ ገዥ መደቦች ዜጎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብታቸውን በነጻነት እንዳይጠቀሙ ሰፊ የአፈና መዋቅር አደራጅተው መብቱን ነፍገውት ቆይተዋል። ባለፉት በርካታ አስርት ዓመታት መላ የሀገራችን ህዝቦች የብሄር፣ የኃይማኖት እና የፖለቲካ ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው በጋራ በከፈሉት ከባድ መስዋእትነት ብልጭ ያለው የለውጥ ብርሀን ዘላቂ ይሆን ዘንድ በህዝብ ይሁንታ ያገኘ መንግስት ሀገርን ሊያስተዳድር ይገባል።
ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ‹‹6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው።›› ብለን እናምናለን። በመሆኑም መላው የሀገራችን ህዝቦች በዚህ ታሪካዊ ምርጫ በንቃት በመሳተፍ በሀገራችን የነጻነት፣ የእኩልነት እና የፍትህ ዘመን እውን ይሆን ዘንድ የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል።

ደካማ እና አሳፋሪ የምርጫ ታሪካችን በምርጫ ላይ ያለን እምነት እጅጉን እንዲሸረሸር አድርጎታል። ይህ ስሜት ሀገራችን ውስጥ ያለው አሳሳቢ የሰላም እና መረጋጋት ስጋት ታክሎበት 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ "ነጻ፣ ፍትሀዊ እና ሰላማዊ" ላይሆን ይችላል የሚል ስጋት በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ እንዲፈጠር አድርጓል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይህ ስጋት ምክንያታዊ እንደሆነ ይረዳል።
ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ‹‹ታሪካዊም ሆኑ ወቅታዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት ከሚረዱ የፖለቲካ መሳሪያዎች አንዱ ምርጫ ነው።›› ብሎ በጽኑ ያምናል። ምርጫ ዜጎች ሉአላዊ የስልጣን ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት፣ የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብ የሚመነጭ መሆኑ በተግባር የሚረጋገጥበት ስርአት ነው። በመሆኑም ይህን የዜግነት መብት አስቸጋሪ በሆነ የፖለቲካ አውድ ውስጥ በሚካሄደው 6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ልንጠቀምበት የሚገባ እና በፍጹም ልናሳልፈው የማይገባ የዜግነት መብት መሆኑን ህዝባችን እንዲገነዘብ እንወዳለን።

ክቡራት እና ክቡራን
6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ካለፉት ስህተቶች የጸዳ እንዲሆን ከምርጫ በፊት፣ በምርጫ ወቅት እና ድህረ-ምርጫ ነጻ፣ ፍትሀዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን መላ የሀገራችን ህዝቦች በምርጫው ሂደት በንቃት በመሳተፍ የዜግነት ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሰላማዊ፣ ሂደቱ እና ውጤቱ በመራጩ ህዝብ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች እና በታዛቢዎች ተቀባይነት ያለው እንዲሆን አቅሙ የሚፈቅደለትን ሁሉ ያደርጋል። መላው የፓርቲያችን አባላት እና ደጋፊዎች የፓርቲያችንን የምርጫ ስነ-ምግባር ደንብ እና አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች ጠብቀን ለምርጫው ሰላማዊነት የበኩላችንን አስተዋጾ እንድናበረክት አደራዬ ከፍ ያለ ነው።
ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ለመሳተፍ ይህን የምርጫ ማኒፌስቶ ሲያዘጋጅ ብሄራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሰነዶችን፣ ግቦችን እና ስትራቴጂዎችን በሚገባ ለመከለስ ሞክሯል። በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት አመታት የሀገራችን ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጡ ግቦች ጋር የተናበበ እንዲሆን ተደርጓል። የአፍሪካ እና ዓለም አቀፍ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ የለውጥ እመርታ ታሳቢ የተደረገ ሲሆን ከፍተኛ፣ የተረጋጋ እና አካታች የኢኮኖሚ እድገት እውን ማድረግን ያለመ ነው።

የሰው ኃይል/ኃብት ልማት፣ አህጉራዊ ተወዳዳሪነት፣ ፈጣን የመረጃና የተግባቦት ቴክኖሎጂ እድገት፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከግንዛቤ ውስጥ ገብተዋል። የመንግስት እና የግል ባለሀብቶች የተቀናጀ ተሳትፎ ይበልጥ በማጠናከር መዋቅራዊ ለውጥ ማረጋገጥ እና ከፍ ወዳለ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ የእድገት ደረጃ ሽግግር ማካሄድ፣ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ የሀገራችንን ሰላም እና መረጋጋት ማስጠበቅ፣ የዜጎችን ሞት እና መፈናቀል ማስቆም የማኔፌስቶው ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው።

በውጭ ግንኙነታችን ኢትዮጵያ በአካባቢ እና አህጉራዊ ጉዳዮች ያላትን ቦታ እና ተሰሚነት ከፍ ማድረግ፣ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ደህነነት፣ ከጎረቤት ሀገሮች እንዲሁም ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ህዝቦች እና መንግስታት ጋር በሰላም እና በጋራ ጥቅሞች ላይ በትብብር መስራት የማኒፌስቶው ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫዎች ተደርገው ተወስደዋል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ምርጫ አሸንፎ ሀገር የማስተዳደር ኃላፊነት ከተረከበ ማኒፌስቶውን ለመፈጸም የሚረዱ ዓመታዊ እቅዶች እና ዝርዝር የአፈጻጸም ስትራቴጂዎች የሚዘጋጁ ሲሆን ጠንካራ የቁጥጥር እና ክትትል ስርአት ይዘረጋል።

በመጨረሻም፣
ይህ ማኒፌስቶ ሲዘጋጅ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ኤክስፐርቶች ተካፍለዋል። በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በአለም-ዓቀፍ ተቋማት፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና በግል አማካሪነት በመስራት ላይ የሚገኙት እኚህ ኤክስፐርቶች በየሙያ ዘርፋቸው ለማኒፌስቶው ዝግጅት መነሻ ጥናታዊ ጽሁፎችን አቅርበዋል። በመላው የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አመራር እና አባላት ስም ላደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

ነጻነት፣ እኩልነት እና ፍትህ በተግባር እንዲረጋገጥ፣ በታማኝነት እና በእውነተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት መላውን የሀገራችን ህዝቦች ለማገልገል ግንቦት 28፣ 2013 የዜጎችን ይሁንታ ለማግኘት ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ተዘጋጅቷል። መላው የሀገራችን ህዝቦች ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ን በመምረጥ ታሪካዊ የዜግነት ግዴታችሁን ትወጡ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

"እኩልነት በተግባር"

ክፍል አንድ
አጠቃላይ

ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ

ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ	7
1. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፡ ራዕይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች	9
2. የእቅዱ ማጠንጠኛ፡ ትምህርት ተኮር የልማት ስትራቴጂ	10
3. ዓለም ዓቀፍ ዳራ	11
4. የልማት ፍልስፍናችን፡- “የሀገር ልማት የዜጎች ነጻነት ነው”	11
5. ሀገራዊ መራር ሀቆች: የሁኔታዎች ትንታኔ	12
5.1. ያልተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር	12
5.2. ግጭት፣ መፈናቀል፣ ስደት እና ሞት በኢትዮጵያ	13
5.3. የድህነት አዙሪት	15
5.4. የኑሮ ውድነት	16
5.5. ስራ አጥነት	18
5.6. ብልሹ የመንግስት አሰራር፣ ደካማ ቢሮክራሲ እና የፍትህ እጦት	18

1. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፡ ራዕይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች

ራዕይ

አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት የተረጋገጠባት፣ ዜጎች የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተ ልዩነት ሳይደረግባቸው በብሄራዊ ጉዳዮች እኩል የሚሳተፉባትና ከልማቷ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑባት የበለጸገችና ዲሞክራሲያዊት ሀገር እውን ሆና ማየት።

ተልእኮ

መልካም አስተዳደር እና የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት፣ የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብና ከህዝብ ብቻ የሚመነጭበት የፖለቲካ ባህል የዳበረበት፣ ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሚጠቀሙበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት።

ዓላማዎች

የፓርቲያችን ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

1. አካታች እና ዘላቂ ኢኮኖሚ በመገንባት ድህነትን መቀነስ ብሎም ማጥፋት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትህን ማስፈን፣
2. በሀገሪቱ የመንግስት አስተዳደርና መዋቅሮች ውስጥ የመልካም አስተዳደር፣ የግልጸኝነትና ተጠያቂነት ስርአት እንዲጎለብት ማድረግ፣
3. የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፤ የህግ የበላይነትን እውን ማድረግና ነጻ የፍትህ ስርዓት መገንባት፣
4. የብሄሮችና ብሄረሰቦችን ቋንቋና ባህል በእኩልነት ለማበልጸግ፣ ሁሉንም የሀገራችንን ክልሎች ልማት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ የሚያስችል እውነተኛ የፌደራል ስርአት መገንባት፣
5. አካባቢ መጠበቅ፣ መንከባከብና ማበልጸግ፤ ምቹ የስራ እና የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር፣
6. ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማስፋፋት፤ በተፈጥሮና ማህበረሰብ ሳይንስ መስኮች ጥናትና ምርምርን መደገፍ፣
7. የገጠር ኢንዱስትሪን ማበረታታትና ማስፋፋት፤ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚውን ማዘመን፣
6. ዜጎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ፣
6. ሴቶችና ወጣቶች በሀገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ እምቅ ኃይላቸውን መጠቀም፣
6. ህጻናት፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን መብቶችና ጥቅሞች ማስከበር፣
6. በአፍሪካ ቀንድ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስርን ማበረታታትና መደገፍ፤ በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አስተዋፅዖ ማድረግ፣
6. ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች ተሰሚነትና የማይተካ ሚና እንዲኖራት ማስቻል፤ የኢትዮጵያን የውጭ ገጽታ ማሻሻል።

የትግል ስልቶች

በመግባባት ላይ የተመሰረተ ከፍጥጫ፣ ከሴራና መጠላለፍ የራቀ የፖለቲካ ትግል፡- ፓርቲያችን ከማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ወይም ድርጅት ጋር በኃላፊነትና በሀገር ፍቅር ስሜት ይሰራል። ሀገራችንን እና ህዝባችንን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ ማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ወይም ፕሮግራም ካለው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በትብብር ይሰራል።

ሚዛናዊነት እና አካታችነት፡ የህዝባችንን የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ብዝሃነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በድርጅታዊ አሰራር፣ በፖሊሲና ፕሮግራም፣ በፖለቲካዊ አቋም፣ ወዘተ ሚዛናዊ እና አካታች መንገድን እንከተላለን። የግለሰብ ወይም የቡድን መብትና ስሜትን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶች በመራቅ ፓርቲያችን ሁሉንም የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እንዲያካትት ጥረት እናደርጋለን።

ተፈጥሯዊ ለውጥ፡ በሀገራችን ያሉት የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቢያንስ ላለፉት በርካታ አስርት-ዓመታት ሲጠራቀሙና ሲደራረቡ የቆዩ በመሆናቸው በአንድ ጀንበር እንደማይቀረፉ ፓርቲያችን

ይገነዘባል። በመሆኑም በሀገር ደረጃ እንዲመጡ የሚፈለጉ ለውጦች እውን እንዲሆኑ የማህበረሰቡን የእድገት ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ለመቀየር እንሰራለን።

አብሮ ማሸነፍ፡ እውነተኛ ማሸነፍ የሀገር እና የህዝብ ማሸነፍ መሆኑን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይረዳል። በመሆኑም በፖለቲካ እንቅስቃሴያችን ከድርጅታዊ ድል እና ስኬት ይልቅ የሀገርንና የህዝባችንን ድልና ስኬት እናስቀድማለን። በተመሳሳይ ሁኔታ የፓርቲያችን ውጤታማነትና ስኬት በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ውድቀት ላይ ሳይሆን አብሮ በማደግ እውነተኛ የአጋርነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

ህዝብን ማገልገል፡ የአንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴና የፖለቲካ ስልጣን ትልቁና የመጨረሻ ግብ ሀገርንና ህዝብን ማገልገል ነው። ህዝብን እንዲያስተዳድሩ የሚወከሉ የፓርቲና የመንግስት ኃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎችና ቢሮክራቶች ከድሀው ህዝብ "ከእጅ ወደ አፍ" ገቢ ከሚሰበሰብ ግብር የሚከፈላቸው ናቸው።በመሆኑም በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ የሚገኙ የፓርቲያችን አባላት የህዝብ አገልጋይ ሆነው የመስራት ግዴታ ይኖርባቸዋል።

እውነተኛነት እና ታማኝነት፡ ኢትዮጵያውያን ለመልካም ስነ-ምግባር እና ግብረገብነት ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን። ህዝባችን በማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለእውነተኛነት፣ ቅንነት እና ታማኝነት ላቅ ያለ ክብር ይሰጣል። በመሆኑም የፓርቲያችን ተርታው አባልም ሆኑ አመራሮች ሀገራችንና ህዝባችንን በእውነተኛነት፣ በታማኝነት እና በፍቅር ያገለግላሉ።

በትብብር መስራት፡ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የዴሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባት፣ ሀገራዊ መግባባትን ለማጠናከር፣ ጤናማ የፖለቲካ ውድድርን እውን ለማድረግ፣ የሀገራችንን የፖለቲካ ፓርቲዎች አቅም ለመገንባት ብሎም የፓርቲያችንን ራዕይና ዓላማዎች በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት የሚያግዝ ሆኖ ሲገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተመዘገቡ እና እውቅና ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመቀናጀት ይሰራል። ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጠሩ የትብብር መድረኮችና ቅንጅቶች የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች መሰረት ያደረጉ ይሆናል።

2. የእቅዱ ማጠንጠኛ፡ ትምህርት ተኮር የልማት ስትራቴጂ

ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ እድገት መሰረቱ ትምህርት ነው። ትምህርት በሰዎች ላይ የሚፈጥረውን ሁለንተናዊ ተጽእኖ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ስብእና መቅረጽ ሲሆን ሁለተኛው ምርታማነትን ማሳደግ እና ዜጎች በተሰማሩበት የህይወት እና የስራ መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ጥራት ያለው ትምህርት ያገኘ ትውልድ በአንድ በኩል የተሟላ ስብእና፣ ሚዛናዊ አመለካከት፣ ሰብአዊነት… ወዘተ ባህሪያትን የተላበሰ ሲሆን በሌላ በኩል ተመራማሪ፣ የፈጠራ ባለቤት እና አምራች፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የመፍታት አቅሙ ከፍተኛ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ ትምህርት የሰዎችን አስተሳሰብ በመቅረጽ እና ክህሎታቸውን በማሳደግ የተሟላ ስብእና ያጎናጽፋቸዋል። ትምህርት ሰዎች በግል ህይወታቸው እንዲያውቁ፣ እንዲሰሩ እና የህይወት ግባቸውን ማሳካት እንዲችሉ የሚያግዛቸው ሲሆን፣ በማህበራዊ ህይወታቸው ሰላምን እና ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብርን እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል። ትምህርት የለውጥ፣ የነጻነት፣ የእኩልነት፣ የእድገት ቁልፍ ነው።

የሀገራችን ኢትዮጵያ ልማት ከምንም በላይ ሰብአዊ ሀብቷን ከማልማት ጋር የተቆራኘ ነው። ከሀብቶች ሁሉ ሀብት የሰው ሀብት (Human Capital) ነው። ሀገራችን ያሉባትን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት ዋናው እና አስተማማኝ መሳሪያ ትምህርት ነው። ሀገራችን ህልውናዋን ከሚፈታተኗት የግጭት እና የድህነት አዙሪት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመውጣት ልዩነትን የሚያከብር፣ ድህነትን የሚጸየፍ፣ ጠያቂ እና ተመራማሪ ዜጋ ልትፈጥር ይገባል። የትምህርትንና የሰው ሀብት ልማትን ምንነት በውል የተገነዘበው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የለውጥ እንቅስቃሴዎቹ ምህዋር የሰው ሀብት ልማት እንዲሆን ገና ከጥዋቱ ወስኗል። ይህ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የለውጥ መስመር ከንድፈ ሀሳባዊ ትክክለኛነቱ በተጨማሪ አለም አቀፍ ተሞክሮን በስፋት እና በጥልቀት ያገናዘበ የልማት ማእቀፍ ነው። ዛሬ ላይ በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መስኮች ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ከደረሱ ሀገሮች ጀርባ ያለው ሚስጥር ሀገራቱ ከምንም በላይ ለሰው ኃይል ልማት፣ ለእውቀት፣ ለጥናትና ለምርምር የሰጡት ከፍተኛ ቦታ ነው። አስተማማኝ እና ዘላቂ የለውጥ ጉዞ የሰዎችን አስተሳሰብ እና አመለካከት በመለወጥ ይጀምራል።

በመሆኑም ፓርቲው ነጻነት እና እኩልነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የቀረጸው ይህ የምርጫ ማኒፌስቶ እና ለማኒፌስቶው መነሻ የሆኑት የፓርቲው ሰነዶች (የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፕሮግራም እና ፖሊሲዎች) የለውጥ ጉዞው ማጠንጠኛ ትምህርት እንዲሆን ወስኗል።

3. ዓለም ዓቀፍ ዳራ

የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም እና ጎራ ከወደቀበት የ1980ቹ አጋማሽ በኃላ ቀደም ሲል ባለ ሁለት ዋልታ የነበረው ዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን በፍጥነት ተቀይሮ በአሁኑ ወቅት በዓለም ፖለቲካ፣ ዲፕሎማሲ፣ ኢኮኖሚ፣ ቴክኖሎጂ፣ ጸጥታ ወዘተ ላይ ተጽእኖ ፈጣሪ ሀገራት ተበራክተዋል። ይህ የዓለም የመሪነት ለውጥ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች ያስገኘ ቢሆንም ከፍተኛ ስጋቶችንም ፈጥሯል። በዚህ ዓለም አቀፍ የለውጥ ሂደት ውስጥ የአፍሪካ ድርሻ እየጨመረ መጥቷል። የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ነድፈው የተንቀሳቀሱ ሀገራት አደጋውን ለመቀነስ እና ጥቅማቸውን ለማሳደግ ችለዋል።

በፈጣን ሁኔታ የሚለዋወጠው ዓለም አቀፍ አውድ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ እንድምታ አለው። ወሳኝ ከሚባሉ ዓለም አቀፍ የለውጥ ሂደቶች መካከል የሚከተሉትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፤

- ባለብዙ ዋልታ የዓለም ፖለቲካ፣
- የኢኮኖሚ ዋልታ ከምእራቡ ዓለም ወደ ምስራቅ ማዘንበል፣
- ፈጣን የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እድገት እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት መጨመር፣
- አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፍ የንግድ እና የኢኮኖሚ ትስስር፣
- ዓለም ዓቀፍ ብሄርተኝነት እና ህዝበኝነት ፖለቲካ መንሰራፋት፣
- ፈጣን የስነ-ህዝብ ለውጥ/እድገት፣
- የከተሞች በፍጥነት ማደግና መስፋፋት፣
- የአካባቢ መጎሳቆል እና ብክለት...

እነዚህ ዓለም አቀፍ አጀንዳዎች ኢትዮጵያን ጨምሮ የበርካታ ታዳጊ ሀገሮችን እጣ ፋንታ ይወስናሉ። በመሆኑም በሀገራችን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም የጊዜ ቀመር በምጣኔ ሀብት እና በማህበራዊ እድገት ማስመዝገብ የምንፈልገው እድገት በውስጣዊ ጉዳዮቻችን ብቻ ሳይሆን በአካባቢ እና ዓለም አቀፋዊ ለውጦች ይወሰናል። በመረጃ እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እድገት የሚመራው የለውጥ ሂደት በሀገራት፣ በህብረተሰብ እና በግለሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀየር አድርጓል። በየግዜው እያደገ የመጣው የሉላዊነት አስተሳሰብ የዓለም ዓቀፍ ንግድ ይበልጥ እንዲስፋፋ የሸቀጥና የአገልግሎት ግብይት እንዲያድግ አስችሏል።

በአፍሪካ ህብረት የበላይ ጠባቂነት በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠናና የተሟላ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስር ለመፍጠር የሚካሄደው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል። የመንግስት አወቃቀርና አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና የብዙሀን መገናኛ ሚና፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አረዳድና አተገባበር በፖለቲካው መስክ ከታዩ አበይት የለውጥ ማሳያዎች ናቸው። በአሜሪካ እና አውሮፓ እያቆጠቆጠ የመጣው ብሄርተኝነት ጽንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች የመንግስት ስልጣን እንዲይዙ አስችሏል። ይህም ዓለም አቀፍ ግንኙነትን በማሻከር እና የአለም አቀፍ ተቋማትን ሚና እና ትብብር እንዲያቀለቁል ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይህን የምርጫ ማኒፌስቶ ሲያዘጋጅ፣ ግቦችን ሲያስቀምጥ እና የሁኔታዎችን ትንታኔ ሲያደርግ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በጥልቀት እና በስፋት በመዳሰስ ነው።

4 የልማት ፍልስፍናችን፡- "የሀገር ልማት የዜጎች ነጻነት ነው"

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ለልማት እና እድገት ያለው እይታ **"ሰዋዊ"** ነው። የኢኮኖሚም ሆነ የማህበራዊ ልማት የመጨረሻ ግብ የዜጎችን ነጻነት ማረጋገጥ፣ ሰላማዊ እና ደስተኛ ኑሮ እንዲኖሩ ማስቻል ነው። **"ሰዋዊ"** ልማት ቁሳዊ እና የስነ-ልቦና መገለጫዎች አሉት። ጠቅላላ ብሄራዊ ምርትን (GDP) አመታዊ ጭማሪ ከፍ ባለ አሀዝ ማሳደግ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በቂ ግን አይደለም። የመሰረተ ልማት መስፋፋት ለልማት ግብአትም ውጤትም ተደርጎ

ሊወሰድ ይችላል። ሆኖም እኒህ ለውጦች የዜጎችን ሁለንተናዊ እና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ካልቻሉ እውነተኛ ልማት ሊሆኑ አይችሉም።

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የልማት ፍልስፍና የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ሳይሸራረፉ መከበር፣ በነጻነት ማሰብ፣ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ (መጻፍ እና መናገር)፣ ዜጎች ወደ ፈለጉት አካባቢ በነጻ መንቀሳቀስ፣ በመረጡት የስራ መስክ መሰማራት፣ የሁሉም ዜጎች እኩልነት፣ እድል እና ከሀገር ልማት በፍትሀዊነት የመጠቀም መብት እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው። የሙብቶች አንዱ መገለጫ የሆነው የመልማት መብት (Right to development) በሁሉም የሀገራችን ክልሎች በፍትሀዊነት እንዲተገበር እና ዜጎች ከሀገራችን ሀብቶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የልማት ፍልስፍናችን አካል ነው።

የልማት ፍልስፍናችን ሌላው ማዕዘን ብሄራዊ ልማታችን ከውጭ እርዳታ እና ብድር ተላቆ በሂደት በዋናነት በራስ አቅም እንዲሸፈን ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዘመናት የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ከውጭ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሚገኝ ድጋፍ ስታካሂድ ቆይታለች። ይህ ሁኔታ ሀገራችንን የውጭ ሀይላት ጥገኛ እንድትሆን እና አንዳንዴም ሉአላዊነታችንን ለሚፈታተኑ ጫናዎች አጋልጦ ሰጥቶናል። በመሆኑም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችንን ወደተሻለ የእድገት ማማ ለማድረስ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከውጭ ኃይላት ጥገኝነት እና ተጽእኖ በሂደት በማላቀቅ በራሳችን የተፈጥሮ፣ የፋይናንስ እና የሰው ኃይል ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን ይሰራል።

5 ሀገራዊ መራር ሀቆች: የሁኔታዎች ትንታኔ

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ለሀገራችን ሊያበረክት ያሰባቸው ሁለንተናዊ የለውጥ ጎዳና በተጨባጭ መረጃዎች፣ ሳይንሳዊ መርሆችን የተከተለ ትንታኔ በማድረግ በተነደፉ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የተመረኮዘ ነው። በዚህ ማኒፌስቶም ሆነ በሌሎች የፓርቲው ሰነዶች የተቀመጡ አቅጣጫዎች ከተለያዩ የመረጃ ቋቶች በተሰበሰቡ ወቅታዊ አሀዛዊ (quantitative) እና ገላጭ (qualitative) መረጃዎች የታገዙ ናቸው። ቀጥሎ በተመረጡ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ አጫጭር የሁኔታዎች ትንታኔ የቀረበ ሲሆን በክፍል ሁለት ለቀረቡ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የፖሊሲ አማራጮች መንደርደሪያ እንዲሆኑ ታስቦ የቀረቡ ናቸው።

5.1 ያልተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር

ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ስልጣን ላይ የቆየው የኢህአዴግ መንግስት በውስጥም በውጭም ግፊት ወደ ለውጥ መንገድ ከገባ በኋላ አዲሱ የለውጥ ሀይል በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል፣ በመውሰድም ላይ ይገኛል። እነዚህ የለውጥ እርምጃዎች የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት በኩል መልካም የሚባል ለውጥ አምጥተዋል። ይሁንና እየተወሰደ ያለው እርምጃ የፖለቲካ ምህዳሩን በማስተካከል ቀጣዩን ምርጫ 2013 ዲሞክራሲያዊ ፋይዳ ያለው እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ሲታይ አሁንም ከባድ ውስንነት ይታይበታል።

ለምሳሌ የፖለቲካ ምህዳርን ከሚወስኑት ጉዳዮች አንዱ የሆነውን የገንዘብ/የሐብት ጉዳይ ብንመለከት በገዥው ፓርቲ እና በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለውን የሀብት አሰባሰብ ፍትሃዊ ለማድረግ በቂ እርምጃ አልተወሰደም። ገዢው ፓርቲ የመንግስትን ሀብት ለድርጅት ጉዳይ በመጠቀም በኩል ባለፉት ‹ምርጫዎች› ይታዩ የነበሩ ክፍተቶች አሁንም አልተቀረፉም። በመሆኑም ከዚህ በፊት እንደነበረው በገዢው ፓርቲ እና ተቃዋሚዎች መካከል የነበረው የሀብት ልዩነት አሁንም የቀጠለ ሲሆን ይህም ምርጫ 2013ን በተስተካከለ ምህዳር ላይ ለማድረግ የሚኖረውን እድል የጠበበ ያደርገዋል።

በሚዲያ በኩል መልካም የሚባሉ ሪፎርሞች የተደረጉ ቢሆንም የተደረገው ለውጥ የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስተካከል አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ብዙም አይደለም። የግል ሚዲያዎች የፈለጉትን እንዳይዘግቡ የነበረው አፈና የቀነሰ ቢሆንም የህዝብ ሚዲያዎች የመንግስት ልሳን በመሆን ለሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚሰጡት ሽፋን አናሳ መሆን የፖለቲካ ምህዳሩ እንደ ከዚህ ቀደሙ ያልተስተካከለ ሆኖ እንዲቀጥል አድርጎታል። ከዚህ በፊት በተለይ ምርጫ 1997ን ተከትሎ የወጡ አፋኝ ህጎችን ለማሻሻል እየተሰራ ቢሆንም የማሻሻል ስራው እስከ አሁን ሙሉ በሙሉ አልተጠናቀቀም።

ተቋማትን በተለይም ምርጫ ቦርድንና ፍርድ ቤቶችን ነጻና ገለልተኛ ለማድረግ የተወሰደው የማሻሻያ እርምጃ

እስከ አሁን ስራው አለመጠናቀቁ ለምርጫ 2013 ከቀረው ጊዜ አንጻር ሲታይ ሁኔታው ስጋት መፍጠሩ አይቀርም። ፍርድ ቤቶችን፤ ምርጫ ቦርድን፣ የጸጥታውን መዋቅር ለማሻሻል በተለይ በፌደራል ደረጃ እየተደረገ ያለው መልካም ጅምር ወደ ክልሎችና ወረዳዎች ለማውረድ በርካታ ማነቆዎች ከመኖራቸውም በላይ ጉዳዩ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ በራሱ ተጨማሪ ተግዳሮት ነው። በዚህ ምክንያት በአንዳንድ ክልሎችና ወረዳዎች ውስጥ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነጻነት ለመንቀሳቀስ ከፍተኛ ችግር እየገጠማቸው ይገኛል። ይህም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከህዝብ ጋር በቀጥታ ተገናኝተው የፖለቲካ ስራቸውን ቀርበው በነጻነት እንዳይሰሩ አድርጓቸዋል። በአዲስ አበባና በአንዳንድ ትልልቅ ከተሞች ላይ ብቻ ተወስኖ በሚደረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ዲሞክራሲን ማረጋገጥ እንደማይቻል ይታወቃል። በተለይ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ስርዓት አልበኝነትና ከመንግስት መዋቅር ውጭ የሆኑ የታጠቁ ኃይሎች እንቅስቃሴ የፖለቲካ ምህዳሩ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ፈጥሯል።

የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር ፍትሃዊ የሆነ የምርጫ ውድድር ለማድረግ አስፈላጊ ነው። ባልተስተካከለ ሜዳ ላይ የሚደረግ ምርጫ ወደ ዲሞክራሲ ለሚደረገው ጉዞ እንቅፋት ይሆናል። በመሆኑም የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳን ማስተካከል በተለይ እንደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ላይ ለሚገኝና ከፊት ለፊቱ ምርጫ ላለበት ሀገር ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ እኩል የሆነ ሀብት፣ ሚዲያና ተቋማትን የማግኘትና መጠቀም እድል ሊኖራቸው ይገባል። አፋኝ ህጎችን ለማስወገድ፣ ተቋማትን ነጻና ፍትሃዊ ለማድረግ የተጀመረው ሪፎርም አለመጠናቀቅ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሀብትና ሚዲያ የማግኘትና የመጠቀም እድል ፍትሃዊ አለመሆን፣ እንዲሁም ገዢው ፓርቲ ሚዲያዎችን ለመጠቀም ያለው የተሻለ እድል ቀጣዩን 6ኛ ጠቅላላ ምርጫ ባልተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር ላይ እንዲካሄድ ያደርገዋል። ይህ ሁኔታ እዚህም-እዚያም ከሚታየው ስርዓት አልበኝነትና ገደብ አልባ የመሳሪያ ዝውውር አንጻር ካየነው የምርጫ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ሀገሪቱን ድህረ-ምርጫ ቀውስ ውስጥ ሊያስገባት ስለሚችል አስቀድሞ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል።

5.2 ግጭት፣ መፈናቀል፣ ስደት እና ሞት በኢትዮጵያ

ግጭት እና ስደት የዜጎቻችን የዘመናት መገለጫ ከመሆን አልፈው የዕለት ከዕለት ዜናዎች አካል ሆነዋል። የዜጎቻችን ግጭት፣ ሞት፣ ፍልሰት፣ ስደትና ብሎም መፈናቀል በየቀኑ የምናየው የምንሰማው ሃቅ ነው። በተደጋጋሚ ከመከሰቱ የተነሳም ሰዎች ከማዘንና ከመቆጨት ይልቅ የተለመደ ተግባር ተደርጎ እየተወሰደ ነው።

በሀገራችን ህጎች እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ቢኖሩም በተጨባጭ መሬት ላይ አልዋሉም። የወረቀት ላይ ጌጥ ከመሆን አልፈው አልተከበሩም አልተተገበሩም። አሁን ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ጨምሮ ባለፉት ገዥዎቻችን በስልጣን ዘመናቸው የፈፀሙዋቸው የሠብዓዊ መብት ጥሰቶች በዓይነታቸው፣ በባህርያቸውና በመጠናቸው የተለያዩ እና ውስብስብ ከመሆናቸው የተነሳ በቂ መረጃ እና ማስረጃ ማግኘት አዳጋች ነው።

በህዝባችን ውስጥ ለብዙ አመታት የተዘሩ የጥላቻ ትምህርቶች፣ የጠላትነት ትርክቶች፣ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ የሚያደርጉ አመለካከቶች፣ ሰበካዎች በዜጎች መካከል ግጭቶች እንዲበራከቱ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል፡ ፡ በዜጎች መካከል ልዩነትን የሚያሰፉ ግድግዳዎች በመገንባታቸው አንዱ በሌላው ወገኑ ላይ በግልም ሆነ በቡድን ግፍን ፈጽሟል። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሰላማዊ እና በመተባበር አብሮ የኖረ የተሳሰረ ህዝብ ነው። ይሄን ነባራዊ እውነታ ሲፈታተኑ የቆዩ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ የብሄር እና የጎሳ መልክ ያላቸው ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል፡፡

አለመግባባት ወይም ግጭቶች በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ሊፈጠሩ ቢችልም እንደ ሀገር ውጤታማ እና ዘላቂ የግጭት አፈታት ዘዴን ባለመተግበር በዜጎች ህይወት እና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጥፋቶችን አስተናግደናል። ህዝባዊ ቅቡልነት የሌላቸው መንግስታት፣ ኢ-ፍትሃዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነት፣ ኢ-ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፣ የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣ የሰብአዊ መብት ረገጣ ለግጭቶች መነሻ እንደ ዋና ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ በየትኛውም ቦታ ተንቀሳቅሰው ሰርተው እና ሃብት አፍርተው የሚኖሩበት ስርአት ባለመረጋገጡ ለዘመናት የለፉበትና ያጠራቀሙት ሃብትና

ንብረት በደቂቃዎች ውስጥ ይወድማል። በቋንቋ፣ በእምነት፣ ወይም በሌላ የማንነት መገለጫዎች ዜጎች ከመኖሪያ ቄያቸው ይፈናቀላል፣ ይሰደዳል፣ ይሞታል። በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት በርካታ ዜጎች ለእንግልት፣ ለእስር፣ ለስደት እና ለሞት ተዳርገዋል፡፡

በዘርፈ-ብዙ ገፊ ምክንያቶች የተነሳ ዜጎቻችን በዋናነት ደግሞ አምራች የሆነው ወጣቱ ክፍል ዛሬም ይፈናቀላል፤ ከገጠር ወደ ከተማ ይፈልሳል፣ ከሀገር ይሰደዳል። ቁጥሩ ቀላል የማይባል ስደተኛ ወገናችን ያሰበበት ቦታ ሳይደርስ በየበረሃው እና በየውቂያኖሱ ቀርቷል። በተለይ ሴቶች ለከፍተኛ ሰብአዊ እንግልት፤ ጥቃት እና ሞት ተዳርገዋል። በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ አለማቀፋዊና አገራቀፋዊ ጥናቶች ይሄንኑ እውነታ ይጠቁማሉ። በአፍሪካ ቀንድ ከፍተኛው የስደተኞች እንቅስቃሴ የሚደረገው ከኢትዮጵያ ሲሆን አብዛኞቹ ወደተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ይሄዳሉ፡፡ ከፍተኛውን የስደተኞች ድርሻ የሚይዙት አዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ናቸው።

በኢትዮጵያ የስደተኝነት መጠን እየጨመረ የሄደ ሲሆን በ1997 ከነበረው 8.8 በመቶ በ2000 ወደ 16.6 በመቶ አድጓል። በ2004 ብቻ 160,000 ዜጎች ተሰደዋል። ከ 2003 እስከ 2006 በተደረገ ጥናት በአራት አመታት ውስጥ ወደ 290,000 የሚጠጉ የተለያየ ዜግነት ያላቸው ሰዎች የመን ባህር ዳርቻዎች የረገጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 78 በመቶው ኢትዮጵያዊያን ናቸው። ይሄም በአማካይ 72,000 ሰዎች በአመት ተሰደዋል ማለት ነው።

ከ1997 ታሪካዊው ምርጫ በኋላ ባሉት ስምንት ተከታታይ አመታት ውስጥ ብቻ በድምሩ 410,000 ዜጎቻችን የመን ገብተዋል። በሜድትራኒያን ባህር አቋርጠው አውሮፓ ለመግባት ያሰቡትን ጨምሮ በግብፅና በሊቢያ ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ዜጎቻችን አሉ።
አለም አቀፉ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) በ2003 ባደረገው ጥናት መሰረት በአማካይ በአመት ከ75,000 እስከ 100,000 ኢትዮጵያውያን ወደ ሊቢያ ይሰደዳሉ። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ባጠናው ጥናት ደግሞ በዓመት ከ18,000 እስከ 37,000 ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ሱዳን ይገባሉ። ወደ 22,000 የሚደርሱ ስደተኞች እስከ 9,000 የሚደርሱ ጥገኝነት ፈላጊዎች በኬኒያ ሲኖሩ በደቡብ አፍሪካና በደቡብ ሱዳንም እንዲሁ ብዙ ጥገኝነት ፈላጊ ኢትዮጵያዊያን አሉ።

እጅግ በሚያሳዝን እና ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ባለፉት ሁለትና ሶስት አመታት ብቻ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን በሞት አጥተናል። ገዥዎቻችን ለዘመናት በተከተሏቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎች እና ተግባሮች በርካታ ዜጎች ዛሬም ድረስ ለስደት እና ለሞት እየተዳረጉ ነው፡፡

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ግጭትን፣ መፈናቀልን፣ ፍልሰትን፣ ስደትን እና ሞትን ለመቀነስ በሂደትም ለማስወገድ የሚከተሉትን ተግባራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፣

- በሀገራችን የተንሰራፋውን እና ለዜጎች ስደት እና እንግልት ዋነኛ ምክንያት የሆነውን ስራ አጥነት ለመቀነስ በየአመቱ ከፍተኛ የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡ ፡ በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎችን ህይወት መቀየር የሚችሉ የማክሮ እና ማይክሮ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ዜጎች ደስተኛ እና ከስደት እና ከጎስቋላ ኑሮ የሚላቀቁበት ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- ዜጎችን ለግጭት የሚዳርጉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህጎች፣ ልማዶች እና አሰራሮች በተሻሻሉ እና በዜጎች መካከል ሰላም፣ አንድነት እና ወንድማማችነት መፍጠር በሚችሉ ህጎች እንዲለውጡ ይደረጋል፣
- ሚዛናዊ አስተሳሰብን በህዝብ ውስጥ በማስፈን፤ ጠርዝ ከረገጠ የጭፍን ጥላቻ ዜጎች እንዲወጡ በማድረግ ምክንያታዊ እና አስተዋይ ትውልድ መፈጠር የሚያስችል የትምህርት ስርአት ተግባራዊ ይሆናል፣
- በሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መርሆች ላይ የተመሠረተ ፍትሃዊ፣ አሳታፊ እና አካታች ስርዓት እና ጠንካራ ተቋማትን በመፍጠር ዜጎች በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ቦታ በነፃነት ተንቀሳቅሰው መስራት እንዲችሉ ምቹ የህግ ማእቀፍ እና ከለላ ይዘጋጃል፣
- ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ዜጎቻችን ባሉበት ቦታ ሁሉ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እንዲጠበቁ፣ ከሚኖሩበት ሀገር መንግስታት ጋር በመተባበር የህይወት እና የንብረት ዋስትና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

5.3 የድህነት አዙሪት

በዓለም ላይ ከሚገኙት እጅግ ደሃ ሀገሮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ይገኛሉ። የአለም የልማት መለኪያ (World Development Indicator) እ.ኢ.አ በ2019 ባወጣው ሪፖርት በአፍሪካ ውስጥ ድህነት በበርካታ ሀገራት ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን በአጠቃላይ ዓለማችን ካሉ ድሀ ሀገራት ውስጥ ከ70% በላይ የሚሆኑት ከሰሃራ በታች ባሉ 10 ሀገራት ውስጥ ይገኛሉ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከነዚህ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ናት።

በሀገራችን ከ30 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይማቅቃል። ድህነት የሚገለጽባቸውን የተለያዩ ዘርፎች ከግምት በማስገባት (Multi Dimensional Poverty Index) የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው 88.2% የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በሁሉም የድህነት መገለጫ ዘርፎች ደሃ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

በሌላ በኩል ሀገራችን ኢትዮጵያ በሰው ልጆች እድገት መለኪያ (Human development Index) ረገድም በአለም ላይ እጅግ ወደ ኋላ ከቀሩ ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ይህ የእድገት መለኪያ ሰዎች መሰረታዊ በሆኑ የአገልግሎት ዘርፎች ለምሳሌ ጤናማ አኗኗር፤ እውቀት ወይም ትምህርት፤ መልካም የሚባል የኑሮ ሁኔታ… ወዘተ የሚያስመዘግቡት አማካይ ውጤት ነው። ሂዩማን ዴቨሎፕመንት ኢንዴክስን ከግምት በማስገባት የተባበሩት መንግስታት የእድገት ፕሮግራም (UNDP) የአፍሪካ ሀገራትን ደረጃ አስመልክቶ ባካሄደው ጥናት ኢትዮጵያ ከ53 የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ 38ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች (HDR, 2020)፡፡ የኢትዮጵያ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ እድገት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ በከተሞች ውስጥ ከሚኖረው ዜጋ በላቀ ሁኔታ የገጠሩ ህዝብ በድህነት ውስጥ እንደሚኖር አሳውቋል (MoFED, 2018)። ከ83% በላይ የሚሆኑ የሀገራችን ሕዝቦች በገጠር እንደሚኖሩ ይታወቃል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ከ50,000 (አምሳ ሺህ) የሚልቁ ሰዎች በጎዳና ላይ እንደሚኖሩ አስታውቋል። ጥናቶች እንደሚያመላክቱት በልመና ከሚተዳደሩ የጎዳና ላይ ነዋሪዎች መካከል ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆኑት ወደ ጎዳና ያስወጣቸው ድህነት ነው (አብዱሰላም, 2019)።

የሀገራትን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ ሀገራቱ ለህፃናትና ወጣቶች እድገትና ትምህርት የሚሰሩት ቀጣይነት ያለው ስራ ነው። ከ40% በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድሜ ከ18 ዓመት በታች እንደሆነ ይገመታል። እድሜአቸው ከ18 በታች የሆኑ ህፃናትና ወጣቶች ከ36 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በተለያዩ የድህነት መለኪያዎች ደሃ መሆናቸው ተረጋግጧል (CSA እና UNICEF, 2019)። እነዚህ የኢትዮጵያ ህፃናትና ወጣቶች በተባበሩት መንግስታት የህፃናት መብት ስምምነቶች ውስጥ ከተካተቱት ዘጠኝ መብቶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን የተነፈጉ መሆናቸውን ጥናቱ ያመላክታል።

የድህነታችን ማህበራዊ ተጽእኖ

በሀገራችን ያለው አስከፊ ድህነት ዜጎቻችንን ለድርብርብ ማህበራዊ ችግሮች ዳርጓቸዋል። በሽታ፣ ርሀብ፣ ስደት፣ ሞት የበርካታ ዜጎቻችን እጣ ፋንታ ሆኗል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ህይወትን ለማሸነፍ ስብእናን በሚያዋርድ የስራ መስክ እንዲሰማሩ ሆነዋል። ህጻናት እና ሴቶች ግንባር ቀደም የድህነት ገፈት ቀማሽ ናቸው። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መመገብ አይችሉም። ከጸሀይ ሀሩር እና ከዝናብ የሚከልል መጠለያ ያላቸው ኢትዮጵያውያን እጅግ አናሳ ናቸው። አብዛኛው ቤተሰብ እጅግ በተጨናነቀ እና የቤተሰብ አባላትን ለከፋ የጤና ችግር በሚዳርግ ሁኔታ ይኖራል። ንጹህ የመጠጥ ውሀ እና በቂ የመጸዳጃ አገልግሎት ማግኘት የሚችለው የማህበረሰብ ክፍል እጅግ ዝቅተኛ ነው። መሰረታዊ የጤና አገልግሎት እና ትምህርት ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ተደራሽ አይደለም። በገጠር እና በከተማ የሚኖሩ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለማስተማር አቅም ስለሌላቸው በርካታ ትውልድ በድህነት አዙሪት ውስጥ ይኖራል።

የድህነታችን ዋናው ምክንያት፡ የበርካቶች ድህነት የጥቂቶች ብልጽግና!!

ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት በሆነችው ሀገራችን የተንሰራፋው አስከፊ ድህነት ለብዙዎች እንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል። ለተዘፈቅንበት አንገት የሚያስደፋ ድህነት በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም የችግሩ ስር መሰረት ፖለቲካዊ ነው። የተሳሳተ ፖለቲካዊ ርዕዮተ-ዓለም፣ ኋላ ቀር የልማት ስትራቴጂ፣ ብልሹ የመንግስት አስተዳደር፣ አይን ያወጣ ሙስና፣ ከብዙ በጥቂቱ ናቸው። ባለፉት ዘመናት በተለይም ላለፉት 27 ሲደመር 3 ዓመታት ገዢው ፓርቲ ሲከተለው የቆየው ኢ-ሳይንሳዊ የምጣኔ ሀብት እና የማህበራዊ እድገት ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ለዜጎቻችን ድህነት ትልቁን ድርሻ ይጫወታሉ።

ሀገራችን በዓለም የታወቁ ጥቂት ባለ ቢሊየን ብር ባለሀብት ግለሰቦች ተፈጥረውባታል። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂት የማይባሉት በህገ-ወጥ መንገድ የበለጸጉ ግለሰቦች የሀገርን ሀብት እና የዜጎቻችንን ላብ በዘረፉት የጥቅም መረብ እየመጠጡ ሀብት ያጋበሱ ናቸው። የፖለቲካ ስርአቱ በፈጠረላቸው ከለላ እና ሽፋን በመታገዝ የግብር ከፋዩን ድህ ገበሬ እና ሰራተኛ ሀብት በመመዝበር የበለጸጉ ጥቂት ፖለቲከኞች እና ጥገኛ ባለሀብቶች ህዝባችን በድህነት አረንቋ እንዲኖር አድርገውታል።

5.4 የኑሮ ውድነት

የምጣኔ ሀብት ሣይንስ ባለሙያዎች የኑሮ ውድነትን ከዋና ዋና የማክሮ-ኢኮኖሚ የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ ይመድቡታል። ሀገራት በዋናነት ሊያሣኩ የሚያልሟቸው አራት የኢኮኖሚ አላማዎች የሚያስቀምጡ ሲሆን እነሱም የስራ እድልን መፍጠር፣ ከፍተኛ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ፣ የክፍያ ሚዛን (balance of payment) መጠበቅ እና ዋጋን ማረጋጋት ናቸው።

የኑሮ ውድነት ሀገራት ከሚያጋጥማቸው የኢኮኖሚ ችግሮች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን ማህበራዊ ቀውስ ከማስከተሉም በላይ ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን እንደሚፈጥር እሙን ነው። የምርትና አገልግሎት ገበያ ዋጋ የተረጋጋ ሲሆን ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማስመዝገብ ከመርዳቱ ባሻገር ኢንቨስትመንትን ያበረታታል። የተረጋጋ ዋጋ ባለበት ሀገር አምራቾች የገበያ ዋጋን በተገቢው መልኩ እንዲተነብዩ በመርዳት በእቅድ እንዲመሩ ያግዛቸዋል።

በአንድ ሀገር የተረጋጋ የዋጋ ምጣኔ መኖር መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ ለሚያስቡ ባለሀብቶች ወጪና ገቢያቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲገምቱ በማስቻል የፕሮጀክቶችን አዋጭነት በአግባቡ እንዲያሰሉ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም የተረጋጋ ዋጋ ባለበት ሀገር ዜጎች የሚቆጥቡት ገንዘብ የመግዛት አቅም እንዳይቀንስ በማድረግ ቁጠባን ያበረታታል። የተረጋጋ የገበያ ዋጋ የውጭ ንግድ ተፎካካሪነትን ያሳድጋል። ከዚህም በላይ የተረጋጋ የዋጋ ምጣኔ ዜጎችን ካልተፈለገና ካልታቀደ ኢ-ፍትሃዊ የገቢና ሀብት ክፍፍል በመታደግ በኑሮ ውድነት ምክንያት ከሚከሰት አላስፈላጊ የገቢ ልዩነት ይታደጋል።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ኢኮኖሚ ባላቸው ሀገራት የዋጋ ውድነትን የሚያስከትሉ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከነዚህም ውስጥ የተስፋፋ የገንዘብ ፖሊሲ (expansionist) እና ውጤቱ ተጠቃሽ ነው።

ባለፉት አስርና ከዚያ በላይ አመታት ውስጥ የተመዘገበው የሀገሪቱ ከፍተኛ የመንግስት ወጪና እሱን ተከትሎ እያደገ የመጣው አጠቃላይ የሀገሪቱ ፍላጎት (Aggregate Demand) ሀገሪቱ ላይ ለተስተዋለው ከፍተኛ የዋጋ ውድነት አብይ አስተዋፅኦ እንደነበረው ይገመታል።

በሌላ መልኩ አንድ ሀገር ላይ በሚከሰቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ተግዳሮቶች ምክንያት የምግብና ምግብ ነክ ውጤቶች ምርት እና አቅርቦት መቀነስ የኑሮ ውድነት ከሚያስከትሉ ብሎም ከሚያባብሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ይጠቀሳል። በተጨማሪም መንግስታት የኢኮኖሚያቸውን አጠቃላይ ፍላጎት ለመጨመርና የበጀት ጉድለትን ለመሙላት ብርን በማተም ኢኮኖሚው ውስጥ ሲያሰራጩ የዋጋ ግሽበት እና ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ይፈጠራል። በኢትዮጵያም የበጀት ጉድለትን ለመሙላትና እያደገ የመጣውን ከፍተኛ የመንግስት ወጪ ለመደጎም መንግስት ብርን በከፍተኛ ደረጃ ሲያትም ቆይቷል። ቋሚ የውጭ ምንዛሬ ተመን (fixed exchange rate system) የሚከተሉ ሀገራት የዋጋ ውድነትን ከውጪ ሀገራት የማስገባትና በአለም አቀፍ የዋጋ አለመረጋጋት ተፅዕኖ ስር የመዋል እድላቸው በአንፃራዊነት ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል።

በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሪፖርት መሰረት ሀገር አቀፍ የዋጋ ግሽበት ከ 1991 እስከ 1994 ባሉት አመታት አማካይ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት መጠን ከዜሮ በታች የተመዘገበ ሲሆን ከ1995 በኋላ ባሉት አመታት አማካይ አጠቃላይ የግሽበት መጠን 14.49 % ሆኖ ተመዝግቧል። ባለፉት ሶስት አመታት ደግሞ የኑሮ ውድነት በከፋ መልኩ ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን አጠቃላይ አማካይ የግሽበት መጠንም ሆነ የምግብ ዋጋ ግሽበት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በዚህም የዜጎችን የኑሮ ሁኔታና ማህበራዊ መስተጋብር እንዲሁም የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ ጎድቶታል። ከእለት ወደ እለት እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት የህዝቡን አቅም እየተፈታተነ ኢኮኖሚውንም እንዳይረጋጋ አድርጓል። ከአመት አመት መሻሻል ያላሳየው የኑሮ ውድነት በያዝነው አመት (2013) በመባባስ እስከ ጥር ወር ያለው አማካይ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት 18.88 %፣ የምግብ ዋጋ ግሽበት ደግሞ በሚያሳስብ መልኩ 21.18 % ደርሷል።

በክልሎች መካከል ያለውን የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ስንመለከት ችግሩ የአዲስ አበባ ወይም የጥቂት ከተሞች ብቻ ሳይሆን ሀገር አቀፍ እንደሆነ ያሳያል። በክልሎች መሀል በኑሮ ውድነት ያለው ልዩነትም ሆነ በክልሎችና በአገር አቀፍ አማካይ የግሽበት መጠን መሀል የሚታየው ልዩነት ዝቅተኛ ነው። ይህም የኑሮ ውድነቱ የሁሉም ከተሞችና የሁሉም ክልሎች መገለጫ፤ የነዋሪዎቻቸው ሰቆቃና የኑሯቸው አስከፊ ገፅታ ሆኖ ዘልቋል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት የ2012 አመት የዋጋ ግሽበት በሁሉም የምርትና አገልግሎት አይነቶች ላይ ታይቷል። በተለየ መልኩ ዳቦ፣ ጥራጥሬ እህሎች፣ ስጋ፣ አትክልትና ፍራፍሬ በመሣሠሉ የምግብ ምርቶች ላይ የሚታየው የኑሮ ውድነት አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱንና የህዝቡን ኑሮ እየተፈታተነ መምጣቱን ማየት ይቻላል። ከምግብ ውጭ ባሉ ምርትና አገልግሎት ላይ የሚታየው የኑሮ ውድነትም ከፍተኛ ሲሆን በትራንስፖርት፣ የቤት ኪራይ፣ የግንባታ እቃዎች፣ ውሃ፣ ኤሌክትሪክ ሀይልና ነዳጅ ምርቶች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ግሽበት ግን በተለየ መልኩ ከፍተኛ መሆኑ ተመዝግቧል። በየካቲት 2013 ወር በመንግስት ድጎማ የሚቀርበው ነዳጅ ላይ የተደረገውን የዋጋ ለውጥ ተከትሎ የተስተዋለው የምርቶችና አገልግሎቶች ዋጋ ግሽበት በቅርቡ የታዘብነው እውነታ ነው።

ሀገራችን ላለፉት በርካታ አመታት አስመዘገበች ከተባለው የኢኮኖሚ እድገት ጎን ለጎን ከፍተኛና ተከታታይ የዋጋ ግሽበት ተስተውሏል። ከሚገመተው ኢኮኖሚያዊ ቀመር ባፈነገጠ መልኩ መንግስት የግብርና ምርትና አቅርቦት መጠን እያደገ እንደሆነ ቢገልጽም የምግብ ዋጋ ግሽበት መጠን ግን ሊቀንስ አለመቻሉ ተመዘገበ የተባለውን የኢኮኖሚ እድገት ተአማኒነት አጠያያቂ አድርጎታል። የኑሮ ውድነቱ ከከተማ ከተማ፣ ከክልል ክልል ሳይለይ የሁሉንም ቤት ያንኳኳ፣ የህዝቡን ኑሮ ያመሰቃቀለና ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋትን ያስከተለ መሆኑ አሳሳቢ ያደርገዋል። ችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ ካላገኝ ወደ ለየለት የፖለቲካ ቀውስ ሊያመራ እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

የተረጋጋ ኢኮኖሚያዊ ከባቢን ለመፍጠር፣ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የቁጠባ ባህልን ለማዳበርና ቁጠባን ለማሳደግ፤ የውጪ ንግድ ተፎካካሪነትን ለማጎልበት፣ የዋጋ ግሽበትን ተከትሎ በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ያልተመጣጠነ የገቢና ሀብት ልዩነት ለመከላከል የምርትና አገልግሎት ዋጋ መጠንን

የተረጋጋ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ገበያውን በማረጋጋት ዜጎች በታቀደ፣ በተረጋጋና በተገመተ መልኩ ስራቸውን እንዲያከናውኑና ኑሯቸውን እንዲገፉ ያስችላቸዋል።

5.5 ስራ አጥነት

የስራ ዕድል መፍጠር ዋና ዋና ከሚባሉ የኢኮኖሚ ግቦች አንዱ ነው። ለዜጎች በቂ የስራ እድል መፍጠር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንድምታ አለው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት የስራ እድል ፈጠራ ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳይ ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ ትርጉም አለው። በኢትዮጵያ በመንግስት ይፋዊ መረጃ መሰረት ወደ 20 በመቶ የሚጠጋ የሰው ኃይል በከተሞች አካባቢ ስራ አጥ ነው። ይህ አሀዝ በኢመደበኛው የተሰማራው የሰው ኃይልን አያካትትም። ነገር ግን በኢመደበኛ የተሰማራው የሰው ሀይል በመደበኛው ዘርፍ ስራ በማጣት ተገዶ የገባ ስለሆነ (disguised unemployment) እንደ ስራ አጥ ይቆጠራል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ የስራ አጥ ዜጎች ምጣኔ ሲሰላ በከተማ የስራ አጥ ምጣኔ ከ40 በመቶ በላይ ከፍ ይላል። ይህ ቁጥር እጅግ አሳሳቢ ነው።

3

ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መንግስት/ገዢዉ ፓርቲ የሚከተለው ግልጽነት የጎደለው እና የተሳሳተ የስራ እድል ፈጠራ ፖሊሲ፣ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት የሚወሰዱ በወጉ ያልተጠኑ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ይበልጥ እንዲባባስ አድርገውታል። መንግስት የስራ እድልን በዋናነት መንግስት ራሱ እንዲፈጥር ከፍተኛ ሀብትና የሰው ሀይል በመመደብ በተሳሳተ የፖሊሲ አቅጣጫ እየተጓዘ ይገኛል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ እጅግ ዝቅተኛ በሆነበትና አብዛኛው ህዝብ በግብርና የስራ መስክ በተሰማራባት ሀገራችን፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በየአመቱ የሚወጡ ተመራቂዎች በኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲሰማሩ ኢኮኖሚው የስራ እድል መፍጠር ስለማይችል ከፍተኛ ስራ አጥ ቁጥር እንዲፈጠር ያደርጋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ «ዋናው የስራ ዕድል ፈጣሪ የግሉ ዘርፍ ሊሆን ይገባል» ብሎ ያምናል። በመሆኑም የግሉ ዘርፍ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረተውን የሰው ኃይል ኢንዱስትሪው እንዲቀበል በሚያስችል መልኩ በተጨባጭ ሊያበረታቱ የሚችሉ ጥቅል ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል። የኢትዮጵያን የስራ አጥ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የአምራች ዘርፉ በፍጥነት እንዲያድግ የሚያስችሉ አሰራሮች ይዘረጋሉ። የአምራች ዘርፉን ለማሳደግ የንግድ፣ የፋይናንስ፣ የታክስ ... ወዘተ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን ማሻሻል፣ የመሰረተ-ልማት አቅርቦትን ማሳደግ እንዲሁም የተቀናጀ የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል።

5.6 ብልሹ የመንግስት አሰራር፣ ደካማ ቢሮክራሲ እና የፍትህ እጦት

መንግስት በዋናነት በግል ዘርፍ ሊሰሩ የማይችሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የፀጥታ እና ደህንነት እንዲሁም የፍትህ አገልግሎት ለህዝቡ ለመስጠት በህዝብ የተወከለ አካል ነው። የመንግስት መዋቅር በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ደካማ ተቋማት ያሉት ከሆነ፣ ብልሹ አሰራር እና ሙስና የተንሰራፋበት ሲሆን፣ እንዲሁም ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጠው አካል ነፃ እና ገለልተኛ ካልሆነ ማህበረሰቡ የተቀላጠፈ፣ የተሳለጠ፣ ተደራሽ፣ ፍትህዊ እና ርትአዊ አገልግሎት ሊያገኝ አይችልም። ይህ ሁኔታ በማሕበረሰቡ ዘንድ የእኩልነት አለመኖርን፣ የፍትህ እጦትን፣ የማሕበራዊ ፍትሕ መጓደልን እና መገለልን ያስከትላል።

ሀገራችን ባለፉት መቶ ዓመታት ዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ከተመሰረተ በኋላ፤ ሀገሪቱ ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በሀገሪቱ ተቋማት ግንባታም (State Building) ሆነ ብሄር ግንባታ (Nation Building) ሂደት የሀገራቸው ባለቤት ሆነው እኩል ተሳትፎ እና ሚና እንዲኖር አለመደረጉ፣ በመንግስት መዋቅር ውስጥ አስቀድሞ የነበረው የጭቆና ስርአት የፈጠረው መንግስታዊ ቢሮክራሲ እና መዋቅር፣ በኢ-መደበኛ አደረጃጀት በአስተሳሰብም ሆነ በአመለካከት ራሱን ሸፍኖና ደብቆ (Deep state) በመቆየቱ በውጤት ረገድ የእኩልነት መርህን ያልተከተለ፣ አካታች እና አሳታፊ ያልሆነ፣ አድሏዊ እና አግላይ ፖሊሲዎች እና ስርአቶች እንዲተገበሩ ሆኗል።

የሀገር እና ህዝብ ተቋማት ለሀገር፣ ለህዝብ እና ለዜጎች ተገዢ እና አገልግሎት ሰጪ ከመሆን ይልቅ፣ መደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ በሆነ ሁኔታ ስልጣኑን የተቆጣጠረው ገዢ ስርአት፣ ቡድን ወይም ብሄር አገልጋይ እና ጥቅም

በክፍል አንድ ሀገራችን ያለችበት እጅግ አሳሳቢ፣ ውስብስብ እና ፈጣን ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች በመጠኑ ተዳስሰዋል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በምርጫ 2013 የሚያስመዘግበው ውጤት በፌዴራል እና በክልሎች ሀገር የማስተዳደር አቅም የሚያገኝ ከሆነ በሚከተሉት የፖለቲካ (ሥነ-መንግስት)፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ የሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ክፍል ሁለት

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ
የአምስት አመት የትኩረት አቅጣጫ

ምዕራፍ አንድ፡ ሥነ-መንግስት	21
1. አካታች ብሄረ መንግስት መገንባት	21
2. ህገ-መንግስት ማሻሻያ	22
3. ብሄራዊ እርቅ እና መግባባት	24
4. የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት	25
5. እውነተኛ ፌዴራሊዝም	27
6. ፓርቲ እና መንግስትን መለየት	30
7. የዜጎች ሰብአዊ ሙብት	30
8. የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ	31
9.መልካም አስተዳደር	34
10.ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ	35
11. የህግ የበላይነት	38
12. የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች	39
13. ብዙሀን መገናኛ (ሚዲያ)	40
14. የአዲስ አበባ ጉዳይ	42
15. የውጭ ግንኙነት እና ሀገራዊ ደህንነት	45
ምዕራፍ ሁለት፡ ጠንካራ እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ	47
1. አካታች የኢኮኖሚ እድገት እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል	47
2. የመሬት አስተዳደር	48
3. ግብርና፣ ገጠር ልማት እና የምግብ ዋስትና	52
4. አርብቶ አደር ልማት፡ የተረሱ ዜጎች	53
5. ቱሪዝም እና ቅርስ ጥበቃ	55
6. ማክሮ ኢኮኖሚ	56
7. የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲ	57
8. የፋይናንስ ተቋማት	57
9. ኢንደስትሪ	59
10. ንግድና ኢንቨስትመንት	61
11. ዲጂታል ኢኮኖሚ	62
12. ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር	66
ምዕራፍ ሶስት፡ መሰረተ ልማት	68
1. መንገድ	68
2. ትራንስፖርት	70
3. የማዕድን ሀብት ልማት	71
4. የኢነርጂ ሀብት ልማትና አጠቃቀም	73
ምዕራፍ አራት፡ ጤናማ እና ደስተኛ ማህበረሰብ	76
1. ትምህርት	76
2. ጤና	77
3. የአካል ጉዳተኞች፡ እኩልነትና አካታችነት	79
4. የውሀ ሀብት ልማት	81
5. ለመኖሪያ እና ለስራ ምቹ አካባቢ፡ ቤቶች እና ከተማ ልማት	[illegible]

ምዕራፍ አንድ

ሥነ-መንግስት

በዚህ ክፍል ከስርአተ መንግስት ጋር በተገናኘ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ስራዎች በዝርዝር ተመልክተዋል። አካታች ብሄረ መንግስት ግንባታ፣ ህገ-መንግስት ማሻሻያ፣ ብሄራዊ እርቅ እና መግባባት፣ ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር መፍጠር፣ እውነተኛ የፌዴራል አወቃቀር መገንባት፣ ፓርቲ እና መንግስትን መለየት፣ የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት ማስከበር፣ የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ማረጋገጥ፣ ጥልቅ እና ስር ነቀል ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ማካሄድ፣ የህግ የበላይነትን ማስከበር፣ የሲቪክ ማህበራትን ማጠናከር እና ጠንካራ የሚዲያ ዘርፍ እንዲፈጠር ማስቻል በዚህ ክፍል ተካትተዋል። ቀጥሎ እያንዳንዱ አጀንዳ በቅደም ተከተል ቀርቧል።

1 አካታች ብሄረ መንግስት መገንባት

ኢትዮጵያ ረዥም የመንግስትነት ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን በየጊዜው እየሰፋና እየጠበበ የሄደ ድንበር የነበራት እና ነጻነቷን ጠብቃ የቆየች ሀገር ናት። ኢትዮጵያ በረጅሙ የታሪክ ጉዞዋ በርካታ የመንግስት ስርአቶችን፣ የህዝቦችን መስተጋብር እና መወራረስ አስተናግዳለች። በዚህ ጥንታዊ፣ መካከለኛና ዘመናዊ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በርካታ ጥሩም መጥፎም ታሪካዊ ክስተቶች ተፈጽመዋል።

የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ ውስጣዊ የፖለቲካ ቀውሶችና ሽኩቻዎች የማይካዱ የታሪካችን አካል ነበሩ። የኢትዮጵያን ታሪክ በተለይም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ያለውን በተመለከተ የተለያዩ ግንዛቤዎች እና አተረጓጎሞች ያሉ ሲሆን ይህ ልዩነት አሁን ላይ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ለሚስተዋለው የጋራ ሀገራዊ አመለካከትና ራዕይ አለመኖር መነሻ ሆኗል።

በሀገራችን ሁለት አይነት የሀገረ መንግስት እይታዎች አሉ። አንደኛው ኢትዮጵያን እንደ ብሄረ-መንግስት (Nation state)፣ ኢትዮጵያዊነትንም ተሰርቶ እንዳለቀ ማንነት፣ ብዝሀነትን እንደ እዳ የሚመለከተው የሀገር ምስረታ/ግንባታ እይታ ሲሆን ሁለተኛው እይታ ብሔራዊ አንድነትን እንደ ስጋት፣ አብሮነትን እንደ እዳ የሚመለከተው እይታ ነው። ሁለቱም አመለካከቶች የኢትዮጵያን ትክክለኛ ታሪክ እና ነባራዊ ሀቅ የሚያንጸባርቁ አይደሉም። የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያን በፍሬ ነገር ደረጃ የሚገልጹበትም ሆነ የሚረዱበት ሁኔታ አካታችነት የሚጎድለው ሲሆን ሁለተኛው የታሪክ አረዳድ ደግሞ የሀገረ መንግስቱን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ ለጠንካራ ሀገር ግንባታ እንቅፋት ይሆናል። ኢትዮጵያን የጭቁን ብሔሮች ሃገር አድርጎ የሚያየው "የብሄራዊ ጭቆና" እይታ በህዝቦች መካከል አለመተማመንና ጥርጣሬ እንዲፈጠር አድርጓል። ሁለቱም የኢትዮጵያ የሀገረ መንግስት ታሪክ አረዳዶች የኢትዮጵያን ታሪክ ምሉዕ (totality) በሆነ መንገድ ካለማየት እና በቁንጽል የታሪክ ሁነቶች እና ኢጋጣሚዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ «ኢትዮጵያ ለነገ ተስፋና አብሮነት መሰረት የሚጥል ሚዛናዊ የሆነ የሀገረ-መንግስት የታሪክ አረዳድ ያስፈልጋታል» ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ የቀደመ ታሪክ የከፍታ ወይም የጭቆና ዘመን ብቻ አልነበረም። እንደ ህዝብ በጋራ ያስመዘገብናቸው የከፍታ ዘመኖች ነበሩን። አድዋን ጨምሮ በተለያየ ጊዜ የተፈጸሙ የነጻነት ተጋድሎዎችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህን የጋራ ታሪኮች በጋራ መዘከርና ማክበር ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ ጭቆና መኖሩም የሚካድ ሀቅ አይደለም። ሁሉም አይነት ጭቆናዎች ማለትም የመደብ፣ የብሄር፣ የቋንቋ፣ የኃይማኖት እንደነበሩ መካድ አይቻልም። ይህንን ሀቅ መካድ ለሀገራችን ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ ለማፈላለግ፣ ወደ እርቅ እና ብሄራዊ መግባባት የምናደርገውን ጉዞ ማደናቀፍ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ በጥቅሉ መካድ ይሆናል። አይነቱና መጠኑ ቢለያይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተጨቆነ ህዝብ ነበር ለማለት አይቻልም። **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**

«የጭቆናው ባለቤት በወቅቱ የነበረው ስርዓት/መንግስት እንጂ በተለየ ጨቋኝ የነበረ ህዝብ አልነበረም» ብሎ በጽኑ ያምናል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ነባራዊ ሀቅ ታሳቢ ያደረገና ነገን የተሻለ ለማድረግ የሚያግዝ ሚዛናዊ የሀገር ግንባታ ታሪክ እና አረዳድ መፍጠር ለዛሬ መግባባትም ሆነ ለነገ አብሮነት ቁልፍ ሚና ይኖረዋል።

ይህ ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሚዛናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ የተቀዳው የሀገር እና የመንግስት የታሪክ እይታ በሀገራችን ከተንሰራፋው የታሪክ አረዳድ በበለጠ የሀገራችን መጻኢ እድል የተሻለ እንዲሆን እጅግ አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ትናንትን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በመረዳት ዛሬ ላይ ነጻነት፣ እኩልነት እና ፍትህ ላይ የተመሰረተች ሀገር በመገንባት፣ ነገን የተሻለ ለማድረግ ይሰራል። ለዚህም አካታች የብሔረ-መንግስት ግንባታ (Inclusive Nation Building) ሂደት እውን እንዲሆን የሚያስችሉ የፖለቲካ ፍልስፍና እና ተግባራዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል።

2 ህገ-መንግስት ማሻሻያ

ህገ-መንግስት የዜጎችን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የመንግስትን አወቃቀርና አሰራር የሚወስኑ መሰረታዊ ህጎችና መርሆችን የሚይዝ የህግ እና የፖለቲካ ሰነድ ሲሆን በአንድ ሀገር ውስጥ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች... ወዘተ መነሻ ነው። ሕገ-መንግስት መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የውጭ ግንኙነት መርሆችን የሚይዝ ለአንድ ሀገር ሰላምና ብልጽግና እንዲሁም ለዜጎች ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ ዋስትና የሚሰጥ የዜጎች የመግባቢያ ሰነድ ነው። ሕገ-መንግስት እንደ ስሙ የሀገርና የመንግስት ህግ ይሆን ዘንድ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት ያለው፣ ግልጽና የማያሻማ ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንጻር የሀገራችንን ሕገ-መንግስት ስንመለከተው መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ እንገነዘባለን።

የህገ-መንግስት ማሻሻያ (Constitutional Amendment) ማለት አንድ ህገ-መንግስት ስርዓት በተከተለ መልኩ ያለበትን ጉድለት የሚሞላበት መንገድ ነው። ህገ-መንግስት የሀገሪቱ ህጎች ማጠንጠኛ እንደ መሆኑ መጠን የማሻሻያው ስርአት ለሌሎች ህጎች ከተቀመጠው የተለየ መሆን ይጠበቅበታል። በዓለማችን ላይ ያሉ የተጻፉ ህገ-መንግስታት ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ ቢያንስ አንድ አንቀጽ ያስቀምጣሉ። በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችም እንደሚያሳዩት በአለም ላይ ዘላለማዊ የሆነ የማይሻሻል ፍጹም የሆነ ህገ-መንግስት የለም። የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት የማሻሻያ ድንጋጌ ቢኖረውም በተግባር ይህ ነው የሚባል ማሻሻያ ሳይደረግበት እስከአሁን ቆይቷል።

የህገ-መንግስት ማሻሻያ አስፈላጊ የሚሆንበት የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ። ከነዚህም ውስጥ፣

1. ህገ-መንግስት የሚፀድቀው በሰው ልጆች እንደመሆኑ መጠን ከስህተት፣ መርሳት እና ተመሳሳይ የሆኑ ክስተቶች አይድንም። በመሆኑም ሰዋዊ ስህተትና ተፈጥሯዊ ክፍተትን ለማስተካከል የህገ-መንግስት ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፣
2. በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ ሐገራዊ፣ አካባቢያዊና አለማቀፋዊ ሁኔታዎችን በማካተት ህገ-መንግስቱን ከዘመን ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል። በፍጥነት ተለዋዋጭ ከሆነው የአለማችን ኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ የአለም አቀፍ ግንኙነት እና የስነ ህዝብ (demography) ሁኔታ ጋር ለመራመድ እንዲያስችል የህገ-መንግስት ማሻሻያ የግድ ይላል፣
3. በተጨማሪም ህገ-መንግስት መቀረፅ ያለበት እየተዳደረበት የሚገኘውን ማህበረሰብ ለማገልገል እንደመሆኑ መጠን የማህበረሰቡን ፍላጎት፣ ተስፋ፣ ፍራቻ እና ህልም የሚያሳይ ሊሆን ይጠበቃል፣
4. በተግባር ያጋጠሙና በጊዜ ሂደት ተለይተው የታወቁ ችግሮችን ለመፍታት እና ቅቡልነትን ለማደስም ማሻሻያ ያስፈልጋል።

የህገ-መንግስት ማሻሻያ መሰረተ-ሐሳቦች

የህገ-መንግስት ማሻሻያ አስፈላጊነት በዋናነት «የሰው ልጅ ፍጹም አይደለም፤ ህገ-መንግስት የሰው እጅ ስራ ውጤት እንደመሆኑ መጠን ዘላለማዊ እውነትነት አይኖረውም» ከሚል እሳቤ የሚመነጭ ነው። ሌላው መነሻ እሳቤ የህዝብ ስልጣን ባለቤትነት አስተሳሰብ ሲሆን ህዝብ ራሱ የሰራውን ህገ-መንግስት በራሱ የማሻሻል፣ አስፈላጊም ሲሆን የመለወጥ ተፈጥሯዊ ስልጣን ያለው አካል እንደሆነ ይታመናል።
በህገ-መንግስት ማሻሻያ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ጥናትም ሆነ ውይይት በህገ-መንግስት ላይ ለውጥ ከማድረግ ባለፈ ስለ አንድ ሐገር ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ማለትም እንደ

ሐገር ስለሚነሱ ቁልፍ ሀሳቦችና ስላለው የሀይል አሰላለፍ ሁኔታ ፍንጭ ይሰጣል። ለምሳሌ በልሂቃኑና በህዝቡ ዘንድ በመሰረታዊ ሐገራዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን የአስተሳሰብ አንድነትና ልዩነት መጠን (level of consensus)፣ ሀገር የሚመራበት ንድፈ ሀሳብና እሴት ምን እንደሆነ፣ በአንድ ሐገር ውስጥ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት እንዲሁም የቅቡልነት ምንጭ ማን እንደሆነ ወዘተ። ለዚህም ነው «ስለአንድ ሐገር ፖለቲካዊ ሁኔታ የበለጠ ለማወቅ ስለ ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ ያለውን ህግና አሰራር መፈተሽ ይገባል፡፡» የሚባለው።

በዓለም ላይ ተግባራዊ የተደረጉ የተለያዩ የህገ-መንግስት ማሻሻያ አይነቶችና መንገዶች ያሉ ሲሆን ቃላዊ/መጽሀፋዊ የማሻሻያ መንገድ (Textual Model)፣ ይዘታዊ የማሻሻያ መንገድ (Substantive Model)፣ ፖለቲካዊ የማሻሻያ መንገድ (Political Model) እና አብዮታዊና ስር-ነቀል የማሻሻያ መንገድ (Revolutionary Model) ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአንድ ህገ-መንግስት አማካይ እድሜ ከ19-23 ዓመት ነው። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ህገ-መንግስቱ መደበኛ በሆነ መልኩ መሻሻል ይኖርበታል ወይም እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት በፍርድ ቤት ትርጉም መደበኛ ባልሆነ መልኩ መሻሻል ይኖርበታል። ይህ ሳይሆን ሲቀር ህገ-መንግስቱ ያለውን ነባራዊ እና ፈጣን ለውጥ ማካተት ስለማይችል በኃይል/በአመጽ እንቅስቃሴ የመተካት ሁኔታ ሊያጋጥመው እንደሚችል ጥናቶቹ ያሳያሉ።

አሜሪካዊው የፖለቲካ ሳይንስ ጠቢብ ዶናልድ ሉትዝ የአንድ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ሰላማዊ ቆይታ በህገ-መንግስቱ የመሻሻል ምጣኔ (Ammendment Rate) ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይገልጻሉ። እንደ ፕሮፌሰሩ ጥናት የአንድ ህገ-መንግስት የመሻሻል ምጣኔ በሚከተለው ቀመር ይሰላል፤ ይህም የተደረጉ ህገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎች ለህገ-መንግስቱ እድሜ ማካፈል ነው። በዚህ ስሌት የሚገኝ ውጤት በ 0.75 እና 1.25 መካከል ከሆነ ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱ የተረጋጋ ይሆናል። ውጤቱ ከ 0.75 በታች ከሆነ ወይም ከ 1.25 በላይ ከሆነ ግን ህገ-መንግስቱ የመሞት አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን በመግለጽ የማሻሻያ ማድረግን አስፈላጊነት አጥብቀው ያስገነዝባሉ።

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ባለፉት ሰላሳ አመታት ሁለት ማሻሻያዎች ተደርገውበታል። ከዚህ አንጻር የሀገራችን ህገ-መንግስት የመሻሻል ምጣኔ (2/30= 0.06) ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ምጣኔ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው ምጣኔ አንጻር እጅግ አነስተኛ ነው። በዚህ ምክንያት ህገ-መንግስቱ በአፋጣኝ ሊሻሻል ይገባል። ህገ-መንግስቱን የማይሻሻል ወይም የማይነካ አድርጎ ማሰብ በራሱ ለህገ-መንግስቱ መቆየት አደጋ መሆኑን መረዳት እና ህገ-መንግስታዊ በሆነ መንገድ ማሻሻያ ካልተደረገበት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የመለወጥ አደጋ የተጋረጠበት መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል።

«የህገ-መንግስት ማሻሻያ ሃሳቡን ማነው ማመንጨት የሚችለው?» ከሚለው ጀምሮ "ማነው የሚያፀድቀው?" "እንዴት ነው የሚፀድቀው?" የሚሉት ጉዳዮች በጣም ወሳኝ ሲሆኑ የህገ-መንግስቱንም ባህሪ የሚወስኑ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ህገ መንግስቶች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን አንደኛው አይነት ለማሻሻል ቀላል የሆነ (Flexible) ሲሆን ሁለተኛው አይነት ደግሞ ለማሻሻል ከባድ የሆነ (Rigid) ተብሎ ይታወቃሉ። ለማሻሻል ቀላል የሆኑ ህገ-መንግስቶች ለምሳሌ በተወካዮች አማካይነት ብቻ ሊቀየሩ ይችላሉ። ለማሻሻል ከባድ የሆኑ ህገ-መንግስቶች ደግሞ የህዝብ ውሳኔ (referendum) ሊጠይቁ ይችላሉ።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ቀላልም ይሁን ከባድ ህዝቡን ያሳተፈ መሆን እንዳለበት ይገነዘባል። የህገ-መንግስት አፅዳቂ እና ባለቤት የአንድ አገር ህዝብ መሆኑን ከምናሳይበት መንገድ አንዱ አሳታፊ የሆነ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ስርአት ነው። አሳታፊነት ስንል ደግሞ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ሃሳብን ከማመንጨት ጀምሮ እስከ ውይይቱ (delibration) እና ማጽደቅን ይጨምራል።
የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት በአንቀጽ 104 እና 105 ስለ ህገ-መንግስት ማሻሻያ የሚተነትን ሲሆን ዘርዘር ያለ ስርአትም አስቀምጧል። በዚህም መሰረት «የህገ-መንግስቱ የማሻሻያ ስርአት ከባድ ተደርጎ ተቀምጧል» ለማለት ይቻላል። የህገ መንግስቱን አንቀፆችም ለሁለት በመክፈል የተለያየ የማሻሻያ ቅድመ ሁኔታዎች አስቀምጦላቸዋል።

የህገ-መንግስት ማሻሻያ ስርአት ህገ-መንግስታዊነትን (Constitutionalism) በሚሸረሽር መልኩ እንዳይተገበር ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን በተለይ የህገ-መንግስት ማሻሻያ የአንድ የፖለቲካ ቡድንን ጥቅም ብቻ በሚያስጠብቅ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዳይውል ማድረግ ያስፈልጋል። በተለያዩ የአለማችን

ክፍሎች መሪዎች በህገ-መንግስት ማሻሻያ በመጠቀም ስልጣናቸውን ሲያራዝሙ ተመልክተናል። በተመሳሳይ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ቅድመ ሁኔታን በጣም ከባድ በማድረግ ህዝቡ የሚፈልገውን ስርአታዊ ለውጥ እንዳያደርግ መከልከልም ከህገ-መንግስታዊ ስርዓት ተፃራሪ ነው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተዘረዘሩ ህገ-መንግስታዊ እሳቤዎችን ታሳቢ በማድረግ በስራ ላይ ያለው የህገራችን ሕገ-መንግስት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት «መሻሻል አለበት» ብሎ ያምናል።

1. .ሕገ-መንግስቱ የሀገራችንን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያስከብር፣ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን የሚያስጠብቅና ሀገራችን ካለችበት ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገትና አስከፊ ድህነት በፍጥነት እንድትላቀቅ በሚያስችል መልኩ ሊቃኝ ይገባል፣
2. የዜጎቻችንን ሰላምና ደህንነት የሚሸረሽሩ፣ መገንጠልና መለያየትን የሚጋብዙ አንቀጾች ብሄራዊ መግባባትን፣ አብሮነትና ወንድማማችነትን በሚያጠናክር መልኩ ሊሻሻሉ ይገባል፣
3. የሕገ-መንግስት አንዱ ባህሪ ለረዥም ጊዜ ማገልገል መቻሉ ነው። በመሆኑም ከሀገራችን የእድገት ደረጃ ጋር በየጊዜው ሊቀየሩ የሚገቡ ድንጋጌዎችን በሕገ-መንግስት ውስጥ ማካተት ህገ-መንግስቱ ወሳኝ የሆኑ ሀገራዊ ለውጦችን ማስተናገድ እንዳይችል በማሰር በአፈጻጸም ላይ ችግር ይፈጥራል። በመሆኑም በየጊዜው ሊቀየሩ የሚገባቸውን አንቀጾች ከህገ-መንግስቱ ማውጣት ያስፈልጋል፣
4. ሕገ-መንግስት የአንድ ሀገር ዜጎች የጋራ ሰነድ በመሆኑ የአብዛኛውን ህብረተሰብና የፖለቲካ አስተሳሰብ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። ይሁን እንጂ በሀገራችን እስከ ዛሬ በስራ ላይ የዋሉ ሕገ-መንግስቶች በጊዜው የነበሩ መንግስታት የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ፕሮግራም ቅጅ ስለነበሩ ፓርቲ እና መንግስትን መለየት አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም በስራ ላይ ያለው ሕገ-መንግስት ከገዥው ፓርቲ ርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ፕሮግራም ተለይቶ በሀገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችን አስተሳሰብና ፕሮግራምም ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሊሻሻል ይገባል፣
5. ቋንቋ፣ ባንዲራ፣ የክልሎች አመሰራረትና ወሰን የመሰሉ አሻሚና አላስፈላጊ ልዩነቶችና ግጭቶችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ህገ-መንግስቱ ግልጽና የማያሻማ መልስ ሊሰጥ በሚችል መልኩ ሊስተካከል ይገባል፣

3 ብሄራዊ እርቅ እና መግባባት

ብሄራዊ መግባባት በአንድ ሀገር ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተዋናዮች እና ባለድርሻ አካላት መካከል ጥልቅ የፖለቲካ ቀውስን ለማስወገድ፣ ጦርነትን ለማስቆም ወይም የተሳካ የፖለቲካ ሽግግር ለማካሄድ በአንድ ሀገር ባለቤትነት የሚካሄድ የፖለቲካ ሂደት ነው። ብሄራዊ መግባባት ለተለያዩ ዓላማዎች የሚካሄድ ሲሆን ዋና ዋና ዓላማዎቹ ከፍተኛ የፖለቲካ፣ የባህል ግጭቶችን ማስወገድ፣ የጦርነት ስጋትን ማምከን፣ የፖለቲካ ስርዓቱን ማሻሻል (ለምሳሌ ህገ-መንግስት ማሻሻል)፣ የመንግስት እና የዜጎችን ግንኙነት ማደስ/መልሶ መገንባት (New social contract)፣ ታሪካዊ ቁርሾዎችን ማከም ናቸው። እነዚህ ዓላማዎች የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ተብለው የሚከፈሉ ሲሆን የአጭር ጊዜ ዓላማዎች በዋናነት ቀውስ መከላከል እና ማስተዳደር ሲሆን የረዥም ጊዜ ዓላማ ስር ነቀል ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ለውጦችን ማምጣት ነው።

የተለያዩ ገፊ ምክንያቶች በአንድ ሀገር ውስጥ የብሄራዊ መግባባት ሂደት እንዲጀመር ሊያደርጉ ይችላሉ። ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ፣ በየጊዜው የሚሰፉ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የፖለቲካ ማሻሻያ ወይም የስርአት ለውጥ ጥያቄ፣ የፍትህ መጓደል፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነት፣ ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት ማጣት እና ተስፋ መቁረጥ፣ ግቡን የሳተ የለውጥ ሂደት፣ በፖለቲካ ልሂቃን መካከል እምነት መጥፋት፣ በቡድኖች መካከል ግጭት፣ የዜጎች ህይወትና ንብረት መጥፋት መፈናቀል፣ በጎረቤት/በሌሎች ሀገሮች የሚደረግ ፖለቲካዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ወዘተ ለብሄራዊ ውይይት መጀመር ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው የብሄራዊ መግባባት ሂደት በተለያዩ አካላት ጥያቄ ፤ በመንግስት፣ በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሲቪክ ማህበራት፣ በልሂቃን ድርድር (elite negotiation)፣ በውጭ ኃይሎች ጥያቄ እና ግፊት ወዘተ ሊጀመር ይችላል።

በታሪካዊ እና ነባራዊ ምክንያቶች የተነሳ በሀገራችን የብሄራዊ ውይይት እጅግ አስፈላጊ እና አጣዳፊ እንደሆነ በፖለቲካ ልሂቃን እና በመላው የሀገራችን ህዝቦች ዘንድ ሙሉ ስምምነት አለ። በኢትዮጵያ ብሄራዊ ውይይት እና

መግባባት ሂደት እንዲጀመር ከሚያስገድዱ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፤ ተገዳዳሪ የሀገረ መንግስት/ብሄር ግንባታ ትርክቶች፣ ዋልታ ረገጥ የፖለቲካ አጀንዳዎች፣ ባህል እና ፖለቲካዊ ዓላማ፣ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል አለመተማመን እና ጥላቻ፣ ጸረ-ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች የፈጠሩት ቀውስ/ውርስ፣ የመንግስት እና የዜጎች ኢፍትሀዊ መስተጋብር፣ ድህነት እና ፍትሀዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል፣ ያልተፈታ የማንነት/የብሄር ጥያቄ፣ አግላይ የፖለቲካ ስርአት እና የተዛባ የስልጣን ክፍፍል፣ ታሪካዊ የተበዳይነት ስሜት (Real or Perception) ይገኙበታል።

ከነዚህ ታሪካዊ ምክንያቶች በተጨማሪ የሚከተሉት አሁናዊ ምክንያቶችም ብሄራዊ ውይይት በአፋጣኝ እንዲጀመር ምክንያት ይሆናሉ። የግጭቶች መበራከት፣ የዜጎች ሞት፣ መፈናቀል፣ ንብረት መጥፋት...፣ የብሄር እና "የኃይማኖት" ግጭቶች መበራከት፣ ሀገራዊው የለውጥ/ሪፎርም ሂደት ከዜጎች ፍላጎት ጋር መጋጨት፣ በለውጥ ማግስት የተሻሻለው የፖለቲካ ምህዳር መልሶ "የመጥበብ" አዝማሚያ፣ ምርጫ 2013፣ በፌደራል እና በክልል መንግስታት እንዲሁም በክልል መንግስታት መካከል ያሉ ግጭቶች፣ ስራ አጥነት ፣ የኑሮ ውድነት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት ወዘተ።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሀገራችንን ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች ለመፍታት ብሄራዊ ውይይት ተካሂዶ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ከስምምነት ላይ መደረስ አለበት ብሎ ያምናል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን፣ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል መተማመን ለመፍጠር፣ ቀጣዩ ሀገር አቀፍ ምርጫ ነጻ፣ ፍትሀዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን ለማድረግ፣ በፖለቲካ ልሂቃን ስምምነት የኢትዮጵያን አዲስ የፖለቲካ ፍኖተ ካርታ ለመንደፍ፣ የተዛነፈውን የለውጥ/ሪፎርም/ ሂደት ለማረቅ ብሄራዊ ውይይት እጅግ አስፈላጊ እና አንገብጋቢ የፖለቲካ አጀንዳ እንደሆነ በጽኑ ያምናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከምስረታው ማግስት ጀምሮ ባለፉት ሁለት አመታት ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ውይይት እንዲካሄድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ በዋናናት መንግስት ለጉዳዩ በሰጠው ዝቅተኛ ትኩረት ምክንያት ብሄራዊ ውይይት ሳይካሄድ ኢትዮጵያ ወደ 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ዝግጅት ገብታለች። ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ውይይት ሳይካሄድ ምርጫ ማካሄድ በምርጫው ሂደት እና ውጤት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይረዳል። ከዚህ ስጋት በመነሳት ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከምርጫ በፊት ባሉት እጅግ ጠባብ ጊዜያት ቢያንስ ለምርጫው ነጻነት እና ሰላማዊነት በሚረዱ አጀንዳዎች ላይ ብሄራዊ ውይይት መካሄድ እንዲችል አበክሮ ያሳስባል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ለብሄራዊ ውይይት እና መግባባት እስከ አሁን የሰጠውን ትኩረት አጠንክሮ በመቀጠል ከምርጫ በኋላም ብሄራዊ ውይይት እና መግባባት እንዲፈጠር ሰፊ ስራ ይሰራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በምርጫው የሚያገኘውን ውጤት ተንተርሶ በሚያገኘው ፖለቲካዊ አቅም፣ ድህረ ምርጫ ኢትዮጵያ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው አጀንዳዎች ውስጥ ብሄራዊ መግባባት አንዱ እና ዋነኛው ይሆናል።

4 የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት

ነጻና ፍትሃዊ የምርጫ ውድድር የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ መገለጫ ከመሆኑም በላይ በምርጫ ወደ ስልጣን መምጣትም ሆነ ስልጣን ላይ መቆየት አንድ መንግስት ለሚኖረው ቅቡልነት ወሳኝ ነው። ምርጫ ህዝብ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት መሆኑ የሚረጋገጥበት እንዲሁም መንግስት በየዘመኑ በህዝብ ድምጽ በሚታደስ ጊዜያዊ-ውል ሀገር የሚያስተዳድር ስለመሆኑ የሚፈተንበት መንገድ ነው። ይሁንና ምርጫ ማድረግ በራሱ ግብ አለመሆኑንና ብቻውን ወደ ዲሞክራሲ የማያደርስ መሆኑን ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የተደረጉ ምርጫዎች በቂ ማሳያ ናቸው። እነዚህ ምርጫዎች በቂ ውድድር የማይደረግባቸው፣ ከምርጫው ቀን በፊት ስልጣን ላይ ያለው አካል ቀድሞ አሸናፊ የሚሆንባቸው፣ የሊጋሽ ሐገሮችን ፍላጎት ለማሟላት ሲባል ብቻ ለይስሙላና ለታይታ የሚደረጉ ውድድሮች ናቸው። እንዲህ አይነት ምርጫዎች ዲሞክራሲን ከማስፈን ይልቅ አምባገነናዊ ስርዓት ህጋዊነት እንዲላበስ በማድረግ እድሜው እንዲረዝም ያደርጋሉ።

ምርጫ ለዲሞክራሲ መጎልበት ፋይዳ እንዲኖረው ውድድሩ ነጻና ፍትሃዊ መሆን ይገባዋል። ለዚህም የፖለቲካ ምህዳሩ ወይም የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳው መስተካከል ይኖርበታል።

4.1.1 የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር ምንነት

በአፍሪካ በተለይ ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገራት በየጊዜው ምርጫ ቢያደርጉም፣ የምርጫ ውድድሩ ለዲሞክራሲ ስርዓት ሽግግርም ሆነ መደላደል ይህ ነው የሚባል አስተዋጾ አላደረገም። በእነዚህ ሐገራት አሁንም ድረስ ከፊል/ ፍጹም አንባገነናዊ ስርዓት መስፈኑን፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚጣሱ መሆኑንና የመንግስት አሰራር ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አለመሆኑን ጥናቶችና መረጃዎች ያሳያሉ። በነዚህ ሀገራት የሚደረገው ምርጫ በእንከኖች የተሞላና ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት በተግባር ማረጋገጥ አልተቻለም። በነዚህ ሀገራት የሚካሄዱት ምርጫዎች ነጻና ፍትሃዊ ባለመሆናቸው ምክንያት ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ለዲሞክራሲ ሽግግርም ሆነ መደላደል ይህ ነው የሚባል አስተዋጾ አላደረገም። ለዚህም ስልጣን ላይ ባለው አካልና በምርጫው በሚሳተፉት ሌሎች ኃይሎች ወይም የፖለቲካ ተወዳዳሪዎች መካካል የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር አለመኖር እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳል። ይሁንና ስለ ፖለቲካ ምህዳር መስተካከል አስፈላጊነት በመሪዎች፣ በሚዲያ እንዲሁም በሙህራን የሚነገረውን ያህል ስለጽንሰ ሀሳቡ ምንነት፣ የመስተካከል መጠኑ ስለሚለካበት አግባብና አመላካች መለኪያዎች ጉዳይ ወጥ በሆነ መልኩ ብዙም አለመባሉ ስልጣን ላይ የመቆየት ፍላጎትና ህልም ላላቸው የአፍሪካ መሪዎች መልካም አጋጣሚ ሆኗል። በመሆኑም የፖለቲካ መጫዎቻ ሜዳውን ለራስ በሚመች መልኩ በማዘጋጀት ተፎካካሪዎቻቸውን በቀላሉ በማሸነፍ ምርጫን "የተበላ እቁብ" ማድረግ ችለዋል።

በፖለቲካ ምህዳር ዙሪያ እ.ኤ.አ. 1990ዎቹ ጀምሮ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን በዋናነት በ Levitsky and Way የቀረበውና በኃላም በ Svein-Erik Helle የዳበረው ሐሳብ ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ከማድረግና የቀደሙ ስራዎችን ክፍተት ከመሙላት አንጻር የጎላ አበርክቶ አድርጓል። በነዚህ ሙህራን አገላለጽ የፖለቲካ ምህዳር (political playing field) በዋናነት የመንግስት ሥልጣን ላይ ባለው የፖለቲካ ኃይል እና በሌሎች ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ውጤታማ የሆነ የምርጫ ውድድር ለማድርግ ያለውን ምቹ ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ይህም በዋናነት ስልጣን ላይ ባለው ፓርቲ (incumbent) እና በተፎካካሪዎች (Oppositions) መካከል በሀብት፣ ሚዲያ እና ተቋማት ላይ በሚኖር ሚዛኑን የጠበቀ ተደራሽነት (a balanced access to resources, media and state institutions) የሚወሰን ይሆናል።

ስለዚህ የፖለቲካ ምህዳር የፖለቲካ ተፎካካሪ የሆኑ አካላት ማለትም የመንግስት ስልጣን በያዘው አካልና በተቃዋሚዎች መካከል ሀብትን፣ መገናኛ ብዙሃንን እንዲሁም ህግን ጨምሮ ተቋማትን በእኩልነትና ሚዛናዊነት ለመጠቀም ያለውን ምቹ ሁኔታ ይመለከታል። የፖለቲካ ምህዳሩን ማስተካከል በዋናነት የመንግስት ስልጣን የያዘው አካል ኃላፊነት ሲሆን ይህ አካል ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እነዚህን ሶስት ነገሮች ለማግኘትም ሆነ ለመጠቀም እንዲችሉ አስቻይና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርበታል። የሚፈጠረው ምቹ ሁኔታም በምርጫው የሚፎካከሩትን ሁሉንም ኃይሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚጠቅም መሆን ይገባዋል።

በዚህም መሰረት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሐብትን፣ ሚዲያንና ተቋማትን ለማግኘትና ለመጠቀም የሚኖራቸው እኩል እድል የፖለቲካ ምህዳሩን ያስተካክለዋል። በሌላ በኩል የመንግስትን ስልጣን የያዘው ገዥ ፓርቲ እጁ ላይ ያለውን መንግስታዊ ስልጣን አላግባብ ተጠቅሞ በሀብት፣ ሚዲያ እንዲሁም ተቋማትን በሚመለከት ለራሱ የሚፈጥረው የተሻለ እድልና ይህ ሁኔታ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ሁለተናዊ አቅምና ተወዳዳሪነት ላይ የሚፈጥረው እክል የፖለቲካ ምህዳሩን ያልተስተካከለ (uneven) ያደርገዋል። በእንዲህ አይነት ወደ አንድ ወገን ባዘነበለ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ ላይ የሚደረግ የምርጫ ውድድር ለዲሞክራሲ መወለድም ሆነ ማደግ ምንም አይነት ፋይዳ አይኖረውም።

4.1.2 የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር መለኪያዎችና ጠቋሚዎች

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የፖለቲካ ምህዳር የተስተካከለ መሆን አለመሆኑን የሚወስኑት ሶስት ነገሮች ማለትም ሀብት፣ ሚዲያና ተቋማት ሲሆኑ እነዚህ ግብዓቶች በጋራ ተጣምረው ሲገኙ የተስተካከለ ምህዳር ይፈጥራሉ። ከሶስቱ አንዱ ላይ የሚኖረው መጓደል

በዛው መጠን የመጫወቻ ሜዳው እንዳይስተካከል ያደርገዋል።

ሐብት/ገንዘብ

ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳን ጨምሮ የተለያዩ የፖለቲካ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል በቂ ሀብት ለማግኘት ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል። የግል ዘርፉ ብዙም ባላደገበትና መንግስት ዋነኛው የልማት አንቀሳቃሽ ሞተር በሆነበት አፍሪካ ከመንግስት የሚደረገው ድጎማ ዋነኛ የፓርቲዎች ገንዘብ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የመንግስትን ሐብት ለራሱ የፖለቲካ ስራ በብዛት በመጠቀም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት ተንቀሳቅሰው አባላት በማፍራት አባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ገንዘብ ማሰባሰብ እንዳይችሉ በማድረግ፣ ባለሀብቶች ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ገንዘብ እንዳይለግሱ ወዘተ የተለያዩ ጫናዎችን ይፈጥራል።

ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የሀብት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ የገንዘብ ምንጮችን በመከልከል፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚሰጥ ድጋፍ እንዳይኖር በማድረግ፣ ድጋፍ በሚሰጥበት ጊዜም የድጋፍ አሰጣጥ መስፈርቱ ለገዢው ፓርቲ ያጋደለ እንዲሆን በማድረግ እንዲሁም ለሌሎች ባልተፈቀደ እንቅስቃሴ ለምሳሌ ንግድ ውስጥ በመግባት ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የራሱን የሀብት የበላይነት በተቃዋሚዎቹ ላይ ሊፈጥር ይችላል። ይህም የመንግስት ስልጣን በያዘው ፓርቲና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ከፍተኛ የሀብት ልዩነት በመፍጠር የፖለቲካ ምህዳሩ እንዳይስተካከል ያደርጋል።

ሚዲያ

ሚዲያ በፖለቲካ ውድድር ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የግል፣ የመንግስት፣ የአካባቢያዊና ማህበረሰብ ሚዲያዎችን እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያን ለመጠቀም የሚኖረው የተሻለ እድል የፖለቲካ ምህዳሩን ያልተስተካከለ ያደርገዋል። በመሆኑም የመንግስት ሚዲያዎች ለገዥው ፓርቲ በማድላት መሳሪያ ከመሆን ወጥተው ለሁሉም ፓርቲዎች በእኩልነት ሽፋን መስጠት ይኖርባቸዋል። የግል ሚዲያዎች ስልጣን ላይ ካለው ፓርቲም ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ወገንተኝነት ነጻ በመሆን መንግስትንም ሆነ ተቃዋሚዎችን በፍትሀዊነት የሚያገለግሉና የሚተቹ መሆን ይኖርባቸዋል። በመሆኑም የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር እንዲኖር የግልም ሆኑ የመንግስት ሚዲያዎች እንዲሁም የአካባቢና ማህበረሰብ ሚዲያዎች ለሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ማገልገል ይገባቸዋል።

ተቋማት

የተቋማት ጉዳይ ህጎችንና እነዚህን ህጎች የሚያስፈጽሙ አካላትን ነጻነትና ገለልተኝነት የሚመለከት ሲሆን የተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር እንዲኖር የሁሉንም መብት በእኩል የሚያስጠብቅ የህግ ማእቀፍ ሊኖር ይገባል። በተለየ መልኩ ተቃዋሚዎችን ለማፈንና እንቅስቃሴያቸውን ለመገደብ ወይም ስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ፍላጎት ለማስጠበቅ በሚል የሚወጡ ህጎች የፖለቲካ ምህዳሩ እንዳይስተካከል ያደርጋሉ። ለተስተካከለ የፖለቲካ ምህዳር ነጻና ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም እንዲሁም ፍርድ ቤት ሊኖር ይገባል። ገለልተኛና ነጻ ያልሆነ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበትና ፍትህ የሚያገኙበት በነጻነት የሚሰራ ገለልተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም ከፖለቲካ ነጻ የሆነ ሁሉንም በእኩልነት የሚያገለግል የጸጥታ መዋቅር በሌለበት ሁኔታ የፖለቲካ ምህዳሩ ሊስተካከል አይችልም።

በመሆኑም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተዘረዘሩትን የንድፈ ሀሳብ እና ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ በተለይ ገዥው ፓርቲ ከምርጫ በፊት የፖለቲካ መወዳደሪያ ሜዳውን በማስተካከል ለሁሉም አካላት ምቹ እንዲያደርግ በጽኑ ያሳስባል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የሚካሄድ ምርጫ በሂደቱም በውጤቱም ነጻ እና ተአማኒ ሊሆን አይችልምና።

5 እውነተኛ ፌዴራሊዝም

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዝሃን ሀገር ናት። የተለያዩ ብሔረሰቦች፣ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ የተለያዩ ባህሎችና እምነቶች የሚገኙባት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ የተለያየ የመንግስት ስርዓትን አስተናግዳለች። ወታደራዊው የደርግ መንግስት ኢትዮጵያን ከአሀዳዊው የፊውዳል ሥርዓት-መንግስት ወደ አሀዳዊ የሶሻሊስት የመንግስት ስርዓት ቀይሮታል። የደርግ ዘመነ-መንግስት "መሬት

ላራሹ” የሚለውን መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄ መመለስ ቢችልም የዜጎችን ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄን በተሟላ መልኩ መመለስ አልቻለም። በዚህም የተነሳ የተለያዩ ‹ነፃ አውጪ› ግንባሮች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እንደ አሸን ፈልተዋል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ብሔረሰቦች ነፍጥ አንስተው የትጥቅ ትግል አካሂደዋል። በመጨረሻም የደርግ መንግስት ወድቆ የኢህአዴግ መንግስት ተመስርቷል።

የኢህአዴግ መንግስት የብሄረሰቦችን ጥያቄ ዋነኛ የፖለቲካ ትርክት በማድረግ የብሔረሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ህገ-መንግስታዊ በሆነ መልኩ ለመመለስ ጥረት እንዳደረገ ላለፉት 27 ዓመታት ሲሞግት ቆይቷል። ኢህአዴግ የመንግስትን አወቃቀር ከአሀዳዊ ስርአት ብሔርን መሰረት ወዳደረግ የፌደራሊዝም ስርዓት ቀይሮታል። ምንም እንኳን ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመማር እና ራሳቸውን የማስተዳደር አንፃራዊ መብት ማግኘት ቢችሉም በህገ-መንግስቱ ቃል የተገባውን እውነተኛና ያልተማከለ የፌደራል ስርአት በተግባር ማዋል አልተቻለም።

ይልቁንም በፖለቲካ ማዕከላዊነት ስም ገዢው ፓርቲ ሥልጣንን ጠቅልሎ በመያዝ ክልሎችን በሞግዚትነት ሲያስተዳድር ቆይቷል። በዚህም የተነሳ የክልል መስተዳድሮች ተጠሪነታቸውና ታማኝነታቸው ለሚያገለግሉት የክልሉ ህዝብ መሆኑ ቀርቶ በማዕከል ላይ ለሚገኙ፣ በጣት ለሚቆጠሩ የገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ልሂቃን ሆኖ ቆይቷል። በተለይ ደግሞ ሶማሌ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላና ሀረሪን አጋር ፓርቲ ብሎ በመፈረጅ በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ ምንም ዓይነት ውሳኔ ሰጪ መሆን ሳይችሉ የዳር ተመልካች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በተቀሩትም ክልሎች ቢሆን የክልል አመራሮች የህዝብን ጥያቄ ከማስተናገድ ይልቅ በገዥው ፓርቲ የተለያየ ስም ተሰጥቷቸው ተሸማቀው እንዲኖሩ ተደርገዋል። በኢህአዴግ የአስተዳደር ዘመን እውነተኛ ፌደራሊዝምም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መተግበር ሳይቻል ቀርቷል።

በፌደራሊዝም ስም ገዥው ፓርቲ ከሁለት አስርተ አመታተ በላይ የወሰዳቸው ኢፍትሀዊ እና ኢዴሞክራሲያዊ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና አሰራሮች በሀገራችን ውስጥ የነበረውን የነጻነት፣ የእኩልነት እና የፍትህ ጥያቄ ይበልጥ እንዲጎመራ አድርጎታል። መንግስት በዜጎች ላይ የሚያደርሰው ግፍ እና በደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመላ ሀገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሰፊ ህዝባዊ ተቃውሞ እና አመጽ ቀስቅሷል። በውጤቱም ገዢው አውራ ፓርቲ ተፍረክርኮ ለህዝብ ጥያቄዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን መልስ እንዲሰጥ ተገዷል።

ሰጠቃለል ባለፉት 30 ዓመታት በሀገራችን እየተተገበረ ያለው የፌደራል ስርአት በርካታ ችግሮች ያሉበት ሲሆን የሚከተሉት አንኳር ማነቆዎችን ማንሳት ይቻላል።

1-እውነተኛ ፌደራሊዝም አልነበረም

ምንም እንኳን በመዋቅር ደረጃ የክልልና የፌደራል መንግስት ቢኖርም በተግባር ግን ግልፅ የሆነና ከህገ-መንግስቱ በተፃረረ መልኩ የስልጣን ጣልቃ ገብነትና የእጅ አዙር አስተዳደር ሲተገበር ቆይቷል። በመሆኑም ገዥው ፓርቲ ሲከተለው የነበረው አካሄድ ክልሎች ራስን በራስ የማስተዳደር ህገ-መንግስታዊ መብቶቻቸውን በተገቢው እንዳይጠቀሙ ሙሉ ለሙሉ እድል ነፍጓቸዋል። በዚህም የተነሳ ፌደራሊዝሙ የሚጠበቀውን ፍሬ ማፍራት አልቻለም።

2- ዴሞክራሲ አልባ ነበር

ፌደራሊዝም ያለ ዴሞክራሲ እውን መሆን አይችልም። ኢትዮጵያ ላለፉት 30 ዓመታት የተለያዩ ምርጫዎችን ማካሄድ ብትችልም በክልልም ይሁን በፌደራል ደረጃ ህዝቡ የሥልጣን ባለቤት ሆኖ ያመነበትን መርጦ ባመነበት መሪ መተዳደር አልቻለም። ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ታሪክ አንድም ጊዜ እውን ሆኖ አያውቅም። በመሆኑም የፌደራል ሥርዓቱን አምባገነናዊና ተቀባይነት የሌለው አድርጎታል። የዴሞክራሲ ጉድለት (Democratic deficit) ባለበት ሀገር የፌደራል ስርአት ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል የበርካታ ሀገሮች ተሞክሮ ያሳያል።

3-የግለሰቦችንና የህዳጣን መብት ማክበር አልቻለም

በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ዜጎችና ህዳጣን የተሟላ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ሲጣሱ ቆይተዋል። በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት አይነት ዜግነት

ሲተገበር ቆይቷል። በመሆኑም አናሳ ቁጥር ያላቸው እና በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ዜጎች በፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተገልለው የሁለተኛ ዜግነት እንዲሰማቸው ተደርገዋል። በዚህም የተነሳ የፌዴራል ሥርዓቱን ፍትሀዊነት ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል።

4-ግጭትና መፈናቀል

ምንም እንኳ የፌደራሊዝም ስርዓት ብዝሀነትን ለማስተናገድ ተመራጭ ነው ቢባልም ሀገራችን ውስጥ በርካታ ግጭቶች ተከስተዋል፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት ተቀጥፏል፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል። ገዥው ፓርቲ እድሜውን ለማራዝም ሲል "በከፋፍለህ ግዛ" እና ልዩነትን በሚያጎሉ ትርክቶችና ዜጎችን እርስ በእርስ እንዳይተማመኑ ብሎም እንዲጋጩ ሰፊ ስራ ሰርቷል። ግጭቱ ተቋማዊ መልክ እንዲይዝ አድርጓል።

5-የህግ የበላይነት አለመከበር

ኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የማይከበርባት ሀገር ሆናለች። የማዕከላዊ መንግስትም ይሁን የክልል መስተዳድር አካላት በህግ ከተሰጣቸው ስልጣን በተጻጻሪ የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚጥሱ በርካታ ህገወጥ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ማየት የተለመደ ተግባር ሆኗል። በህግ ማስከበር ስም በርካታ ህገ-ወጥ እና የህግ የበላይነት መርህን የሚጻረሩ ስራዎች ይሰራሉ። የህግ የበላይነት አለመከበር የሀገራችን ህዝቦች ከፌደራል ስርአቱ የሚጠብቁትን ፍሬ እንዳያጣጥሙ አድርጓቸዋል። ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት አለመኖር፣ የዜጎች በህግ ፊት እኩል አለመሆን፣ ከህግ የበላይነት ይልቅ ለገዥው ፓርቲ ፍላጎት እና ፕሮግራም ቅድሚያ መስጠት፣ የፌደራሊዝም ስርዓቱ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገባ እና ውጤታማ እንዳይሆን ትልቅ እንቅፋት ሆኗል።

6-ሀገራዊ አለመግባባት

ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ ተስማሚ የመንግስት ስርአት ነው ሲባል «የሀገራችንን የብዝሀነትን ጥያቄ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሀገራዊ መግባባትና አንድነት እንዲያሰፍን እንዲሁም አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል።» ከሚል እምነት በመነሳት ነው። በተግባር የሆነው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። በአሁኑ ወቅት ቁልፍ እና መሰረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች እንኳን የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ አልተቻለም። ይልቁንም በተለይም በልሂቃን መካከል እየሰፋ የመጣው ልዩነታችን አልፎ አልፎ ወደ ህዝብ እየወረደ ለግጭት እና ሀገራዊ አለመረጋጋት ምክንያት ሆኗል።

በሀገራችን የፌደራል ስርአቱ የተጋረጡበትን ከላይ የተጠቀሱ አንኳር ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ህብረ-ብሄራዊ ጠንካራ የፌዴራል ስርአት በሀገራችን እንዲገነባ ለማድረግ **ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ** ሰፊ የማስተካካያ እርምጃዎችን ይወስዳል።

ከዚህ አንጻር በሀገራችን ያለውን ከፍተኛ የዴሞክራሲ ጉድለት በመሙላት እውነተኛና ዴሞክራሲያዊ የፌደራል ስርአት እንዲገነባ ምቹ የፖለቲካ እና የህግ ማዕቀፍ ይፈጥራል። ሀገራዊ አንድነት ብዝሃነትን ባከበረ መልኩ እንዲተገበር፣ የህዳጣን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ በተሳሳተ የፌደራሊዝም አተገባበር ምክንያት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰውን የወሰን እና ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ለማስወገድ፣ ሀገራዊ መግባባትን ለመፈጠር እና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ሰፊ የመዋቅር ማሻሻያ ስራዎች ይሰራሉ።

በክልሎች መካከል እኩልነት እንዲኖር ፍትሀዊ እና ተመጣጣኝ የሀብት እና የፖለቲካ የኃይል ሚዛን እንዲፈጠር የሚያስችል የህግ ማእቀፍ ይዘጋጃል። ክልሎች በማዕከላዊ መንግስቱ ላይ ተመጣጣኝ ውክልናና ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያስችል አውድ እንዲኖር፣ በህዝቦች መካከል፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጠንካራ ትስስርና መተማመን እንዲፈጠር ይደረጋል። በክልሎችና በፌደራል መንግስት መካከል የሚኖረው የስልጣን ክፍፍል ክልሎች ያለምንም ጣልቃ ገብነት ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን ሙሉ ለሙሉ መተግበር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። የሚገነባው የፌደራል ስርዓት የክልሎች የድንበር አወሳሰን የህዝብ ፍላጎትን፣ ቋንቋና ባህልን፣ ያስተዳደር ምቹነትና፣ መልክዓ-ምድርን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል።

6 ፓርቲ እና መንግስትን መለየት

ባለፉት ሶስት አስርት አመታት በሀገራችን ከታዩ መሰረታዊ የፖለቲካ ችግሮች አንዱ የፓርቲ እና የመንግስት መቀላቀል የፈጠረው ውስብስብ ሂደት ነው። የመንግስት ስልጣንን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው ገዥ ፓርቲ የመንግስትን መዋቅር እና ሀብት በመጠቀም በትረ ስልጣኑን ለማራዘም ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንገዶችን ሲጠቀም ቆይቷል። በአንጻሩ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በመገደብ አመራሮቻቸውን እና አባላቱን በማሰርና በማዋከብ የሀገራችን የፖለቲካ ምህዳር እንዲጠብ ሲያደርግ ቆይቷል።

በሀገራችን በተጀመረው የለውጥ ሂደት ከሚጠበቁ ውጤቶች አንዱ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት እና በእኩልነት የሚደራጁበትና ስራቸውን በነጻነት የሚያካሂዱበት ስርአት መፍጠር ነው። ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት ውስጥ፣ ገዥው ፓርቲ እንደ አንድ ፓርቲ የሚታይና የገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች ከመንግስት መዋቅር ሙሉ ለሙሉ ተለይተው የሚካሄዱበት ይሆናሉ። የገዥው ፓርቲ የሀብት ምንጭ እንደ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአባላቱ እና ከደጋፊዎቹ ብቻ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ ከመንግስት ካዝናም ይሁን፣ ማንኛውንም የመንግስት መዋቅር ተጠቅሞ ሀብት የመሰብሰብ መብት አይኖረውም።

ይህ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሁላችንም ስንጠብቀው የቆየነው የመንግስት እና የፓርቲ ልዩነት በትክክል እየተተገበረ አይደለም። ይህም የለውጡን መንፈስ እና አዲሱን የምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ በእጅጉ የሚቃረን ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ገዥው ፓርቲ የተለያዩ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን በመጠቀም ከባለሀብቶች ገንዘብ ሲሰበስብ የቆየ ሲሆን ይህ አሰራር በተለያዩ ክልሎችም በስፋት እየተፈጸመ ይገኛል። በተመሳሳይ በፌደራል እና በክልል መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች የፓርቲ አባልነት መዋጮ በፔሮል ከደመወዛቸው ላይ የመቁረጥ አሰራር ዛሬም ድረስ እንዳልቆመ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ እና ሌሎች አሰራሮች ፓርቲ እና መንግስትን በማቀላቀል በሀገራችን የሚፈለገው ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት አዳጋች አድርገውታል።

ገዥው ፓርቲ የመንግስት መዋቅርን በመጠቀም እና ባለሀብቶች ላይ ጫና በመፍጠር የሚያጋብሰው ከፍተኛ ገንዘብ፣ ፓርቲዎች ከደጋፊዎቻቸው በሚያገኙት ገቢ ላይ ተመስርቶ ከምርጫ ቦርድ በሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ላይ ኢ-ፍትሀዊ ክፍፍል እንዲፈጠር የሚያደርግ በመሆኑ የፖለቲካ ምህዳሩን በከፍተኛ ደረጃ ያዛንፋል። ፓርቲ እና መንግስት በተቀላቀሉባት ሀገር ፓርቲው ችግር ውስጥ ሲወድቅ ዳፋው ለሀገር ይተርፋል። ፓርቲ እና መንግስት የመለየት አስፈላጊነት ላይ ጽኑ እምነት ያለው ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከዚህ አንጻር የሚከተሉትን የአሰራር ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል፣

- በዴሞክራሲ፣ የፍትህ እና የጸጥታ ተቋማት ውስጥ የሚመደቡ ኃላፊዎች ከፓርቲ አባልነታቸው እንዲለቁ፣
- መንግስታዊ አገልግሎት ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ በማድረግ በክልልም ሆነ በፌዴራል መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የሆኑ የመንግስት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚሰጡትን አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ በእኩልነት እንዲሰጡ፣
- ገዥው ፓርቲም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከደጋፊዎቻቸው የሚሰበስቡትን ድጋፍ ከመንግስት መዋቅር ውጪ በፓርቲ ድርጅታዊ መዋቅር ብቻ እንዲያካሂዱ፣
- በተለይ ሀገርን የሚያስተዳድር ገዥ ፓርቲ ለሀብት ማሰባሰብ ለባለሀብቶች የሚያደርገውን ጥሪ ከመንግስት መዋቅር ውጪ ግልጽ በሆነ መንገድ በፓርቲው ስም እንዲያከናውን፣ ለፓርቲው ሀብት ማሰባሰብ ስራ ላይ የሚሰማሩ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የመንግስት ስልጣናቸውን ተጠቅመው ጫና ከማሳደር እንዲቆጠቡ፣
- የፖለቲካ ፓርቲው በፌደራል መንግስት እና ክልል መስተዳድር ውስጥ ከሚሰሩ አባላቱ የሚሰበስበው የአባልነት መዋጮ ከመንግስት መዋቅር ውጪ በራሱ በፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር እና ጽ/ቤት እንዲሰበስብ፣

7 የዜጎች ሰብአዊ መብት

ሰብአዊ መብቶች

ሰብአዊ መብት አንድ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ የሚቀዳጀው፣ ከልደቱ እስከ ህልፈቱ የሚጎናጸፈው፣ በጊዜ እና ቦታ የማይገደብ መብትን ያካትታል። በህይወት

የመኖር፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመስራት እና ሀብት የማፍራት፣ ከፍርሀት ነጻ የመሆን፣ ቤተሰብ የመመስረት፣ በህግ ፊት እኩል የመሆን፣ ጥገኝነት የማግኘት… ወዘተ ከሰብአዊ መብቶች ጥቂቶቹ ናቸው። ከእነዚህ መብቶች በተጨማሪ የቡድን መብት፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መብቶች፣ የመልማት መብት፣ የባህል መብት … ወዘተ የሰብአዊ መብቶች አካል ተድርገው ይቆጠራሉ።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሰብአዊ መብት መከበር የኢትዮጵያ ቁጥር አንድ አጀንዳ መሆን አለበት ብሎ ያምናል። አገራችን ላይ እየተፈጠሩ ያሉት የሰላም እጦት፣ የዜጎች ሞት እና መፈናቀል፣ የፖለቲካ ቀውሶች፣ እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መሰረታዊው ምክንያት የዜጎች ሰብአዊ መብቶች አለመከበር የወለዳቸው ናቸው። በሀገራችን የሰብአዊ መብቶች ለገዥ መደቦች የተከለለ የጥቂቶች መብት ብቻ ሆኖ፣ ሰፊው የሀገራችን ህዝብ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እየተጣሱ ዛሬ ላይ ደርሰናል። ይህ የተሳሳተ የሰብአዊ መብት አያያዝ ታሪክ እና አሁናዊ ሀቅ በአፋጣኝ ሊሻሻል ይገባዋል። ባለፉት ጥቂት አመታት የሰብአዊ መብት አያያዝ ለማሻሻል የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ስር የሰደደውን የሀገራችንን የሰብአዊ መብት አያያዝ ችግር ሊቀርፉ አልቻሉም። ለዚህም ዋናው ምክንያት ችግሩ መዋቅራዊ መሆኑ እና ላለፉት ሶስት አስርት አመታት በሀገራችን የነገሰው ኢ-ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ህዝባችንን ከሰብአዊ መብቶች ቀውስ አዙሪት ለማውጣት የሚያስችል የሰብአዊ መብቶች ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስልቶችን በዝርዝር ያወጣ ሲሆን፣ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ለማድረግ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል።

1. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ «የቡድንና የግለሰብ መብቶች ለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሚያስፈልጉና ተጣጥመው መተግበር የሚችሉ ናቸው።» ብሎ የሚያምን ሲሆን የግል እና የቡድን መብቶችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. ለሀገር ሰላምና ጸጥታ ወይም ለጠቅላላው ህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብአዊ መብቶች ላይ ገደብ ሊደረግ የሚችል መሆኑን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ያምናል። ነገር ግን ይህን ሁኔታ የመንግስት አካላት የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች ለመርገጥ እንደ ቀዳዳ እንዳይጠቀሙበት ዋስትና የሚሰጥ አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፣
3. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በህግ አውጪው አካል ተቀባይነት ያላገኙ እና በአስፈጻሚው አካል ውሳኔ ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ የሰብአዊ መብቶችን የሚገድቡ አሰራሮችን ሙሉ ለሙሉ ያስቆማል። በዚህ መሰረት የትኛውም የመንግስት አካል በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት የሰብአዊ መብቶች ላይ እቀባ ሊያደርግ አይችልም፣
4. ሰብአዊ መብቶችን መንግስት ራሱ ከማክበርና ከማረጋገጥ በተጨማሪ ከሶስተኛ ወገን በኩል የሚቃጣን የመብት ጥሰት የመከላከል ግዴታ አለበት። መንግስት ይህን ግዴታ ሣይወጣ ሲቀር ከጥቃት አድራሹ እኩል ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል።
5. የሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ መንግስት አራት አይነት ግዴታዎች ያሉበት ሲሆን እነዚህም የሰብአዊ መብትን ማክበር፣ ማስከበር፣ ማሟላትና የማቀንቀን ናቸው። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ እነዚህን የመንግስት ግዴታዎች ለመተግበር በከፍተኛ ኃላፊነት ይሰራል፣
6. በሰው ኃይል፣ በፋይናንስ፣ በሎጂስቲክ፣ በቴክኖሎጂ … ወዘተ የተጠናከረ የሰብአዊ መብት ተቋም በማደራጀት በሀገራችን የሰብአዊ መብቶች በተሻለ ሁኔታ እንዲከበሩ በትኩረት ይሰራል፣
7. የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት በማቋቋም በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እልባት እንዲያገኙ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
8. የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ

8 የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ

ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ታሪካዊ ዳራ

የግለሰብ መብቶች እንዲከበሩ ከማድረግ ባሻገር ዜጎች በቡድን የራሳቸው ማንነት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ እና እሴቶች ያሏቸው እንደመሆኑ መጠን በዲሞክራሲያዊ ስርአት የብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የማንነት (identity) እና የእውቅና (recognition) ጥያቄ የበለጠ እየተጠናከረ እንደሚመጣ የማህበረሰብ እድገት ሳይንስ እና የተለያዩ ሀገሮች ታሪክ ያሳያል። በዚህም ምክንያት የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በበለፀጉት ሀገሮችም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት እውቅና ተሰጥቶት የሰብአዊ እና

ዲሞክራሲያዊ መብት አካል ተደርጎ ምላሽ እንዲያገኝ ተደርጓል። ይህ እውነታ በተለይ የካፒታሊዝም ዕድገት እየጨመረ በሄደ ቁጥር ይበልጥ ዓለም ዓቀፍ እውቅና እና ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል።

የዜጎች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ከሀገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ የመሆን ትግል ጋር ተያይዞ የአለም አቀፍ ህግ አካል ተደርጓል። በተለይ በተባበሩት መንግስታት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን እና የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የባህል መብቶች ኮንቬንሽን እንዲሁም በአፍሪካ የሰብአዊ መብት እና የህዝቦች ቻርተር ላይ ሁሉም ህዝቦች ፖለቲካዊ አቋማቸውን፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የባህል መብቶቻቸውን ነፃ ሆነው የመወሰን እና የማሳደግ እንዲሁም ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እንዳላቸው በግልፅ ተቀምጧል።

ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ይበልጥ እየተጠናከረ የመጣው በአውሮፓ ከበርካታ ጦርነት እና ግጭት በኋላ የተፈጠሩት ብሄርን መሰረት ያደረጉ ሀገሮች ብሄረ-መንግስት (Nation State) መቋቋም ጋር ተያይዞ ነው። በተለይ የተለያዩ ብሄሮች አንድ ሀገር በመሰረቱበት ሂደት በአንድ ሀገር ውስጥ የበርካታ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ እና እምነት ባለቤት ከመሆን ጋር ተያይዞ የግለሰቦችን የተናጠል መብት በመጠበቅ የህዝቦች የቡድን መብቶች ለማስጠበቅ በቂ እንዳልሆነ ተስተውሏል። በአንድ ሀገር ውስጥ ማንነትን (ቡድንን ወይም ስብስብን) መሰረት ባደረገ መልኩ የሚደርሱ ጭቆናዎች፣ በደሎች፣ ልዩነቶች እየጎሉ በመምጣታቸው በካፒታሊስት ስርአትም ቢሆን ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የቡድን መብቶችን የመጠየቅ እንቅስቃሴዎች በሰፊው እየጎሉ መጥተዋል።

በዚህም አግባብ በአንድ ሀገር የሚገኙ የሀገሬው ተወላጅ መብት፣ የስደተኛው መብት፣ የሴቶች መብት፤ የብሄሮች መብት ወዘተ በሰፊው እየጨመረ መጥቷል። ይህም በመሆኑ የካፒታሊስት ስርአት የፈጠራቸውን የመብት ምህዳሮች፣ ልዩነቶች እና ቡድናዊ መድሎዎች መሰረት በማድረግ ሊብራል ብሄርተኝነት (Liberal Nationalism) የሚል የፖለቲካ አስተሳሰብ በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተፈጥሯል። በዚህ አግባብ የብሄር ብሄረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር (Self Rule) እና በራስ ጉዳይ የመወሰን (Internal Self Determination) መብት በአለም ደረጃ በብዙ ሀገሮች ህጋዊ፣ ህገ-መንግስታዊ እና ፖለቲካዊ እልባቶች እየተሰጡት ይገኛል።

ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ

ወደ ሀገራችን ስንመጣ ሀገራችን ከ80 በላይ የሆኑ የተለያዩ ብሄሮች የሚኖሩባት ሀገር በመሆኗ በፌደራልም ሆነ በክልል ህገ መንግስታት የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ክልሎች በዚሁ አግባብ ሊደራጁ ችለዋል። ህገ,መንግስቱ በሀገራችን ለረዥም ዘመናት የፖለቲካ ጥያቄ ሆነው ለቆዩት የመደብ እና የብሄር ጥያቄ መልስ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተቀረጸ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የሀገር ግንባታ ታሪክ ሁሉን አቀፍ ጠንካራ ህብረ-ብሄራዊ ሀገር ለመፍጠር ያሉበትን ክፍተቶች ለመሙላት፣ ዜጎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እንዲጎናጸፉ ፈቅዷል።

ይሁንና በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው የብሄሮች መብት ባለፉት 30 ዓመታት የታለመለትን ግብ ሳይመታ፣ ህገ-መንግስታዊ አደረጃጀቱን ገዢዉ ፓርቲ የራሱን ስልጣን ማራዘሚያና ማበልፀጊያ አድርጎት ቆይቷል። የብሄር ግንባታ እና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማጎልበት ረገድ የዜጎችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ገዢው ፓርቲ የመብት ጥያቄው ወደ አንድ ፅንፍ እንዲሄድ በማድረግ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ተጠቅሞበታል። በውጤቱም ብሄረሰቦች እርስ በራሳቸው የበለጠ የሚተጋገዙበት እና የሚደጋገፉበት እንዲሁም እንደ አንድ ሀገር ዜጋ ወንድማማችነታቸውን የሚያጠናክሩበት ሳይሆን እርስ በራሳቸው በጥርጣሬ የሚተያዩበት እና የጥላቻ ስሜት የሚያዳብሩበት በማድረግ ፅንፍ የረገጠ ብሄርተኝነት እንዲጎላ አድርጓል። ባለፉት ሶስት አስርተ አመታት የፌዴራል ስርአቱ በተሳሳተ መንገድ በመተግበሩ ዜጎች እንደ አንድ ሀገር ልጅ እንዳይተያዩ፣ አካታች ኢትዮጵያዊ ማንነት እንዳይፈጠር ማንነትን ማዕከል ያደረጉ ለበርካታ ዜጎች መፈናቀል እና ግድያ ምክንያት የሆኑ ግጭቶች ተፈጥረዋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተዘረዘሩትን የማህበረሰብ እድገት ታሪክ፣ አለም አቀፍ ተሞክሮ እና የሀገራችንን ተጨባጭ እውነታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ራስን በራስ ከማስተዳደር ጥያቄ ጋር በተያያዘ እንደ ሀገር ያጋጠሙንን ውስብስብ የሰላም፣ የልማት እና የዴሞክራሲ ችግሮች በአስተማማኝ ሁኔታ በሚቀርፍ እና ልዩነቶች በሚያስታርቅ መልኩ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡-

1) ኢትዮጵያዊ ማንነትን በመገንባት ረገድ፣

- ኢትዮጵያዊነትን መልሶ በመገንባት እና በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋ ሁሉን አቀፍ እና አካታች የሆነ ሁሉም ብሄሮች እና ብሄረሰቦች ባላቸው የተለያየ የብሄር፣ የኃይማኖት፣ የአካባቢ የማንነት መሰረቶች ራሳቸውን እንደ መስታወት ኢትዮጵያ ላይ እንዲያዩ በማድረግ የጋራ እና አካታች የሆነች ጠንካራ እና ታላቅ ኢትዮጵያን የመገንባት ስራ ስትራቴጂና እቅድ ተነድፎ ይሰራል።
- የሀገር ሉአላዊነትንና አንድነትን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል በሚል ሰፊ የፖለቲካ ልዩነት ያስነሳው የብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የመገንጠል መብትን በተመለከተ ጉዳዩ ለህዝብ ውይይት የሚቀርብበትን ሰፊ ምህዳር የማመቻቸት ስራ ይሰራል።

2) የብሄር ብሄረሰቦችን ራስ በራስ የማስተዳደር መብት በማስከበር ረገድ፣

- ኢትዮጵያ ህዝቦቿ እንደ ሌሎች ሀገሮች (ለምሳሌ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ) ከተለያዩ ሀገራት በፈለሱ ግለሰባዊ ዜጎች የተገነባች ሳይሆን ሁሉም ህዝቦቿ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጥንታዊ እና ሀገር በቀል ህዝቦች ያሏት ሀገር እንደሆነች ይታመናል። ከዚህም አንፃር ሁሉም ህዝቦች ማንነታቸው እና እሴቶቻቸው የሚከበሩበትን፣ ባህል እና ቋንቋቸው የሚጎለብትበት ስራ ይሰራል፣
- ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የአስተዳደር ምቹነትን፣ የህዝብ ፍላጎትን፣ ቋንቋና ባህልን፣ መልክዓ-ምድርንና ሌሎች የጋራ እሴቶችን ታሳቢ ያደረጉ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶች እንዲከበሩ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ይፈጥራል። የህዝቦች የአስተዳደር አከላለል የፌደራሊዝም ስርአትን መሰረት ባደረገ መልኩ፣ በህዝብ ፈቃድ እና ፍላጎት በሪፈረንደም በሚፈልገው የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚተዳደርበት ወይም ራሱን ችሎ የራሱን አስተዳደር የሚፈጥርበት በህዝባዊ ተሳትፎ እና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን መሰረት ያደረገ አሰራር ይመቻቻል።

3) በከተማ የሚኖሩ ህብረ-ብሄራዊ ህዝቦችን መብት በማስከበር ረገድ፣

- በከተማ የሚኖሩ ህዝቦችን በተመለከተ፣ በህገ-መንግስቱ የህዝቦች መብት እንደሚከበር በግልፅ የተቀመጠ ቢሆንም፤የከተማው ነዋሪ ህዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የመምረጥ እና የመመረጥ መብት፣ እንዲሁም ሌሎች ህገ-መንግስታዊ መብቶች ላለፉት ሶስት አስርተ ዓመታት ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ቆይቷል፣
- በሌላ በኩል የከተሞች ራስን በራስ የማስተዳደር ሁኔታ ሲታሰብ፣ በአብዛኛው ከተሞች የሚፈጠሩት በአካባቢው ያለውን አርሶ አደር እና አርብቶ አደር በማፈናቀል ከመሆኑም በላይ ሲፈናቀልም በከተማ ለመኖር የሚያስችለው በቂ ካሳ የማይሰጠው በመሆኑ፣ የአካባቢው የገጠር ነዋሪ ከድህነት ወለል በታች እንዲኖር ተደርጓል። ከዚህም አልፎ ከተሞች እየተስፋፉ በሄዱ ቁጥር አርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን ከመሬቱ የሚያፈናቅሉ ከመሆኑም ባሻገር የኢንዱስትሪ መስፋፋት በገጠሩ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ብክለት እና የአካባቢ መጎሳቆል አስከትሏል፣
- ስለዚህም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የከተማ ነዋሪውን መሰረታዊ መብቶች እና በከተማው ዙሪያ የሚኖረውን ማህበረሰብ መብቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ያጣመረ የአስተዳደር እና የልማት ስርአት ይቀይሳል። በዚህም መሰረት፡-
  - የከተማ ነዋሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳደሩበት፣ የሚመርጡበት እና የሚመረጡበት፣ መሰረታዊ ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ ይመቻቻል፣
  - በከተሞች ዙርያ የሚገኙ አርሶ አደር እና አርብቶ አደር ማህበረሰቦች በከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች በቂ ውክልና እንዲኖራቸው የሚያደርግ የህግ ማእቀፍ እንዲፈጠር ያደርጋል፣
  - o የካሳ ህጉ በከተሞች ዙሪያ የሚኖረው ማህበረሰብ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን እና የከተማ መስፋፋት ስጋት ሳይሆን መልካም ዕድል አድርጎ እንዲመለከት በሚያደርግ መልኩ ይሻሻላል፣
  - ከተሞችን በዙሪያቸው ካለው የአካባቢው ነዋሪ ጋር የሚያስተሳስሩ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ የመብራት እና የስልክ እንዲሁም ሌሎች የልማት ተግባራት በተቀናጀ የከተማ ልማት ስትራቴጂ እንዲፈፀም ይደረጋል፣

- የከተማ መስተዳድሮች የስራ ቋንቋ የየክልሎቹ የስራ ቋንቋ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተጨማሪነት አብዛኛው የከተማ ነዋሪ የሚናገረው ቋንቋ የስራ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል።
- የከተማ ነዋሪዎችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተሟላ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር ፖሊሲ እና የህግ ማእቀፎች ይዘጋጃሉ።

9 መልካም አስተዳደር

የመልካም አስተዳደርን ይበልጥ ለመረዳት የመጥፎ አስተዳደር መገለጫዎችን መመልከት ጠቃሚ ነው። መጥፎ አስተዳደር (Bad Governance) ሙስና፣ አስተዳደራዊ በደል (Mal Administration)፣ የማስፈጸም ብቃት ማጣት፣ የፍትሕ መጓደልን ያካትታል። የመጥፎ አስተዳደር ባህሪዎች በተለያዩ የአለም ሀገሮች ቢኖሩም፣ የችግሩ ጥልቀት፣ የማሕበራዊ ምጣኔ ሀብታዊ ተጽእኖ እና በማሕበረሰብ የፖለቲካ ሕይወት ላይ የሚያሳድሩት ውጤት፣ መጠን እና ደረጃ በጣም ይለያያል።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች የመጥፎ አስተዳደር ዉጤት እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህም ለድህነት፣ ደካማ የጤና አገልግሎት፣ ለከፋ መሀይምነት፣ ፍትሀዊ ያልሆነ የገቢ እና ሀብት ክፍፍል፣ ዝቅተኛ የምጣኔ ሀብት እድገት፣ ደካማ ተቋማዊ ጥንካሬ እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ፈጥሯል። እነዚህ ችግሮች በአንድ በኩል መጥፎ አስተዳደር የሚፈጥሩ ሲሆን፣ የመጥፎ አስተዳደር ውጤትም በመሆን ሀገሮች በዚህ ዑደት ውስጥ እንዲገፉ አስገድዷል። የዚህን የዑደት ክበብ መስበር የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ዋናው የፖሊሲ አቅጣጫ ነው።

የኢትዮጵያን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመረዳት እና ችግሮቹን ለመተንተን የምንጠቀምባቸው መለኪያዎች ዩሮ ሴንትሪክ በመሆኑ፣ ችግሮቹን በጠቋሚነት ለመመልከት ያገለግል እንደሁ እንጂ የኢትዮጵያን የመልካም አስተዳደር ችግር ምንጭ እና መፍትሄዎቹን ሙሉ በሙሉ አያሳይም። በመሆኑም ችግሩን በትክክል ተገንዝቦ መፍትሄ ለማበጀት የኢትዮጵያን የመንግስት አስተዳደር ታሪካዊ ዳራ እና አሁናዊ ይዘት መመልከት የግድ ይላል።

ዘመናዊ ኢትዮጵያ ተመሰረተች ከሚባልበት ጊዜ አንስቶ ብሄራዊ ተቋማት የገዢ መደቡን ፍላጎት እንዲያገለግሉ ተደርገው በመገንባታቸው ተቋማቱ የህብረተሰቡን መሰረታዊ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች የመመለስ አቅም እና አደረጃጀት አልነበራቸውም። በዚህም ምክንያት ህዝቦች ለድርብርብ ጭቆና፣ አድልዎ እና ድህነት ተዳርገዋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እውን እንዲሆን እና የችግሩ ቋጠሮ ከስር መሰረቱ እንዲፈታ የመንግስት ተቋማት ግንባታ ሁሉን አቀፍ፣ አካታች እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲከለስ ይሰራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የመልካም አስተዳደር ስራ በአንድ ተቋም ብቻ የሚሰራ ሳይሆን በሁሉም ተቋማት ወጥ ስትራቴጂ ተቀርፆ መሰራት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የመልካም አስተዳደር ስራ ዘርፈ-ብዙ አካላትን በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራዊ ያደርጋል።

በዚህም መሰረት ጠንካራና ውጤታማ የመልካም አስተዳደር ተቋማት እንዲጎለብቱ በተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ማለትም በመንግስት ተቋማት፣ በሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በግል ሴክተሩና በፍትህ ተቋማት ዙሪያ የመልካም አስተዳደር የሪፎርም ስራዎች ይሰራሉ።

9.1.1 የመልካም አስተዳደር ትግበራን የሚከታተሉ እና የሚጠብቁ ተቋማት

ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከል መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ለማድረግ ልዩ ልዩ ሚና ያላቸው በርካታ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ያሉ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት፣ የዋና ኦዲት መ/ቤት፣ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ የሲቪክ ተቋማት፣ የሚድያ ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ተቋማትንም መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ አካላት በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላት ስልጣናቸውን ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዱ እንዲሆኑ ከፍተኛ ሚና አላቸው። እነዚህ አካላት ከአስፈፃሚው እና በተዋረድ ካለው መንግስታዊ መዋቅር ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ መልኩ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ ሰፊ የሪፎርም ስራ ይሰራል።

- ህግ አዉጪ ምክር ቤቶች (Paliament)፡ ህግ አውጪ ም/ቤቶች የዕለት ተዕለት ስራዎቻቸውን የሚያከናውኑት በም/ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ሲሆን እነዚህ ኮሚቴዎችም ቢያንስ ለም/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ መ/ቤቶችን እና የአስፈፃሚ አካላትን ስራ በየግዜው በመገምገም እና በሚቀርብላቸው አቤቱታ ተመርኩዘው በመመርመር ለሰሩት ስራ የፖለቲካ፣የአስተዳደር እና የህግ ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው ለማድረግ አይነተኛ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።
- የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (Anti-Corruption Commission)፡ በሀገራችን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከተቋቋመ በርካታ አመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም፣ ከገዢዉ ፓርቲ እና ከፖለቲካ ስርአቱ ተጣብቆ፣ የፖለቲካ አካሉ የሚፈልገውን ባለስልጣን ከመመርመር ውጪ ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የሀገር እና ህዝብ ተቋም ሆኖ ስራውን እየሰራ አልነበረም። ይባስ ብሎም አሁን የኮሚሽኑ የምርመራ እና ክስ ዘርፍ ወደ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ውስጥ ገብቶ የአስፈፃሚው አካል ትዕዛዝ ማስፈፀሚያ ሆኗል። በዚህ ረገድ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኑን ከዳኝነት አካሉ ባልተናነሰ ሁኔታ ነፃ ሆኖ እንዲቋቋም ተደርጎ የአስፈፃሚው ወይም የገዢው ፓርቲ ቡራኬ ሳያስፈልገው የሀገር እና የህዝብ ተቋም ሆኖ የማስተማር፣ የመከላከል፣ስነ-ምግባርን የመቆጣጠር እና የመከታተል፣ እንዲሁም የመመርመር እና የመክሰስ ስራዎችን የሚሰራበት ተቋማዊ ነፃነት እንዲኖረው ተደርጎ እንደአዲስ እንዲደራጅ ይደረጋል።
- የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም (Ombudsman)፡ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ በአስፈፃሚው እና በአስተዳደር አካላት የሚደርስን አስተዳደራዊ በደል ለማረም እና መፍትሄ ለመስጠት ታልሞ ከተቋቋመ በርካታ ግዜያት ቢሆኑም እስከ አሁን የአስፈፃሚውን ፍላጎት ከመጠበቅ ውጪ በጎላ ሁኔታ የዜጎችን እንባ ሲያብስ አልተስተዋለም። የዚህን ተቋም አደረጃጀት እና ስልጣን በማጠናከር ዜጎች የሚያጋጥማቸውን የመልካም አስተዳደር እጦት በሚፈታበት ቁመና እንዲዋቀር ይደረጋል።
- የዋና ኦዲተር (Auditor General)፡ ይህ መ/ቤት ለመንግስት መ/ቤቶች የተመደበ በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በህገ-መንግስት እውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመ ሲሆን፣ የተጣለበትን ኃላፊነት በወጉ እየሰራ ነው ለማለት ያስቸግራል። በተለይም ተቋሙ የኦዲት ምርመራ አድርጎ ባገኘው ውጤት ተንተርሶ እርምጃ የሚወሰድባቸው ባለስልጣናት እና ሌሎች የስራ ኃላፊዎች በጣም ውስን ናቸው። ከመረመራቸው ሂሳቦች ውስጥ ጉድለት ተገኝቶባቸው ወይም ምዝበራ መፈፀሙ ተረጋግጦ ለህግ የቀረቡ አካላት የሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ ትንሽ ናቸው። ይህን ተቋም ነፃነቱንና የመመርመር አቅሙን እንዲጠናከር የማድረግ እና እንደገና የማደራጀት ስራ ይሰራል።

- የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች (Civil Society)፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊም ሆነ የግል ሚዲያ ተቋማት የመልካም አስተዳደር እንዲጎለብት በማድረግ ረገድ አይነተኛ ሚና አላቸው። በመሆኑም የሲቪክ ማህበራት እንዳይደራጁ እና ነፃ ሆነው እንዳይንቀሳቀሱ የሚያደርጉ ህጎች እና አሰራሮች በተሻሉ ህጎች እና የአሰራር ማዕቀፎች ይቀየራሉ።

- ሚዲያ (Media)፡ የሚዲያ ተቋማት የገዢውን ፓርቲ እና አስፈፃሚውን በዋናነት ከማገልገል እና በእርሱ እስትንፋስ ልክ ከመተንፈስ ውጪ፣ በመንግስት ተቋማት እና በባለስልጣናት የሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮች እና ሙስና በማጋለጥ ረገድ እየተጫወቱ ያለው ሚና እጅግ አናሳ ነው። በመሆኑም የሚዲያ ተቋማት ከፓርቲ እና ከአስፈፃሚ ጉያ ወጥተው ለሀገር እና ለህዝብ ብቻ እንዲሰሩ ለማድረግ ሰፊ የሪፎርም ስራ መስራት እና ተቋማዊ ነፃነታቸውን በመጠበቅ ሚናቸውን እንዲወጡ የማስቻል ስራ ይሰራል።

10 ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ

በኢትዮጵያ ውስጥ 'ዘመናዊ' የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ከተዘረጋ ቢያንስ አንድ ምዕተ አመት እንዳስቆጠረ ድርሳናት ይመሰክራሉ። ይሁን እንጂ የሲቪል ሰርቪሱ ስርዓት በከፍተኛ ሁኔታ የተቀየረው ወታደራዊው መንግሥት ከወደቀ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ነበር። በኢትዮጵያ ከሀገሪቱ GDP በአማካኝ አንድ አምስተኛ የሚሆነው ህዝባዊ አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ላይ እንደሚውል ይገመታል። እ.ኤ.አ. ከ 1991/92 ጀምሮ በሀገሪቱ ያሉት የመንግስት ሰራተኞች ቁጥር በፍጥነት እያደገ የመጣ ሲሆን በ1991 ከ223 ሺህ በላይ ነበር። ይሔው አሀዝ በ 2013 ወደ 1,102,316 አድጓል። በአሁኑ ወቅት 1,256,946 እንደሚሆን የገመታል። ከጠቅላላው

ሲቪል ሰርቫንት ውስጥ 10 በመቶ (125,333) የሚሆኑት በፌዴራል ተቋማት ውስጥ ያገለግላሉ ።

ካለፉት 50 ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የተከናወኑት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያዎች በሦስት ታሪካዊ ዓውዶች ተከፍለው ሊቀርቡ ይችላሉ። የተቋማት ግንባታ ጊዜ (1941-1974)፣ የውጥረት ጊዜ (1974-1991) እና የመልሶ ማቋቋም ዘመን (restructuring) (1991 እስከ አሁን)። ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ለመገንባትና እንደገና ለማዋቀር ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ሙከራ አድርጓል። በኢህአዴግ መራሹ መንግሥት የታቀዱት አንዳንድ የተሃድሶ ሥራዎች መጠነኛ የሆኑ ለውጦችን የፈጠሩ መሆኑ ባይካድም የተሃድሶ ጥረቶቹ በዋናነት የገዢውን ፓርቲ ፖለቲካዊ ርዕዮት-ዓለም ለማሳካት የታለሙ ነበሩ።

ኮሶስት አመት በፊት ከተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ማግስት በርካታ የከፍተኛ መንግስት አመራሮች ለውጥ እና የተቋማት መልሶ ማዋቀር ስራዎች ለመስራት ቢሞከርም የዜጎችን ፍላጎት ማሟላት የሚችል የሲቪል ሰርቪስ አቅምና ነፃ ተቋማት እስካሁን ድረስ ዕውን መሆን አልቻሉም። የተቋማት ብቃት ማነስ እና የህዝብ ቅሬታ አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ቀጥሏል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሀገራችን ሲቪል ሰርቪስ ያሉበትን ውስብስብ ችግሮች በመገንዘብ በዘርፉ ስር-ነቀል ለውጥ ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ያምናል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ችግር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ደርዝ ያለው እና መፍትሄውም በዚያው ልክ-ዘርፈ ብዙ እንደሆነ ይረዳል።

የኢኮኖሚ ልማት እና ጠንካራ የመንግስት አስተዳደር ሊኖር የሚችለው ነፃ እና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ሲኖር ነው። **ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ** የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዘርፍ በውስብስብ ችግሮች የተተበተበ እና ከፍተኛ የሆነ የአቅም ውስንነት ያለበት መሆኑን በመረዳት አፋጣኝ እና መጠነ ሰፊ የሪፎርም ስራ እንደሚያስፈልግ ይገነዘባል። በዚህም መነሻነት የችግሮችን መንስኤዎች እና ምልክቶች ነቅሶ በማውጣት ውጤታማና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ክፍተቶች እና ሳንካዎች

ከታሪክ አኳያ ቀደምት የኢትዮጵያ መንግስታት በቴክኖክራቶች ፋንታ ለአገዛዙ ታማኝ የሆኑ ፖለቲከኞችን ወደ ሹመት በማምጣት ሲቪል ሰርቪሱን የመንግስት አሽከር ለማድረግ ተጠቅመውበታል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲቪል ሰርቪስ ሴክተሩ በነፃነት እንዲሰራ እድል ያልነበረው ሲሆን የህዝብ ተቋማት በፖለቲካ ቁጥጥር ስር ውለዋል። የሲቪል ሰርቪስ ዘርፍ እድገት በጭቃ ውስጥ ተቸንክሮ የሚንተት ጋሪ አይነት ነው። የጥናት ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያሉ ችግሮች ከታሪክ አኳያ በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው።

በኢትዮጵያ በተከታታይ የመንግስት ለውጥን ተከትሎ ወጥነት የሌለው ተቋማዊ አወቃቀር ተፈጥሯል። በዚህ ሂደት ውስጥ በተዋንያን መካከል ባለው የኃይል ሚዛን ለውጥ ምክንያት **ተቋማዊ ማህደረ ትውስታ (institutional memory)** ጠፍቷል። በዚህም ምክያት ነፃ የተቋም ግንባታ ሂደት ሲሰናከል ይታያል። በሹመኞች አጭር የሥልጣን ዘመን ምክንያት ብዙዎቹ የህዝብ ተቋማት **የገፅታ ቀውስ (identity crisis)** የገጠማቸው ናቸው። ባለስልጣኖች እና የመንግስት ሰራተኞች በአንድ የስራ ቦታ ተረጋግቶ ባለመስራት ምክንያት የአመራር ውጤታማነትን ሲያደናቅፉ እና የኢንዱስትሪ ሠላም (industrial peace) ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሲፈጥሩ ቆይተዋል።

በኢትዮጵያ ወደ ስልጣን የመጡት ሦስቱ ተከታታይ መንግስታት ተቋማትን በፖለቲካዊ ፍልስፍናቸው መሠረት ለማዋቀር ሞክረዋል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ አጀንዳዎች በገዢው ፓርቲ ርዕዮት-ዓለም የተቀየሱ እና በገዢው ፓርቲ አደረጃጀት የሚዘወሩ የፖሊሲ ቤተ-ሙከራ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ችግሩን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው የፌዴራል እና በክልል የሚገኙ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት **በማንነት ፖለቲካ (identity politics)** ተጽእኖ ስር መውደቃቸው ነው። ይህም በመሆኑ በመንግስት ተቋማት እና በሲቪል ሰርቪስ ዘርፍ ላይ ያለው የህዝብ አመኔታ መሸርሸር ችግሩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አድርጎታል።

ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ባሻገር፣ የላሸቀ የሥራ ሥነ-ምግባር (poor work ethic) የህዝብ አገልግሎቱን ቀልጣፋነት በእጅጉ የጎዳው ሲሆን ለዚህም ዝቅተኛ የስራ ባህል እና ልማዶች አስተዋጽኦ አበርክቷል። በተጨማሪም ኢ-መደበኛ የሆነ ቢሮክራሲ፣ በቴክኖሎጂ ያልዘመነ የህዝብ አገልግሎት ስርዓት የመንግስት ተቋማትን ውጤታማነት በእጅጉ ጎድቶታል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ደካማነት እና ኋላ ቀርነት አንዱ ምክንያት ብቁ ባለሙያዎችን መመልመል እና ማቆየት አለመቻሉ ነው። ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተገኘ መረጃ መሠረት በሁሉም የመንግሥት አደረጃጀት ውስጥ ካሉት ጠቅላላ ሠራተኞች ውስጥ 12.5% የሚሆኑት ከ12ኛ ክፍል በታች ሲሆኑ 18.75% ደግሞ ከ12ኛ ክፍል በላይ ሆነው የምስክር ወረቀት የላቸውም። 20% የሚሆኑት የምስክር ወረቀት ያላቸው እና 18.75% የሚሆኑት ዲፕሎማ ያላቸው ናቸው። ከሰራተኞቹ 10% የሚሆኑት ብቻ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቅ ናቸው።

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ አነስተኛ የደመወዝ ስኬል ሌላው መሰረታዊ ችግር ሆኖ ይነሳል። ደመወዛቸው ዝቅተኛ የሆኑ የመንግስት ሰራተኞች በተለይም ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ሰራተኞች 2 ወይም 3 ስራዎችን እንዲሰሩ ይገደዳሉ። ግብር ሰብሳቢ ኤጀንሲዎች፣ የጉምሩክ ቢሮዎች፣ ክፍለ ከተሞች፣ ቀበሌዎች/ ወረዳዎች እና የመሬት አስተዳደር ኤጀንሲዎች ወዘተ ባሉ የመንግስት ተቋማት ዙሪያ ለተስፋፋው የሙስና እና የኪራይ ሰብሳቢነት ዝንባሌዎች የኑሮ ሁኔታውን ያላገናዘበ የክፍያ ሥርዐት ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ ይገመታል። ለአብነት ያህል በአዲስ አበባ እና ሌሎች የክልል ከተሞች እየተካሄደ ያለው ህገ-ወጥ የመሬት አስተዳደር እና ህገ-ወጥ የንብረት ይዞታ የችግሩ ግልጽ ማሳያ ናቸው።
ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ተጠቃለው ሲቀርቡ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ሴክተር እና የመንግስት ተቋማት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች የሚከተሉትን ያካትታል፣

1. ተመጣጣኝ ያልሆነ እና የኑሮ ውድነትን/የዋጋ ግሽበትን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የክፍያ ስርዓት፣
2. የባለስልጣኖች እና የአስተዳዳሪዎች አጭር የስራ ዘመን፣
3. ቴክኖክራቶች የህዝብ ተቋማትን የመምራት ዕድል ያለማግኘት፣
4. ጠንካራ የቢሮክራሲያዊ መዋቅር አለመኖር፣ ከፍተኛ የሠራተኛ የፍልሠት ምጣኔ፣
5. ተነሳሽነት የጎደለውና ሞራሉ የላሸቀ ሲቪል ሰርቫንት እንዲሁም የሙያ ሥነ-ምግባር ብልሹነት፣
6. ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እና ከገዥ ፓርቲ መዋቅር ጋር የተጋመደ ቢሮክራሲ፣
7. የተንሰራፋ ሙስና እና አድልዎ፣ ብልሹ የግዥ ሂደት፣
8. በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ላይ የህዝብ አመኔታ መሸርሸር
9. የመፍትሄ አቅጣጫዎች

ሲቪል ሰርቪስ ሴክተር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳለጥ እና ዴሞክራሲን ለማስፈን እንዲሁም በተለያዩ ደረጃ የሚወጡ የመንግስት ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም ዋነኛ ማዕከል ነው። እነዚህ ተቋማት በህዝብ እና በመንግስት መካከል እንደ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። ደካማ ሲቪል ሰርቪስ ሴክተር መኖር ማለት ድልድይ ያልተገነባላቸው ሁለት አውራ ጎዳናዎች ማለት ነው። ደካማ የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር በመንግስትና በህዝብ መካከል ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የኢትዮጵያን ሲቪል ሰርቪስ በትክክለኛ መዋቅር ላይ ለማሳረፍ «በቅድሚያ የባህል አብዮት ያስፈልጋል።» ብሎ ያምናል። የችግሮቹን ጥልቀት እና ስፋት በመገንዘብ ፓርቲያችን በዘላቂነት ሊተገበሩ የሚችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ያደርጋል። ከፓርቲያችን መሰረታዊ መርሆች አንፃር የቀረቡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሲቪል ሰርቪሱን ከፖለቲካ ነፃ የሚያደርጉ እና ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚያግዙ ናቸው። በዚህ አስተሳሰብ ላይ በመመርኮዝ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተሉትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ይከተላል፣

- የሲቪል ሰርቪሱን ከፖለቲካ ወገንተኝነት ማላቀቅ፣
- ከፖለቲካ ሹመት ይልቅ በቴክኖክራቶች የታነጹ እና የሚመሩ የህዝብ ተቋማትን መመስረት፣
- ብቃትን ያማከለ ስርዓተ-መዋቅር (ሜሪቶክራሲ) መፍጠር፣

- የሲቪል ሰርቪስ ደመወዝ ከግል ዘርፎች እና ከግል ተቋማት ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት። በዚህ መሰረት የሲቪል ሰርቪስ የደመወዝ ስኬል ክለሳ በማድረግ በተመጣጠነ የክፍያ ስርዓት መተካት፣
- ፕራይቬታይዜሽን፡ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ በግሉ ሴክተር ቢተዳደሩ የተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወደ ግል ለማዞር በጥናት ላይ የተመሰረተ ስራ ይሰራል፣
- የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ያልተማከለ እና ዲጂታል ማድረግ፡ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የዜጎችን ደህንነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስርአተ መዋቅር መዘርጋት ሁለንተናዊ የሆነ መፍትሄ ያመጣል ብሎ ያምናል። ዜጎች በሚሰጣቸው የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (ወይም የብሄራዊ መታወቂያ) ቁጥር አማካኝነት አስፈላጊ መረጃዎች በተማከለ ዘይቤ ተሰናድቶ በመረጃ ቋት ይያዛል። በዚህም መሰረት የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሰጡ ይደረጋል። በእንደዚህ ዓይነት የተዋቀረ ስርዓት ሙስናን ለመቅረፍና ወንጀልን ለመከላከል አይነተኛ ሚና ይጫወታል።

11 የህግ የበላይነት

የህግ የበላይነት ማለት በህግ የሚገዛ ሳይሆን ለህግ የሚገዛ መንግስት፣ በግለሰብ ሳይሆን በተቋማት እና በስርአት የሚተዳደር መንግስት ማለት ነዉ። የህግ የበላይነት ዋና ዋናዎቹ መርሆች፡

- ለህግ፣ ለህገ መንግስታዊ መርሆች እና ስርአት ተገዢነት፣
- ግልፅ የሆነ የስልጣን ክፍፍል እና ቁጥጥር ስርአት፣
- ለህግ ስርአት እና ስነ-ስርአት መገዛት፣
- ውሳኔ በመስጠት ሂደት አሳታፊነት፣
- ህግን አለአግባብ አለመገልገል
- በህግ ፊት እኩልነት፣
- የህግ ተገማችነት፣
- ግልጸኝነት
- ተጠያቂነት፣

የህግ የበላይነትን የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነት የሁሉም ዜጎች፣ የህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ፣ ህግ አስከባሪ እና ህግ ተርጓሚ አካላትን ተሳትፎ ይጠይቃል። የመንግስት አካላት ከህግ በላይ ሲሆኑ ወይም ደካማ የህግ አውጪ፣ አስከባሪ እና ተርጓሚ አካል ሲኖር ውጤቱ ስርአት አልበኝነት እና አምባገነንነት ይሆናል።

መንግስት የማህበረሰቡን ሰላምና ፀጥታ እንዲሁም ደህንነት የሚያስጠብቀው፣ ዜጎች ፍትህ የሚያገኙት እና የዜጎች እኩልነት የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ወይም ለህግ ተገዢነት ሲረጋገጥ ነው። የህግ የበላይነት በሌለበት ሁኔታ ሀገር እንደ ሀገር የምትቀጥልበት ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ይገባል። ስርአት አልበኝነት፣ ዜጎች በመንግስት ላይ እምነት ማጣት እና የህግ ተገማችነት እየተሸረሸረ ይመጣል። በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን ወይም አካል ህጉን ወደ ራሱ በመውሰድ ወደ አመፅ እና እርስ በርስ ጦርነት የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል።

የህግ የበላይነትን ማክበር እና ማስከበር ከአስፈፃሚው አካል መጀመር ያለበት ሲሆን በተለይ የህግ የበላይነትን ለማስከበር አይነተኛ ሚና የሚጫወቱት የፀጥታ፣ የደህንነት እና የፍትህ ተቋማት ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት፣ ውግንና እና አድልኦ ነፃ ሆነው ሀገር እና ህዝብ የማገልገል ቁርጠኝነት እና ተቋማዊ ጥንካሬ ሊኖራቸዉ ይገባል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተጠቀሱትን መርሆች ታሳቢ በማድረግ የህግ የበላይነትን ለማስከበር የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይፈጽማል፣

- የፍትህ እና የጸጥታ ተቋማት ሙያዊ እና ተቋማዊ ነፃነት እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ አሰራሮችን ይዘረጋል፣
- ከህግ የበላይነት መሰረታዊ መርሆች ጋር የተያያዙ የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

- በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላት የህግ የበላይነት መርሆችን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለህግ ተገዢ እና ተጠያቂ የሚሆኑበት ግልፅ ፕሮግራሞች ተነድፈው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
- የህግ አውጪው አካል ከአስፈፃሚው ጋር ግልፅ የስልጣን ክፍፍል ኖሮት፣ ጠንካራ ተቋማዊ ጥንካሬ እንዲኖረው ይደረጋል፣
- የህዝብን መብትና ጥቅም ማዕከል ባደረገ መልኩ ብቻ ህጎች የሚወጡበት አሰራር በመዘርጋት የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ማእቀፍ ተዘርግቶ ይተገበራል፣
- የዳኛነት ስርአቱ ነፃ፣ ግልጽ እና ተጠያቂ እንዲሁም ከአስፈፃሚው አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ እና ገለልተኛ ሆኖ እንዲሰራ የዳኝነት አካሉ ተቋማዊ ጥንካሬ የሚጎለብትበት አሰራር ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል።

12. የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የመንግስትን የሀብት እና የማስፈጸም አቅም ውስንነት በመሙላት ለዜጎች ሰፊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አገልግሎት ይሰጣሉ። በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ እና መልሶ ማቋቋም በመስጠት፣ ግጭትን በመከላከል እና በማስቆም ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ በቅርስ እና አካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ፣ በፖሊሲ ቀረጻ እና ግምገማ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰላም እና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አይተኬ ሚና አላቸው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ልዩ ልዩ ማህበራዊ እና ሰብአዊ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን የሚያካትት ሲሆን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የእርዳታ ድርጅቶች፣ የሙያ ማህበራት፣ የሰራተኛ ማህበራት፣ እንዲሁም በርካታ ሀገር በቀል የመረዳጃ ማህበራት እና ድርጅቶችን ያቅፋል።

ይሁን እንጂ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ካላቸው አቅም አንጻር በኢትዮጵያ የነበራቸው ሚና እና ተሳትፎ እጅግ አናሳ ነው። በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን ሚና በሶስት ደረጃ ከፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል። የመጀመሪያው ደረጃ በሀገራችን የሲቪክ ማህበራት ተሳትፏቸው በዋናነት በተለይም በድርቅ እና ርሀብ ለተጎዱ ወገኖች ሰብአዊ የእለት እርዳታ በማቅረብ ላይ የተወሰነ ነበር። ከዚህ አንጻር የእርዳታ ድርጅቶች ልብስ፣ ውሀ፣ መጠለያ፣ ልዩ ልዩ አልሚ ምግቦች፣ የመጀመርያ የህክምና እርዳታ፣ መሰረተ-ትምህርት ያቀርቡ ነበር። በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የተከሰቱ ድርቅ እና ርሀብን ለመከላከል እና የዜጎችን ህይወት ለመታደግ በጊዜው የነበሩ የእርዳታ ድርጅቶች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ሁለተኛው ደረጃ የእርዳታ ድርጅቶች ከሰብአዊ እና የእለት ደራሽ ስራዎች በተጨማሪ በአፈር ጥበቃ፣ ደን ማልማት እና ሌሎች መሰል ዘላቂ ልማት ስራዎች ውስጥ የተሰማሩበት ወቅት ነበር። ሶስተኛው ደረጃ በመባል የሚታወቀው ምእራፍ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በመልካም አስተዳደር፣ በሰብአዊ መብት መከበር እና በህግ የበላይነት፣ የግለሰብ እና የቡድን መብቶች መከበር እና መሰል ተግባራት የተሰማሩበት ምእራፍ ሲሆን ይህ ምእራፍ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ መጠነኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የቻሉበት ውቅት ነበር ማለት ይቻላል።

አገራዊ ለውጡን ተከትሎ መንግስት ቀደም ሲል ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥር የነበረውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 በመሻር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ማውጣቱ ይታወሳል። በህግ ማሻሻሉ ሂደት የሲቪል ማህበራት መንግስት ለዘርፉ ሊሰጠው የሚገባውን ቦታ በማመላከት እና ጫና በመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የሲቪል ማህበራት ሚና፡

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሰፊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካ ሚና ያላቸው ሲሆን የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የሰብአዊ

መብቶች ጥበቃን ማጎልበት፣ በዴሞክራሲ ባህል ግንባታ፣ የስነ-ዜጋ ትምህርት በመስጠት ዜጎች ስለመብቶቻቸውና ኃላፊነታቸው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ እና መብቶቻቸውን የሚያስከብሩባቸውን መንገዶች ማመላከት፣ በሃገራዊ አጀንዳ ቀረጻ ላይ ዜጎች የተጠኑና ፋይዳ ያላቸው አማራጮች እንዲንሸራሸሩ መድረክ መፍጠር፣ ፖሊሲዎችና ህጎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግና ዜጎችም በጉዳዩ ላይ እውነተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማስቻል፣ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ማጋለጥ፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ተጠያቂነት እና ግልጸኝነት እንዲሁም የዜጎች ተሳትፎ እንዲኖር ማስቻል።

ይሁን እንጂ በሀገራችን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሚናቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ በርካታ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ፣ እና ቴክኒካዊ ተግዳሮቶች ተጋርጠውባቸዋል። የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ውስጣዊ እና ውጫዊ በሚል ከፍሎ ማየት ይቻላል።

ውስጣዊ ተግዳሮት

ሀ. እንደ ዘርፍ ሃገራዊ አጀንዳ ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆኑ፣

ለ. በህዝብና በመንግስት ዘንድ ያላቸው ታማኝነት ዝቅተኛነት፣

ሐ. ሚናና ተልዕኮ ላይ ቁርጠኝነትና ግልጸኝነት ማነስ፣

መ. የሲቪል ማህበራት በውስጣዊ አደረጃጀታቸው የዲሞክራሲ ልምምድ ያለመኖርና ልል የሆነ ተጠያቂነት፣

ሠ. በአዋጅ ቁጥር 621/2011 ውርስ ምክንያት ድርጅቶቹ ከነበሩበት ቆፈን ያለመውጣት፣

ረ. የበጎ ፍቃድ ተነሳሽነት ላይ የአቅም ውስንነት መኖር፣

ሰ. ፖለቲካዊ ገለልተኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ መግባት፣

ውጫዊ ተግዳሮት

ሀ. የክልልና የፌደራል መንግስታት ሴክተሩን እንደ ልማት አጋር በማየት ረገድ ውስንነት መኖር፣

ለ. በቂ የፋይናንስ ምንጭ ያለመኖር፣

ሐ. የሃገራችን በሰላም እጦትና አለመረጋጋት አዙሪት ውስጥ መውደቅ።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ለዘርፉ ተገቢውን ቦታ መስጠት እና መደገፍ አስፈላጊ መሆኑን በጽኑ ስለሚያምን ለዘርፉ መጎልበት አበክሮ ይሰራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሴክተሩ ካሉበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተላቆ በሀገራዊ ልማት፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እና በሰላም ግንባታ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችል ዘንድ ለዘርፉ መጎልበት ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

13 ብዙሀን መገናኛ (ሚዲያ)

ሚዲያ የመንግስት አካል በሆኑት የህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና ህግ ተርጓሚ አካላት መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል ለመቆጣጠር እና ሚዛን ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን በዚህም አራተኛው የመንግስት አካል በመባል ይታወቃል። የሚዲያ ተቋማት ህዝብ ስለ መንግስት እንቅስቃሴ፣ ስለ ሀገሩ ልማትና እድገት፣ ወቅታዊ ሀገራዊ እና ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ የሚያገኝበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት ስለ ህዝቡ ችግር፣ ፍላጎትና ስሜት የሚያውቅባቸው መገናኛ ድልድዮችና የዲሞክራሲ መሰረቶች ናቸው።

ሚዲያ የዜጎችን ማህበራዊ ግንኙነት ብሎም አስተሳሰብና አመለካከት በመቅረጽ ሂደት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የሚዲያ ተቋማት በቴክኖሎጂ ባደጉ ሀገራት ጠቀሜታና ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው ከፍተኛ ነው። በሃገራችን የሚዲያ እና የጋዜጠኝነት ሙያ እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦም አናሳ ነው።

በሀገራችን የመገናኛ ብዙሀን ለገዥ መደቦች የፖለቲካ እና የፕሮፖጋንዳ መሳሪያነት ከማገልገል በዘለለ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የረባ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትኩረት አልተሰጠም። የሚዲያ ሴክተሩ አሁን የደረሰበት የእድገት ደረጃ የመጀመሪያው የሀገራችን ጋዜጣ “አእምሮ” በተጀመረበት ወቅት ከነበረበት ብዙም አልተሻለም። ይህም የዘርፉ ዕድሜና ዕድገት በጭራሽ እንዳልተመጣጠኑ ያሳያል። በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ሚዲያ ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወት

የዲሞክራሲ ባህል ያዳበሩና ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ ሀገሮች ተሞክሮ ያረጋግጣል። ህዝብ በፕሬስ ውጤቶች አማካይነት ስለመረጣቸው ባለስልጣናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል። የሚነድፋትን ፓሊሲዎች፣ መመሪያዎችና አዋጆች እንዲሁም ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚደረጉትን ግንኙነቶች ይገመግማል። ድጋፍን ወይንም ተቃውሞውን በእነዚህ የመገናኛ ብዙኀን አማካይነት ይገልፃል።

ባደጉት ሀገራት መገናኛ ብዙሃን ከህግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚው የመንግስት አካላት ቀጥሎ ባለው ረድፍ ላይ በመሰለፍ የሦስቱን የመንግስት አካላት እንቅስቃሴዎች የህዝብ አይንና ጆሮ ሆነው ይቆጠራሉ። ይህ አሰራር በሃገራችን ተግባራዊ አልሆነም።

የሀገራችን ብዙሀን መገናኛ ዘርፍ ከዚህ በተፃራሪው ሲንቀሳቀስ የቆየ በመሆኑ በህዝቡ ዘንድ ተገቢው ክብር አላተሰጠውም። በመንግስትና በባለሙያው የነበረው ስሜትም ከዚህ የተለየ አይደለም። በሙያውና በባለ ሙያው ላይ የነበረውን የተዛባ የህዝብ አመለካከት ለመቀየር ከሁሉም በላይ ሙያዊ አሰራሩን ከዘፈቀዳዊነት ማላቀቅ ያስፈልጋል። ሙያው በሌሎች ሀገሮች ያለውን ሚና ይጫወት ዘንድም ባለሙያው በተገቢው መልኩ ወደ ሙያው እንዲመጣና የብቃት ደረጃው አስተማማኝ እንዲሆን መጣር ያሻል። የባለሙያው ከህዝብ ቀድሞና አውቆ መገኘት ብሎም በህግና ስርዓት መመራት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ ነግሶ የቆየውን የተዛባ አመለካከት ለማስተካከል ይረዳል።

በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት እና ሉአላዊነት ከሚያረጋግጡ ተቋማት አንዱ ነፃና ገለልተኛ ፕሬስ መሆኑ ይታወቃል። ፕሬስ እንደሙያ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በህብረተሰቡ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ጉልህ ሚና አበርክቷል ። ለፖለቲካ ግልፅነትና ለተጠቃሚነት መስፈን ግንባር ቀደም ሚና ተጫውቷል። በምርጫ ሂደት በእውነት ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ አስተሳሰቦች በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲንሸራሸሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የመንግስት ባለስልጣናት እና ፖለቲከኞች በህግ ማእቀፍ ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የብዙሀን መገናኛ አይተኬ ሚና አላቸው። ሚዲያ ህዝቡ ለመብቱ እንዲታገል በማስተማርና በማሳወቅ የፖለቲካ አቅጣጫዎችን በመጠቆም እና በማስተካከል ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል።

አንድ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ምን እየሰራ እንዳለ፣ ምን እንዳልሰራ እና ምን ሊሰራ እንዳሰበ ለመራጩ ወገን በበቂ ሁኔታ እና በግልጽ የማያሳውቅ ከሆነ በመንግስትነት ሊመረጥም ሆነ ሊታሰብ አይችልም። መራጩ ዜጋ በዋና ዋና የመንግስት አካላት የሚሰራውንና ሊሰራ የታቀደውን ለማወቅ የሚችልበት መንገድ በብዙሀን መገናኛ አማካኝነት ነው። ብዙሀን መገናኛ ከህዝብ ጎን በመወገን የመንግስትን እንቅስቃሴ እየተከታተለ ለህዝብ ያቀርባል። በዚህ ምክንያት ነጻ ፕሬስ የአንድ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት ምሰሶ ለመሆን በቅቷል። ከዚህ ተግባሩ በመነሳትም የብዙሀን መገናኛ የዲሞክራሲ ስርዓት ተንከባካቢ ወይም ጠባቂ (watchdog) የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል።

የብዙሀን መገናኛ ተቋማት የመንግስት ጭፍን ደጋፊ ወይም ጭፍን ጠላትነት በመራቅ የሃቅ ተሚጋች እና የዜጎች ጠበቃ በመሆን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ፕሬስ በፖለቲካ ስልጣንና በፖለቲከኞች ዙሪያ የሚያከናውነው እውነትን የማረጋገጥ ሒደት እንደ አንድ የዲሞክራሲ ዋስትና እንዲታይ አድርጎታል። በእውነት ላይ የተመሰረተና በሃላፊነት መንፈስ የሚከናወን የፕሬስ ተግባር በህዝቡ ዘንድ ተአማኝነትና ተቀባይነት ይኖረዋል። ተቀባይነት ያለው ፕሬስ የአንድን የፖለቲካ ስርዓት ሂደትና አቅጣጫ የመምራት ድርሻው ከፍተኛ ሲሆን አጀንዳ በመቅረጽ እና በህዝቡ አስተሳሰብና ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ለህዝብ ፍላጎት የቆመ ማንኛውም መንግስት መልካም የመንግስት አስተዳደር ስር ሊሰድ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅበታል። መልካም አስተዳደር ከሚንጸባረቅባቸው በርካታ መስፈርቶች መካከል አንደኛው የመንግስትን አሰራር ለህዝብ ግልጽ ማድረግ ነው። ስልጣን የሚመነጨው ከህዝብ እንደመሆኑ መጠን ህዝቡ የመንግስት ተቋማትን እንቅስቃሴዎች የማወቅ መብት አለው። ስለሆነም የህግ የበላይነት መከበሩንና አለመከበሩን መንግስት የሚያወጣው እቅድና ፖሊሲ ላይ የህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊ ስለሆነና ተጠያቂነት ከሌለ መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊፈጠር ስለማይችል ፕሬስ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ የማይተካ ሚና አለው ።
ፍርድ ቤቶች የመንግስት ተቋማት እንደመሆናቸው አሰራራቸው ለህዝብ ግልጽ ሊሆን እንደሚገባ አጠያያቂ አይደለም። በፍርድ ቤቶች የሚከናወኑ ስራዎች በመሰረቱ

ለህዝብ ክፍት እንዲሆኑ ህገ-መንግስቱ ግድ ይላል። (ኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 12 (1)። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሰው የፍርድ ቤቶችን ውሎ በአካል ተገኝቶ መከታተል አይችልም። ስለዚህ መገናኛ ብዙኀን የፍርድ ቤቶችን የስራ እንቅስቃሴ ለህዝብ በማድረስ ህዝብ የህግና የህግ ተጠያቂነት ግንዛቤውን እንዲያሳድግ ፍርድንም ሰምቶ እንዲማርበት እና እንዲተችበት በማድረግ የማይተካ ሚና አላቸው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተመለከቱትን የብዙሀን መገናኛ እሳቤ እና መርሆች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሀገራችን የሚዲያ ዘርፍ ለሀገራችን የሰላም፣ የዴሞክራሲ እና የልማት እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ ሚና መጫወት በሚችል መልኩ እንዲደራጅ አስፈላጊ የህግ ማሻሻያና ተገቢውን ሁሉ ድጋፍ ያደርጋል።

14 የአዲስ አበባ ጉዳይ

የፌደራል ስርዓት በሚከተሉ ሀገሮች የዋና ከተማ አስተዳደር ጥያቄ አከራካሪ ጉዳዮች ያሉት ሲሆን ይህ ውዝግብ ለዋና ከተማነት የሚሆነውን ቦታ ከመምረጥ ጀምሮ ዋና ከተማው የሚተዳደርበት መንገድና የከተማው የወደፊት እድገት ወዘተ ያካትታል፡፡ የዋና ከተማ አስተዳደር ጥያቄ **በአሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ቤልጀም፣ ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ** በሌሎች የፌደራል ስርአት በሚከተሉ ሀገራት ውስጥ ተከስቷል፡፡ አዲስ አበባን በተመለከተ የሚታየው የአስተዳደር፣ የወሰን፣ የባለቤትነት፣ የልዩ መብት ውዝግብ የዚህ ዓለም አቀፍ የፌዴራል ሀገራት ተሞክሮ መገለጫ ነው፡፡ ከዋና ከተማ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥያቄዎች የሶስት ዋና ዋና ፍልጎቶች ግንኙነትጭት የወለዷቸው ችግሮች ሲሆኑ እነሱም፣

- የመጀመሪያው እና ዋነኛው ፍልጎት የዋና ከተማው ነዋሪዎች ፍላጎት ነው፡፡ ይህ ፍላጎት የከተማው ነዋሪ ህዝብ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ያለው መብት ሳይሸራረፍ እንዲከበር ለማድረግ የሚደረግ ትግል ነው፣

- ሁለተኛው የፌደራል መንግስቱ ፍላጎት ሲሆን ይህም የፌደራል መንግስቱ አንድ ጠንካራ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ከክልሎች ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ እንዲያካሂድ ለማድረግ የሚፈጠር ፖለቲካዊ ፍላጎት ነው፡፡ ይህ የፌዴራል መንግስት በዋና ከተማ ላይ ያለው ፍላጎት ማዕከላዊው መንግስት የሀገሪቱን ብሄራዊ ልማት ለማቀላጠፍ፣ የሀገሪቱን ደህንነት ለማስጠበቅ እና በክሎች መካከል ፍትሀዊ እድገት ለማስመዝገብ ያለበትን ህገመንግስታዊ ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይህ አሰራር ዋና ከተማው ጠንካራ ብሔራዊ ሚና (National Role) እንዲኖረው እና የሁሉም ዜጎች ብሔራዊ ምልክት (National Symbol) እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ለመፍጠር ያስችላል፣

- ሶስተኛው የፌደሬሽኑ አባል በሆኑ ክልሎች የሚንጸባረቅ ፍልጎት ሲሆን በተለይ በጂኦግራፊ ወይም በታሪክ ከዋና ከተማው ጋር ግንኙነት ያላቸው ክልሎች የዋና ከተማው እድገት ለሚፈጥርባቸው አሉታዊ ተጽኖ በቂ ምላሽ መስጠቱን ለማረጋገጥ የሚዘረጋ ፖለቲካዊ/አስተዳደራዊ ዘዴ ነው፣

ከላይ ከተጠቀሱት በዋና ከተማ ላይ ከሚፈጠሩ ፍላጎቶች በተጨማሪ እንደ ብራሰልስ (ቤልጄም) ያሉ ከተሞች ደግሞ ከአውሮፓ ህብረት ማዕከልነት ጋር በተያያዘ የሚነሳ አራተኛ ፍልጎት አለ፡፡ ከዚህ አንጻር እንደ ብራሰልስ ያሉ ከተሞች በውስጣቸው ላሉት አህጉራዊ ተቋማት ምቹ እንዲሆኑ ከብሄራዊ ማንነት ባለፈ “አህጉራዊ ማንነት” እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ከዋና ከተማ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ተደራራቢ ፍልጎቶች በፌዴራሊዝም አውድ ሲታዩ፣ የአዲስ አበባ አስተዳደራዊ ሁኔታን አስመልክቶ የሚኖሩ የፖሊሲ እና የህግ አማራጮች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ የፌዴራል ስርአት ያላቸው የዓለም ሀገራት ዋና ከተሞቻቸውን ለማስተዳደር የሚከተሏቸው አማራጭ የህግ ማእቀፎች (ሞዴሎች) ቀጥለው ቀርበዋል፣

◆ **ራሱን ችሎ በክልልነት የተቋቋመ ዋና ከተማ (A Member State Model)፡** በዚህ መንገድ የተመሰረተ ዋና ከተማ እንደ አንድ የፌደሬሽኑ አባል የህግ እውቅና የተሰጠው ክልል ሲሆን፣ የከተማው ኗሪ እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር የተሻለ እድል ይሰጣል፡፡ የቤልጀም ዋና ከተማ ብራሰልስ አስተዳደር ይህን ሞዴል የሚከተል ሲሆን ከተማዋ እንደ አንድ የፌደሬሽኑ አባል ክልል እንድትቆጠር አድርጓታል፡፡ ይህ አሰራር አዲስ አበባ ከተማ

በሽግግር ወቅት ራሷን ችላ እንደ አንድ ክልል ከነበራት አደረጃጀት ጋር ይመሳሰላል፡፡

◆ **በፌዴራል መንግስት ስር የሚተዳደር ዋና ከተማ፡** ይህ አሰራር (a Federal District Model) **በመባል የሚታወቅ** ሲሆን ዋና የአንድ ሀገር ዋና ከተማ መላ የሀገሪቱ ዜጎች በእኩልነት እንዲገለገሉበት የተሻለ እድል ይሰጣል፡፡ የአሜሪካ ዋና ከተማ የሆነችው ዋሽንግተን ዲሲ ይህንን የዋና ከተማ ሞዴል የሚከተል ነው፡፡ ይህ ሞዴል ዋና ከተማን የማስተዳደር ስልጣን ሙሉ ለሙሉ ለፌዴራል መንግስት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

◆ **በአንድ ክልል ውስጥ የሚገኝ ዋና ከተማ (A City in a Member State Model)፡** ይህ አሰራር የአንድ ሀገር ዋና ከተማ በአንድ የፌዴሬሽኑ አባል በሆነ ክልል ውስጥ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው፡፡ የካናዳ ዋና ከተማ ኦትዋ ይህንን የዋና ከተማ ሞዴል የሚከተል ነው፡፡ በአዲስ አበባ ላይ የባለቤትንት መብት የሚያነሱ አካላት የሚያቀርቡት የአስተዳደር አማራጭ ከዚህ አሰራር ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

እያንዳንዱ ሞዴል የራሱ ጥንካሬና ድክመት አለው፡፡

ብራሰልስ (ቤልጀም) የምትከተለው **"A Member State Model"** ዋና ከተማዋ ማንኛውም ክልል ያለውን መብት ያለው ሲሆን በተጨማሪ የዋና ከተማነት ሚናም ይኖረዋል፡፡ የከተማውን ኗሪ እራሱን የማስተዳደር መብት በማረጋገጥ በኩል የተሻለ ቢሆንም የፌደራል መንግስትን እንቅስቃሴ ይገድባል፡፡ እንዲሁም እንደ ዋና ከተማ እያገለገለ ያለው ክልል ያልተገባ ተጽእኖ በመፍጠር በፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች መካከል እኩል የሆነ ቁመና እንዳይኖር ስለሚያደርግ በሌሎች የፌዴሬሽኑ አባላት ዘንድ ቅሬታን ይፈጥራል፡፡

ዋሽንግተን (አሜሪካ)፣ አቡጃ (ናይጀሪያ) የሚከተሉት እና **"Federal District Model"** የተሰኘው የዋና ከተማ አስተዳደር ፌደራል መንግስቱ በዋና ከተማው ላይ ሰፋ ያለ መብትና ቁጥጥር እንዲኖረው የሚያደርግ ሲሆን የፌደራል መንግስቱ ስራውን በነጻነት እንዲሰራ ከማድረጉም በላይ ዋና ከተማው የሁሉም የሀገሪቱ ህዝቦች እና ክልሎች ማዕከል እንድትሆን ሰፊ እድል ይሰጣል፡፡ ይሁን እና የከተማውን ህዝብ እራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተወሰነ መልኩ የሚገድብበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በሁለቱም ሞዴሎች ከተሞቹ እያደጉ ሲመጡ ከአጎራባች ክልሎች ጋር ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

ኦትዋ (ካናዳ) የመሰሉ ከተሞች የሚከተሉት **"A City in A Member State Model"** ዋና ከተማው በሚገኝበት ክልል ህግ እንዲተዳደር ስለሚያደርግ የፌደራል መንግስቱ ዋና ከተማው ለሚገኝበት ክልል ጥገኛ ይሆናል፡፡ የፌደራል መንግስቱ እንቅስቃሴ በክልሉ ይሁንታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የፌደራል መንግስቱን ጥንካሬ ይጎዳዋል፡፡ እንዲሁም ዋና ከተማው የሚገኝበትን ክልል ባህል፣ ቋንቋ ብቻ እያንጸባረቀ በሌሎች ፌደሬሽን አባላት ላይ ቅሬታና ግጭት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ የዚህ ሞዴል ዋነኛ ጥቅም ከዋና ከተማ መስፋት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማስቀረት ብቻ ነው፡፡

አዲስ አበባን አስመልክቶ የሚነሱ አስተዳደራዊ አማራጮች ከላይ ከተዘረዘሩት ዓለም አቀፍ አሰራሮች ጋር እጅግ ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን በአዲስ አበባ ላይ የሚንጸባረቁ ፖለቲካዊ ፍልጎቶችን በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

- አንደኛ አዲስ አበባ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናት የሚል በዋናነት የአዲስ አበባ ነዋሪን ፍልጎት የሚያንጸባርቅ ፍላጎት፣ ሁለተኛ አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ናት የሚል በይዘቱ የፌደራል መንግስት ሊይዘው የሚገባውን ፍልጎት የሚያንጸባርቅ ፍላጎት፣
- ሶስተኛ ጅኦግራፊን፣ ታሪክንና ህገ-መንግስትን በመጥቀስ የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ላይ የሚያነሳው የልዩ ጥቅም ጥያቄ የሚያንጸባርቅ ፍላጎት፣

በመሆኑም በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚነሱ የህግ እና የፖለቲካ አስተሳሰቦች መካከል ያለው ልዩነት አዲስ አበባ በየትኛው ሞዴል ትተዳደር የሚለው ነው፡፡ አዲስ አበባ በሽግግር መንግስት ወቅት እንደ አንድ ክልል (ክልል 14) እንድትተዳደር **(A Member State Model)** የተወሰነ ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ይህን የአዲስ አበባ የክልልነት ደረጃ አስቀርቷል፡፡ የኢፌደሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 አንዳንድ ነገሮችን በለሆሳስ ማለፋ አሁን ለሚታየው ውዝግብ አስተዋጾ አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡ ህገ መንግስቱ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት ከማለት ባለፈ ፌደራል መንግስት በአዲስ

አበባ መሬት ላይ ያለው የባለቤትንት ወሰን፣ በአዲስ አበባ ጉዳይ ህግ የማውጣት ስልጣኑ ወዘተ በግልጽ አለመቀመጡና ጉዳዩን በገደምዳሜ ማለፉ አሁን ላለው ችግር አስተዋጾ አድርጓል፡፡ ህግ አውጭዎቹ ያሰቡትን የአስተዳደር ሞዴል በግልጽ ህገ መንግስቱ ላይ አለማስቀማጣቸው አሁን ለሚታየው ውዝግብ በር ከፍቷል፡፡

በዋና ከተማ ላይ የሚነሳ የባለቤትነት ጥያቄ በዋናናት በራሳቸው ሉአላዊ የነበሩ ግዛቶች ተሰባስበው አንድ ፌደሬሽን ሲፈጥሩ (Coming Together Federations) የሚነሳ ጥያቄ ሲሆን እነዚህ በራሳቸው ሉአላዊ የነበሩ ግዛቶች ለዋና ከተማነት የሚሆን ቦታ አዋጥተው ይሰጣሉ ወይም አንዱ ግዛት በፈቃደኝነት ቦታ ይሰጣል ወይም በአንዱ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ከተማ ለዋና ከተማነት ይመረጣል፡፡ የኢትዮጵያ ያለው የፌዴራል ስርአት እንደ ሀገር አብረው የኖሩ ህዝቦች እና አካባቢዎች አንድነታቸውን ይበልጥ ለማጠንከር የፈጠሩት የፌዴራል ስርአት (Holding together Federation) በመሆኑ ክልሎች በአዲስ አበባ ላይ የባለቤትነት ጥያቄ ሊያነሱ የሚችልበት አጋጣሚ ጠባብ ነው፡፡

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥያቄ በፌደራሊዝም አውድ እና የሌሎች ሀገሮችን መልካም ተሞክሮ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ሊታይ ይገባል ብሎ ያምናል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ በዋናነት የአዲስ አበባ ነዋሪን፣ ከዚያም የፌደራል መንግስቱን እና የመላው ኢትዮጵያውያንን ተመጋጋቢ ፍልጎቶች በፍትሀዊነት ማስታረቅ በሚችል የህግ ማእቀፍ ሊታይ ይገባል፡፡ የአዲስ አበባ የአስተዳደር ጥያቄ የከተማዋን ነዋሪ ህዝብ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ እንዲሁም ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት እንዲኖር በሚያደርግ ሁኔታ ሊመለስ ይገባል፡፡ ነእፓ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያለው እይታ ከላይ የተጠቀሱትን የንድፈ ሀሳብ እና አለም አቀፍ ተሞክሮ እንዲሁም ለከተማዋ ነዋሪ የፍላጎት ቅደም ተከተል (Hihrarchy of needs) መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ነእፓ የተለያየ የፖለቲካ ፕሮግራም እና ፍላጎት ያላቸው ኃይሎች በአዲስ አበባ አስተዳደር ዙሪያ ከሚያደርጉት የተካረረ “የባለቤትነት” ጥያቄ ባሻገር የከተማዋን ነዋሪ መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት ትኩረት ሊሰጡ ይገባል ብሎ ያምናል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ እጅግ አስከፊ በሆነ ድህነት እና ድህነቱ በወለዳቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ውስጥ ይኖራል፡፡ የከተማዋ የስራ አጥ ቁጥር በየእለቱ እያሻቀበ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የምግብ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና እና የትምህርት ችግሮች አብዛኛውን የከተማዋ ነዋሪ አስመርሮታል፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ ከስድሳ ሺህ የሚበልጥ ዜጋ ኑሮውን በጎዳና ላይ መስርቷል፡፡ የከተማዋ ነዋሪዎች ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ የተለያየ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ቀለም፣ ያላቸው ሲሆኑ እያንዳንዱ የከተማዋ ነዋሪ በከተማዋ የተንሰራፋው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ችግሮች ገፈት ቀማሽ ነው፡፡

ይህንን አሳዛኝ እውነታ ታሳቢ በማድረግ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚደረጉ ክርክሮች በዋናነት የከተማዋን ነዋሪ መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት ያለሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት ነእፓ መሰረታዊ የሆኑ የከተማዋ ነዋሪዎች ቁሳዊ ፍላጎቶች (Physiological needs) ማለትም የምግብ፣ ውሀ፣ መጠለያ፣ ንጹህ አየር እና አካካቢ ወዘተ ቅድሚያ ሰጥቶ ይሰራል፡፡ በመቀጠል የነዋሪዎቿ ደህንነት፣ የስራ እድል፣ ጤና፣ ሀብት የማፍራት ፍላጎቶች እንዲሟሉ የሚያደርግ አቅጣጫን ይከተላል፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንዲሁም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ከመሆኗ አንጻር የከተማዋ አስተዳደር እና እድገት በከተማይቱ የሚኖሩ የውጭ እንግዶችን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

ከአዲስ አበባ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በቀጥታ ተጽእኖ የሚደርስባቸው በከተማዋ ዙርያ የሚኖሩ በግብርናና እና በሌሎች የስራ መስኮች የተሰማሩ ዜጎች የከተማውን መስፋፋት እንደ ስጋት ሳይሆን እንደ እድል የሚያዩበት ለህይወታቸው፣ ለንብረታቸው እና ለማህበራዊ እሴቶቻቸው ትኩረት የሚሰጥ የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ስራ ላይ ይውላል፡፡ ለዚህም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚኖሩ ወገኖች ከአካባቢያቸው ሳይፈናቀሉ በከተማው ውስጥ ተካተው የከተማው ነዋሪ እና እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ በልማት ምክንያት ከቦታቸው መነሳት ግድ በሚሆንበት ወቅት በቂና ተመጣጣኝ ካሳ በመስጠት ከአካባቢያቸው ሳይርቁ የተሻለ የስራ እድል እንዲያገኙ እና የተሻለ ህይወት መኖር እንዲችሉ ይደረጋል፡፡

ላለፉት በርካታ አመታት በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ ገበሬዎች ከሞኖሪያ ቂያቸው፣ ከንብረታቸው እና ከሞቀ ቤታቸው "በልማት" ስም እንዲፈናቀሉ፣ ቤተሰባቸው እና ማህበራዊ ኑሯቸው እንዲናጋ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህ የተሳሳተ የመንግስት አሰራር በርካቶች ለከፋ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተዳርገዋል፡፡ ድሀ ገበሬዎች መሬታቸው "በነጻ" ተወስዶ ፖለቲኮኞች እና የእነሱ ተለጣፊ ኪራይ ሰብሳቢ ነጋዴዎች እንዲበለጽጉበት ተደርጓል፡፡ ይህ አሰራር ከአዲስ አበባ አልፎ የሀገራችን ፖለቲካ ከፍተኛ የግጭት መነሻ ሆኗል፡፡

በመሆኑም ነእፓ በከተማው ዙሪያ የሚገኙ ገበሬዎችን ከቦታቸው በማፈናቀል ለከፋ ድህነት እንዲጋለጡ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወታቸው እንዲፋለስ ብሎም በከተሞች የጎዳና ተዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያደርገው ኃላፊነት የጎደለው የመንግስት አሰራር በማስቆም ለዜጎች ሁለንተናዊ ደህነነት፣ ለንብረታቸው እና ለኑሯቸው ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ አሰራር ያሰፍናል፡፡

ከአንድ በላይ ዋና ከተማ

የአዲስ አበባ ከተማ የሀገራችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል ማዕከል ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ሁኔታ የከተማዋ ነዋሪ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እንዲሄድ፣ ማህበራዊ አገልግሎቶቿም እንዲቃወሱ፣ የከተማዋ ሰላም እና ጸጥታ እንዲታወክ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ ባሻገር የከተማዋ አስተዳደር የህግ ማዕቀፍ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች በከተማዋ ላይ የይገባኛል ጥያቄ እና ውዝግብ ያስነሳ ሲሆን ይህም የከተማዋ እድገት እንዲግታ አድርጓል፡፡

በከተማዋ ላይ የተፈጠረውን አወዛጋቢ የአስተዳደር ጥያቄ ለመፍታት በከተማዋ ላይ ያሉትን የተለያዩ ፍላጎቶች እና ስጋቶች ሊቀርፍ የሚችል ሚዛናዊ እና ፍትህዊ የህግ ማዕቀፍ መፍጠር የሚያስፈልግ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎን በከተማዋ ላይ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጫና ለመቀነስ እንደ ሌሎች ፌደራል ሀገሮች ሁለት እና ከዚያም በላይ ዋና ከተማዎችን መመስረት እንደ አንድ አማራጭ ሊታይ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ነእፓ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተጨማሪ ዋና ከተሞች በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች እንዲመሰርቱ ያደርጋል፡፡

15 የውጭ ግንኙነት እና ሀገራዊ ደህንነት

የውጭ ግንኙነትና የብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት። ይሁን እንጂ ይህ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረው ግንኙነት የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ከማስከበር አንጻር የነበረው ፋይዳ እጅግ ውስን ነበር ለማለት ይቻላል። ባለፉት ስርዓቶች ሀገሪቱ ስታራምዳቸው የነበሩ የውጭ ግንኙነት እና የብሔራዊ ደሕንነት ፖሊሲዎች በዋናነት በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበሩ አካላትን ፍላጎቶች ለማስፈፀሚያ እንደ ዋና መሳሪያነት ስያገለግሉ ነበር። ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ የውጭ ግንኙነት የፖሊሲ አቅጣጫችን በዋናነት የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም እና የዜጎችን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ ሊዘጋጅ እንደሚገባ በፅኑ ያምናል ለዚሁም ይሠራል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ግኑኘነት ፖሊሲዎች የተዛቡ በሆኑ የታሪክ ትርክቶች እና አረዳዶች ተፅእኖ ስር የወደቁ እንደሆኑ ይታመናል። በቅርብ እና ሩቅ የሚገኙ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ስልታዊ ጠቀሜታ ያሏቸውን አጋር ሀገሮች በጅምላ የመፈረጁ ሂደት ኢትዮጵያ ከነዚህ ሀገራት ማግኘት ያለባትን የተለያዩ ጥቅሞች በተገቢው ሁኔታ እንዳታገኝ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ከዚህ አንፃር ፓርቲያችን ኢትዮጵያ የምታደርጋቸው ማናቸውም ዐይነት የሁለትዮሽ እና የብዙ ወገን ግንኙነቶች ሀገራቱ የሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት አንፃር ያሏቸውን አንድምታ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በመተንተን እና በመረዳት ሊታገዝ እንደሚገባ ያምናል።

እንደሚታወቀው በአሁኑ ሠዓት በአለም አቀፉ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስሪት ውስጥ እየተስተዋሉ ከሚገኙ ዐበይት ለውጦች አንዱ በሀገራት መካከል ያለው የሀይል አሠላለፍ ሚዛን ለውጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው። ከቅርብ አመታት ወዲህ በተለያዩ አለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ታዳጊ ሀገሮች ያላቸውን ተሰሚነት እና ሚና እያሳደጉ መጥተዋል። በሌላ በኩል ሃያላን መንግሥታት በተለያዩ አለምአቀፋዊ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ላይ የነበራቸውን የውሳኔ ሰጭነት ሚና ለማስጠበቅ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛሉ። ይህ ሂደት በተለያዩ አለምአቀፋዊ መድረኮች ላይ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ላይ የራሡ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው ይታወቃል።

በመሆኑም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይህን ተጨባጭ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ኢትዮጵያ ከኃያላን መንግሥታት እና ታዳጊ ሀይሎች ጋር የሚኖራት ግንኙነት ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ እንዲተገበር አፅንኦት ሰጥቶ ይሰራል። በዚህ ረገድ በማናቸውም ሁኔታ ሀገራችን ወደ ተወሠኑ መንግሥታት የምታደርገው ሚዛኑን ያልጠበቀ መዘንበል ብሔራዊ ጥቅማችን እና ሀገራዊ ደህንነታችንን አደጋ ላይ የሚጥል አካሄድ መሆኑን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይረዳል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሊኖራት ስለሚገባው ግንኙነት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። አብዛኛዎቹ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ባሕላዊ እና ፀጥታ ነክ የሆኑ አጀንዳዎቻችን ከጎረቤት ሀገራት ደህንነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ እንደሆነ ይታወቃል። የወደብ አገልግሎት፣ የድንበር ላይ ንግዶች፣ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች (ወንዞች፣ የግጦሽ መሬቶች...) ተጠቃሾች ናቸው። በእነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ሀገራችን ብሔራዊ ጥቅሟን በዘላቂነት ከማስጠበቅ አንጻር በጎረቤት ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት እና በእውነተኛ መከባበር ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ ማራመድ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ፓርቲያችን ይገነዘባል። ከዚህም በተጨማሪ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ባሕላዊ እና የፀጥታ ግንኙነት ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ አሳታፊ የሆነ የጉርብትና ፖሊሲ (Good Neighborhood Policy) ትልቅ ሚና እንዳለው በመገንዘብ ለተግባራዊነቱ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራበታል።

እንደሚታወቀው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የቆየ እና ከፍተኛ ለሆነ የሰው ህይወትና ንብረት ውድመት ምክንያት የሆነ አለመረጋጋት ያለበት ቀጠና ነው። ይህ ቀውስ ሃያላን መንግሥታት በቀጠናው ላይ ያላቸውን ስልታዊ ፍላጎቶች ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ፉክክር የበለጠ እየተወሳሰበ እና አድማሱን እያሠፋ የሄደበት ሁኔታ አለ። ይህም ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጠናው ላይ ያላትን ፍላጎቶች በማስጠበቅ ረገድ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ከዚህ በመነሳት በቀጠናው ላይ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ሊፈጥርና የሃገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ሳይሸራረፍ ለማስጠበቅ የሚያስችል የፖሊሲ አማራጭን ለማቅረብ በከፍተኛ ተነሳሽነት መንቀሳቀስ እንደሚገባ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ያምናል። ከዚሁ ጎን ለጎን በአካባቢው ላይ ከሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ቀጠናዊና አህጉራዊ ድርጅቶች ለምሳሌ ኢጋድ፣ አፍሪካ ህብረትና ሌሎችም ተቋማት ጋር በንቃትና በተቀናጀ ሁኔታ አብሮ በመስራት ለአካባቢው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ኢትዮጵያ የበኩሏን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርባት ፓርቲያችን ይገነዘባል፤ ለዚህም ያለመታከት ይሠራል።

ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እና የድንበር አንድነቷን አስጠብቃ ለመቆየት የውጭ ግንኙነትና የብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲዋን የምታስፈፅምባቸው ስልቶች ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ይታወቃል። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ መልካም ተፅዕኖ መፍጠር በምትችልባቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባህል መልካም ዕሴቶችና የዲፕሎማሲያዊ ተግባራት (soft power) እንዲሁም ወታደራዊ ተግባራት (hard power) በተገቢው ሁኔታ እና ጊዜ መጠቀም ያስፈልጋል።

በተለያዩ ጊዜያት እዚህም እዚያም የሚስተዋሉ ግጭቶችና በቀጠናው ብዛት ያላቸው የታጠቁ ቡድኖች በስፋት መገኘት ለአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ፀጥታ ትልቅ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። እነዚህን ተግዳሮቶች በተገቢው ሁኔታ በመመከት ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን ማስጠበቅ ትችል ዘንድ ወታደራዊ ሃይሏን እና የፀጥታ ተቋሞቿን የበለጠ ማጠናከር በከፍተኛ ትኩረት መሠራት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ እናምናለን።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በተለያዩ እርከኖች የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ፖሊሲዎችን የማስፈፀም ኃላፊነቱን የሚወስዱ አካላትን አቅም መገንባትንም ከፍተኛ ትኩረት ከሚቸራቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የሆነ የዲፕሎማሲ ሥራን በማከናወን ረገድ አምባሳደሮች እና ዲፕሎማቶች የማይተካ ሚና አላቸው። በመሆኑም እነዚህን አስፈፃሚ አካላት በመመልመል እና በመሾም ሂደት ላይ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቁ ረገድ ያላቸውን ብቃትና ተነሳሽነት በሚገባ መፈተሽ ያስፈልጋል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችንን ወክለው በተለያዩ ሀገራት እና አለም ዓቀፍ ተቋማት የሚሰሩ ኃላፊዎች የዲፕሎማሲ እና የውጭ ግንኙነት ሙያ ያላቸው (Carrier Diplomat) እንዲሆኑ እንዲሁም በመንግሥታት መካከል ከሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጎን ለጎን ፓርቲያችን ፐብሊክ እና ዳያስፖራ ዲፕሎማሲም የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቁ ረገድ ለሚኖራቸው አስተዋጽኦ ትልቅ እውቅና ይሠጣል። በተለያዩ የአለማችን አካባቢዎች የሚኖሩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሀገራችንን መልካም ገፅታ በማስተዋወቅ ሀገራችን የተሻለ የቱሪዝም እና የውጭ ኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ማድረግ እንዲችሉ አስፈላጊው የህግ እና የአሰራር ስርአት ይዘረጋል።

ምዕራፍ ሁለት

ጠንካራ እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ

1 አካታች የኢኮኖሚ እድገት እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ «ሰፊ መሰረት ያለው፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ለዘላቂ ልማት ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው።» ብሎ ያምናል። አካታች የፖሊሲ ማዕቀፍ ሀገራችን ኢትዮጵያ ድህነትን ለመቀነስና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በምታደርገው ጥረት ከፍተኛ እገዛ አለው። ኢ-ፍትሀዊ እና የተዛቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድሎች ሀገራችን ዛሬ ላይ ላለችበት ሁለንተናዊ ቀውስ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው።

በሀገራችን በዜጎች መካከል የሀብት ልዩነት እንዲሁም በክልሎች መካከል ያለው የልማት ክፍተት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የሀገሪቱ በርካታ አካባቢዎች እድገት እና የዜጎች የኑሮ ደረጃ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አካታች የልማት ፖሊሲና ፕሮግራም እንዲሁም ፖለቲካዊ ፍላጎት እንዳልነበረ እና አሁንም እንደሌለ በግልጽ ያሳያሉ።

ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዘመናት ጥቂቶችን ብቻ የሚያበለጽግ እና ሰፊውን ህዝብ የበይ-ተመልካች የሚያደርግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የእድገት አቅጣጫ ስትከተል ኖራለች። አካታች ያልሆነው የእድገት አቅጣጫ የፈጠረው መዋቅራዊ ስብራት የሀገሪቱ አንድ ሶስተኛ ህዝብ ከድህነት ወለል በታች እንዲኖር ምክንያት ሆኗል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አካታች እድገትን ለማረጋገጥ ድሀ-ተኮር (pro-poor) ፖሊሲዎችን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ለዚህም የተቀናጀ እና የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ እቅድ እና ስትራቴጂዎችን ቀርጾ ይተገብራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አካታች የኢኮኖሚ እድገትን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ዘርፈ ብዙ የሰው ኃይል ልማትን እንደ ቁልፍ መሳሪያ ይጠቀማል።

ፍትሀዊ የሀብት እና የገቢ ክፍፍል

በአንድ ሀገር ውስጥ ፍትሃዊ የሀብት ስርጭት እንዲኖር ማድረግ በዋናነት የመንግስት ኃላፊነት ነው። በዜጎች መሀከል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ጠንካራ ተቋማት፣ መዋቅር እና ህዝባዊ ስርዓት መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዜጎች መሀከል የሚኖረው የሀብት ክፍፍል የህዝባዊ መንግስትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት አመላካች መገለጫ እየሆነ ነው። በአብዛኛው ታዳጊ ሀገራት በተለይም አፍሪካና ደቡብ አሜሪካ የጎንዮሽ እና በቀጥታ በዜጎች መካከል ያለው የሀብት ክፍፍል በጊዜ ሂደት እየሰፋ እየመጣ ነው። በእነኝህ ሀገራት ውስጥ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገት በሚያስመዘግቡበት ጊዜ የሀብት ክፍፍሉ የስርጭት መጠኑ ጎላ ባለ መልክ እንደ ችግር አይታይም ነበር። ነገር ግን የሀገራቱ የኢኮኖሚ እድገት እየጨመረ በመጣ ቁጥር በቡድኖችና ዜጎች መሀከል ያለው የሀብት ክፍተት እየሰፋ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። በኢትዮጵያም የሀብት ክፍፍሉ በጎንዮሽ በገጠር እና በከተማ፣ በክልሎች መሀከል፣ "በማዕከል" እና "በዳር" በጊዜ ሂደት እየሰፋ እየመጣ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎች ይታያሉ።

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አንዱ እና ዋነኛ የፖሊሲ ምሰሶ የሆነው በዜጎች መካከል እኩልነትን ማረጋገጥ በመሆኑ አሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ «ጥቂቶች የሚበለጽጉባት እና የተትረፈረፈ ሀብት ባለቤት የሚሆኑባት በአንጻሩ አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ በቀን አንዴ እንኳ ምግብ ለማግኘት የሚቸገርባት ወቅት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማብቃት አለበት።» ብሎ ያምናል። ስለዚህ በምጣኔ ሀብት ረገድ አንዱ የፖሊሲ ትኩረታችን እድገትን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን የሀብት ክፍፍሉን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ ነው። የተረጋጋ የፖለቲካ ከባቢ እና ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ የጎንዮሽ ግጭቶችን ለመቀነስ እና በዜጎች መካከል ትብብርን ለማጎልበት ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ኢኮኖሚያዊ እኩል ተጠቃሚነትና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን በዘላቂነት እንደ ስርዓት ለማስፈን በሁለት ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል። የዜጎች ተጠቃሚነት መጠንን ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ በምርት ሂደት ላይ ያላቸው ተሳትፎ በመሆኑ ዜጎች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ እኩል ዕድል እንዲኖራቸው የሚያደርጉ የህግ ማእቀፎችን ያዘጋጃል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የዜጎች በእኩልነት የመሳተፍ ዕድል የሚፈጥሩ የትምህርት እና ስልጠና አገልግሎት፣ መረጃ እና ሌሎች ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች በፍትሀዊነት ለዜጎች እንዲደርሱ ይደረጋል። በመሆኑም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ እየሰፋ የመጣውን በዜጎች መካከል የገቢ እና የሀብት ክፍፍል ለመቀነስ በጥናት ላይ የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን የሚያዘጋጅ ሲሆን ይህን መዋቅራዊ ችግር ተቋማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሰራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ለዘላቂ ልማት እና እድገት መረጋገጥ ወሳኝ ነው ብሎ ያምናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር እና እኩል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መሰረተ-ልማቶች አቅርቦት ላይ በትጋት ይሰራል። የመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮግራሞች ህዝብን ያማከሉና የዜጎችን ህይወት በመቀየር ላይ የሚያተኩሩ እንዲሆኑ ይደረጋል።

የግል ሴክተሩ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ፍትሃዊ የሀብት ስርጭትን በሚያጠናክር መልኩ እንዲፈጸሙ ልዩ ልዩ የማበረታቻ ፓኬጆች ይዘጋጃሉ። ከዚህ አንጻር አሁን በመንግስት እየተተገበሩ ያሉት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ፓኬጆች እንዲሻሻሉ ይደረጋል። ለምሳሌ የግብር ክፍያ እፎይታ ማበረታቻ (tax holiday) በግል ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ውሳኔ ላይ ያለው ተፅእኖ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ይህንን አሰራር በመቀየር የኢንቨስትመንት ውሳኔ የፕሮጀክቶች ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል።
በሀገራችን በአብዛኛው የህዝብ የሃብት ምንጭ መሬት መሆኑ ይታወቃል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ በመሬት ላይ ፍትሃዊ የጥቅም ክፍፍል እንዲኖር ማስቻል እንደ ሀገር በዜጎች መካከል ለሚኖረው የሃብት ስርጭት ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። የመሬት ይዞታ ኢኮኖሚያዊ እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፖሊሲዎች እንዲታገዝ ይደረጋል።

2 የመሬት አስተዳደር

የመሬት ፖሊሲ ታሪካዊ ዳራና አሁናዊ ሁኔታ በኢትዮጵያ ከ1966ቱ አብዮት በፊት በሀገራችን የተለያዩ የመሬት ስሪቶች እንደነበሩ የሚታወቅ ሲሆን፣ የመንግስት-አርሶ/አርብቶ አደር ግንኙነት፣ የግብርና ስልተ-ምርት እና ተያያዥ ጉዳዮች በወቅቱ የነበረው የፊውዳል ስርዓት መገለጫዎች ነበሩ። ከ‹ዘመናዊት› ኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ምስረታ በኋላ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የርስት ስርዓት ከሞላ ጎደል በስፋት የቀጠለ ሲሆን በደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍል በዋናነት የጉልት ስርዓት የበላይነቱን ወሰደ። የኋላ ኋላም ከጉልት ስርዓት በተጨማሪ የግል መሬት ይዞታ እየተጠናከረ መጣ። ይህ ሁኔታ በደቡባዊው የሃገሪቱ ክፍል የሚገኘውን አርሶ/አርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ አመሰቃቀለው። ባለ መሬት የነበሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች መሬት አልባ ጭሰኛ ሆኑ። ይህ በጉልት ስርዓት የተጀመረው አርሶ/አርብቶ አደሩን ጭሰኛ የማድረግ ስርዓት የኋላኋላ የግል ኢንቨስትመንትና የግል መሬት ይዞታ ስርዓት ሲጨመርበት ሁኔታውን በከፍተኛ ሁኔታ አባባሰው። በዚህም ምክንያት በፊውዳል ስርዓቱ የመጨረሻ አመታት በአብዛኛው የደቡባዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች የጭሰኝነት ምጣኔው ከ50%-80% ደርሶ ነበር።

የፊውዳል ስርዓቱ ዋነኛ የገቢና የስልጣን ምንጭ በመሬት ላይ ያለው ፈላጭ ቆራጭነት ነበር። ስርዓቱ አዳዲስ በተቆጣጠራቸው ደቡባዊ የሃገሪቱ ክፍሎች መሬት ለፖለቲካ ስልጣን ማደላደያነትና የሃብት ምንጭ አደረገው። የስርዓቱ ቀኝ እጅ የሚባሉ አካላት መሬት በጋሻ እየተለካ ሲወስዱ በአንፃሩ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አርሶ/አርብቶ አደር ጭሰኛ ሆነ። አርሶ/አርብቶ አደሩ ከሚያመርተው ምርት አብዛኛው ክፍል ለባለ መሬቶች፣ ለመንግስት፣ ለሀይማኖት ተቋማት እየተባለ ይወሰድበት ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ተደጋጋሚ የሆነ ግብር እንዲገብር ተደረገ። በአጠቃላይ አብዛኛው የሃገሬው አርሶ/አርብቶ አደር በመሬቱ ባይተዋር የሆነበት ስርዓት ተፈጠረ።

የደርግ መንግስት ስልጣን ሲቆጣጠር በገጠርና ከተማ ስር ነቀል የመሬት አዋጅ አወጀ። በመሬት ላይ የነበሩ ውስብስብ የይዞታና ስልተ-ምርት ግንኙነቶችን ሁሉ አፍርሶ መሬት የመንግስት መሆኑን አወጀ። በመሬት

ከበርቴዎችና የፊውዳል ስርዓቱ በዘረጋቸው የብዝበዛ መሳሪያዎች ተማሮ የነበረው አርሶ/አርብቶ አደር ለጊዜውም ቢሆን ነፃ ወጣ። በከተሞችም የተወሰኑ የመሬት ከበርቴዎች ተቆጣጥረውት የነበረው መሬትም በሌላ አዋጅ የመንግስት ተደረገ። አቅማቸው ለቻለ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቦታ ከመንግስት በነፃ የሚሰጥ ስርዓት ተዘረጋ። ከመሬት ከበርቴዎችና ከውጭ ባለሃብቶች የተወረሱ ቤቶች በኪራይ ቤቶችና በቀበሌ ቤቶች አስተዳደር በኩል በአነስተኛ ወርሃዊ ክፍያ ለተከራዮች ተላለፉ። ይህም ለከተማው ድሃ ከፍተኛ እፎይታ የሰጠ እርምጃ ነበር።

ኢህአዴግ የደርግን መንግስት ጥሎ ሀገሪቱን ሲቆጣጠር የመሬት ፖሊሲውን በተመለከተ ከፍተኛ ለውጥ አላደረገም። መሬት የመንግስት ሆኖ ቀጠለ። የብሄር ብሄረሰቦች የሚል አሻሚ ቃል ህገ-መንግስቱ ውስጥ ከመግባቱ ውጭ ለረጅም ጊዜ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አላደረገም። ኢህአዴግ የተከተለው ገበያ-መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ግዴታ ያደረጋቸው አንዳንድ የመሬት አስተዳደር አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸው ግን አልቀረም። ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት ከአርሶ/አርብቶ አደሮች እየተነጠቀ ለግል ባለሃብቶችና ለውጭ ኢንቬስተሮች በስፋት ተሰጠ። ይህ መሬት በመንግስት እጅ መሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሩን ዳግም ጭሰኛ ላለማድረግ ዋስትና እንደማይሆን ማሳያ ነው።
የመሬት ፖሊሲው ዋና ዋና ችግሮች

1. የይዞታ ዋስትና

ደርግና የኢህአዴግ መንግስታት ከአርሶ/አርብቶ አደሩ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ብዙ የዘርፉ ምሁራን እንደገለፁት «ከፊውዳሊዝም ጭሰኝነት አውጥቶ የመንግስት ጭሰኛ አደረጋቸው።» የሚል ነው። የአርሶ/አርብቶ አደሮች የመሬት ይዞታ ዋስትና ዛሬም ድረስ አልተረጋገጠም። የይዞታ ዋስትና አለመረጋገጡ አርሶ/አርብቶ አደሩን ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ አለማደግ እንደ አንድ ማነቆ የሚወሰድ ነው።

2. መሬትን ከኢኮኖሚያዊ ግብ ይልቅ ለፖለቲካዊ ግብ ዓላማ ማዋል

አርሶ/አርብቶ አደሩ በምርቱ ላይ ያለው መብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም በመሬቱ ላይ ያለው መብት ግን አሁንም የተከበረ አይደለም። መንግስት መሬትን እንደ ፈለገ የሚያከፋፍልበት ሁኔታ በአርሶ/አርብቶ አደሩ ውስጥ ከፍተኛ ፍርሃትና አለመረጋጋት የፈጠረ ነው። በግብርና ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ እያደረጉ የመሬት/የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ አለመቻሉ ለፖሊሲው ውድቀት እንደ አንድ ምክንያት የሚወሰድ ነው። ይህ ከአቅም ወይም ከእውቀት ማነስ የመነጨ ሳይሆን ገዢ መንግስታት መሬትን የፖለቲካ አቅማቸው ማጠናከሪያ አድርገው መውሰድ በመፈለጋቸው ነው።

3. የመሬት ገበያ

የመሬት አዋጆች «መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ነው።» ቢሉም ዛሬም ድረስ በተለያየ መልኩ የመሬት ግብይት እየተካሄደ ነው። መደበኛው የመሬት ገበያ በአንድ አቅራቢ (መንግስትና) የትየለሌ ፍላጎት ባላቸው የመሬት ፈላጊዎች መካከል የሚደረግ የሞኖፖል ገበያ ሆኗል። ይህ ደግሞ የመሬት ገበያው ላይ ጥቁር ገበያ በመፍጠር ህገ-ወጥነትን እያስፋፋ ህዝብ ከመሬት ግብይቱ ተገቢውን ጥቅም እንዳያገኝ አድርጓል። በሌላ በኩል መንግስት ከገበሬው በነፃ የወሰደውን መሬት ለለባለሃብቶች በውድ የሚቸበችብ የመሬት ነጋዴ ሆኗል። ይህ ሁኔታ በአንድ በኩል ገበሬውን ለዳግም ጭሰኝነት እየዳረገ ሲሆን በከተሞች አካባቢ ያለውን የመኖሪያና የመስሪያ ቤት ችግር ክፉኛ እያባባሰው ይገኛል። የመንግስት ሹመኞች ውዱን መሬት በመቸብቸብ ከፍተኛ ሃብት የሚያጋብሱበት ሁኔታ መፈጠሩ በሀገራችን ፍትህና ተጠያቂነት እንዲሁም መልካም አስተዳደር ለማስፈን እየተደረገ ያለውን ጥረት ወደ ኋላ የሚጎትት ነው።

ምርትና ምርታማነት

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሰረቱ ግብርና ነው። ያለፉት ሶስት ስርዓቶች የተለያዩ የግብርናና የመሬት ፖሊሲዎች ተግባራዊ ቢያደርጉም የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ አኳያ ተቀራራቢ በሚባል ደረጃ ወድቀዋል። በተለይም የምርታማነት አለማደግ የሀገሪቱ የምርት ዕድገት ተጨማሪ መሬትን ወደ ስራ በማስገባት ላይ የተመሰረተ፣ ዘላቂ ያልሆነና የተፈጥሮ ሃብትን በማውደም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን አድርጎታል። ለግብርናው ዘርፍ ችግር ማነቆ ከሚባሉት አንዱ ምርትና ምርታማነትን የሚያበረታታ የመሬት ፖሊሲ አለመኖሩ ነው።

የተፈጥሮ ሃብት ውድመት

ይህ ያለፉት ስርዓቶች አርሶ/አርብቶ አደሩን አንድ ጊዜ የፊውዳል ሌላ ጊዜ ደግሞ የመንግስት ጭሰኛ በማድረግ ገበሬው የመሬቱ ባለቤት ወይም ደግሞ የይዞታ ዋስትና የሌለው በማድረጋቸው የመጣ ችግር ነው። በፊውዳል ስርዓቱም ሆነ ቀጥለው በመጡት የወታደራዊውና ኢህአዴግ አገዛዞች ገበሬው የመሬቱ ባለቤት መሆን አልቻለም። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ አርሶ/አርብቶ አደሩ «የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራዎች ይሰራል።» ማለት የማይታሰብ ነው።

የአርብቶ አደር አካባቢዎች ችግር

ያለፉት ተከታታይ ስርዓቶች በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያለውን አንጻራዊ ሰፊ ይዞታ የተረዱበትና የአካባቢውን የልማት ፖሊሲ የነደፉበት መንገድ የአርብቶ አደሩን ህይወት ያመሰቃቀለ ነው። አንዳንዶች የኢትዮጵያ ገዢዎች ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ይልቅ ከብትና መሬቱን ይፈልጉታል የሚለው አባባል ባዶ ክስ አለመሆኑ ባለፉት ተከታታይ ስርዓቶች የአርብቶ አደር አካባቢዎች ከደረሰባቸው ዘርፈ ብዙ ችግር መገንዘብ ይቻላል። በጋምቤላ፣ አፋር፣ ሱማሌና ቦረና በመሳሰሉ አርብቶ አደር አካባቢዎች በግዙፍ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ኢንቨስትመንቶች ስም ሰፊ የማፈናቀል ተግባር ያሳደረው ችግር ቀላል አይደለም። አርብቶ አደሩን ከጋርዮሽ ይዞታው እያፈናቀሉ መሬቱን ቸብችበውታል። በዚህም ምክንያት የስነ-ህዝብ መዛባት ተፈጥሯል።

የመኖሪያና የስራ ቦታ ችግር

በኢትዮጵያ ባለፉት አመታት የከተሞች አመታዊ ዕድገት ምጣኔ እያደገ መጥቷል። ይህ ዕድገት በሃገሪቱ ካለው የህዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ ነው። በሌላ በኩል በከተሞችም ሆነ በገጠሮች ያለው የመሬት ጥበት እየተባባሰ መሬት አልባነትም እየተስፋፋ ነው።

የገጠር መሬት አልባነትና የይዞታ መበጣጠስ

የደርግና የኢህአዴግ የመሬት ፖሊሲዎች መሬትን ለሁሉም የማዳረስ ፖሊሲ ቢከተሉም በተለይ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ከ30% ያላነሰው አርሶ/አርብቶ አደር መሬት አልባ ነው። በሀገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች ከግብርና ውጭ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ ዘርፎች ባለመስፋፋታቸው የገጠር ስራ-አጥነት ከመሬት አልባነቱ ዕኩል እየተስፋፋ ነው። ሀገራዊ የገበሬዎች የነፍስ ወከፍ ይዞታም ከግማሽ ሄክታር በታች ወርዷል። እነዚህ ሁኔታዎች ዘላቂ የሆነ ገበያ-መር የግብርና ዕድገት ለማስመዝገብ ፈተና እየሆኑ ነው።

የካሳ ስርዓትና የከተማ-አጎራባቾች ግንኙነት

መንግስት የመሬት ብቸኛ ባለቤት በመሆኑና መሬትን የስልጣንና የሃብት ማደላደያ አድርጎ በመውሰዱ ከተሞች በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ጎን እየተለጠጡ በመጡ ቁጥር በከተሞች አጎራባች ያለው ገበሬ ህይወት እየተመሰቃቀለ ነው። መንግስት ከገበሬዎች በዝቅተኛ ካሳ የሚቀበለውን መሬት ለግል ባለሃብቶች በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ እየቸበቸበው ነው። በአንድ በኩል ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ገበሬዎች ለከፋ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ እየተዳረጉ ሲሆን በሌላ በኩል በከተሞች አካባቢ የመኖሪያና የስራ ቦታ ውድነት እየተባባሰ ነው። በከተሞች አጎራባች ያሉ ገበሬዎች የከተሞችን መስፋት እንደ ዕድል ሳይሆን እንደ ዕርግማን የሚያዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ፖሊሲ አማራጮች

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሃገራችንን የመሬት ፖሊሲና አስተዳደር በተመለከተ የሚወስዳቸው የፖሊሲ አማራጮች በዝርዝር የፖሊሲ ሰነዱ ውስጥ የተብራሩ ሲሆን አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ፡

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ላለፉት በርካታ አስርት አመታት ሀገሪቱን ባስተዳደሩት የፊውዳል፣ የደርግ እና ኢህአዴግ ስርአቶች ሲተገበር የነበረው መሬትን ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ይልቅ ለፖለቲካ ዓላማዎች ማስፈፀሚያ የሚያደርጉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓቶች ጉልህ ለውጥ ይፈልጋሉ ብሎ ያምናል። በፖሊሲ አቅጣጫችን መሬት በመንግስት እጅ እንዳለ ባለ ይዞታዎች በመሬታቸው ላይ የሚኖራቸው ቁጥጥርና ተጠቃሚነት የሚያሰፉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። በአንድ በኩል መሬት

በጥቂት ግለሰቦችና በውጭ ባለሃብቶች እጅ እንዳይወድቅ በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት መሬት ላይ ያለውን ፍፁማዊ ቁጥጥርና ስልጣን በመገደብ ላይ ያተኮሩ እርምጃዎች ይተገበራሉ። በገጠርም ሆነ በከተማ ያሉ የመሬት ባለ ይዞታዎች ሰፊ ነጻነትና ዋስትና ሊሰጣቸው ይገባል። ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት፣ ለተፈጥሮ ሃብት ልማትና እንክብካቤ፣ እንዲሁም ለምርታማነት ዕድገት ቁልፍ የሆነው የመሬትና የንብረት ዋስትና ይረጋገጣል። ለዚህም በከተማና በገጠር የሚገኘውን እያንዳንዱ መሬት የመመዝገብ፣ የማልማትና ባለቤትነትን ማረጋገጥ የፖሊሲው ቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

የመሬት ተደራሽነት

የደርግና የኢህአዴግ ስርዓቶች ፖሊሲ «መሬት ለሁሉም አርሶ/አርብቶ አደር እናዳርሳለን።» የሚል ነበር። በውስን የመሬት ሃብት አቅርቦት እና እያደገ በሚመጣው የመሬት ፍላጎት መካከል መሬትን ለሁሉም ማዳረስ የሚቻልበት ዘላቂ ሁኔታ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በገጠር አካባቢዎች በአነስተኛ መሬት ወይም በአጠቃላይ ከግብርና ውጭ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ የልማት ስራዎች መስራት የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል። መሬትን ለሁሉም የማዳረስ ሙከራ አሁን ያለውን የተበጣጠሰና አነስተኛ ይዞታ ለምርትና ምርታማነት እጅግ አስቸጋሪ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። በተለይ የእርሻና የግጦሽ መሬት ለሚፈልገው ሁሉ ማዳረስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በመሆኑም ከነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ተግባራዊ ይደረጋል።

የመሬት አጠቃቀም

መሬትን በፍትሃዊነት ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት በዋናነት መሬትን በተሻለ ዘላቂነትና ምርታማነት ለሚጠቀሙ ቅድሚያ የሚሰጥ አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል። ሀገራችን ያላትን ውስን የመሬት ሃብት መሬት ላይ የተሻለ እሴት ለሚጨምሩ ዜጎች በማዳረስ የሃገራችንን የልማት ጎዳና ማፋጠን ዋናው የፖሊሲው ዓላማ ይሆናል። ከዚህ ጎን ለጎን በማህበረሰብ ውስጥ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶችና ተጋላጭ የማህበረሰብ አካላት ልዩ ትኩረት ይሰጣል። እንዲሁም መሬት በዋናነት በዜጎች በበላይነት መያዙን ለማረጋገጥ ለውጭ ኢንቨስትመንት የሚሰጠው መሬት ከፍተኛ ጣሪያ (ገደብ) የሚኖረውና ጉልህ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ላላቸው ፕሮጀክቶች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ትምህርት-መር ሀገራዊ የልማት ማእቀፍ እና ፖሊሲ የሚከተል በመሆኑ በትምህርትና ምርምር ዘርፍ ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ከፍተኛ የመሬት ማበረታቻ ይሰጣል። በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለውን የወል ይዞታ እንዲጠበቅ በማድረግ አሁን ያለውን ከፍተኛ መፈናቀል እንዲቆም ይደረጋል። ለመኖሪያና ለስራ ቦታ የሚሆኑ ቦታዎች በአነስተኛ የሊዝ ዋጋ በማቅረብ የቤትና የስራ ቦታ ችግር ለማቃለል ከፍተኛ ስራ ይሰራል።

የመሬት ገበያ

አሁን ያለውን ህገ-ወጥ የመሬት ገበያ በማስቀረት ህጋዊ መስመር እንዲከተል በማድረግ መንግስትና ሃገር ከመሬት ገበያ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር መሬት ለተሻሉ ተጠቃሚዎች የሚተላለፍበት አሰራር ይዘረጋል። የሊዝም ሆነ የይዞታ ማረጋገጫዎች በገበያ እንደ ባንክ ዋስትና የሚዘዋወሩ ንብረቶች ይሆናሉ። የሊዝና የይዞታ ማረጋገጫዎች ለረጅም አመታት ሞርጌጅ እንዲሆኑ በማድረግ የኢንቨስትመንት ዋስትና ይረጋገጣል። ይህ አሁን ያለውን አርሶ/አርብቶ አደሩን የአነስተኛ ይዞታ እስረኛ የሚያደርገውን አሰራር ይቀርፋል። መሬት የትንበያ ገበያ መጫወቻ ሳይሆን ቶሎ ጥቅም ላይ ውሎ ኢኮኖሚውን የሚደጉም እንዲሆን ጥብቅ የመሬት አስተዳደርና ልማት መመሪያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። ከከተሞች ማስተር ፕላን ጋር የማይጣረሱ ይዞታዎችን በተገቢው ክፍያ ህጋዊ እንዲሆኑ በማድረግና ለህገ-ወጥ የመሬት ወረራ የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ይደረጋል። ለልማትና ለብሄራዊ ጥቅም ሲባል ከይዞታቸው የሚፈናቀሉ ዜጎችን በተመለከተ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ዜጎች ቢያንስ ከመፈናቀላቸው በፊት የነበራቸው ማህበራዊ ህይወት እንዲቀጥሉ ሲቻልም የተሻለ ካሳ እንዲያገኙ ለማድረግ የመሬት ዋጋ አተማመን ማሻሻያ ያደርጋል። በመሬት አተማመን ማሻሻያው መሬት ላይ ያለው ንብረት ብቻ ሳይሆን መሬቱ ያለበት ቦታ ከግምት እንዲገባ ይደረጋል።

የተቀናጀ የገጠር-ከተማ ልማት፡

ከተሞች ወደ ጎን በሰፉ ቁጥር ከአጎራባች ገጠሮች ጋር የሚስተዋለውን ጤናማ ያልሆነ የልማት አቅጣጫ ለመፍታት በሃገሪቱ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል። አሁን ላይ የምናየው ከተሞችና ገጠሮችን በተለያየ ማዕቀፍ ውስጥ የሚመለከተው አሰራር ለዘርፈ-ብዙ ችግሮች የዳረገ ነው። በመሆኑም የከተሞች ዕድገት የአጎራባች ገጠሮች ስጋት ሳይሆን ተስፋ እንዲሆን የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ አሰራር በከተሞች መስፋፋት የሚነሱ የአጎራባች ገጠር ነዋሪዎችን ህይወት ከከተሞች ዕድገት ዕኩል የሚያለማ ይሆናል። ፍትሃዊና ወቅታዊ የገበያ ዋጋን መሰረት ያደረገ ተመን እንዲያገኙ ከማድረግ ጎን ለጎን የልማት ተነሺዎችን ህይወት በዘላቂነት የሚለውጥ የመሬት አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል። የረጅም አመታት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ተግባራዊ በማድረግ ገበሬውን አሁን ላይ ከምናየው ድንገተኛ መፈናቀል በመታደግ የከተሞች መስፋፋትና የገጠሮች ትራንስፎርሜሽን በእቅድ የሚመራ እንዲሆን ይደረጋል።

የመሬት ሪፎርም ፕሮግራም

አርሶ/አርብቶ አደሩን እንዲሁም የከተማውን ነዋሪ የይዞታ ዋስትና የሚያረጋግጡ የህግና አስተዳደራዊ ሪፎርም ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ። የከተማ መኖሪያና የስራ ቦታን፣ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ግብርና መሬት፣ የመሰረተ-ልማት፣ ኢንቨስትመንትና ሌሎች መሬቶች ይዞታ ዋስትና በማረጋገጥ የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የህግና የአስተዳደር ማሻሻያዎች ይደረጋሉ።

ምዝገባና ሰርተፍኬት፡

በኢህአዴግ መንግስት ተጀምሮ የፖለቲካ ስልጣን መጠቀሚያ የተደረገው የመሬት ምዝገባና ሰርተፍኬት ፕሮግራም ደረጃውን በጠበቀና አርሶ/አርብቶ አደሩን የይዞታ ዋስትና በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሁም የመሬትና የድንበር ጭቅጭቆችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሚፈታ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል።

የመሬት ካሳ:

በገጠርም ሆነ በከተማ ለኢንቨስትመንትና ሐገራዊ ፋይዳ ባላቸው ፕሮጀክቶች ምክንያት ከይዞታቸው የሚፈናቀሉ ዜጎች ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙና በመንግስት ድጋፍ እንዲቋቋሙ ይደረጋል። የካሳ ስርዓቱም የገበያ ዋጋን፣ የመሬቱ አቀማመጥን፣ እንዲሁም በመሬቱ ላይ ያረፈው ንብረት የገበያ ዋጋን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል። ተፈናቃዮች ቀድሞ ከነበራቸው ህይወት ተቀራራቢ ወይም በተሻለ ሁኔታ መሆናቸውን ማረጋገጥ የመንግስት ግዴታ ይሆናል።

3 ግብርና፣ ገጠር ልማት እና የምግብ ዋስትና

አገራችን ኢትዮጵያ ያላት የመልክአ ምድርና የተፈጥሮ አቀማመጥ ለግብርና ልማት ምቹና እምቅ ሃይል ያላት ያደርጋታል። ሆኖም ሀገሪቷ እስከ አሁን ከምግብ እጥረት እና ከረሃብ አልተላቀቀችም። የግብርናው ዘርፍ ለሀገራችን ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሲሆን ለሀገራችን አጠቃላይ ብሄራዊ ምርት (GDP) 35 ከመቶ በላይ እንዲሁም ለሀገሪቱ ህዝብ 70 ከመቶ በላይ የስራ እድል ፈጥሯል።

ሀገራችን ወደ ውጭ ከምትልካቸው እቃዎች ከፍተኛው የግብርና ውጤቶች ሲሆኑ ዋናው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። የግብርናው ዘርፍ የምርታማነት ማሽቆልቆል፣ የተቀላጠፈ የግብይት ስርአት አለመዘርጋት፣ ዘርፉ ተጨማሪ እሴት መፍጠር አለመቻል፣ የተፈጥሮ ሀብቶች መጎሳቆል እና የተጋላጭነትና አደጋ ተግዳሮቶች ተጋርጠባታል። የግጦሽ መሬት፣ የእርሻ መሬትና የደን መመናመን በሰፊው ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ በአንድ ሄክታር የእርሻ መሬት የሚመረተው የሰብል ምርት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። ኋላ ቀር የግብርና አሰራር ስርአት እና ዘመኑ ያፈራቸውን የግብርና ግብአቶች እና ቴክኖሎጂዎችን አለመጠቀም ለግብርና ምርቶች መቀነስ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው። የሰብል ተባዮች እና በሽታዎች ሰላሳ በመቶ (30%) የሰብል ምርት መቀነስን ያስከትላሉ።

የግብርና ስራ ከሚጠይቀው ጉልበት እና ድካም አንጻር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ዝቅተኛ መሆን እና ጠንካራ የገበያ ትስስር ያለመኖሩ የግብርናው ሴክተር የገበሬው ምርት ከእጅ ወደ አፍ ብቻ እንዲሆን አድርጓል። የዜጎች የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እና መቀንጨር በዜጎች ላይ በተለይ ሴቶችና ህጻናት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

ዘርፉ ካለው ሀገራዊ ፋይዳ አንፃር ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው። በስራ ላይ ያሉት የግብርና ልማት፣ የምግብ ዋስትናና የአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ዘርፉን ከተጋረጡበት ውስብስብ ችግሮች በማላቀቅ ለጠቅላላ የኢኮኖሚ እድገት ሚናውን እንዲጫወት አላስቻሉትም። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የግብርና ዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ይሰራል።

- የሰብል እህሎችን አይነታቸውን ማብዛትና በስፋት ማስፋፋት፣ አዳዲስ የእህል ዝርያዎችን ማስተዋወቅ፣ የተሻሻሉ የእርሻ ዘዴዎችን መጠቀም፣ እንዲሁም ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ግብርናን በማዘመን ምርታማነትን ማሳደግ። በተጨማሪም ብሄራዊ የዘር ሴክተርን ማቋቋምና ማልማት፣ የሰብል ተባዮችና በሽታዎች መከታተልና መቆጣጠር የኤክስቴንሽን ስርአቱንና የተጠቃሚዎችን አቅም የማጎልበት ስራ እና የገበያ ትስስረን በማጎልበት ምርታማነትን ማሳደግ።
- አልሚና ተመጣጣኝ ምግብነት ያላቸው እፅዋት እንዲመረቱና ህዝቡም እንዲመገባቸው በማበረታታት የአመጋገብ ባህልን መቀየር፣
- የግብርና ንግድ እድገትን እንዲሁም በዘርፉ ያሉትን የእሴት ትስስሮች ማጠናከር፣ በሰብል አሰባሰብ ወቅት የሚያጋጥሙ ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ ዘመናዊ የምርት አሰባሰብ ስርአትን መዘርጋት፣ የተሰበሰበ ምርት አያያዝን ማዘመን፣
- ለአየር ንብረት ምቹ የግብርና አሰራርን ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫና የብቃት ማሻሻያ ስልጠናዎች ለገበሬው መስጠት፣
- የመሬት ባለቤትነት እና የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲዎችን መከለስ፣
- አነስተኛ ግብርና አምራቾችን የተሻለ የውሃ አጠቃቀም ዘዴዎችን ማስተዋወቅ፣ ዘላቂ የመሬት አያያዝና አስተዳደር ስርአት መዘርጋት፣ ብዝሀ-ህይወት የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ፣ የአነስተኛ ገበሬዎችን የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ማሻሻል፤ የእንስሶች መጠጥ ውሃ ማቆሪያ ጣቢያ መፍጠር፤ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አያያዝና አስተዳደር ማስተዋወቅ፣
- የተሻሻለና የተጠናከረ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መረጃ መገንባት። ይኸውም በመስኖ፣ በመሬት አጠቃቀም፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ የመረጃ ቋት፣ ብሄራዊ የደን ልማት ቁጥጥር እና ልኬት፣ ከደን መመናመን ጋር የተያያዙ የአየር መበከልን ለመቀነስ የሚረዱ የተሻሻሉ የሪፖርት አቀራረብ ስርአት መዘርጋት፣
- ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚላመድ ብሄራዊና ክልላዊ የአቅም ግንባታ ስትራቴጂዎችን መፍጠር እንዲሁም ለመተግበር የሚረዱ የአየር ንብረት ለውጥን መቀነሻ ስትራቴጂዎችን፣ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችና ስልጠናዎች፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ማስተዋወቅ፣ የደን ልማትና የግጦሽ መሬት አስተዳደር ማሻሻያ፣ ሀይል ቆጣቢ እና ብዝሀ-ህይወት የማይበክሉ ዘላቂ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣
- በምግብ ራስን ለመቻል የሚያስችሉ አሰራሮችና መረጃዎችን ማሻሻል፣ የሀገሪቱን ዋና ዋና የድርቅና የጎርፍ ተጋላጭ ቦታዎችን ለይቶ በማስቀመጥ የቅድመ-ማስጠንቀቂያና ቅድመ-መከላከል ላይ የተመሰረተ የመረጃ አሰራር መፍጠር፣ የመከላከልና አደጋን የመቀነስ ስትራቴጂዎችን መንደፍ፣ ተገቢ በሆኑ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ማህበራዊ ጥበቃና የእርሻና ግብርና መረጃ ትስስርን ማሻሻል።
- የጋዝ ልቀትን ለመቀነስ የታለመ ከአየር ንብረት ጥገኝነት የተላቀቀ አረንጓዴ ኢኮኖሚ (Climate Resilient Green Economy)፣ የአደጋ ተጋላጭነትን ቅነሳ አስተዳደር (Disaster Risk Management)፣ ብሄራዊ የስነ-አመጋገብ ፕሮግራሞች (National Nutrition Strategy) የተናበቡ እና እርስ በርስ የሚመጋገቡ ወጥ ሃገራዊ ፖሊሲዎች መቅረጽ፣
- የግብርና እና የምግብ ዋስትና ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ እና ዘርፉ ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ እንዲከለሱ ይደረጋል።

4 አርብቶ አደር ልማት፡ የተረሱ ዜጎች

ከሀገራችን የቆዳ ስፋት ከግማሽ በላይ የሚሆነው ክፍል የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ እንደሆነ ይገመታል። በአብዛኛው በጠረፋማና ቆላማ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩት አርብቶ አደሮች እጅግ አስከፊ በሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና

አስተዳደራዊ ተግዳሮቶች ውስጥ በቂ የመንግስት ትኩረት ሳያገኙ ረዥም ዘመን አልፏል። ቢያንስ ላለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት በሀገሪቱ የተፈራረቁ ስርአቶች የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ እና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ልማት ትኩረት በመንሳት ህዝቡ በድህነት አዙሪት ውስጥ እንዲማቅቅ አድርገዋል።

ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ህይወትና ደህንነት ይልቅ ለእንስሳቱ፣ ለሰፋፊና ለም የእርሻ መሬቱ እንዲሁም ሌሎች የከርሰ ምድር ሀብቶቹ ቅድሚያ ሲሰጡ የቆዩት ቀደምት የሀገራችን መሪዎች ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች በከፋ ሁኔታ የአርብቶ አደሩን ህብረተሰብ በልማት ወደ ኋላ እንዲቀር ከፍተኛ አስተዳደራዊ በደል ፈጽመውበታል።

የከብት እርባታ ንዑስ ሴክተሩ ከቤተሰብ ደረጃ እስከ ሀገር ኢኮኖሚ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሲሆን በሀገር ደረጃ ከ35-49% የሚሆነውን የግብርና ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትን (GDP) ሲሸፍን፣ ከ15% በላይ የሚሆነው የብሄራዊ ኢኮኖሚ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትን (GDP) እየሸፈነ ይገኛል።

የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ካሉበት ዘርፈ-ብዙ የህይወት ውጣውረዶች የሚታደገው ልዩ የመንግስት ድጋፍ እና የፖሊሲ አማራጭ በእጅጉ የሚሻ ቢሆንም፣ ዛሬም ድረስ በሀገራችን ፖለቲካ በቂ ትኩረት አላገኘም። የአርብቶ አደሩን የህብረተሰብ ክፍል ካሉበት ተደራራቢ ችግሮች ለማላቀቅ፣ በሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት ውስጥ በቂ ተሳትፎ እና ከልማቷም ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል።

1. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ ከተንቀሳቃሽ የኑሮ ዘይቤ ተላቆ ህይወቱን በተረጋጋ መንገድ መምራት የሚያስችለው የልማት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይሆናሉ፣
2. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ የተረጋጋ ኑሮ እንዲመሰርት የሚያስችሉት አነስተኛ መንደሮች ይገነባሉ። መንደሮቹ የተሟላ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ይኖሯቸዋል፣
3. የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ይበልጥ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ የተቀናጁ የአርብቶ-አደር ልማት መርሀ-ግብሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤ የልማት መርሀ-ግብሮቹ በዋናነት ውሀን ማዕከል ያደረጉ ይሆናል፣
4. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ የአካባቢውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች መምራት ይችል ዘንድ የተጠናከረና ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፣
5. የአርብቶ አደር ስልተ-ምርት በሀገሪቱ ህጎች በቂ እውቅና እንዲያገኝ፣ ለአርሶ አደርና ሌሎች ስልተ-ምርቶች የሚሰጠው ትኩረት እና የሚደረገው መንግስታዊ ድጋፍ ለአርብቶ አደሩም እንዲሰጥ የሚያደርጉ የህግ ማእቀፎች ይሰናዳሉ፣
6. የተሻሻሉ የከብት መኖዎች ማስተዋወቅ፣ የተሻሻሉ የከብትና የዶሮ ዘሮችን መጠቀም፣ የእንስሳ ጤና አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ የገበያ ትስስር መፍጠርና ማሻሻል እንዲሁም ለዘርፉ የሚያግዙ ፖሊሲዎች ይቀረጻሉ፣
7. የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ኑሮ ከእንስሳቱ ህይወት እና ደህንነት ጋር እጅግ የተቆራኘ በመሆኑ ጥራት ያለው የእንስሳት እንክብካቤና የጤና አገልግሎት በመዘርጋት አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ብሎም አጠቃላይ ሀገራችንን ከእንስሳት ሀብታችን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርዓት ይዘረጋል፣
8. የአርብቶ አደር አካባቢዎችን መልክዓ-ምድር፣ ስነ-ምህዳርና የአየር ፀባይ ወዘተ ታሳቢ ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ለመንደፍ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ጥናቶች እና ምርምሮች ይደረጋሉ፤ በዘርፉ የተሳኩ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን ለመቅሰምና ጥቅም ላይ ለማዋል ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፣
9. በአብዛኛው በቆላማ እና ጠረፋማ አካባቢ የሚኖረው አርብቶ-አደር ህዝባችን ከሌላው የሀገራችን ህዝብ ጋር ያለው የባህል እና የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጠናከር የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
10. የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ አባላት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽ ከመሆናቸው አንጻር ከሌሎች አርብቶ አደር ማህበረሰብ አባላት እና በአዋሳኝ ከሚገኙ አርሶ አደር ማህበረሰብ ጋር ለግጭት ስለሚዳረጉ ህይወታቸው ለአደጋ የተጋለጠ ነው። ይህንን የአርብቶ አደሩን የደህንነት ስጋት በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፣
11. የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ልማትና ብልፅግና ለማፋጠን ልዩ የበጀት ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል።

5 ቱሪዝም እና ቅርስ ጥበቃ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የረዥም ታሪክና ስልጣኔ ባለቤት ናት። ሀገሪቱ ያለችበት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ያላት ስነ-ምህዳርና ለመካከለኛው ምስራቅ ያላት ቀረቤታ፣ የቅርሶቻችን ብዛት ይዘትና ስብጥር ትልቁን ድርሻ ይዟል። በአፍሪካ ቀንድ ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋው ታላቁ የአፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ላይ የተመሰረተ ብቻ ሳይሆን ከርሰ-ምድሯም ላለፉት ብዙ ዘመናት ሳይረበሽ መቆየቱ፣ በምድራችን የሰው ዘር አመጣጥን የሚመሰክሩ ቅሪተ-አካሎች ቀዳሚ መገኛ እንድትሆን አድርጓታል።

በተመሳሳይ ለመካከለኛው ምስራቅ ያላት ቀረቤታና ጠንካራ ግንኙነት መሰረታቸው በመካከለኛው ምስራቅ የሆኑ ሶስቱ ጥንታዊ ኃይማኖቶች (ክርስትና፣ ኢስላም እና ጁዳይዝም) ቀደም ብለው ወደ ሀገራችን በመግባታቸው በሂደት ለአምልኮ መከወኛ የተሰሩ ቤተ-እምነቶች የሀገራችን ሀገር በቀል የኪነ-ህንጻ መገለጫዎች በመሆን በብሔራዊ ቅርስነታቸው የጋራ ዕሴቶቻችን ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

በተጓዳኝ የሀገራችን መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ እና ስነ-ምህዳር ለሀገራችን ቅርስ እና የባህል ብዝሀነት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ከባህር ጠለል በላይ 4620 ሜትር ከፍታ ካለው ከታላቁ የራስ ዳሽን ተራራ እስከ ከባህር ጠለል በታች 200 ሜትር ዝቅታ ያለው በምድር ዝቅተኛው ዳሎል ኢትዮጵያን አስገራሚ የንጽጽር ምድር አድርጓታል። እነዚህ የተለያዩ የስነ-ምህዳር ቀጣናዎች ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ተብለው የተለዩ የአየር ንብረቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ሀገራችን የበርካታ የዱር እንስሳት፣ የደን ሀብቶች፣ የባዮ ስፌር ቀጣናዎች፣ የአያሌ ዕጽዋት፣ እንስሳትና አዕዋፋት መገኛም ነች።

ከዚህም ሌላ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰቦች በጋራ የሚኖሩባት ምድር በመሆኗ እነዚህ የተለያዩ ማህበረሰቦች የሚነጋገሩባቸው የተለያዩ ቋንቋዎች፣ የፈጠሯቸው የመንደር አመሰራረቶች፣ ባህላዊ ዕሴቶች፣ የሚፈጥሯቸው የዕደ-ጥበብና የጥበብ ውጤቶች፣ የአምልኮ ስርዓቶች፣ ሀገራችንን ሕያው የብዝሃ ህዝቦች ሙዝየም እንድትሆን አብቅቷታል። ከላይ በቅንጭቡ የተገለጹት የሀገራችን ልዩ መስህቦች ሀገራችን በቅርስ ሃብቶቿ ብዛትና ስብጥር በአፍሪካ የቀዳሚነቱን ደረጃ ለመጨበጧ በዓለም የቅርስ መዝገብ ያስመዘገበቻቸው የቅርሶች ብዛትና ዓይነት ጉልህ ማሳያዎች ናቸው።

ሀገራችን እነዚህን ሰፊ የቅርስ ሃብት በዘመናዊ የቅርስ አስተዳደር ዘዴ ለመምራት፣ ለመጠበቅና ለማልማት የሚረዱ የቅርስ ተቋማት ካቋቋመች ሰባ ዓመታትን አስቆጥራለች። ብሔራዊ ሙዝየም፣ ብሔራዊ ቤተ-መጽሃፍትና መዛግብት ከነዚህ ተቋማት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁንና እነዚህ ተቋማት ቅርሶችን በመመዝገብ በመጠበቅና በማልማቱ ረገድ የሄዱበት ርቀት ሲፈተሽ፣ ብዝሃ የቅርስ ሀብቶቿ ሃገሪቱ የተያያዘችውን ልማት የሚያግዙበት ደረጃ ላይ አለመሆናቸውን እናስተውላለን። ለዚህ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ፡

- የቅርስ ተቋማት አቅም (በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቴክኖሎጂ) ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ከሃገሪቱ ዕድገት ጋር የሚመጣጠን ፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር፣
- ከሀገሪቱ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ጋር የተቃኘ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ አለማድረግ፣
- ዓለም ዓቀፍ የጥናትና የመስክ ምርምሮች ዛሬም ከሀገሪቱ ፍላጎት ጋር እንዲሳለጡ አለማድረግ፣
- በሀገሪቱ በቅርስ ዙርያ በጋራ ለመስራት የሚያግዙ ተባባሪና ባለድርሻ አካላትን አቅም አሟጦ አለመጠቀም፣

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሀገራችን የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዘርፍ ያሉበትን ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዘርፍ እንዲሁም ብሄራዊ ባህላችንን ከመጠበቅ አንጻር የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይፈጽማል፣

- ቅርሶች ታዳሽነት የሌላቸው የሀገር ሃብቶች በመሆናቸው ለጥበቃና እንክብካበያቸው ተገቢ ትኩረት እንዲቸራቸው ይደረጋል፣
- ጥገና የሚሹ ሀገር በቀል የኪነ-ህንጻ ሀብቶቻችንን ለመታደግ ዓለም አቀፍ መፍትሄ ይልቅ ሀገራዊ መፍትሄ የሚፈጠርበትን አሰራር ይቀይሳል፣
- በቅርስ ጥበቃና ልማት የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በማንኛውም መመዘኛ ፍትሃዊ እንዲሆኑ፣ በሁሉም የሀገራችን ክፍል የሚገኙ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ታሪክ፣ ኃይማኖት፣ ቅርሶች

ተመጣጣኝ ትኩረት፣ ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

- የዕምነት ተቋማቶቻችን የአያሌ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ባለቤቶች በመሆናቸው እነዚህን ቅርሶቻችንን ለመጠበቅና ለማስተዳደር ተከታታይነት ያለው አቅም ግንባታ ስልጠናዎች የሚያገኙበት አሰራረ ይቀየሳል፣
- በየክልሉ የተቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በከፈቷቸው የቅርስ አስተዳደርና የአርኪዎሎጂ የትምህርት ክፍል በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የሚሰጡትን ትምህርትና ስልጠና በተግባር እንዲታገዙ በማድረግ በአካባቢያቸው ያሉ ቅርሶችን በመጠበቅና በማልማት ረገድ አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ድጋፍ እና ማበረታቻ ይሰጣል፣
- ቅርሶቻችንን በዓለም ቅርስ መዘገብ ለማስመዝገብ የምናሳየውን ትጋት ቅርሶቹን ካስመዘገብን በኋላም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፣

ቱሪዝም ዘርፍ

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቅርሶች ለሀገር ልማት እንዲያግዙ ለማድረግ ዘመናዊ የቱሪዝም ንግድና አገልግሎት ማስፋፋት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በጽኑ ያምናል። ኢትዮጵያ የቱሪዝም መዳረሻዎቿን በዘመናዊ የቱሪዝም አስተዳደር ለመምራት ብሔራዊ የቱሪዝም ተቋም ካቋቋመች አምሳ ዓመታትን ብታስቆጥርም ዘርፉ አሁንም እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። የሀገራችን የቱሪዝም ዘርፍ በሀገራችን የተቀያየሩ የመንግስት አደረጃጀቶች የየራሳቸውን አሻራ ጥለውበት አልፈዋል። በአጼ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ሀገር ዓቀፍ መንግስታዊ የቱሪዝም ተቋም ተቋቋመ። በማስከተልም በቱሪዝም መዳረሻነት ዛሬ በግንባር የምናስተዋውቀውን በተለምዶ የሰሜን መስመር የምንለውን (ላሊበላ፣ ጎንደርና አክሱም) ለማልማት በቃ። ይሁንና ጥቂትም ሳይቆይ ታላቁ ረሃብ በሀገራችን በመከሰቱ አስከዛሬ ድረስ ተፅዕኖው ያልተላቀቀን የገጽታ ብልሽት አስከተለ።

የደርግ መንግስት የተከተለው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለምና እሱን ለማስፈጸም የግል የንግድ ድርጅቶችን ወደ መንግስት ማዛወሩ በቱሪዝምና በሆቴል አገልግሎት የተሳተፉትን ጥቂት የግል ባለሃብቶች አዳከማቸው። ይህንን ተከትሎ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ሆድና ጀርባ በመሆኑ ከዚህ ሀገር የሚመጡ ቱሪስቶች እግራቸውን ሰበሰቡ። ሌላው ቀርቶ በሰው ዘር አመጣጥ ዙርያ ጥናት በማድረግ በሚያገኟቸው አዳዲስ ግኝቶች ሀገራችንን በአንጻራዊ መልኩ የሚያስተዋዉቀውን የመስክ ጥናት እንዲቆም በመደረጉ ሀገራችን ይበልጥ ተገለለች። በእንቅርት ላይ እንደሚባለው ለአስራ ሰባት ዓመታት ያላባራው የእርስ በርስ ጦርነት የቱሪዝምን ዘርፍ ክፉኛ አዳከመው ።

ኢ.አ.አ. በ1995 የጸደቀው ህገ መንግስት እና በዚህም ላይ ተመስርቶ የወጡት የባህልና የቱሪዝም ፖሊሲዎች የቱሪዝም ዘርፍ እንዲያንሰራራ መጠነኛ አስተዋጾ አድርጓል። ይሁን እንጂ የሀገራችን የቱሪዝም ዘርፍ አሁንም በበርካታ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ ማእቀፎች ተተብትቦ ሀገራችን ከሴክተሩ ማግኘት የምትችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል።

የቱሪዝም ዘርፉ በርካታ የፖሊሲ፣ አስተዳደራዊ እና ቴክኒካዊ ችግሮች ያሉበት ሲሆን የሚከተሉት አንኳር ችግሮች በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በፌደራልና በክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተናበ አለመስራት፣ የቱሪዝም ንግድ ማህበረሰብ ተኮር አለመሆን፣ የሀገሪቱ የቱሪዝም ንግድ በውጭ ቱሪስቶች ላይ መንጠልጠሉ፣ የተቀያየሩ መንግስታት ቱሪዝምን የሀገሪቱ ዋንኛ የኢኮኖሚ አውታር አድርጎ አለመቁጠር፣ በመዳረሻዎች ዙርያ በቂ እና ጥራት ያላቸው የመሰረተ-ልማቶች አለመዘርጋት፣ የቱሪዝም አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ዓመቱን ሙሉ ሳይሆን የወራት እንቅስቃሴ አድርጎ መቁጠር፣ ዘርፉ በሰለጠነ ሰው ኃይል አለመመራት፣ ባንኮች የቱሪዝምን ዘርፍ የሚያዩበት መነጽር ዝቅተኛ መሆኑ፣ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ማራዘም አለመቻል፣ የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህላዊ ዕሴቶችን የሚሸረሽር፣ የአካባቢ የተፈጥሮ ጥበቃን የማያበረታታ እና ማህበራዊ ችግሮችን ማስከተሉ፣ ከቀረጥ ነጻ ማበረታታቻዎች ጋር ተያይዞ የጉምሩክና የገቢዎች ቢሮዎች የአሰራር ማነቆዎች፣ በሀገር ደረጃ የቱሪስት መዳረሻዎችን በስፋት ለማስተዋወቅ የተሄደበት ርቀት አናሳ መሆን፣ በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡ የቱሪዝም ኮርሶች ከሀገሪቱ ፍላጎት ጋር አለመጣጣም፣ ለዘርፉ የሚመደበው ሃብት አነስተኛነት፣ ሀገራችን በየጊዜው የሚከሰቱ የጸጥታ መደፍረሶች በዘርፉ የተለዩ አንኳር ችግሮች ናቸው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተጠቀሱትን አንኳር ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሀገራችንን የቱሪዝም ዘርፍ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ለማስቻል የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፤

- በሀገራችን የሚገኙ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታዎች የቱሪስት መዳረሻዎችን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- በየዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ የቱሪዝም የስልጠና ኮርሶችን በየጊዜው በመከለስ ከሃገር ወቅታዊ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙበትን አግባብ ማመቻቸት፣
- ሁሉም የቱሪስት መዳረሻዎች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ በመላ ሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- የውጭ ቱሪስቶችን ለመሳብ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለሀገር ውስጥ ቱሪዝም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፣
- የሀገራችን የቱሪዝም አገልግሎቶች ማህበረሰብ ተኮር እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በፌደራልና በክልል የቱሪዝም አካላት እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ተባባሪና ባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አሰራር ማስፈን፣ የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥ ዘመኑ ባፈራቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲታገዝ ማበረታታት፣
- ወጣቱ፣ ሴቶች፣ ገበሬው፣ የዕድ ጥበብ ባለሙያዎች በቱሪዝም ስራ ውስጥ ድርሻቸውን የሚያበረክቱበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- የቱሪስት መዳረሻ ልማትና ተጠቃሚነት ፍትሃዊ ማድረግ፣
- የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ልማት በመንግስትና የግል የልማት ድርጅቶች በትብብር እንዲሰራ ምቹ ሁኔታዎችን እና ማበረታቻ መፍጠር፣

6 ማክሮ ኢኮኖሚ

በሀገራችን ባለፉት 30 አመታት መንግስት ይከተለው በነበረው መንግስት-መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ተፈጥሯል። ይሄ የመንግስት የልማት ስትራቴጂና የፖሊሲ አቅጣጫ፣ በአገሪቱ ላይ ኢኮኖሚያዊና መዋቅራዊ ሽግግር እውን እንዳይሆን እንቅፋት ከመሆኑ ባሻገር ከፍተኛ የማክሮ-ኢኮኖሚ አለመረጋጋትን አስከትሏል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእዳ ጫና፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ሰፊ የስራ አጥ ቁጥር፣ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ እንዲሁም የውጭ ክፍያ መዛባት ካለባቸው ሀገራት መካከል ትመደባለች። “የልማታዊ መንግስት” ፍልስፍና እከተላለሁ ያለው የኢህአዴግ አስተዳደር መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና በማሳደግ የግሉ ኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲቀጭጭና የተገደበ ሚና እንዲኖረው አድርጓል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ባለ ሁለት አሀዝ እድገት እንዳስመዘገበች መንግስት ቢገልጽም በዜጎች ኑሮ ላይ ያመጣው ለውጥ አናሳ ነው። በከፍተኛ የመንግስት ኢንቨስትመንት ላይ የተመሰረተው “እድገት” አብዛኛው ከውጭ በሚገኝ እርዳታ እና ብድር ፋይናንስ የተደረገ ነው። በቂ የአዋጭነት ጥናት ባልተሰራላቸው ፕሮጀክቶች ላይ የፈሰሰው የውጭ ብድር ሀገሪቱን ለከፋ የውጭ እዳ ጫና ዳርጓታል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን ያለባትን የከፋ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ለመቀየር የተቀናጀ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ መሳሪያዎችን በማስተባበር የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ይሰራል። የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

7 የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲ

7.1.1 የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲ

የገንዘብ ፖሊሲ (Monitary Policy) የአንድን ሀገር አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመምራትና ለመቆጣጠር ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖር የገንዘብ መጠንና ፍሰትን ለመወሰን የሚያገለግል የፖሊሲ መሳሪያ ነው። የገንዘብ ፖሊሲ መሰረታዊ ዓላማ የሀገር ውስጥ አጠቃላይ የምርት እድገትን፣ የዋጋ ግሽበትን፣ የስራ እድል ፈጠራን እና የውጭ ምንዛሪን ሁነኛና የተሻለ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በየጊዜው የሚዋዥቀውን የሀገራችን ማክሮ-ኢኮኖሚ ለማረጋጋት በመረጃ ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ፖሊሲ መቅረጽ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተሉትን የገንዘብ ፖሊሲ ዓላማዎች እውን ለማድረግ ይሰራል።

1. የገንዘብ ፍሰትን በመቆጣጠር የሀገራችን ገንዘብ (ብር) የመግዛት አቅሙ የተረጋጋ እንዲሆን ሳይንሳዊ እና በጥናት የተደገፉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣

2. በገበያ የሚመራና አስፈላጊም ሲሆን የመንግስት ቁጥጥር የሚደረግበት የውጭ ምንዛሬ ግብይት ስርዓት በመዘርጋት የውጭ ምንዛሬ የተረጋጋ እንዲሆን ይደረጋል፣
3. የካፒታል ፍሰትን ከሀገር ኢኮኖሚ ልማት ጋር የተጣጣመ በማድረግ የተረጋጋ የዋጋ መጠን እና የውጭ ምንዛሬ እንዲፈጠር ይደረጋል፣
4. የሀገር ውስጥ የቁጠባ አቅምን በማሳደግ ለልማት የሚውል በቂ የካፒታል አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፣
5. የኢኮኖሚ መቀዛቀዝንና ድባቴን (Recession and depression) ለመከላከል የሚረዱ የገንዘብ ፖሊሲ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
6. የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ተቋማትን ማለትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ወዘተ ሁለንተናዊ አቅም በማጠናከር እና የተቀናጀ አሰራር በመፍጠር ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም፣ ውጤታማ የገንዘብ፣ የገቢ እና ብሄራዊ የልማት አስተዳደር ስርአት እንዲኖር ይደረጋል።

የመንግስት በጀት እና እዳ

የአንድን ሀገር የማክሮ-ኢኮኖሚ እድገት እና ይዘት ከሚወስኑት ነገሮች መካከል የመንግስት በጀትና ብድር ዋነኛዎቹ ናቸው። የተመጣጠነ የመንግስት ገቢ እና ወጪ የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከፍተኛ የዋጋ ንረትን ከሚፈጥሩ ጉዳዮች መካከል ገቢን ያላገናዘበ ከፍተኛ የመንግስት ወጪና ብድር ናቸው። ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ሲባል በርካታ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት መንግስት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባንኮች፣ ከዓለም ዓቀፍ አበዳሪ ድርጅቶችና ከሌሎች አካላት የሚበደረው ገንዘብ ኢኮኖሚው እንዳይረጋጋ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል። በእዳ የሚገኝ ገንዘብ የረዥም ጊዜ ጥቅም በሌላቸው እና በሚገባ ባልተጠኑ ፕሮጀክቶች ላይ ሲውል ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳቱ ድርብርብ ይሆናል። ያልተመጣጠነ የመንግስት በጀትና እዳ ለሀገራችን ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ከፍተኛ ምክንያቶች ናቸው። ከመንግስት በጀት እና እዳ ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚከተሉት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

1. የመንግስት ጠቅላላ ወጪ ከገቢ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የመንግስት ወጪ ከተለያዩ ምንጮች ከሚሰበሰበው የመንግስት ገቢ ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ እንዲሆን ይደረጋል፣
2. የመንግስት የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ያለው ምጣኔ ወይም መጠነ-ጉድለት (Budget deficit/ GDP ratio) ለጤናማ ኢኮኖሚ ከሚያስፈልገው ደረጃ እንዳያልፍ የቁጥጥር ስርአት ይዘረጋል፣
3. የሀገሪቱ የብድር ጫና ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ያለው ምጣኔ ወይም መጠነ-ብድር (Debt/GDP ratio) በህግ እንዲወሰን በማድረግ መንግስት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ የመበደር ስልጣኑ እንዲገደብ የህግ ማዕቀፍ ይበጃል፣
4. የመንግስት የበጀት ስርዓትን በማጠናከር ዘላቂ ልማታችንን የሚያውክ እና ለከፍተኛ የወለድ ክፍያ የሚዳርግ ብድርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
5. የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ ተከታታይ፣ ሳይንሳዊና በጥናት ላይ የተመሰረተ የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ይካሄዳል፣ የግብር ዓይነቶችና መጠን እንዲሻሻሉ ይደረጋል፣
6. ሁለቱን የማክሮ-ኢኮኖሚ ተግዳሮቶችን፣ ማለትም የዋጋ ግሽበትና ስራ አጥነት፣ በማመጣጠን የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ አውድ ለመፍጠር የሚረዱ የተቀናጀ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ ስርአቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

7.1.2 ገቢ ፖሊሲ

በቀጣይ አምስት አመት ለማሳካት ያስቀመጥናቸውን ግቦች ለመተግበር የሚያስፈልገውን ገንዘብ በዋናነት ከሀገር ውስጥ ለማመንጨት ታሳቢ ተደርጓል። ይህ በተለይ በመላው አለም በተስፋፋው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ከውጪ የሚገኝ እርዳታ እና ብድር በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን ታሳቢ ያደረገ የመፍትሄ አቅጣጫ ነው። በዚህ ምክንያት ከአለም አቀፍ ለጋሾች እና አበዳሪዎች የሚጠበቀው የፋይናንስ መጠን በእጅጉ ዝቅ እንዲል ተደርጓል።

የታክስ አይነቶችን (መሰረት) ማስፋት፣ የታክስ አሰባሰብ ስርአታችንን ዘመናዊ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማድረግ፣ የህዝባችንን ታክስ እና ግብር የመክፈል ባህል ማዳበር፣ ከታክስ ያልሆኑ የመንግስት ገቢዎችን ከፍ ማድረግ (Non tax incomes) የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ እና እቅዳችንን ለማሳካት የሚያስፈልገውን

ፋይናንስ ለማመንጨት ከምንጠቀምባቸው መንገዶች መካከል ናቸው።

8 የፋይናንስ ተቋማት

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ክፍል ኢኮኖሚ ባንኮችን፣ የኢንሹራንስ ድርጅቶችን እና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን ያካትታል። በቅርቡ ደግሞ የካፒታል ገበያ ይህንን ክፍል ኢኮኖሚ ይቀላቀላል ተብሎ ይጠበቃል። በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን 2 የመንግስትና 17 የግል ባንኮች፣ 1 የመንግስትና 17 የግል የኢንሹራንስ ድርጅቶች እንዲሁም 38 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ ባንክ በቅርቡ ሴክትሩን የተቀላቀለ ሲሆን ጥቂት የማይባሉ ባንኮች ፈቃድ ለመውሰድና ወደ ስራ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። የ2013 የባንኮች ሪፖርት እንደሚያሳየው የመጀመርያ ሩብ ዓመት አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ መጠናቸው 1.14 ትሪሊዮን ብር የደረሰ ሲሆን የብድር ክምችታቸው ደግሞ ከ623 ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል።

ምንም እንኳን የግል ባንኮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና አፈጻጸማቸው እየተሻሻለ ቢመጣም፣ ግዙፉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመላ ሃገሪቱ ባሉት ቅርንጫፎች 57 በመቶ ተቀማጭ ገንዘብ በማሰባሰብና 45 በመቶ አመታዊ ትርፍ በማስመዝገብ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪን በበላይነት በመቆጣጠር የባንኩን ሴክተር ይመራል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ደግሞ በሃገሪቱ የሚገኙትን የፋይናንስ ተቋማት በበላይነት በመቆጣጠር የተረጋጋ የፋይናንስ ሲስትም እንዲኖር ማድረግ፣ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ መረጋጋትን ለማስጠበቅና የሃገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የሚሰራ ተቋም ነው።

የፋይናንስ ሴክተሩ ተግዳሮቶች

የፋይናንስ አካታችነት

መስራት ከሚችለው የአለም ወጣቶች መካከል ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት ወይም በቁጥር ሲገለፅ 2 ቢሊየን አካባቢ ህዝብ የፋይናንስ ተጠቃሚ እንዳልሆነ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናት ይጠቁማል። ከፋይናንስ ተጠቃሚነት የተገለለው ብዙሃኑ ህዝብ ደግሞ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ይገኛል። ሃገራችን ኢትዮጵያም እንደ ሌሎች ታዳጊ ሀገራት በፋይናንስ ተቋማት የዜጎች ተሳትፎ እዚህ ግባ የማይባል ነው። እኤአ በ2017 በተደረገው የአለም ባንክ ጥናት መሰረት ከ15 አመት በላይ ካሉ ጎልማሶች 35 በመቶ የባንክ አካውንት ባለቤት ሲሆኑ 22 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ይቆጥባሉ። በተመሳሳይ አመት 11 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የፋይናንስ ተቋማት ብድር እንደወሰዱ ጥናቱ ይጠቁማል።

እኤአ በ2014 ከተደረገው ተመሳሳይ ጥናት ጋር ሲነጻጸር በ2017 ብዙ መሻሻሎች ቢኖሩም የሀገራችን የፋይናንስ አካታችነት ከሌሎች የአፍሪካ ሃገሮች ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ በኬንያ የባንክ ሂሳብ ባለቤት የሆኑ ጎልማሶች ወደ 82 በመቶ ሲሆኑ በሩዋንዳ ደግሞ 50 በመቶ ናቸው። በአጠቃላይ ከሰሃራ በታች ባሉ ሃገራት በአማካይ 43 በመቶ ጎልማሶች በፋይናንስ ተቋማት ሂሳብ ባለቤት ሲሆኑ ከአማካዩ ጋር ሰነጻጸር አሁንም የኢትዮጵያ ዝቅተኛ ነው።

የፋይናንስ አካታችነት ዋና ዋና መሰናክሎች ሂሳብ ለመክፈት የሚጠየቀው በቂ ገንዘብ ያለመኖር፣ የፋይናንስ ተቋማቱ በቅርበት አለመገኘት፣ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች እጥረት፣ ሃይማኖታዊ ምክንያቶችና የፋይናንስ ተቋማትን አለማመን ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ። የሀገራችን የፋይናንስ አገልግሎት ከከተሞች ውጭ የሚኖረውን ብዙሃኑን የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ አይደለም። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በሃገሪቱ ካሉት የባንክ ቅርንጫፎች 35 በመቶ የሚሆኑት አዲስ አበባ ይገኛሉ። በተጨማሪም አገልግሎቱ ለኢኮኖሚ እድገት፣ ስራ ፈጠራና ድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ ለሚያበረክቱት አነስተ
ኛና መካከለኛ ተቋማት በበቂ ሁኔታ እየተሰጠ አይደለም። የፋይናንስ አካታችነት ታዳጊ ሃገሮች ድህነትን ለመቅረፍ እና አካታች የኢኮኖሚ እድገት ከሚያሳኩባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በተለይ ዝቅተኛውንና መካከለኛውን የህብረተሰብ ክፍል የፋይናንስ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በአግባቡ ከተገበሩት ደንበኞቻቸው ስራ ፈጥረው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት የሚቀይሩበትን እድል እንዲያመቻቹ ያግዛቸዋል።

ሌሎች ተግዳሮቶች

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር ከአካታችነት ችግር በተጨማሪ ሌሎች ተደራራቢ ችግሮች አሉበት። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች ለሴክተሩ እድገት ማነቆ በመሆን እንዳይሻሻል ከማድረጋቸው በተጨማሪ ሴክተሩ

ለሌሎች ዘርፎች ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ በብቃት እንዳይወጣ አቅበውታል፡፡

የባንክ ሴክተር ተግዳሮቶች፡

- የፋይናንስ አገልግሎቱ ኋላ ቀር፣ አዳዲስ ፈጠራ ያልታከለበትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጎድለው መሆኑ፣
- የወለድ ምጣኔ በገበያ ውድድር ሳይሆን በብሄራዊ ባንክ መወሰኑና ከዋጋ ግሽበት ምጣኔ በታች መሆኑ፣
- በባንኮች መካከል የሚፈለገው ውድድር አለመኖር፣
- የውጭ ምንዛሬ እጥረትና በመንግስት ባንኮች ቁጥጥር ስር መሆን

የኢንሹራንስ ሴክተር ተግዳሮቶች፡

- ደካማ የኢንሹራንስ ስትራቴጂያዊ ትኩረት መኖር፣
- የሰለጠነ የኢንሹራንስ ባለሙያዎች እጥረት፣
- አዳዲስና በፈጠራ የታገዙ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች አለመኖር፣
- በሴክተሩ ፍትሃዊ ያልሆነ ውድድር መኖር፣
- ስለኢንሹራንስና አገልግሎቱ በቂ የሆነ ግንዛቤ አለመኖር፣
- የተቀናጀ መረጃ ወይም የመረጃ ቋት አለመኖር ወዘተ

የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ተግዳሮቶች፡

- ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ተበታትኖ የሚኖር ማህበረሰብ በመኖሩ የፋይናንስ አገልግሎት ማዳረስ አለመቻሉ፣
- የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት አቅም ማነስ፣
- የተጠቃሚዎች ግንዛቤ እጥረትና አማራጭ ባህላዊ መንገዶችን መምረጥ፣
- የብድር አገልግሎቶች ውድ መሆናቸው፣
- በርካታ የሰነድ ማስረጃዎች መጠየቃቸው፡፡

የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት

የወለድ አልባ የባንክ አገልግሎት በእምነታቸው ምክንያት ከፋይናንስ ስርአቱ የራቁትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለማቀፍ ብቻ ሳይሆን የሃገራችን የፋይናንስ ስርአት የሚጎድለውን አማራጭ አገልግሎቶችን ለሁሉም ተገልጋዮች ያለ አድሎ ለመስጠት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህ አካታች አገልግሎት ወደ ፋይናንስ ስርአቱ እንዲካተት ለረጅም ጊዜ ሲጠየቅና መስመር ከያዘ በኋላ ሲፈርስ ቆይቶ በቅርቡ በተደረገ ለውጥ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ የወለድ አልባ ባንክ ወደ ስራ ለመግባት በቅቷል፡፡ በተጨማሪም ከ10 በላይ መደበኛ ባንኮች በመስኮትና በቅርንጫፍ አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የሃገሪቱ ግዙፉ ባንክ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እ.ኤ.አ ግንቦት 2020 መጨረሻ ድረስ በወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ጠቅላላ የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑ 30.3 ቢሊዮን ብር መድረስ መቻሉንና ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎትን የሚጠቀሙ ደንበኞች ብዛትን 2.7 ሚሊዮን መድረሱን እንዲሁም በተለያዩ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ደንበኞች 3 ቢሊዮን ብር የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረቡን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከተቀማጭ ገንዘብ አንጻር ለፋይናንስ (ብድር) አገልግሎት የዋለው ወደ 10% የሚጠጋው ብቻ ሲሆን ይህም በንጽጽር ዝቅተኛ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ወደ ስራ እየገቡ ያሉት ሙሉ በሙሉ የወለድ አልባ ባንኮች ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚሰጡ መደበኛ ባንኮች የሚያጋጥማቸው ጠንከር ያለ ውድድር እና ከብሄራዊ ባንክ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ግልጽ አለመሆን እንደ ተግዳሮት ሊቆጠር ይችላል፡፡

አማራጭ የኢንሹራንስ አገልግሎት በሃገራችን እስካሁን በስራ ላይ ያልዋለ ሲሆን ከመደበኛው አገልግሎት ጎን ለጎን እና ራሱን የቻለ የኢንሹራንስ አገልግሎት ለመጀመር እንቅስቃሴዎች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወለድ አልባ የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎት በአንዳንድ የሃገራችን ክፍሎች ከመደበኛው አገልግሎት ጋር ጎን ለጎን እና በአንድ ተቋም ደግሞ ሙሉ በሙሉ እየተሰጠ ቢሆንም ብዙሃኑ ዜጋ ከከተማ ርቆ የሚኖር መሆኑና ዝቅተኛ የፋይናንስ አካታችነት ባለባት ሀገራችን ማይክሮ ፋይናንስ የሚጫወተው ሚና ተገቢው ትኩረት እየተሰጠው አይደለም፡፡

የፖሊሲ አማራጮች

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር በበርካታ ችግሮችና መሰናክሎች ያለፈና በማለፍ ላይ ያለ እንደሆነ ይታወቃል። ሁሉንም ዜጎች ያሳተፈና ያካተተ የፋይናንስ ስርአት መዘርጋት ለሃገራችን እድገትና ወደ ፊት መራመድ ጉልህ ሚና ይጫወታል ብለን እናስባለን። ስለዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የፖሊሲ አማራጮችን ስራ ላይ ማዋል እንዳለብን እናምናለን።

- የፋይናንስ ሴክተሩ ብሎም የሀገራችን ዋነኛ ተግዳሮት የማክሮ ኢኮኖሚው መዛባትና አለመረጋጋት ነው። የዋጋ ግሽበት መናር፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የስራ አጥ ቁጥር መጨመር፣ የውጭ ንግድ ሚዛን መዛባት፣ አለቅጥ የተቆለለው የመንግስት እዳ ወዘተ ሲሆኑ ለነዚህ ምስቅልቅሎች ነባራዊውን ሁኔታ ያላገናዘበ እቅድ፣ በአግባቡ ያልተመራ የኢኮኖሚ ስርአትና በሙያና ችሎታ ላይ ያልተመሰረተ የስራ ምደባና የማስፈጸም አቅም አለመኖርም ተጠቃሾች ናቸው። ስለዚህ ከእቅድ፣ ትግበራ እስከ ግምገማ ያሉትን ደረጃዎች በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ለፋይናንስ ሴክተሩም ይሁን ለአጠቃላዩ ኢኮኖሚያችን ጥንካሬ ወሳኝ ሚና እንዲጫወት መደረግ አለበት
- አስፈላጊውን መሰረተ ልማት በማሟላት የፋይናንስ ተቋማት ከከተማ ርቆ ላለው የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር
- በባንኮች መካከል ፍትሃዊ ውድድር እንዲኖርና ደንበኞች ጥራት ያለው አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበትን እድል ለማመቻቸት አሳሪ የሆኑ መመሪያዎችን መከለስ/መቀየር
- ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለስራ ፈጠራ፣ ድህነት ቅነሳና ኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክቱትን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት ባንኮችና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የሚደግፉባቸውን ማእቀፍ መፍጠርና ክትትል ማድረግ
- የፋይናንስ አገልግሎቶችን መጠቀም የሚያስገኛቸውን ፋይዳዎች ለህብረተሰቡ በማስረዳት የግንዛቤ እጥረትን መቀነስና ከኢ-መደበኛ አገልግሎቶች ቀስ በቀስ ወደ መደበኛ የፋይናንስ ስርአት የሚመጡበትን ዘዴ ማመቻቸት
- ትምህርት ለፋይናንስ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት እሙን ነው። የሀገራችንን የፋይናንስ ስርአተ ትምህርት ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለሴክተሩ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት መንደፍና የጥናትና ምርምር ዘርፎችን ማበረታታትና ማገዝ
- አዳዲስ አሰራር ወደ ሴክተሩ ይዘው የመጡ ባንኮች (ወለድ አልባ ባንኮች፣ የቤቶች ባንክ፣ ምናልባት የኢንቨስትመንት ባንኮች ወዘተ) አስፈላጊውን የፖሊሲና የመመሪያ ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- በቅርቡ ስራ ላይ እንደሚውል የሚጠበቀውን የካፒታል ገበያ በተገቢው መንገድ በማስተዳደር የሃገራችንን የካፒታል እጥረት ለመቅረፍና የረዥም ጊዜ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን ለማበረታታትና ለመደገፍ እንዲውል እና የሃገራችንን የኢኮኖሚ እድገት የሚደግፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት

9 ኢንደስትሪ

በአገራችን የሕዝብ ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ በመምጣት ላይ ይገኛል። ይህንን ሕዝብ ደግሞ ውስን በሆነ የእርሻ መሬት ተጠቃሚና ባለቤት እያደረጉ መሄድ ረዥም መንገድ የሚያስኬድ አይሆንም። ከዚህ በተጨማሪ በአገራችን በየአመቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በኢኮኖሚው ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ ለመጫዎት የሚያስችላቸው የስራ እድል ይፈልጋሉ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛውን የአገሪቱን የስራ እድል የተሸከመውን የግብርናና እርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያግዝ የስራ መስክ ያስፈልጋል።

ከሀገራችን ተጨባጭ ወጣ ብለን አህጉራዊ እና ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎችን ስንመለከት አገራት በቴክኖሎጂ ልማት ከፍተኛ እሽቅድድም ውስጥ ገብተው እናገኛለን። አገራት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠቀሙባቸው ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከሌላ አገር ከመግዛት ይልቅ በመስኩ ራሳቸውን የሚችሉበትን እድል ለመፍጠር የሚጣጣሩበት ዘመን ላይ በመድረሳችን ለኢንዱስትሪ ልማት የምንሰጠውን ትኩረት ማሳደግ እንዳለብን ይታመናል።

ኢንዱስትሪ ልማት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ከፍተኛ የማዕድን፣ የእንስሳትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት የሆኑ አገራት ያላቸውን ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት በጥሬው ለአለም ገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት እየጨመሩ ማልማት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ቁልፍ የልማት አጀንዳ ሆኗል። ሀገራት የኢንዱስትሪ አቅማቸውን ሲያሳድጉ በጥሬ ሀብቶቻቸው ላይ እሴት ከመጨመር ባለፈ በእያንዳንዱ

የእሴት ሰንሰለት ውስጥ አዳዲስ የስራ እድሎችን፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አቅጣጫ በሶስት የጊዜ ማእቀፎች የተከፈለ ሲሆን እነሱም የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ናቸው። የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ፕሮግራም ከኢንዱስትሪ ከመጠን እና የካፒታል ፍላጎት አንፃር በሁለት የተከፈለ ሲሆን አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ኢንዱስትሪዎች በአንድ ፈርጅ እንዲሁም ከፍተኛና ልዩ ልዩ (ስፔሻል) ኢንዱስትሪዎችን በሁለተኛ ዘርፍ ከፍሎ ይመለከታል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሚቀጥሉት አምስት አመታት በኢንዱስትሪ መስክ ትኩረት የሚሰጠው ለዜጎች ሰፊ የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ፣ ሀገራችን ካላት ዝቅተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል አንፃር ተግባራዊ መሆን የሚችሉ፣ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እና የውጭ ምንዛሬ የማይጠይቁ፣ አስፈላጊ ግብዓቶች በሙሉ በአገር ውስጥ በቀላሉ ሊገኙና ሊመረቱ የሚችሉ፣ ማሽነሪዎቹና መለዋወጫቸው በአብዛኛው በአገር ውስጥ ሊመረቱና ሊገጣጠሙ የሚችሉ፣ የሚያመርቷቸው ምርቶች በጥራትና በብዛት ለመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ እንዲሁም አነስተኛ ኢንዱስትሪዎቹ ራሳቸው በሂደት ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ማደግ እንዲችሉ ይሰራል።

መካከለኛ ጊዜ የምንለው ከአምስት አመት እስከ አስር አመት ያለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ወደ መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያድጉበት፣ አዳዲስ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በብዛት የሚፈጠሩበት፣ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መሰረት የሚጣልበት እንዲሆን የሚሰራበት ጊዜ ይሆናል። በመካከለኛ ጊዜ አገሪቱ ከፍተኛውን የኢኮኖሚ ድርሻ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ እንድታገኝ የሚሰራበት ጊዜ ይሆናል። የአገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅር ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚዞርበት ወቅት እንዲሆን ይሰራል። አገሪቱ የኢንዱስትሪውን እድገት መመገብ የሚችል የሰው ሃይል ማፍራት ቅድሚያ የሚሰጥበት፣ በኢንዱስትሪው መስክ የሰለጠነ የሰው ሃይል ከአገር አልፎ በአጎራባች አገሮች በመላክ የቀጠናውን የኢንዱስትሪ መስፋፋት ከፍተኛውን ድርሻ የምንይዝበት ጊዜ እንዲሆን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አበክሮ ይሰራል።

በመካከለኛ ጊዜ የሚስፋፉ ኢንዱስትሪዎች ትኩረት ከሚሰጡባቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶች መካከል አገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ ከውጭ የምታስገባቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በመተካት፣ ከፍተኛ ፍላጎት የሚታይባቸውን የግንባታ እቃዎች እና የማምረቻ መሳሪዎች በአገር ውስጥ ለመፈብረክ የሚያስችሉ የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት፣ እንዲሁም የግብርና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን ሊያሳድጉ የሚችሉ የግብርና ኬሚካሎችንና ለሜካናይዜሽን የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማምረት ላይ ትኩረት ይሰጣል።

በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የረዥም ጊዜ የኢንዱስትሪ ልማት ዘመን ሲሆን በዚህ ወቅት አገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ማዕከል ከሆኑ አገራት ተርታ የምትሰለፍበት ወቅት ይሆናል። በዚህ የጊዜ ማእቀፍ ከትላልቅ አለም አቀፍ የኢንዱስትሪ ምርት አምራቾች ጋር በጥራት፣ በዋጋ፣ በመጠን ወዘተ በመወዳደር አለምአቀፍ ገበያው ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ጥረት የሚደረግበት ወቅት ይሆናል። በሶስተኛው የኢንዱስትሪ ዘመን ባሕሪያቸው ውስብስብ የሆኑና ከብሄራዊ ደህንነት አኳያ በሀገር ውስጥ ሊበለፅጉ የሚገባቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶች ማምረት የሚጀመርበት ወቅት ይሆናል። ይህንን ከፍተኛ የኢንደስትሪ ትልም እውን ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ አስፈላጊ የሰው ኃይል ግንባታ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል።

የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲን በተሳካ ሁኔታ ውጤታማ ለማድረግ ለኢንዱስትሪው ልማት አጋዥና ግብዓት የሚሆኑት መስኮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። የኢንዱስትሪ ምርቶች ጥራት የሚጀምረው ከግብዓት ጥራት በመሆኑ፣ ለኢንዱስትሪ ልማት አስተዋፅኦ ላላቸው የግብርና እና የማዕድን ልማቶች ልዩ ማበረታቻ ይደረጋል።

የኢንዱስትሪ ልማት ሲታሰብ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የኢንዱስትሪ ልማቱና የአካባቢ መስተጋብር ነው። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው ነጥቦች አንዱ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን በአገሪቱ የሚስፋፉ ኢንዱስትሪዎች ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ በምርት ሂደትም ይሁን፣ በተረፈ-ምርት አወጋገድ ላይ ዘመናዊ እና ከአካባቢ ጋር የተስማሙ ቴክኖሎጂዎችንና የአመራረት ስራ አመራር እንዲከተሉ ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የሚስፋፉ ኢንዱስትሪዎች ሃይልን በቁጠባ የሚጠቀሙና ኃይላቸውን ከታዳሽ የሃይል ምንጭ እንዲያገኙ ይደረጋል።

10 ንግድና ኢንቨስትመንት

ንግድና ኢንቨስትመንት ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝና ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በተለይ አሁን ያለንበት ሉላዊ ዘመን የአለም ሀገራት በንግድና ኢንቨስትመንት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ የተሳሰሩበት ወቅት ነው፡፡ ሀገራት ከድህነት ለመላቀቅና እድገታቸውን ለማፋጠን ንግድና ኢንቨስትመንት ላይ በትኩረት በመስራታቸው የዜጎቻቸውን ህይወት በመለወጥና ድህነትን በእጅጉ በመቀነስ ወደ እድገት ማማ በመገስገስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም የወጪና ገቢ ንግዷን ለማሻሻልና ለማሳደግ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ባለፉት መንግስታት የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን በማውጣትና በመተግበር ሂደት አሳልፋለች፡፡ ይሁን እንጂ በሚፈለገው ደረጃ የታለመውን እድገትና ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡

የወጪ ንግዱን ዘርፍ ስንመለከት በጥሬ እቃና የግብርና ምርት ላይ የተወሰነና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ድርሻ በጣም አናሳ ነው፡፡ በአንጻሩ የገቢው ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህም የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ከማጋጠሙም በተጨማሪ የንግድ ሚዛኑ ትልቅ ክፍተት ያሳያል፡፡ በ 2012 የወጪ ንግድ 2.67 ቢሊዮን፣ የገቢ ንግድ 15.11 ቢሊዮን ሲሆን የንግድ ልዩነቱ 12.44 ቢሊዮን ዶላር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት ጥቂት አመታት የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩና በሀገር ውስጥ ያለው አምራች ኢንዱስትሪ አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ በውድ ተገዝተው የሚገቡ ምርቶች ዋጋ መጨመር ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት እያስከተለ ይገኛል፡፡

የወጪ ንግዱን ለማሳደግ ጠንካራና ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ መሰረት በመጣል የማኑፋክቸሪንግ ሴክተሩን ማሳደግ ይጠይቃል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ መስፋፋት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የስራ እድል ለመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ንግድ ለማስፋፋት በሀገር ውስጥ ያለው ሀብት ውስንና የቴክኖሎጂ እድገት ዝቅተኛ በመሆኑ ቀጥተኛ የውጭ ሀገር ኢንቨስትመንት የማይተካ ሚና አለው፡፡ ይሁን እንጂ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመሳብ በኩል ባለፉት አመታት የተሰራው ስራ ሀገሪቱ ካላት እምቅ አቅም አንጻር እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

ሀገራችን ንግድን ከማሳለጥ አንጻር በአለም አቀፍ ደረጃ እጅግ በጣም ቀርፋፋ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ የምትመደብ ሲሆን ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት አማካይ አፈጻጸምም ወደ ኋላ የቀረች ናት፡፡ በሀገሪቱ ያለው መሰረተ-ልማት ኋላ ቀር ከመሆኑ በተጨማሪ የመንግስት አገልግሎት ተቋማት በብልሹ አሰራር የተተበተቡና ውጤታማ ያልሆነ አሰራርን የሚከተሉ መሆናቸው ችግሩን አባብሶታል፡፡ ለምሳሌ ቢዝነስ ለመስራት ያለውን ቅለትና ምቹ ሁኔታ በተመለከተ የአለም ባንክ በየአመቱ በሚያወጣው የደረጃ ሰንጠረዥ በፈረንጆቹ 2020 በአለም ላይ ካሉ 190 ሀገራት 159ኛ ደረጃ ላይ እንዳለች ያመለክታል፡፡ ከዚህም አንጻር የተንዛዛና የተጓተተ የጉምሩክ አሰራር፣ ሸቀጦችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቅ መሆኑና በቂ የሆነ የብድርና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ያለመኖሩ በዋና ችግርነት ይጠቀሳሉ፡፡

ንግድን ለማሳደግና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ቀጠናዊ የንግድ ትስስርን ማጠናከርና የውስጥ አቅምን መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ የኮሜሳ አባል እና የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና የፈረመች ሲሆን የአለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን በሂደት ላይ ትገኛለች፡፡ ይሁን እንጂ ኢኮኖሚያዊ ውህደቱ አስፈላጊ እንደመሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚከወን መሆን አለበት፡፡

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከንግድ እና ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ከላይ የተመለከቱትን እውነታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን የንግድ እና ኢንቨስትመንት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ንግድና ኢንቨስትመንት ተመጋጋቢ እና የማይነጣጠሉ ሲሆን ከሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ፖሊሲዎች ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡

1. አብዛኛው የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እሴት በማይጨምሩ የስራ ዘርፎች (ለምሳሌ ህንጻ ግንባታ) ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እሴት በሚጨምሩ የስራ ዘርፎች በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፡፡
2. የሀገር ውስጥ የንግድ ህጎች ተወዳዳሪነትን የሚያበረታቱና ፍትሀዊ አሰራርን የሚያሰፍኑ፣ ለሁሉም ዜጎች እኩል የውድድር መድረክና መደላድል

የሚፈጥሩ እንዲሁም ብቁ የሆነ የመንግስት አሰራርና መዋቅር እንዲጠናከርና እንዲዘረጋ የሚያግዙ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

3. ቀጥተኛ የውጭ ሀገር ኢንቨስትመንት የተሳለጠና ዘመናዊ አሰራርን የሚፈልግ ነው:: የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ከሙስናና ከብልሹ አሰራር በማላቀቅ ተወዳዳሪና የተሳለጠ አገልግሎት እንዲሰጡ በሚያስችል መልኩ እንዲዋቀሩ ይደረጋል፣
4. ኢንቨስትመንት ሰላምና መረጋጋትን አጥብቆ ይሻል:: ለሰላምና መረጋጋት ቅድሚያ በመስጠት ለባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ዋስትና እንዲያገኙ በትኩረት ይሰራል፣
5. ንግድን ለማሳለጥና ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ መሰረተ-ልማቶች የማስፋፋትና ልዩ ልዩ አሰራሮች ይዘረጋሉ:: የወጪና ገቢ ንግድን የሚያሳልጡ መሰረተ-ልማቶች ማለትም የመንገድ፣ ትራንስፖርት፣ የሀይልና የደረቅ ወደብ ግንባታ ማስፋፋትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም አሰራር ይዘረጋል፣
6. የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚውን እንዲመራ የማበረታታት እና የመደገፍ ስራ ይሰራል:: ወደ ግሉ ዘርፍ የሚዘዋወሩ በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኙ ተቋማትን በጥንቃቄ በመለየት የሀገርን ጥቅምና ሉአላዊነት ባስጠበቀ መልኩ እንዲከወን ይደረጋል፣
7. ሀገሪቱን በአለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ የነጻ ንግድ ትስስር ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንድትሆን የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፣
8. በአህጉራዊና ቀጠናዊ የነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነቶች ተወዳዳሪና አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ከፍተኛ የምርት አቅም ያለውን የንግድ ዘርፍ የመለየት ስራ ይሰራል:: ለምሳሌ በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ሰፊ እድል ያለ በመሆኑ ተገቢው ትኩረት ይሰጣል::
9. የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ ኣዳዲስ አሰራሮችን በመፈተሽ ተግባራዊ ይደረጋል::

11 ዲጂታል ኢኮኖሚ

ቴክኖሎጂ እጅግ በፈጠነ ሁኔታ በማደግ ላይ በሚገኝበት በዚህ ክፍለ ዘመን የግለሰቦች፣ የተቋማት እና የሀገራት አጠቃላይ እንቅስቃሴ በቴክኖሎጂ ተጽእኖ ስር ወድቋል። ትናንሽ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ ግብርና፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ሆቴል እና ቱሪዝም፣ የትምህርት እና የምርምር ተቋማት፣ የሀገር ውስጥ እና ዓለም ዓቀፍ ንግድ በቴክኖሎጂ እገዛ የሚከናወን ሆኗል። በዚህ ፈጣን የለውጥ ሂደት ውስጥ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን ካልቻልን ድህነትን ለማጥፋት እና እድገትን ለማረጋገጥ አዳጋች ከመሆኑም ባሻገር በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረን ድርሻ እየቀነሰ መሄዱ አይቀሬ ነው። ፈጣን እና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ቴክኖሎጂን በስፋት መጠቀም አማራጭ ሳይሆን ግዴታ ሆኗል። ይህንን ሀቅ በመገንዘብ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጠንካራ የዲጂታል ኢኮኖሚ እውን ለማድረግ መጠነ ሰፊ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት በመዘርጋት በቴክኖሎጂ የታገዘ ኢኮኖሚ ይገነባል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የኢትዮጵያን የዲጂታል ኢኮኖሚ በአፍሪካና በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ እና በሁሉም ኢኮኖሚያዊ ሴክተሮች የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ዘርፈ-ብዙ የቴክኖሎጂ ስራዎች ይሰራል። የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ሶስት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም ሀገራዊ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሥራዎች በዲጂታል ትራንፎርሜሽን መልማታቸውን ማረጋገጥ፣ የሀገራዊ ሉዓላዊነትና ደህንነት ማስጠበቅ፣ የተረጋጋና ስጋትን ያስወገደ የዲጂታል ስርዓት ያሰረጸ ኢኮኖሚ መገንባት ናቸው። የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ስራ በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም የጊዜ ምእራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

የአጭር ጊዜ ዕቅድ (3-5ዓመት)

1. በዲጂታል ቴክኖሎጂ የበቃ የሰው ኃይል ለማብቃት የሚያስችል ስትራቴጂያዊ ኃብቶችን መለየትና መጠቀም፣

2. ከዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ማስረጽ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመፍታት/ለመቀነስ የሚያስችል የለውጥ አመራር ስርዓትና የኢኮኖሚያዊ ሽግግር መሳሪያዎችን መፍጠር፣
3. ዘላቂና ተወዳዳሪ ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ጥናትና የልማት ፕሮግራሞችን ተቋማዊ ማድረግ፣
4. በዲጂታል ንግድ ስራና ፈጠራ ዙሪያ ላይ ለሚሰሩ የፈጠራና የምርምር አካላት አስቻይ ሁኔታ መፍጠርና መደገፍ፣
5. ፖርታሎች (Portals) እና የተቀናጀ የወል መጠቀሚያ መተግበሪያዎችን/አውታሮችን (APIs-Application Programming Interfaces) በመጠቀም የተቀናጀ የመረጃና የኢንፎርሜሽን አቅርቦትን መፍጠር፣
6. በመጨረሻም ለሚቀጥሉት 15 ዓመታት የሚሆን ሁሉን አቀፍ/አካታች የብሔራዊ ቴክኖሎጂ ፍኖተ-ካርታ ማልማትና መተግበር፣
7. ጥቅም ላይ የሚውሉ ወሳኝ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች

1	የ መ ን ግ ስ ት ቴክኖሎጂ	Government Technologies (GovTech)
2	የ ቴ ሌ ኮ ም ቴክኖሎጂ	Telecom Technologies (TelecomTech)
3	የኢነርጂ ቴክኖሎጂ	Energy Technologies (EnergyTech)
4	የ ት ም ህ ር ት ቴክኖሎጂ	Educational Technologies (EdTech)
5	የግብርና ቴክኖሎጂ	Agriculture Technologies (AgriTech)
6	የጤና ዘርፍ ቴክኖሎጂ	Health Technologies (HealthTech)
7	የትራንስፖርትና የ ሎ ጂ ስ ቲ ክ ስ ቴክኖሎጂ	Transport & Logistics Technologies (LogiTech)
8	የንግድና የሸቀጥ ቴክኖሎጂ	Trading & Commerce Technologies (Trade-Tech)
9	የሸማችና የንግድ ቴክኖሎጂ	Consumer & Commerce Technologies (Cosumer-Tech or e-Commerce)
10	የፋይናንስ ዘርፍ ቴክኖሎጂ	Financial Technologies (FinTech)
11	የቁጥጥር ሥርዓት ቴክኖሎጂ	Regulatory Technologies (RegTech)
12	የመረጃ ቴክኖሎጂ	Data Technologies (DataTech) etc

ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን የሚያስፈልጉ ዋና ዋና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች

(ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቴክኖሎጂዎች አዲስ እንደመሆናቸው ለሁሉም ሰው ግልጽ የሆነ አቻ ትርጉም ስላልተሰጣቸው እንዳይዛነፉ ስያሜዎቹ በእንግሊዝኛ ተቀምጠዋል)

1. Biometrics and Cryptography
2. Distributed Ledger Technology (DLT), Block chain and Graph Technology
3. Algorithms and Automation
4. Data Mining (DM) and Big Data Analysis (BDA)
5. APIs (Application Programming Interfaces) and Interlink ages
6. Machine Reading (MR) and Machine Learning (ML)
7. Robotics
8. Artificial Intelligence (AI)

በዲጂታል ትራንፎርሜሽን ሥርዓት ውስጥ መሰረት ለመጣል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር

1. ዲጂታል መታወቂያ (Digital Identification ID)
2. ዲጂታል ዳታ እና የሚስጥር መጠበቂያ ስርአት(Digital Data and Privacy Management)
3. ዲጂታል የሪስክ ትንተና (Digital Risk Analysis)
4. የገበያ/የዋጋ ትመና፣ ንግድ እና ታማኝነት (Market Pricing, Trading and Integrity)
5. የደንበኛ መገናኛ (Client Interface፡ Web Application, Mobile Application, USSD (Short SMS) Application)
6. የሳይበር ምህዳር ደህንነት (Cyber Security)
7. ቁጥጥር እና ደንብ ማስከበር (Regulation and Compliance)
8. ሪፖርት፣ ክትትል፣ ፈልጎ ማግኘት (Reporting, Monitoring and Detection (Traceability)

ዕቅድና ምሰሶዎች፡- ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ

1. የዲጂታል መሰረተ-ልማት

01. በሀገሪቱ የ24 ሰዓት ያልተቆራረጠ ኢንተርኔት አቅርቦት ማረጋገጥ፣
02. በሀገሪቱ በሁሉም ስፍራ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማሟላት፣
03. የፋይናንስ አካታችነትና የዲጂታላይዝድ ፋይናንስ አገልግሎትን ማረጋገጥ፣
04. የዲጂታል መጠቀሚያ መሳሪያዎችን (ኮምፒዩተር፣ ሞባይል ወዘተ) አቅርቦትና ተደራሽነት ማረጋገጥ፣

2. የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት

01. የግሉ ዘርፍ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎትና የንግድ ሞዴሎችን እንዲያቀርብ ማስቻል፣

i. የዲጂታል የክፍያ ስርዓት
ii. የዲጂታል የታክስ ስርዓት
iii. የዲጂታል የዋስትና ግብይት አገልግሎት

3. የዲጂታል አውድ

01. የበይነ-መረብ ንግድ አውድ
02. የበይነ-መረብ የአገልግሎት አቅርቦት መፍጠር፣

4. የዲጂታል የፈጠራ ሥራ

01. ፈጠራን የመጀመር ባህልንና በዲጂታል በማገዝ ዓለም አቀፍ ተሸጋጋሪ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ድርጅቶች መፍጠር

5. የዲጂታል ዕውቀት

ዜጎች አዎንታዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ብሔራዊ እሴት መፍጠር እንዲችሉ የዲጂታል ክህሎት እንዲያዳብሩ የትምህርት እና ስልጠና ስራ ይሰራል።

ትኩረት የሚሰጣቸው አስቻይ ጉዳዮች፣

1. የኃይል አቅርቦትን አስተማማኝ ማድረግ፡- የግሉን ዘርፍ የሚያሳትፍ በግልና በመንግስት ትብብር የኃይል አቅርቦት ማረጋገጥ፣
2. የማያቋርጥ የቴሌኮምና ከፍተኛ አቅም ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ማቅረብ፣
3. የተቀላጠፈ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የታክስ አሰባሰብ ስርአቱን ዲጂታል በሆነ መልኩ መተግበር።

የረጅም ጊዜ ዕቅድ (10-15 ዓመት)

ከላይ የተዘረዘሩት የአጭር ጊዜ የዲጂታል ስራዎችን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የረዥም ጊዜ ስራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የመጀመሪያው በሀገር ውስጥ አቅም ብሔራዊ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማትንና ብሔራዊ ጥቅምን ያስጠበቀ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ልማትና የማስፋፋት ስራን ማጎልበት ሲሆን ሌላው ቴክኖሎጂን ለዓለም አቀፍ ገበያ በማቅረብ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የቀጠናው መሪ መሆን ነው።

12 ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር

በቴክኖሎጂ ታግዞ በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ንቁ ተዋናይ እና ተወዳዳሪ ለመሆን ሀገራት አካባቢያዊ እና ዓለማቀፋዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ትስስሮችን እንዲፈጥሩ አስገድዷል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በዚህ እጅግ ፈጣን እና ተለዋዋጭ ዓለማቀፍ የንግድ እና የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እና የዜጎቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ አስገድዷል።

ከኢትዮጵያ የመልክዓ-ምድር አቀማመጥ፣ የህዝብ ብዛት፣ ወደብ-አልባነት እና ካላት የኢኮኖሚ መዋቅር አንጻር ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብሎም ጂኦ-ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳለው የበርካታ የአውሮፓ፣ እስያ እና አፍሪካ ሀገሮች ተጨባጭ ተሞክሮ ያሳያል። ቀጠናዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትስስር አገራት የሸቀጥ፣ የአገልግሎት፣ የካፒታል እና የሰው ኃይል እንቅስቃሴን የሚገድቡ አሰራሮችን እንዲያስወግዱ ያስችላል። እነዚህ እንቅፋቶች በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሃገራት የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

ስኬታማና ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ሀገራት ያለባቸውን የመሰረተ-ልማት እና የካፒታል ውስንነት እንዲሁም የፖሊሲ እንቅፋቶችን በመቅረፍ በአባል አገራት መካከል የንግድ፣ የካፒታል፣ የሰው ሀብት እና የቴክኖሎጂ ፍሰትን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያግዛል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ወደብ አልባ እና ትልቅ የህዝብ ቁጥር ላላቸው ታዳጊ አገራት፣ ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ ብሎም አህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስር እምቅ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለመጠቀም ላቅ ያለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ አለው። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት ያለባቸውን የኢኮኖሚ አቅም ውስንነት በመቅረፍ በአለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍ እንዲል ትልቅ የፖሊሲ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። የኢትዮጵያ አምራች ድርጅቶች (የግል ዘርፍ) ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን በአለም አቀፍ እና ቀጠናዊ የእሴት ሰንሰለት (Value chain) ጠንካራ ተሳትፎ የላቸውም።

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በተለያዩ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች (የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ COMESA እና የምስራቅ አፍሪካ በይነ-መንግስት IGAD) አባል ብትሆንም በብዙዎቹ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ያላት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ውስን ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ነጻ የንግድ ቀጠና (Free Trade Area) የኢኮኖሚያዊ ትስስር ደረጃ ላይ ቢደርስም ኢትዮጵያ እስከ አሁን ይህንን ነጻ የንግድ ቀጠና አልተቀላቀለችም። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ የአለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል ለመሆን ብታመለክትም እስከ አሁን የአባልነት ሁኔታዎችን ማሟላት ባለመቻሏ ድርጅቱን አልተቀላቀለችም።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ማጠናከር ለሀገራችን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትሩፋቶችን እንደሚያስገኝ በጽኑ ያምናል። ፈጣን እና የተሳለጠ የውጭ ንግድ እንዲሁም ቀልጣፋ የገበያ ስርአት፣ የላቀ አለማቀፋዊ እና ቀጠናዊ ተወዳዳሪነት፣ ከፍተኛ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ-ነዋይ (FDI) ፍሰት፣ መዋቅራዊ ሽግግርን በአጭር ጊዜ ማረጋገጥ፣ አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት፣ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር፣ ፈጣን ድህነት ቅነሳ፣ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣ ቀልጣፋ የንግድ ልውውጥ እና የካፒታል ፍሰት ከብዙ በጥቂቱ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ካለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተጨማሪ ሰላም ለራቀው እና የግጭት አውድማ ለሆነው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ይረዳል። የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እና የባህል ትስስር የአካባቢያዊ ቁርኝት ሌላው ጠቀሜታ ነው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራዊ የልማት ራእዩን እውን ለማድረግ ከሚከተለው የምጣኔ ሀብት እና የማህበራዊ ፖሊሲዎች ጎን ለጎን ከጎረቤት ሀገራት እና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል። ከጎረቤት ሀገራት እና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር የሚፈጠረው ቀጠናዊ የገበያ እና የኢኮኖሚ ትስስር በኢትዮጵያና በአካባቢው ሀገራት መካከል መንገድን ጨምሮ ሌሎች የመሰረተ ልማቶች፣ የንግድ ህጎች እና ቀጠናዊ ተቋማት ግንባታን ያፋጥናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጠንካራና ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ለመፍጠር ልዩ ልዩ አስቻይ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሲሆን ከእነዚህ መካከል የንግድ እና መዋዕለ-ነዋይ ዝውውር ለማቀናበር የሚያስችሉ ፖሊሲና አሰራሮችን ይቀርጻል፣ የትራንስፖርት፣ ኢንፎርሜሽ ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና የኢነርጂ መሠረተ ልማት ፕሮግራሞች ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በቅንጅት እንዲነደፉ/ እንዲዘረጉ ያደርጋል፣ የሀገራችን የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ፖሊሲ የአፍሪካ እና አለም አቀፍ የፖሊሲ ማእቀፎችን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ እንዲከለሱ ያደርጋል፣ የተፈጥሮ ሀብቶች እንዲሁም ትምህርት እና ጤናን ጨምሮ ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች ቀጠናዊ ድርጅቶች ካወጧቸው መስፈርቶች ጋር የተዋጁ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን እስከ ዛሬ በነበራት ተሞክሮ በአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ትስስር ውጤታማ እንዳትሆን የሚያድርጉ አሰራሮችን በመለየት በተሻለ አሰራር እንዲለወጡ ያደርጋል፣ የእርምት እርምጃዎችንም ይወስዳል። በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በተለያዩ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች ውስጥ አባል መሆን (overlapping membership) የአፍሪካን የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጓተት ካደረጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያም የዚህ የተሳሳተ አሰራር ሰለባ መሆኗ ይታወቃል። ይህ ተደራራቢ አባልነት የሀገራትን ፖሊሲ የመተግበር አቅምና ከኢኮኖሚ ትስስሩ የሚያገኙትን ጥቅም ይገድባል። በመሆኑም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ከተመሰረቱ የኢኮኖሚ ስብስቦች የተሻለ ተጠቃሚ በሚያደርጋት ውስጥ ብቻ እንድትወሰን ይደረጋል።

ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር አሸናፊዎች እና ተሸናፊዎችን (Winners and Losers) እንደሚፈጥር ይታወቃል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን ከአካባቢው ሀገሮች ጋር በምትፈጥረው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትስስር በየትኛውም ሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት በመቀነስ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር እንዲፈጠር ይጥራል።

ሀገራችን ካላት ሰፊ እና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፣ ቁጥሩ ከፍተኛ የሰው ሀብት፣ ሰፊ የቆዳ ስፋት እና በአፍሪካ ቀንድ ካላት አማካኝ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ አንጻር ከአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ ተጠቃሚ እንደምትሆን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ብሎም የአለም የንግድ ድርጅትን እንድትቀላቀል እንሰራለን።

ምዕራፍ ሶስት

መሰረተ ልማት

1 መንገድ

መሰረተ ልማት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት የጀርባ አጥንት ነው፡፡ በተለይም የመንገድ መሰረተ ልማት ለገጠራማው ኢትዮጵያና ህዝቦቿ የህይወት መስመር (life line) ሲሆኑ ሁሉም ሊያስብል በሚባል መልኩ የሸቀጦችና አገልግሎቶች ልውውጥ የሚካሄደው መንገዶችን በመጠቀም ነው፡፡ እንደ ፓርቲያችን መርህ በሀገራችን ያለው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ችግር ላለፉት በርካታ አመታት ሲደራረቡ የቆዩ በመሆናቸው በአንድ ጀንበር ሊቀረፉ አይቻልም፡፡ የመንገድ መሠረተ ልማት ከዚህ እውነታ ውጭ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሀገር ደረጃ እንዲመጡ የሚያስፈልጉ ለውጦች የማህበረሰቡን የዕድገት ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ለመቀየር ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

የኢትዮጵያ መንገድ አውታር ወቅታዊ ሁኔታ

ወደብ አልባዋና ከ1.1 ሚሊዮን ካሬ ኪ.ሜ በላይ ስፋት ያላት ሃገራችን ከውጭው ዓለም ጋር የምትገናኘው በአብዛኛው በጅቡቲ ወደብ ሲሆን የመጀመሪያውና ረጅሙ አውራ ጎዳና የተገነባው በጣልያን የወረራ ዘመን ከአዲስ አበባ ምፅዋ የተዘረጋውና "Imperial Road" ተብሎ የሚታወቀው መንገድ ነው፡፡ በርግጥ በ17ኛውና በ18ኛው ክ/ዘመን ብዙ አነስተኛና የእግር መንገዶች በወቅቱ በነበሩ ነገስታት የተገነቡ ሲሆን በጣልያን ወረራ ወቅትም ለወታደራዊ እንቅስቃሴ የሚያገለግሉ 6000 ኪሜ ያህል መንገዶች (2500 ኪ.ሜ ቀላል የአስፋልት ሽፋን ያላቸው) ተገንብተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ መንገዶች የሃገሪቱን ልማት በሚያሳድግ መልኩ የተዘረጉ አልነበሩም፡፡ ከነፃነት በኋላም ወራሪው ሃይል በሸሸት ወቅት መልሶ ያበላሻቸውን መንገዶች ለመጠገንና ለመገንባት በነበረው የገንዘብ፣ የባለሞያና የመሣሪያ እጥረት ምክንያት አልተቻለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 115/1951 የተቋቋመው የአሁኑ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከ60 ዓመታት በፊት ጀምሮ የተለያዩ የመንገድ ልማት ፕሮግራሞችን አካሂዷል፡፡

የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (RSDP) የ22 ዓመት አፈፃጸም ሰነድ እንደሚያመለክተው የ "URRAP" ፕሮግራም እ.አ.አ. በ2014/15 በ707 ወረዳዎች ውስጥ 15602 የገጠር ቀበሌዎችን በክረምት ከበጋ መንገድ ለማያያዝ ታቅዶ 11,871ዎቹ (76%) ያህሉ ተገናኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል የገጠር ተደራሽነት Rural Acces Index (RAI) መለኪያ ክረምችና በጋ (All-Season) መንገድ በሁለት ሰዓት ርቀት ያለን የገጠር ህዝብ ምጣኔ መለኪያ ሲሆን በ1997 13% የነበረው እ.ኤ.አ በ2019 60% መድረሱን ያመለክታል፡፡ ይህም ከ82.3 ሚሊዮን የገጠር ህዝብ ውስጥ 49.8 ሚሊዮን ያህሉ ክረምት ከበጋ መንገድ በሁለት ሰአት ርቀት ውስጥ እንደሚኖር ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ እ.ኤ.አ በ1997 22% የነበረው የመንገድ አውታር በ2019 71% የደረሰ ሲሆን የመንገድ ጥግግቱ (Rood Density) 130.9 km /1000 (ኪ.ሜ)2 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ 1.43 ኪ.ሜ/1000 ሰው ሲደርስ ከ5 ኪ.ሜ ውጭ ያለው ህዝብ 27% እንዲሁም 3.6ኪ.ሜ ውጪ አማካይ ርቀት ከክረምት ከበጋ መንገድ ደርሷል፡፡ በዚህ ወቅት (2019) የሃገሪቱ የመንገድ አውታር (URRAP & Municipalities) 144,027.8 ኪ.ሜ የደረሰ ሲሆን የአገሪቱ አማካይ የመንገድ አውታር ዕድገትም 8% በዓመት ነበር፡፡

የመንገድ ልማት ተግዳሮቶች

ባለፉት አሥር አመታት 83,780 ኪ.ሜ ተጨማሪ መንገድ በመገንባት በሀገሪቱ ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ጠቅላላ ርዝመት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 53,997 ኪ.ሜ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 137,777 ኪ.ሜ ማድረስ መቻሉን የኢፌዲሪ ፕላን ኮሚሽን ሪፖርት ያሳያል፡፡ ሴክተሩ የሚከተሉት ተግዳሮቶች ነበሩበት፡፡ እነሱም

- ኢትዮጵያ ከ80% በላይ በገጠር የሚኖር ህዝብ ያላት በመሆኑና ከዳሎል እስከ ራስ ዳሸን መካከል የሚገኝ የህዝብ አስፋፈርና የመልክዐ ምድር አቀማመጥ በመንገድ ማዳረስ ስራ ላይ በዕውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በገንዘብም ሆነ በጊዜ ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል፣
- የአስፈፃሚ አካላት እና የግል ሴክተሩ ተሳታፊዎች የመፈፀም ብቃት ችግር እና የክህሎት ክፍተት መኖር፣
- የበጀት እጥረት ልምድ ያላቸው ባለሞያዎች ከስራቸው መልቀቅ በተለይም ከአስፈፃሚ ድርጅቶች፤

- የመንገድ ሴክተሩን በስልጠና የሚደግፉ የትምህርት ተቋማት እና የስልጠና ማዕከላት አለመኖር፣
- በመንገድ ሴክተር የውጭ ስራ ተቋራጮች ተፅእኖ ከፍተኛ መሆን እና የሀገር ውስጥ የስራ ተቋራጮች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፣
- የመንገድ ልማት አገር አቋራጭ ድንበር ተሻጋሪ በመሆኑ የመንገድ ወሰን ማስከበር የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በከፍተኛ ሁኔታ ማጓተት፣

በመንገድ መሠረተ ልማት የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አቅጣጫዎች

የትራንስፖርት አግልግሎት ፍላጎት መነሻ የሚያደርገው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ በቱሪዝም፣ በግብርናና፣ ኢንዱስትሪ ወዘተ ዘርፎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ነው። በሌላ በኩል የመንገድ አውታር በትክክለኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲደገፍ የምርት ዋጋን ይቀንሳል፤ አቅርቦትን ይጨምራል፤ ወጪን ያስተካክላል። ይህ ደግሞ ለድህነት ቅነሳ እንዲሁም ዘላቂ እና አካታች ልማትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። የመንገድ አውታር መስፋት የስራ እድል ለመፍጠር እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ አይተኬ ሚና ይጫወታል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሀገር ደረጃ ለማሳካት የወጠናቸውን ግቦች ለማሳካት በመንገድ ዘርፍ የሚከተሉትን አምስት አቅጣጫዎች ተፈፃሚ ለማድረግ ይሰራል።

ፍትሀዊ የመንገድ ስርጭት

የመንገድ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ‘ድሃ-ተኮር’ (pro-poor) ወይም ሚዛናዊ እና አካታች ሀገራዊ እድገትን እውን ለማድረግ በተቀናጀ መንገድ ይፈጸማል። በዚህም የመንገድ ልማት ፕሮግራሞቻችን በልማት ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎችን ታሳቢ ያደረጉና ከድህነት ቅነሳ እቅዶቻችን ጋር የተቀናጁ ይሆናሉ። የመንገድ አውታር ስርጭት የግብርና እና ኢንደስትሪ የፊት እና የኋላ ትስስርን (Backward and forward linkage) ለማጠናከር በሚያስችል መልኩ ይተገበራል። በ2010 የመንገድ አማካይ ጥግግት 125 ኪ.ሜ /1000ኪ.ሜ2 ሲሆን የዓለም አማካይ የመንገድ ጥግግት 944 ኪ.ሜ /1000 ኪ.ሜ2 ነው። በመሆኑም ፓርቲያችን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በአጭር ጊዜ የአፍሪካን አማካይ ጥግግት (204 ኪ.ሜ /1000 ኪ.ሜ2) ለማድረስ ይሰራል።

የመንገድ ልማት ለከተሞች መስፋፋት

ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች አንዱ ፈጣን የከተሞች እድገት እና የህዝብ ብዛት ነው። ይህ ክስተት በከተሞች አካባቢ ውስብስብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ችግሮችን ያስከትላል። ያልተመጣጠነ የህዝብ እድገት እና ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰት ለከተሜ ድህነት በር ይከፍታል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የነባር ከተሞችን ውስብስብ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቀነስና የገጠር ከተማ ፍልሰትን ለመገደብ ፈጣን እና ፍትሀዊ የመንገድ መሰረተ ልማት ስራ ያካሂዳል። የመንገድ መሰረተ ልማት ፕሮግራሞች ለአዳዲስ ከተሞች መፈጠርና የተበታተነ አሰፋፈርን በማሰባሰብ የዜጎችን ኑሮ ቀላል እና ምቹ ለማድረግ ይቀረፃሉ።

የመንገድ ሃብት ጥገናና ጥበቃ

የመንገድ ሃብት ዘላቂነት የሚረጋገጠው ተገቢ የመንገድ ጥገናና ጥበቃ ስልት ሲዘረጋ ነው። ጤናማ እና ምቹ የመንገድ ይዞታ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አይተኬ ሚና አለው። ምቹ የመንገድ ይዞታ ምርት ወደ ገበያ የሚቀርብበትን ጊዜ በመቀነስ፣ የስራ ዕድሎች በመፍጠር፣ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራትን ለማሳደግ ወዘተ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። የመንገድ ጥገናና ጥበቃ መንገዶች ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግና ህልውናቸውን ከሚፈታተነን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አደጋ መጠበቅ እንዲሁም ቅድመ አደጋ መከላከልን ያጠቃልላል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የመንገድ ህግ (ROAD ACT) ተግባራዊ ያደርጋል። ጠንካራና ቀልጣፋ የመንገድ ጥገና ስርአት የሚያግዝ የመንግስት እና የግል ሴክተር ጥምረት (PPP) እንዲኖር ያደርጋል። በሃገራችን በመንገድ ልማት ላይ የተሰማሩ የፌደራል እና የክልል ተቋማት የተቋቋሙባቸው አዋጆች፣ የአሰራር ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የጥራት እና የቴክኒክ መለኪያዎች እንዲከለሱ ይደረጋል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ‘የመንገድ ህግ’ ወይም ‘ROAD ACT’ በኢትዮጵያ ተግባራዊ በማድረግ የሀገራችን መንገዶች ምቹ አስተማማኝ እንዲሆኑ ብሎም ለሀገራችን አጠቃላይ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋል። ተግባራዊ የሚደረገው የመንገድ ህግ የመንገድ ደረጃዎችን፣ የመንገድ ባለቤትነት፣

የፋይናንስ ምንጭ፣ የመንገድ ዓይነትን፣ በመንገድ ዘርፍ ባለድርሻ እና ባለሚና አካላትን ግንኙነት፣ መብት፣ ኃላፊነት እና ግዴታ፣ የክፍያ መንገዶችን ደረጃ እና የክፍያ መጠንን ወዘተ የዓለም አቀፍ ልምድን በጠበቀ ሁኔታ ያካትታል። የመንገድ ህጉ የሀገራችንን የመንገድ ሽፋን ለማሳደግ፣ የመንገዶችን ጥገና ወጪ ቆጣቢ እና በፍጥነት ለማከናወን፣ የሀገራችንን የትራንስፖርት ዘርፍ ለማዘመን ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

የሀገር ውስጥ አቅምን መገንባት

የሃገራዊ ልማት ዘላቂነት የሚረጋገጠው የሀገር ውስጥ አቅምን አሟጦ በመጠቀም እና ከውጭ ጥገኝነት በሂደት መላቀቅ ስንችል ነው ብሎ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ያምናል። ይህ አጠቃላይ የልማት ፍልስፍና በመንገድ ዘርፍ ላይ ቀጥተኛ አንድምታ አለው። ባለፉት ሁለት አስርት-አመታት በሃገራችን የመንገድ ልማት 162.8 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው 675 ፕሮጀክቶች በሃገር በቀል ስራ ተቋራጮች የተገነቡ ሲሆኑ 172 ፕሮጀክቶች ደግሞ በ171.9 ቢሊዮን ብር የኮንስትራክሽን ዋጋ በውጭ ኮንትራክተሮች ተገንብተዋል። በዚህም ተቀራራቢ በሆነ ወጭ አራት እጥፍ ቁጥር ያላቸው ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተገንብተዋል። በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የመንገድ ፕሮጀክቶች ወጪ 84% በኢትዮጵያ መንግስት የተሸፈነ ሲሆን ቀሪው 16% ደግሞ በውጭ የልማት አጋሮች ተሸፍኗል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የግሉ ዘርፍ በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ እንዲሳተፍ በማበታታት የአዳዲስ መንገዶች ግንባታ፣ የደረጃ ማሳደግ ስራ፣ የመንገድ ጥገና እና ሌሎች ተያያዥ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥ ኮንትራክተሮች እንዲሰሩ ያደርጋል። ይህ የፖሊሲ አቅጣጫ ሀገራችን ለመንገድ ዘርፍ በየአመቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በመቀነስ በአብይ ኢኮኖሚው (Macro economy) ላይ የሚታየውን መፋለስ በተወሰነ ደረጃ መቀነስ የሚያስችል አቅጣጫ ይከተላል። የሀገር ውስጥ የስራ ተቋራጮችን ለማሳደግ የምንከተለው አቅጣጫ ቢያንስ በአፍሪካ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ አገር በቀል የስራ ተቋራጮችን በአጭር ጊዜ ለማፍራት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ይህ የፖሊሲ አቅጣጫ በሀገራችን የተንሰራፋውን የስራ አጥነት ለመቀነስ እና ለወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። አስገዳጅ የሰብ ኮንትራክተር (subcontractor) መመሪያዎችን በመተግበር ከውጭ የስራ ተቋራጮች ልምድና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር ይደረጋል።

ለአካባቢ ተፅዕኖ ትኩረት መስጠት

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የመንገድ መሰረት ልማት ፕሮግራሞች ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተሳሰሩ እና የተቀናጁ እንዲሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ባለፉት ጊዜያት የተከናወኑ የመንገድ እና ጥገና ግንባታ ፕሮጀክቶች በነበራቸው ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር ምክንያት በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳይ ደርሷል። የመንገድ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚፈጥሩትን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ በሀገራችን የሚካሄዱ የመንገድ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች በተለይም ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የፌደራል መንገዶች ተገቢ የአካባቢ ተፅዕኖና የአዋጭነት ጥናት እንዲሰራላቸው ይደረጋል።

ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ባላቸው የገጠር መንደሮችና ከተሞች እንዲሁም ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባሉባቸው አካባቢዎች የሚገነቡ መንገዶች ከፍተኛ ጥንቃቄ እና የጥራት ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ብሄራዊ የመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎችን በተባ ዲዛይን (optimized design)፣ የመሬቱን አገልግሎት ያማከለ የግንባታ ስርአት (land use oriented construction) የተናበበ የልማት ዕቅድ (integrated development plan) እንዲኖር የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና ተግባራዊ በማድረግ የመንገድ መሰረተ ልማት ከአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል።

2 ትራንስፖርት

የትራንስፖርት አገልግሎት የአንድ ሀገር ማህበረ ኢኮኖሚ እና ፖለቲካ እንቅስቃሴ የደም ስር ነው። የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶችን እንዲሁም የህዝብን እንቅስቃሴ ለማሳለጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በዓይነትና በብዛት ሰፊ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖር ምርትንና ምርታማነትን ለማሳለጥ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ንግድን ለማሳደግ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ የምርት ዋጋን ለማረጋጋት፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ወዘተ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። መንገድ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የባህል መስተጋብር ለመፍጠር በዚህም ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው።

በሀገራችን የመንገድ፣ የአየር፣ የውሀ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎቶች የሚሰሰጡ ሲሆን የመንገድ ትራንስፖርት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ከ95 በመቶ በላይ የሀገር ውስጥ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚስተናገደው በመንገድ ትራንስፖርት ነው። የህዝብ ትራንስፖርት ከመንገድ ትራንስፖርት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን ከህዝብ ብዛት መጨመር ጋር ተያያዞ በየአመቱ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመር ይገኛል።

በሀገራችን የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ የባቡር መስመር ርዝመት 902 ኪ.ሜ ብቻ መሆኑ ሴክተሩ ምን ያክል ትኩረት እንደተነፈገው ያመለክታል። የባቡር ትራንስፖርት በህዝብ እና በእቃ ማጓጓዝ የሚሰጠው አገልግሎት እጅግ ዝቅተኛ ነው። በሀገራችን ብቸኛ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ያላት ከተማ አዲስ አበባ ስትሆን 34 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው መስመር አላት። የአየር ትራንስፖርት ሶስተኛው አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ሲሆን፣ ይህም ዘርፍ እንደሌሎቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፎች ሁሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በኢትዮጵያ ውስጥ 22 የአየር ትራንስፖርት መዳረሻዎች ያሉ ሲሆን ይህ ምጣኔ ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት እና የህዝብ ብዛት አንጻር እጅግ አናሳ ነው፡

የሀገራችን የትራንስፖርት አገልግሎት በርካታ የፖሊሲ፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የሰው ኃይል ወዘተ ውስንነቶች ያሉበት ሲሆን የህዝብ ትራንስፖርት የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም፣ የትራንስፖርት ስምሪት እና ማኔጅመንት ስርዓት ደካማ መሆን፣ በገጠርና በከተማ የሚስተዋሉ የተደራሽነት ክፍተቶች፣ የግል ባለሀብቱ የሚበረታታበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት አለመስፋፋት እና አቅርቦቱና ድርሻው አነስተኛ መሆን፣ የትራንስፖርት መለዋወጫ ግብዓቶች እጥረት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በሀገራችን ያለውን ከፍተኛ የትራንስፖርት እጥረት ለመቅረፍ፣ የህዝብ እና የእቃ ማጓጓዣ አገልግሎትን ለማሳደግ፣ ዘርፉ ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲወጣ የሚከተሉትን ግቦች ለማሳካት ጥረት ይደረጋል፤

1. የትራንስፖርት አገልግሎትን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ የመንገድ፣ የባቡር እና የአየር ትራንስፖርት መሰረተ ልማት አውታሮች በስፋት ይገነባሉ፣
2. በፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ ካለው የሀገራችን ህዝብ ብዛት አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ የትራንስፖርት መሰረተ ልማት አውታር ይዘረጋል፤ በተለይም በከተሞች አካባቢ ያለውን ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ ዘመናዊ እና አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፣
3. የግሉ ዘርፍ በትራንስፖርት ዘርፍ ግንባታ እና አቅርቦት ላይ እንዲሳተፍ ማበረታታቻና ድጋፍ ይሰጣል፣
4. በሀገር አቀፍ ደረጃ የትራንስፖርት መሰረተ ልማት አውታር ስርጭት እና አገልግሎት ፍትሀዊ እንዲሆን ልዩ ትኩረት ይደረጋል፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አዋጭነት ባላቸው የጠረፍ እና ዝቅተኛ (Low land) አካባቢዎች የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፣
5. የትራንስፖርት ዘርፍ ከፍተኛ የስራ እድል መፍጠር ይችል ዘንድ ከስራ ፈጠራ ጋር የተቀናጁ ፕሮግራሞች ይዘረጋሉ፣
6. በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚሞተውን ህዝብ ቁጥር በ2012 ከነበረበት በ10000 ተሽከርካሪ 34 ሞት ወደ 20 ሞት መቀነስ። ይህንን ግብ ለማሳካት ልዩ ልዩ ደንቦች እና መመሪያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት ማሳደግ፣ የመንገድ ዲዛይን እና ግንባታ ጥራት ማሳደግ፣ የአሽከርካሪዎች የሙያ ብቃትና ሥነምግባር ማሳደግ እና ሌሎችም ይገኙበታል፣

3 የማዕድን ሀብት ልማት

እስካሁን በማዕድን ዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች በሀገራችን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው በርካታ የማዕድን ዓይነቶች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተከማችተው እንደሚገኙ ያመለክታሉ። ከእነዚህም ውስጥ ብረት ነክ የሆኑ (ወርቅ፣ ታንተለም፣ ፕላቲኒየም፣ ኒኬል፣ መዳብ፣ ሊድ፣ ዚንክ ወዘተ)፣ ጌጠኛ የከበሩ ማዕድናት (ሩቢ፣ ሳፋየር፣ ኢመራልድ፣ ኦፓል፣ ጋርኔት ወዘተ) የኢንዱስትሪ ማዕድናት(ሶዳ፣ ፎስፌት፣ፖታሽ፣ ቤንቶናይት፣ ዳያቶማይት፣ ካኦሊን፣ የኖራ ድንጋይ፣ ጂፕሰም፣ ኳርትዝ ወዘተ)፣ ጌጠኛ የግንባታ ማዕድናት (እምነ በረድ፣ ግራናይት፣ ላይም ስቶን፣ ወዘተ)፣ የተፈጥሮ የነዳጅ

ማዕድናት (የነዳጅ ዘይት፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ የድንጋይ ከሰል ወዘተ) እና በርካታ የግንባታ ማዕድናት (ባዛልት፣ አሸዋ፣ የሸክላ ዐፈር፣ ወዘተ) ተጠቃሾች ናቸው። ነገር ግን ከእነዚህ መካከል እስካሁን መልማት የቻለው በጣም ጥቂት ነው። ውስን የሆነው የምርት መጠናችንም ቢሆን ጥሬ ዕቃ ከማውጣት በዘለለ እሴት ጨምሮ ወደ ተለያዩ ምርቶች መቀየር ላይ ረጅም ርቀት መሄድ አልተቻለም። ለዚያውም በአነስተኛ ደረጃ እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ በሚያደርስ መልኩ። በመሆኑም ሀገሪቱም ሆነ ህዝቦቿ ከተፈጥሮው ፀጋ የሚገባውን ያህል ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም።

ለዘርፉ ልማት ዝቅተኛ መሆን ምክንያት ከሆኑት መካከል አስተማማኝ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ አለመኖር፣ የቴክኖሎጂና የሰለጠነ የሰው ኃይል ግብአት ዝቅተኛ መሆን፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አናሳ መሆን፣ የአሰራር ስርዓቱ አለመዘመን እና ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ዝቅተኛ መሆን ተጠቃሾች ናቸው። ይህም ያለንን ሀብት በአግባቡ አጥንተን ማወቅ እንዳንችልና የተለዩትንም ቢሆን በብቃት ማምረት እንዳንችል አድርጎናል።

ለዘመናት ባነበርነውና አሁን እየተከተልን ባለው አሰራር ከቀጠልን የሀገራችንን አጠቃላይ እድገትና የህዝባችንን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አንችልም። ከዚህም ባሻገር በኋላ ቀር አመራረት እና ልል በሆነ ክትትል ሳቢያ እየተባባሰ የመጣውን የአካባቢ ብክለትና የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት መቀነስ አንችልም።

በመሆኑም የማዕድን ሀብታችንን በተመለከተ

- ያለንን እምቅ የማዕድን ሀብት በጥናት መለየት
- የማዕድን ሀብትን የማልማት እሴት በማሳደግ የዘርፉ ኢንዱስትሪ ልማት እንዲጎለብት ማድረግ እና ለሌሎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ሰፊ ግብአት እንዲያቀርብ ማስቻል
- የማዕድን ሀብት ልማት ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ያለውን አስተዋፅዖ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የማዕድን ምርት ተኪነት ማሳደግ
- በማዕድን ሀብት ጥናት፣ ምርምር እና ምርት ላይ የግሉ ዘርፍ ግንባር ቀደም ተሳታፊነት እነዲጎለብት ምቹ ሁኔታ መፍጠር
- የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማጎልበት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ስምሪትን በማሳደግ እና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት የማእድን ሀብት ጥናት፣ ምርምር እና ልማት ብቃትን ማሳደግ
- ከማዕድን ሀብት ልማት ህበረተሰባችን በየደረጃው ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የማዕድን ሀብት ጥናትን በተመለከተ

ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት በሀገራችን የሚገኘው የማዕድን ሀብት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እና ብቁ የሰው ኃይል በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ በዝርዝር እንዲለይ ያደርጋል። ለዚህም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሚና እንዲጎለብት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በአጭር ጊዜ ውስጥም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ እና ክህሎት ያላቸው አካላት ዓለም ዐቀፍ የሙያ አገልግሎት ግዢ በመፈፀም በሂደት ደግሞ የቴክኖሎጂ እና የክህሎት ሽግግር እንዲፈጠር በማድረግ የማዕድን ሀብት ልየታውን ያሻሽላል። በዚህም በሀገራችን እድገት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የማዕድን ሀብቶች እንዲለዩ እና በዳሰሳ ጥናት ደረጃ የተለዩት ደግሞ ዝርዝር ምርመራ ተደርጎባቸው በፍጥነት ወደ ልማት እንዲገቡ ይደረጋል።

በዚህ ረገድ በነዳጅ ሀብታችን ዙሪያ ያሉ ብዥታዎችና አሉባልታዎች ጠርተው በሳይንሳዊ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ የጥናት መረጃ የማደራጀትና የሀገር ደህንነትን ታሳቢ ያደረገ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ይደረጋል፡፤

የማዕድን ሀብት ልማትን በተመለከተ

የማዕድን ሀብት ልማቱ በዋናነት በግሉ ዘርፍ እንዲከናወን በማድረግ ህዝቡ ብሎም ሀገራችን ከልማቱ መጠቀም የሚገባንን ያህል (Optimal benefit) ተጠቃሚ መሆን እንድንችል የህግ ማዕቀፍ እና ዝርዝር የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

አሁን ያለውን በአብዛኛው ጥሬ ምርቱን ወደ ውጭ የመላክ አሰራርን በማሻሻል የማዕድን ሀብታችን በኢንዱስትሪዎች ፕሮሰስ ተደርጎ ውጤቶቹ ለሌሎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ግብዓት እንዲሆን ማድረግ እና ፕሮሰስ የሆኑ የማዕድን ውጤቶች በስፋት ወደ ውጭ የሚላኩበትን አሰራር ይፈጥራል።

ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በተመለከተ

ማዕድን ሀብት ልማት በባህሪው በሃብት ግኝት ብቻ በአካባቢው ያለ ህብረተሰብ ወይም የአካባቢው አስተዳደር ወይም የሀገሪቱ መንግስት ቁጭ ብሎ ጥቅም የመሰብሰብን ወይም ኪራይ የመሰብሰብ (rent seeking) ፍላጎትን ስለሚፈጥር በህብረተሰቡ የስራ ባህል እና በሀገሪቱ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ጉዳት ያደርሳል። ከዚህም አልፎ ለተለያዩ ዓይነት ግጭቶች መፈጠር መንስዔ ይሆናል። ስለዚህ እነዚህንና መሰል የጎንዮሽ ጠንቆችን በመከላከል ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ለማጎልበት ሁሉም በየድርሻው ለልማቱ ባበረከቱት አስዋፅዖ መጠን በፍትሃዊነት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ

የማዕድን ሀብት ልማት በተፈጥሮ እና በልማት አካባቢ በሚኖሩ ህዝቦች ብሎም በሀገር ደረጃ ሰፊ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ይታወቃል። እስካሁንም በተጭባጭ በርካታ ጉዳቶችን በማስከተል ላይ ይገኛል። በመሆኑም ከማዕድን ልማቱ በዘላቂነት መጠቀም እንዲቻል ፓርቲያችን አሁን እየደረሱ ያሉ የአካባቢ ብክለቶችን ለማከም እና በቀጣይ በሚኖሩ ሰፊ የማእድን ልማቶች ሳቢያ ሊመጡ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል አጠቃላይ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ አዘጋጅቷል። ከዚህም ባሻገር ለማዕድን ሀብት ልማቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ልማቱ ከማዕድን ሀብት ልየታ ጥናት ጀምሮ ሙሉ የምርት፣ የሽያጭና የፍጆታ ሂደቱ ሊፈጠሩ የሚችሉ ተፅዕኖዎች አስቀድመው የሚለዩበትንና ቅድመ መከላከል የሚደረግበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

4 የኢነርጂ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

የኢነርጂ ሀብት ልማትና አቅርቦት ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት መሰረት ከመሆኑም ባሻገር የሀገርን ደህንነትና ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ የተደረጉ ጥናቶች ሀገራችን ሰፊ የኢነርጂ ሀብቶች እንዳሏት ያመለክታል። በጥናት ደረጃ ያለውን የነዳጅ ዘይት ሀብታችንን እና አነስተኛ የሆኑትን የጂኦተርማል፣ የንፋስ እና የፀሃይ ሀይል ሀብት ትተን የውሀ ሀብታችንን ተጠቅመን ልናመርት የምንችለውን የሃይድሮ ፖወር ሀብት ብቻ ብናይ 45000 (አርባ አምስት ሺህ) ሜጋ ዋት የማምረት አቅም እንዳለን እንረዳለን። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እያመረትን ያለውን የሀይል መጠን ስንፈትሽ ልዩነቱ የተየለሌ ሆኖ እናገኘዋለን። በአሁኑ ወቅት እያመረትን ያለነው ካለን እምቅ ሀብት ከ 5 በመቶ በታች ነው።

የሃይል አጠቃቀማችንን ስንፈትሽ ደግሞ 90 በመቶ የሚሆነው የሀይል ምንጫችን ከባህላዊ የሃይል ምንጭ (እንጨት፣ ከሰል እና የመሳሰሉት) የሚገኝ ሆኖ እናገኘዋል። ከዘመናዊ የሀይል ምንጭ (የነዳጅ ምርቶች እና የኤሌክትሪክ ሀይል) የምንጠቀመው ከ 10 በመቶ በታች ነው። ከዚህም ባሻገር አማካይ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ሀይል ፍጆታችን ከ100 ኪሎ ዋት ሰዓት (በዓመት) በታች ሆኖ እናገኘዋለን። የዚህ ዓይነቱ የሀይል አጠቃቀም ዓይነትና ደረጃ በሁሉም መስፈርቶች ሲመዘን እጅግ አስከፊ ደረጃ ላይ መገኘታችንን ገላጭ ነው። በመሆኑም አብዛኛው የህብረተሳባችን ክፍል በዘመናዊ የሀይል አቅርቦት እጦት ሳቢያ ለከፋ የጤና ችግር እንዲሁም ለልማት ምቹ ሁኔታ ባለመፈጠሩ ሳቢያ በአስከፊ ድህነት ውስጥ እንዲኖር ተገዷል።

አጠቃላይ የኢነርጂ ሀብት በማልማትና ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አበረታች ጅምሮች ቢታዩም ከህዝባችን ፍላጎት እና ዓለም ከደረሰበት የዘርፉ ልማት አንፃር ሲታይ ግን ከዝቅተኛው ደረጃ ፈቀቅ አለማለታችንን እንገነዘባለን።

በመሆኑም ካለንበት አስከፊ ደረጃ ተስፈንጥሮ በመውጣት የህዝባችንን ኑሮ ለማሻሻል እንዲሁም አስተማማኝ የሀገር ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ውጤታማ የኢነርጂ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ያለንበትን ተጭባጭ ሁኔታ ገምግሞ በቀጣይ አምስት ዓመታት የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እና የሀገራችንን ፈጣን እድገት ለማሳለጥ የኢነርጂ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ፖሊሲ ቀርጿል።

4.1.1 በኢነርጂ ሴክተሩ ትኩረት የሚሹ አንገብጋቢ ጉዳዮች

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት በኢነርጂ ልማትና አጠቃቀም ረገድ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ትኩረት የሚሹ እና አንገብጋቢ ጉዳዮች የሚከተሉት እንደሆኑ ለይቷል።

- ለበርካታ ዓመታት ባህላዊ የኢነርጂ ሀብት በሰፊው በመጠቀማችን ሳቢያ እየደረሰ ያለውን

የተፈጥሮ ሀብት መራቆትና የህዝባችንን የጤና ጉዳት መቀነስ ብሎም ማስወገድ፣

- ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ለህዝብ ጤናማ ኑሮ አስፈላጊ የሆነው ዘመናዊ እና ከብክለት ነፃ የሆነ የኢነርጂ ሀብት በበቂ አምርቶ ማቅረብ፣
- ሀገራችንን ከኢነርጂ ጥገኝነት በማላቀቅ በኢነርጂ ምርት ራሷን እንድትችል ማድረግ፣
- የኢነርጂ ሀብታችንን በስፋት በማምረት እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የሀገራችንን የውጭ ምንዛሪ መሰረት ማስፋት እና ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለውን የኢኮኖሚ ትስስርን ማጠናከር።

አበይት ተግባራት

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በኢነርጂ ሀብት ልማት ረገድ የሚከተሉትን አበይት ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ. የኢነርጂ ሀብት ልማት

ባህላዊ የኢነርጂ ልማትን በተመለከተ

ምንም እንኳ ከባህላዊ ኢነርጂ መጠቀም በአንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ መውጣት ባይቻልም ከሚያስከትለው የተፈጥሮ ሀብት እና የጤና ጉዳት አንፃር በፍጥነት መውጣት ያስፈልጋል። በመሆኑም ፓርቲያችን ይህን ለማሳካት የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል።

- ዘመናዊ የሀይል ምንጭን በስፋት በማምረት ለሰፊው ህዝባችን በፍትሃዊነት ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣
- ሙሉ በሙሉ ወደ ዘመናዊ የኢነርጂ አጠቃቀም እስከንሸጋገር ድረስ የሚኖረው የባህላዊ ኢነርጂ አጠቃቀም እንዲሻሻል በጥናት፣ ምርምርና ቴክኖሎጂ የታገዘ የኢነርጂ አጠቃቀም ማሻሻያ ስራዎች መስራት፣
- በባህላዊ የኢነርጂ አቅርቦት ላይ የተሰማራው የህዝባችን ክፍል በሚኖረው ፈጣን ሽግግር ተጎጂ እንዳይሆን ሰፊ የስራ ዕድልና አማራጭ የገቢ ማግኛ ዘዴዎች እንዲዘርጉ ማድረግ፣
- ከዘመናዊ ቴክኖጂ ማስፈፋት ጎን ለጎንም በባህላዊ ኢነርጂ አጠቃቀም የተጎዳው የተፈጥሮ ሀብት ፈጥኖ እንዲያገግም እንክብካቤ ማድረግ።

ዘመናዊ የኢነርጂ ልማትን በተመለከተ

የዘመናዊ ኢነርጂ ልማትና አቅርቦት ውጤታማ እንዲሆን የሀብት ክምችት መኖር፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል መኖር፣ የጥናትና ምርምር አቅም መጎልበት፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦት መኖር እንዲሁም ኢንቨስት ሊደረግ የሚችል ካፒታል መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ፓርቲያችን

- ተጨማሪ የዘመናዊ ኢነርጂ ሀብቶች በጥናትና ምርምር እንዲለዩ እና የተለዩት ደግሞ ውጤታማ እንዲሆኑ የኢነርጂ ጥናት፣ ምርምርና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዘመናዊ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣
- በኢነርጂ ሀብት ጥናት፣ ምርምር፣ ልማትና ስርጭት ረገድ የግሉ ዘርፍ በስፋት ተሳታፊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
- የኢነርጂ ልማትና ስርጭት ለዜጎች ሰፊ የስራ ዕድልና የገቢ ማግኛ አማራጭ እንዲሆን ዝርዝር ማስፈፀሚያ ህጎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
- የዘመናዊ ኢነርጂ ሀብት ወደ ጎረቤት ሀገር በስፋት እንዲሰራጭ በማድረግ ሰፊ የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲኖር፣ የኢኮኖሚ ትስስራችን እንዲጠናከር፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት ሚዛን እንዲጠብቅ ብሎም የሀገራችን ጂኦ-ፖለቲካዊ ሚና እንዲጎለብት ያደርጋል፣
- ለዘመናዊ ኢነርጂ ልማትና ስርጭት የሚያስፈልገው ፋይናንስ በጣም ከፍተኛ ቢሆንም ከአበዳሪ አካላት ፋይናንስ ማሰባሰብ በሉዓላዊነታችንና በደህንነታችን የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢነርጂ ልማት ፈንድ እንዲቋቋምና የኢነርጂ ልማታችን በራስ የፋይናንስ አቅም እንዲለማ ያደርጋል።

አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች ልማትን በተመለከተ

ከውሀ ሀብት የሚገኘው የኢነርጂ ሀይል ዋናው የዘመናዊ ኢነርጂ ምንጫችን ሲሆን ከሌሎች አማራጭ ምንጮች (ጂኦተርማል፣ ፀሀይ፣ ነፋስ፣ ኒውክሊየር፣ ወዘተ) በተጨማሪነት እንዲለሙ ጎን ለጎን ይሰራል። በተለይ ደግሞ ከብክለት ነፃ የሆኑ ታዳሽ የኢነርጂ ሀብቶች (የፀሀይ፣ የነፋስ እና ሌሎች) በጥናት እንዲለዩ እና የተለዩትም በብቃት እንዲለሙ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

ለ. የኢነርጂ አቅርቦትን በተመለከተ

የመኖሪያ ቤት የአነርጂ አቅርቦት

የኢነርጂ ሀብት ልማት በፍትሀዊነት ለዜጎቻችን ተደራሽ እንዲሆን ለማስቻል የዜጎችን የአሰፋፈር ሁኔታን፣ የኢኮኖሚ አቅምን፣ የፍጆታ መጠንና የአጠቃቀም ብቃትን መሰረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት የኢነርጂ አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር የአፈፃፀም ህጎች ይዘጋጃሉ።

የትራንስፖርት ሴክተር የኢነርጂ አቅርቦት

እስካሁን ባለው ሂደት የትራንስፖርት ዘርፉ በዋናነት የነዳጅ ምርቶችን የሚጠቀም በመሆኑ የአየር ብክለትን በማባባስ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማስከተሉም በላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቅ በመሆኑ ኢኮኖሚው ላይ ላይ ያለው ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። በመሆኑም ፓርቲያችን መሰል ችግሮችን ለመቅረፍና ውጤታማ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ይከተላል።

- ንፁህ የሀይል ምንጮችን የሚጠቀሙ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች (የኤሌክትሪክ ባቡር፣ መኪኖች ወዘተ) እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
- ንፁህ የሀይል ምንጮች በስፋት ጥቅም ላይ እስኪውሉ በሀገር ውስጥ ከአግሮ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ የሀይል አቅርቦቶች (ኢታኖል) እንዲስፋፋ እና ከተክሎች የሚገኙ አዳዲስ አማራጭ የሀይል ምንጮች እንዲለሙ ይደረጋል፣
- በርካታ ህዝብ ሊያጓጉዙ የሚችሉና ብቃት ያላቸው የህዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች እንዲስፋፉ በማድረግ በበርካታ በግልና በአነስተኛ የህዝብ ተሽከርካሪዎች አማካይነት ፍጆታ ላይ የሚውለውን የነዳጅ መጠን እንዲሁም የብክለት መጠን እንዲቀንስ ይደረጋል፣
- በአሮጌ እና ብልሽት ባላቸው ተሽከርካሪዎች ሳቢያ የሚደርሰውን የነዳጅ ብክነትና የብክለት መጠን ለመቀነስ ጥብቅ ክትትል የሚደረግበትና ተገቢው ማሻሻያ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- እስካሁን ለትራንስፖርት ዘርፍ ለሚውለው የነዳጅ ፍጆታ የሚደረገው ድጎማ ፍትሃዊነትን የተከተለ እንዳልነበር ይታውቃል። አንፃራዊ የኑሮ ደረጃው የተሻለ ሆነው ዜጋ ለሚያሽከረክረው የግል ተሽከርካሪ ዝቅተኛ ገቢ ካለው ዜጋ ላይ ከተሰበሰበው ግብር ድጎማ ሲደረግ ተስተውሏል። አሁንም ቢሆን መሰል ግድፈቶችን ማስቀረት የሚችል የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም። በመሆኑም ፓርቲያችን ፍትሀዊ የሀብት አጠቃቀምን የሚያሰፍን የትራንስፖርት ዘርፍ የኢነርጂ አቅርቦትና ፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የኢነርጂ አቅርቦት

የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተው ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ፓርቲያችን ለዘርፉ አስተማማኝ የኢነርጂ አቅርቦት እንዲኖር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። ለዚህም በመንግስት ደረጃ የሚኖረው ዘመናዊ የኢነርጂ ሀይል አቅርቦት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች አማራጮች ማለትም የግሉ ዘርፍ ታዳሽ የኢነርጂ ሀብቶችን (ፀሀይ፣ ነፋስ ወዘተ) እንዲሁም በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰልና ሌሎች የሀይል አማራጮችን አልምተው የሚያሰራጩበት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

ምዕራፍ አራት

ጤናማ እና ደስተኛ ማህበረሰብ

1. ትምህርት

የአንድን ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና ከሚወስኑ ጉዳዮች መሀል የሰለጠነ የሰው ኃይል ዋነኛው ነው። ከዚህም በተጨማሪም ሀገራችንን ከተበተቧት ዘርፈ-ብዙ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች መላቀቅ የምትችለው በየዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲኖራት እንደሆነ እሙን ነው። የሰለጠነ የሰው ኃይል ያላቸው ሀገራት የተፈጥሮ ሀብታቸው እጅግ ውስን ቢሆን እንኳ የተሻለ ዕድገት ለማስመዝገብ እምብዛም አይቸገሩም። ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንም እንኳ አያሌ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሯትም እነዚህን ሀብቶች በአግባቡ ለመጠቀም የካፒታል እጥረትና በየዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር ትልቅ እንቅፋት ሆኖባት ቆይቷል።

ባለፉት በርካታ ዓመታት የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ዒላማ ያደረጉ ከቅድመ-መደበኛ እስከ ከፍተኛ ያሉ በርካታ የትምህርት ተቋማት ተከፍተዋል። በአንዳንድ ጥናቶች መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ 99.9 በመቶ ደርሷል። ይህም እጅግ ሊበረታታ የሚገባው እመርታ እንደሆነ ፓርቲያችን ያምናል። ይሁን እንጂ የትምህርት ደረጃው ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ይህ የትምህርት ተሳትፎ ቁልቁል ሲወርድ ይታያል።

በመደበኛነት ከተመዘገቡት ተማሪዎች 15 በመቶ የሚጠጉት 5ኛ ክፍል ከመድረሳቸው በፊት ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። እስከ 8ኛ ክፍል የሚደርሱት ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 54 በመቶ ብቻ እንደሆነ የዩኒሴፍ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህም በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ከነበረባቸው መቶ ተማሪዎች መሀል 46 ተማሪዎች አይገኙም ማለት ነው። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አስመልክቶ ያለው ደግሞ ከዚህም የባሰ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርታቸውን መከታተል ከሚገባቸው ዜጎቻችን መሀል የትምህርት እድል ያገኙት 25 በመቶ ብቻ ናቸው። በዚህ የትምህርት ክልል ውስጥ መማር ከሚገባቸው ዜጎቻችን መሀል 75 በመቶ የሚሆኑት ከትምህርት ውጪ ሆነው ሳለ እድገትን ማሰብ አይቻልም።

ከትምህርት እድል ውጪ የሆኑት አብዛኞቹ ዜጎቻችን ደግሞ የሚገኙት አርብቶ አደርና ግጭቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ነው። ይህም በትምህርቱ ዘርፍ ያለው መጠነኛ እድገት እንኳ በማህበረሰቦች መሀል የተመጣጠነ እንዳይሆን አድርጎታል። ከዚህ በተጨማሪ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ሆነ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የትምህርት ጥራት እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ በርካታ ጥናቶች ያሳያሉ። ፓርቲያችን በተለያዩ አካባቢዎች ባደረጋቸው ምልከታዎችም ሆነ በተለያዩ አካላት በተደረጉ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የሀገራችን የትምህርት ጥራት በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚደረገው ጥረት እጅግ የራቀ ነው። በዩኒሴፍ ጥናት መሰረት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች መሀል 63 በመቶ የሚሆኑት ከክፍል ክፍል ለመዘዋወር የሚያስፈልገውን 50 ከመቶ ውጤት ማግኘት የማይችሉና መሰረታዊ የትምህርት ግቦችን እንኳ ማሳካት ያቃታቸው ናቸው።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው ሁኔታም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የተለየ አይደለም። በመሆኑም ፓርቲያችን በትምህርቱ ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ያምናል። በፓርቲያችን ምልከታ ትምህርትና ስልጠና እንደ ሌሎች የልማት ዘርፎች ሁሉ እንደ አንድ ሴክተር ለብቻው ተነጥሎ መታየት የለበትም። ይልቁንም ትምህርት የአጠቃላይ ሀገር አቀፍ ልማት መሰረት ሆኖ የሚያገለግል ቁልፍ ተግባር እንደሆነ ፓርቲያችን አጽንኦት ይሰጠዋል። ትምህርት እና ስልጠና ለአጠቃላይ የሰው ልጆች ስልጣኔ የተጫወተውን ሚና ከግምት በማስገባት፣ በልማት የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገራትን ሂደት በመመርመርና ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና የተሻለው መንገድ ትምህርት መር ብሔራዊ የልማት ስትራቴጂ እንደሆነ እናምናለን። ይህንን ታሳቢ በማድረግ ትምህርትና ስልጠና ከሌሎች ዘርፎች በተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት አምስት አመታት፣

- ለትምህርት የሚመደበው በጀት እንዲጨምር ይደረጋል፣
- ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚሆኑ ዜጎቻችን መሰረታዊ ችግሮች ተጠንተው እንዲቀረፉና ሁሉም ዜጎች ቢያንስ የ10 ዓመት መሰረታዊ ትምህርት እንዲማሩ የመንግስትና የቤተሰብ ግዴታ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ከትምህርት ተደራሽነት ባሻገር በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ለጥራት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፣
- የትምህርት ተደራሽነት ለሁሉም ማህበረሰቦች በተለይም ግጭት በሚበዛባቸውና አርብቶ አደር በሆኑ አካባቢዎች እኩል ተደራሽ እንዲሆን የተለየ መንገድ ይቀየሳል፣
- ሳይንስ፣ ምህንድስና፣ ቴክኖሎጂ እና ሂሳብ ትምህርቶች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል፣

- የትምህርት ስርዓታችን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነታችንን ከፍ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይቀረጻል፣
- በትምህርት ዘርፍ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ልዩ ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል። በግል ትምህርት ተቋማት ላይ ብቻ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር ብልሹ አሰራር እንዲቀየርና የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ተቋማት የቁጥጥርና ግምገማ ስርዓት ተመሳሳይ እንዲሆን ይደረጋል፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚታዩ የበጀት ብክነቶች፣ ሙስና እና ሌሎች ብልሹ አሰራሮች ጠንካራ የቁጥጥር መንገድ ይዘረጋላቸዋል፣
- ተቋማቱ የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት አቅም የሚያጎለብቱ ከየትኛውም የፖለቲካ ተጽእኖ ነጻ ሆነው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፣
- ከህጻናትና ወጣቶች በተጨማሪ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤና ባህል ግምት ውስጥ ያስገቡ የጎልማሶችን
- ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር በቀጥታ የሚገናኙና አስፈልጎታቸውን መነሻ ያደረጉ የክህሎት ስልጠናዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፣
- ❖ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የማህበረሰባችንን ህብረ-ብሄራዊነት ታሳቢ ያደረገ የየትኛውንም ባህል እና ሀይማኖት ሥርዓት የማይጋፋ የትምህርት ከባቢ እንዲፈጠር ይደረጋል።

2 ጤና

የጤናው ዘርፍ ነባራዊ ሁኔታ

በጤናው ዘርፍ ሊመዘገቡ ከሚገባቸው ውጤቶች (የሞትና ህመም መቀነስ፣ የህይወት ጥራት መጨመር) አንጻር ሲታይ ሀገራችን ያለፉትን ሁለት አስርት አመታት መሻሻሎች አሳይታለች። በዚህም መሰረት የእናቶች ሞት፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት እንዲሁም ጥቅል የመሞት ምጣኔ በመቀነሱ የዜጎች በህይወት የመቆየት ምጣኔ ላይ መሻሻሎች ታይተዋል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ሀገራችን በእነዚህ መለኪያዎች በዓለም ከሚገኙ ሀገራት የከፋ ሁኔታ ላይ የምትገኝ ናት።

በጤናው ዘርፍ የሚጠበቁት ውጤቶች የሀገሪቱ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ነጸብራቅ በመሆናቸው በጤናው ሴክተር በሚደረጉ ማሻሻያዎች ብቻ ለውጥ ለማስመዝገብ አዳጋች መሆኑ ቢታመንም ዘርፉ ከሚጠበቅበት ውጤት አኳያ እንኳ ሲመዘን ሀገራችን ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች፣ የእናቶችና ህጻናት ጤና እክሎች፣ እንዲሁም ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት ዜጎች የሚታመሙበትና የሚሞቱበት ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከጤና ተቋማት ተደራሽነት ጋር ተያይዞ ሰፊ ክፍተት ያለ ሲሆን ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት ውስንነት የጤና ዘርፉን ችግሮች አባብሶታል።

አገልግሎቶቹ ኢ-ፍትሃዊ ተደራሽነት ያላቸው (በከተማና በገጠር፣ በአርሶ አደርና አርብቶ አደር፣ ወ.ዘ.ተ.) ከመሆናቸውም ባለፈ ጥራታቸውን የጠበቁ አይደሉም። ለዚህም እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ የህክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶች አለመሟላት፣ የጤና ባለሙያዎች ሙያ ማሻሻያ ስልጠና እና ማነቃቂያ አለማግኘት፣ መንግስት በጤናው ዘርፍ የሚያወጣው የወጭ ድርሻ አናሳ መሆንና በእርዳታ ላይ ጥገኛ መሆኑ፣ የህክምና አገልግሎት ወጪ መናር፣ የግብዓት አቅርቦቱ ከውጭ በሚገቡ መድሀኒትና ህክምና መሳሪያዎች ላይ ጥገኛ መሆኑ... ወ.ዘ.ተ. ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከዚህም ባለፈ የጤና ፖሊሲያችን ከማህበረሰብ ፍላጎትና ዘመናዊነት አንጻር አለመቀረጹና ከጊዜ ጋር አለመሻሻሉ፣ የጤና መረጃ ስርዓቱ ኋላቀርነት እና በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ፣ የጤና ስርዓቱ እያደገ ለመጣው የህዝብ ቁጥርና ስብጥር መልስ መስጠት በሚያስችል ቁመና አለመደራጀቱ ችግሩ እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል።
ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሀገር እድገትና ሰብዓዊ ልማት የሚመጣው ጤናማ ማህበረሰብ በመፍጠር እንደሆነ ጽኑ እምነት አለው። ከዚህ ጠንካራ እምነት በመነሳት የሃገራችንን የጤና ስርዓት ለማሻሻል የሚያስችሉ የሚከተሉትን ተጨባጭ እርምጃዎችን ይወስዳል።

የጤናው ዘርፍ ግብ

የጤና ዘርፍ ግባችን ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በመስጠት ጤናው የተጠበቀ እና ደስተኛ ማህበረሰብ መፍጠር ነው። የጤና ስርዓታችን ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲኖር፣ ፍትሃዊ ተደራሽ እንዲሆን፣ የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት የሚችል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስጋቶችን የሚቀርፍና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ይደረጋል።

አበይት ተግባራት

በጤናው ዘርፍ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት የሚከተሉት አበይት ተግባራት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፧

ሀ. የጤና ዘርፍ አመራርና አስተዳደር ሪፎርምን በተመለከተ

- በ 1993 (እ.ኤ.አ) ተግባራዊ የሆነው የሀገራችን የጤና ፖሊሲ ዘመኑን በሚዋጅ፣ ቴክኖሎጂን መሰረት ባደረገና በዓለም የላቀ እመርታ ያመጡ ሀገራት የሚከተሏቸውን መርሆችና ተግባራት ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ባገናዘበ መንገድ ይሻሻላል፣
- የጤናው ዘርፍ በፌደራል ስርዓቱ ውስጥ ወጥ በሆነ መንገድ የሚተገበርበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

- የጤና ሴክተሩ ከፖለቲካ ፓርቲ አገልጋይነት ወጥቶ በሙያው የላቀ ደረጃ ላይ በደረሱ ሰዎች እንዲመራ ይደረጋል፣
- በጤናው ዘርፍ ያሉ ኤጀንሲዎችና ማዕከላት ሚናቸውን ማሳደግና ለጤናው ዘርፍ ያላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያድግ ይደረጋል።
- የከተማና የአርብቶ-አደር ጤናን በተለየ ሁኔታ ለመምራትና ለማቀናጀት በሚያስችል መንገድ ሊያግዙ የሚችሉ ኤጀንሲዎች ይቋቋማሉ።

ለ. የጤናው ዘርፍ ፋይናንስን በተመለከተ

- መንግስት በጤናው ዘርፍ ያለው የወጪ ድርሻ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ይሻሻላል። ከዚህ አንጻር በአቡጃ ስምምነት (Abuja Declaration) እና የዓለም ጤና ድርጅትን ምክረ-ሃሳብ መሰረት ያደረገ ለዜጎች የነፍስ ወከፍ ወጭ 86 ዶላር እንዲደርስ ይደረጋል። ይህም ሲሆን ጥቅል የጤና ወጪን ከ GDP አንጻር ከ 5 በመቶ በላይ ማድረስና በዚህ ውስጥ የመንግስትን ድርሻ ከ 50 በ መቶ በላይ ለማድረስ ይሰራል።
- የአገልግሎት ተደራሽነትና ጥራትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተጨማሪ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። ከዚህ አንጻር፣
  - የመሰረተ-ልማት ማሻሻል፣ ኢ-ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማጥበብ፣ ግዙፍ የህክምና መሳሪያዎች መትከል የሚያስችል የጤና-ተቋማት ግንባታና ማስፋፊያን ትኩረት የሚያደርግ የጤና ዘርፍ ካፒታል ፋይናንስ ስትራቴጂ ይተገበራል፣
  - የጤና ባለሙያዎችን ለማበረታታትና የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ የክፍያ ስርዓት (Pay for Performance) ይተገበራል።
- የጤናው ዘርፍ የፋይናንስ ስርዓትን ዘላቂና የተረጋጋ ለማድረግ የሚረዱ ተግባራት ይፈጸማሉ። ከዚህ አንጻር :-
  - የማህበረሰብ-አቀፍ እንዲሁም የማህበራዊ የጤና መድህን ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፣
  - መንግስት ከድህነት ወለል በታች ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን የጤና መድህን ሽፋን (targeted subsidy) አገልግሎት ይሰጣል፣
  - ዐየጤና መድህን ስርዓቱን ለመደጎም ይወጣ የነበረውን የ10 በመቶ ድጎማ (general subsidy) ወደ 15በመቶ በማሳደግ የጤና መድህን ስርዓቱ ዘላቂና የተረጋጋ ይደረጋል።

ሐ. የመድሃኒት፣ ቴክኖሎጂና ሌሎች ግብዓቶችን በተመለከተ

- የመድሃኒት፣ ህክምና መሳሪያና ግብአቶች ምርት በሃገር ውስጥ ለማከናወን የሚያስችሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ ለባለ-ሃብቶች ይሰጣል፣
- በህሙማንና ጤና ተቋማት ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ለሚፈጥሩ የጤና እክሎች (የኩላሊት፣ የልብ፣ የካንሰር ወ.ዘ.ተ. ህመሞች) የግብዓት አቅርቦት መንግስት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፣
- የባህል ህክምናንና አገር-በቀል እውቀቶችን ለማዘመን የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፣
- የምግብ፣ መድሃኒትና ሌሎች ግብዓቶችን ጥራት የማረጋገጥ ተቀዳሚ ተግባር የሚደረግና በቴክኖሎጂ ታግዞ የሚተገበር እንዲሆን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል።

መ. አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ

- የጤና ስርዓቱ የበሽታ መከላከልን መሰረት ያደረገ፣ የማህበረሰቡን ጤና-ነክ ክህሎት (health literacy) በሚያሳድግና የጤናን ማህበራዊ ወሳኞች (social determinants of health) ማዕከል ባደረገ መንገድ ይደራጃል፣
- በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ የበሽታ መከላከልና የፈውስ ህክምና አገልግሎቶች ለማስፋትና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የጤና ተቋማዊ መዋቅር ይዘረጋል። በዚህ ሂደት በጤና ጣቢያና በጤና ኬላ መካከል ያሉ መለስተኛ የጤና ተቋማት ይደራጃሉ፣
- ተደራሽ ባልሆኑ የገጠር እና የአርብቶ-አደር አካባቢዎች የጤና አገልግሎትን ለማዳረስ ተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎት ስርዓት በበቂ ግብዓትና አደረጃጀት እንዲሰጥ ይደረጋል፣

- የመሰረታዊ የጤና አገልግሎቶችን ዓይነት፣ የመስጫ ደረጃ እና ይዘት በማሻሻል የመንግስትን አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት የማስፋት ተግባር ይከናወናል፣
- ጥራቱን የጠበቀ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ የጤና አገልግሎት ስርዓት ይደራጃል።

ሠ. የጤናው ዘርፍ ሰራተኞችንና ባለሙያዎችን በተመለከተ

- የጤና ባለሙያዎችን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ተከታታይ የስራ ላይ ስልጠናዎችና የደረጃ እድገት ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- የጤና ባለሙያዎችንና ሰራተኞችን ለማበረታታት የሚያስችሉ የገንዘብና ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ማበረታቻዎች ይዘረጋሉ። ይህም ስርዓት የስራ አፈጻጸምን፣ የአገልግሎት መስጫ አውዶችን፣ የአገልግሎት ጥራትን ወ.ዘ.ተ. መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣
- የሰው ሀብት ልማት ስርዓቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የአገልግሎት ይዘቶችን ባማከለ መንገድ የሚሰራበት ሂደት ይዘረጋል።

ረ. የጤና መረጃ ስርዓትን በተመለከተ

- የጤና መረጃን የሚያፈልቁ ተቋማት የተሻለ አቅም እንዲኖራቸው በማድረግ በየደረጃው ያሉ የጤና ተቋማት መረጃን ለውሳኔ አሰጣጥ መጠቀም የሚችሉበት አሰራር ይዘረጋል፣
- የጤና ስርዓቱ የሚያመነጨው መረጃ እውነታን መሰረት ያደረገና ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም ስርአት ይፈጠራል፣
- የጤና መረጃ በቴክኖሎጂ የታገዘ ዲጂታል እንዲሆን የሚያስችል ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ይደረጋል፣

ሰ. የማህበረሰብ ተሳትፎን በተመለከተ

- የግል የጤና ተቋማት ሚና እንዲያድግ የሚያስችሉ አሰራሮች ይዘረጋሉ። በዚህ ረገድ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የመንግስትና የግል ተቋማት በትብብርና በቅብብሎሽ መስራት የሚያስችላቸው አሰራር ይዘረጋል፣
- የጤና ሙያ ማህበራት በጤናው ዘርፍ እድገት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ። ከነዚህም መካከል የሙያ ማህበራት በጤና ሙያ ስታንዳርድ ዝግጅት፣ ምዘናና የሙያ ማረጋገጫ የመስጠት ተግባራት ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- በጤናው ዘርፍ የበጎ-ፈቃደኞች፣ ተጽእኖ ፈጣሪ የማህበረሰብ መሪዎች፣ ወጣቶችና ሴቶችን ሚና ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራት ይሰራሉ።

3. የአካል ጉዳተኞች፡ እኩልነትና አካታችነት

አካል-ጉዳተኝነት በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለ እውነታ ሲሆን ዘር፣ ቋንቋ፣ ብሄር፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜ ወ.ዘ.ተ የማይለይና ማንኛውንም ሰው ሊያጋጥም የሚችል ክስተት ነው። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2006 የፈረንጆች ዓመት የአካል-ጉዳተኞች መብት ስምምነት መሰረት አካል ጉዳተኝነት ማለት ረዘም ላለ ጊዜ የአካል፣ የአዕምሮ፣ የማስታወስ ወይም የስሜት ህዋሳት መዳከም ወይም መጎዳትን የሚያካትት ሲሆን ከሌሎች መሰናክሎች ጋር ተዳምሮ በማህበረሰቡ ውስጥ በሙሉና በብቃት እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ነው። ከዓለማችን ህዝብ መካከል ከቢሊዮን የሚበልጡ (15 በመቶ የሚጠጋው የዓለማችን ህዝብ) የአካል ጉዳተኛ መሆኑ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ወደ 80 በመቶ የሚሆኑት አነስተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ እንደሚገኙ እ.አ.አ በ2011 የተደረገ የዓለም ጤና ድርጅትና የዓለም ባንክ ጥናት ያሳያል።

ይሄው ጥናት እንደሚጠቁመው በአገራችን ኢትዮጵያ 17.6 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን ቢያንስ አንድ የአካል-ጉዳተኝነት መገለጫ ያለበት ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ወደ 2.5 ሚሊዮኑ ህፃናት ናቸው። አብዛኛዎቹም በገጠር የሚኖሩ ሲሆን ወደ 95 በመቶ የሚሆኑት ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል። ዋናው የአካል-ጉዳተኝነት ፈተና በቀጥታ ከጉዳቱ ጋር የተያያዘው እክል ሳይሆን እንደ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት፣ ሥራ፣ ማህበራዊና ህጋዊ የድጋፍ ስርዓቶች በእኩል ለማግኘትና ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች አለመኖራቸው ነው።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአካል ጉዳተኞች ዛሬም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ሲሆን በማህበረቡ ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ራሳቸውን ችለው በነፃነት እንዲኖሩ የሚደረገው ድጋፍ እጅግ አነስተኛ ነው። የአካል-ጉዳተኞች ላይ የሚደርስ መድሎና የመብት ጥሰት ከመቀነስ ይልቅ

እየጨመረ የሄደበትና ከእኩል ተጠቃሚነት መርህ ጋር የሚጋጩ ተግባራት አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ ሲፈፀሙ በሰፊው ይስተዋላሉ። በአይን ሊታዩ በማይችሉ ጉዳቶችም ጭምር (የአዕምሮና የውስጥ አካል ችግሮች) ተጠቂ የሆኑ ወገኖች ስራ ማግኘትና በስራ ላይ መቆየትም አዳጋች ሆኖባቸዋል። እንደ ትራንስፖርት፣ መንገድ እና መሰል የማህበራዊ አገልግሎቶችን ባግባቡ መጠቀም መቻል ዛሬም ለአካል ጉዳተኞች ፈተና ነው። ውሳኔ በሚሰጥባቸው መድረኮች ላይ የአካል ጉዳተኞች ውክልና እጅግ ዝቅተኛ ባስ ሲልም ምንም በሚባል ደረጃ በመሆኑ በችግሮቻቸው ለመወያትና የመፍትሄ አማራጭ ለማቅረብ ያላቸው ዕድል እጅግ የጠበበ ነው።

በሀገራችን ስለ አካል-ጉዳተኝነት በሰዎች ዘንድ ያለው መረጃና ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም የአካል ጉዳተኝነቱ በሴቶች ላይ ሲሆን ሴቶች በአገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ከመሆኑ አንጻር ችግሩን ይበልጥ ውስብስብ ያደርገዋል።

ቀደም ባሉት ዓመታት ኢትዮጵያ የተሻለ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች አስመዝግባለች ቢባልም በዚያው ልክ የአካል-ጉዳተኞች የተገለሉበት ወይም የተዘነጉበት ተጨባጭ ሁኔታዎች ታይተዋል። የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት ከመርህ ወይም ከህግና ከፖሊሲ ደረጃ የዘለለ አይደለም። በአንፃራዊነት የተሻለ ግንዛቤ ተፈጥሯል የሚባልባቸው ከተሞቻችንም ቢሆኑ ለአካል-ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ የላቸውም። ከዓለም የፖለቲካ ማዕከሎች አንዷ የሆነችው አዲስ አበባ የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ መዲናነቷን ያህል እንኳን፣ መንገዶቿ፣ ህንፃዎቿ፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋሞቿ ምን ያህል ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንደሚጎድላቸው ለማወቅ ብዙ ምርምርና ጥናት አይጠይቅም።

የስራ ዕድል በማግኘት ረገድ በተለይ በአሰሪዎች ዘንድ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በሚደረግ የማግለልና መድሎ ጫና ምክንያት በተቀጣሪ የአካል ጉዳተኞችና አካል ጉዳተኛ ባልሆኑት መካከል ያለው ከፍተት አልጠበበም። በዘመናችን እንደተከሰተው የኮሮና በሽታ አይነት በቤት መዋልን የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር ትርፋማ ያልሆኑ ድርጅቶች ደሞዝን ጥቅማጥቅሞችን ሲከፋም ሰራተኞችን በሚቀንሱበት ወቅት የአካል ጉዳተኞች ጫና እጅግ የተባባሰ ሆኗል። የአካል ጉዳተኞች እንዲደራጁ እና የብድር አገልግሎትና ድጋፍን በማግኘት የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ተሰማርተው ህይወታቸውን እንዲመሩ የሚያደርግ ተጨባጭ ተግባር ብዙም የለም።

የአካል-ጉዳተኞች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ማህበራዊ፣ አካላዊና የስነልቦና ጫናዎችን ይጋፈጣሉ። ይህንን አስከፊ የህይወት ጫና ለመቀየር የጉዳዩ ባለቤት እና ገፈት ቀማሽ የሆኑት ራሳቸው የአካል-ጉዳተኞች በነገአቸው ላይ መወሰን መቻል አለባቸው። በውሳኔ ሰጭነትና የአመራር ቦታ ላይ በመገኘት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለመስጠት ግንባር ቀደም ሚና ይጫወቱ ዘንድ የህግ ከለላ ይደረጋል። ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ሌሎችም የህግ-ድንጋጌዎች የአካል-ጉዳተኛ ዜጎችን አካላዊ እና የስነ-ልቦና ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ይከለሳሉ። በዚህም የአካል ጉዳተኞች የሙሉ ተሳታፊነት፣ ተካታችነት እና ተቀባይነት በህብረተሰባችን ውስጥ እንዲፈጠር ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ይሰራል።

ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተዘረዘሩትን እና ሌሎችንም ተግዳሮቶች በማጤን ከፍተኛ መድሎን፣ መገለልን ድህነትን፣ ጭፍን ጥላቻንና የመሳሰሉትን ፈተናዎች እየተጋፈጡ ላሉ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎቻችን ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በተጨባጭ የአካል-ጉዳተኞች ነፃነት፣ እኩልነት፣ ደህንነትንና ሰብአዊ ክብሮቻችው የተረጋገጡ ይሆን ዘንድ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮች ላይ በፅናት ይሰራል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የአካል ጉዳተኞችን እኩልነትና ተካታችነት በተግባር ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የፖሊሲ እና የህግ ማእቀፎች ያመቻቻል፤

➢ የህግ ማሻሻያን በተመለከተ

- አካታች የሆኑ የአካል ጉዳተኞች ህግጋት፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በአግባቡ በማውጣት ተግባራዊ ይደረጋል፣
- አካል ጉዳተኞች ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ማናቸውም ህግጋት እንዲገመገሙና ከዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት ህጎች ጋር በሚስማማ መልኩ እንዲቀረፁ ይደረጋል፣
- በመላው የአገራችን ክፍሎች ለህግ አስፈጻሚዎች በቂ ስልጠና እንዲሰጥ በማድረግ በአካል ጉዳተኞች ላይ መድሎና መገለል እንዳይፈጸም የሚያደርግ የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣
- በማህበራዊ ተቋማት ውስጥ እኩልነትንና አካታችነትን መሰረት ያደረገ ስርዓት በመዘርጋት

ሁሉም አሰሪዎችና አገልግሎች ሰጪ ተቋማት ተግባራዊ እንዲያደርጉት የሚያስገድድ አሰራር ይቀየሳል፣

➢ የአካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ እና ለማበረታታት የሚሰሩ ስራዎች

- የአካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ የስራ እድል እንዲያገኙ የህግ ማእቀፍ ያዘጋጃል (Afirmative action)፣ የከፋ የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ዜጎች ልዩ ድጎማ እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- ዘላቂነት ያለውን ድጋፍ በማድረግ በተለይም ውጤታማነታቸው በተረጋገጡ የስራ ፕሮግራሞች ላይ መስራትና የአካል ጉዳተኞች በምርጫቸው ይሰሩ ዘንድ እገዛ ይደረጋል።
- የአካል ጉዳተኞችን በተመጣጣኝ ዋጋ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ ግለሰቦችና ማህበራት በጉዳዩ ዙሪያ ከሚሰሩ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ እንዲገኝ ምቹ የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣
- የአካል ጉዳተኞችን አካታች የትምህርት ስርዓት በተጨባጭ እንዲኖር በማድረግ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ፍላጎት እንዲሟላ ይሰራል።
- የአካል ጉዳተኞች በሚዲያ፣ በባህል፣ በጥበብ ስራዎች፣ በስፖርትና በመሳሰሉት መድረኮችና እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉና ሚናቸውን እንዲጫወቱ ድጋፍ ይደረጋል፣
- የማህበራዊና ሰብአዊ መብቶችን ባገናዘበ መልኩ አሰሪዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገራዊ የስልጠና መለኪያ (National training standard) እንዲኖራቸው ይደረጋል።
- በአገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃ የአካል ጉዳተኞች እንዲሳተፉ በማድረግ እኩልነትና አካታችነትን ለማሳደግ ይሰራል።

4 የውሀ ሀብት ልማት

ምንም እንኳ ሀገራችን መጠነ ሰፊ የውሃ ሀብት ቢኖራትም ህዝቦቿ ግን በተገቢው ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም። ሀገሪቱ ያላት የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት ለተለያዩ ግልጋሎቶች ማለትም ለመጠጥ፣ ለመስኖ፣ ለሃይል ማመንጨት፣ ለአሳ ማስገር፣ ለቱሪስት መስህብ … ወዘተ መልማት ቢችልም ካለን እምቅ አቅም አንፃር መጠቀም የቻልነው በጣም ኢምንት ነው። በመሆኑም በሀገራችን ለዘመናት ሰፍኖ በቆየው የአስተዳደርና የማልማት ብቃት ማነስ ሳቢያ ህዝባችንን ተፈጥሮ ከለገሰችን ሀብት በሚገባ ተጠቃሚ ማድረግ አልቻልንም። ዛሬም ድረስ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ የህብረተሰባችን ክፍል በንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እጦት ሳቢያ ለበሽታ እና ለሞት እየተዳረገ ይገኛል። በርካታ ወንዞቻችን በህዝባችን መሃል እየፈሰሱ ሀገር አቋርጠው የሚወጡ ቢሆንም ግብርናችንን ከዝናብ ጠባቂነት ባለማላቀቃችን ህዝባችንን ከተረጂነት ማውጣት ተስኖናል።

በውሀ ሀብት ልማት ረገድ በየትኛውም ልኬት ስንመዘን በኋላቀርነት ተጠቃሽ ከሆነው ከሰሀራ በታች ካለው የአህጉራችን ክፍል አንፃር እንኳ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ስለመገኘታችን ዋቢ ሰነዶች ይመሰክራሉ። ይህም በከተማም ሆነ በገጠር ባለው የንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን ዝቅተኝነት በዋናነት ይገለፃል። የእውነቱን መራራነት የሚያጎላው ደግሞ ካለን ከፍተኛ እምቅ የውሀ ሀብት አንጻር መጠቀም የቻልነው ኢምንት መሆኑን ስንገነዘብ ነው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው በዓለማችን እየተከሰተ ያለው የአየር ንብረት ለውጥ ችግራችንን ጥልቅና ውስብስብ እያደረገው ይገኛል። ለዘመናት በዝናብ ውሀ ላይ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ጥገኛ የሆነው ግብርናችን እየተባባሰ ከመጣው የአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተዳምሮ አብዛኛውን ህዝባችን ለርሀብና ድርቅ እንዲሁም ምፅዋት ጠባቂነት ተጋላጭ አድርጎታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዘመናት የውሃ ልማት ዘገምተኛ ጉዞችን ትንሽ ፈቀቅ በማለት የአባይ ወንዝን ጨምሮ ሌሎች የውሀ ሀብቶቻችንን ለማልማት የተደረገው ጥረት ተስፋን የፈነጠቀ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ ፍሬውን ማየት አልተቻለም። የገነገነው የአስተዳደር ዘይቤ ድክመታችን ከፖሊሲ አቅጣጫ ውሱንነቶቻችን ጋር ተዳምሮ የተስፋ ሰጪ ጅማሮዎችን መቋጫ አሳሳቢ አድርጎታል። በአጠቃላይ ፈርጀ ብዙ ለሆኑት የውሀ ሀብት ልማት ችግሮቻችን ምንጭ ሳይንሳዊ እውቀትን መነሻ ያደረገና መሬት ላይ ያለውን እውነታ ያገናዘበ ፖሊሲ ማዘጋጀትና መተግበር አለመቻላችን መሆኑን በመገንዘብ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሚቀጥሉት አምስት አመታት የውሀ ሀብት ዘርፉን በላቀ ብቃት ለማልማትና የሀገራችንን ትንሳኤ እውን ለማድረግ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገባ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለይቷል።

የውሃ ልማት ዘርፍ ግብ

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የውሃ ሀብት ልማት ግብ የውሀ ሀብታችንን በብቃት በማልማት ህዝባችንን የሀብቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡

ዓላማዎች

- ያለንን እምቅ የውሀ ሀብትና ጠቀሜታ በጥናት መለየትና ማመላከት፣
- የውሀ ሀብት ልማታችንን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በሳይንሳዊ መንገድ በማጥናት መከላከል እና መቋቋም፣
- የተቀናጀ የውሀ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ፕሮግራም በማዘጋጀት እና ተግባራዊ በማድረግ የህዝባችንን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
- የውሀ ሀብት ልማታችን ብቁ፣ ፍትሃዊ እና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ፣
- የውሀ ሀብት ልማታችን አጠቃላይ የህዝባችን ኑሮ በማሻሻል እና የሀገራችንን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ የሚኖረውን ሚና በላቀ ደረጃ ማሳደግ፣
- በውሀ ሀብት ልማት ረገድ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ ሊኖረን የሚገባንን ሚና በአግባቡ በማጥናትና በመተንተን ተግባራዊ ማድረግ ፡፡

የትኩረት አቅጣጫዎች

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በውሀ ሀብት ልማት ረገድ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡-

ሀ. ቅንጅታዊ የውሀ ሀብት አጠቃቀም ስርዓትን ማስፈን

አንድ የውሀ ሀብት ለአንድ ወይም ለፈርጀ ብዙ የውሀ ግልጋሎቶች በአንድ ጊዜ ወይም በተለያየ ጊዜ ሊለማ ይችላል፡፡ በመሆኑም የውሀ ሀብት ልማት ዕቅዶች ቢያንስ ከሚከተሉት ጠቀሜታዎች አንፃር ተቀናጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

- ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት
- ለመስኖ ልማት
- ለዓሳ ሀብት ልማት
- ለቱሪዝም አገልግሎት
- ለሀይል ማመንጨት
- ለትራንስፖርት... ወዘተ

ከዚህም ባሻገር የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት ተመጋጋቢነት ያላቸው በመሆኑ በአንድ አካባቢ የሚደረግ የውሀ ሀብት የልማት እቅድ ይህን ታሳቢ በማድረግ እንዲለማ ይደረጋል፡፡

ለ. ፍትሃዊ የውሀ ሀብት አጠቃቀም ማስፈንን በተመለከተ

- ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገራችን ባለው የውሀ ሀብት ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል
- የአስተዳደር ወሰን ተሻጋሪ ወንዞችን በተመለከተ የሚከናወን ማንኛውም ዓይነት የውሀ ሀብት ልማት ዕቅድና ትግበራ የፌዴራል መንግስትን፣ የአዋሳኝ መስተዳደር አካላትን እና የልማት አካባቢ ማህበረሰብን ባሳተፈ መልኩ እንዲዘጋጁ፣ እንዲገመገሙ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
- ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችንን በተመለከተ ሀገራችን በሙሉ ዕውቀትና ያለማንም ተፅዕኖ በፈረመቻቸው ዓለም ዐቀፍ የውሀ ልማት ህጎች መሰረት በፍትሀዊነት እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ሐ. ሁነኛ (Optimal) የውሀ አጠቃቀም ማስፈንን በተመለከተ

የውሀ ሀብት ልማት ዕቅዶቻችን ሳይንሳዊ ዕውቀትን፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና የህብረተሰብ ተሳትፎን መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት የሚረዳ ቀጣይነት ባለው የመሻሻል መርህ የሚመራ የውሀ ሀብት ልማት ዘርፍ የጥናት፣ ምርምርና ስርፀትን የሚመራ ተቋም እንዲመሰረት ይደረጋል፡፡

መ. የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎን በተመለከተ

የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፡- በውሀ ሀብት ጥናትና ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውሀ ሀብት ልማት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት የሚለማበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ደረጃና ፍትሀዊነት የሚመሩበት ዝርዝር ህጎች ይዘጋጃሉ፡፡

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ፡- ዓለም አቀፍም ሆነ ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትርፍን መሰረት ባላደረጉ የውሃ ሀብት ጥናቶችና ልማቶች ላይ

ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል። ተግባራዊነቱ የሚመራበት ዝርዝር ህጎች ይዘጋጃሉ።

የምርምር ተቋማት ተሳትፎ፡- የመንግስትም ሆነ የግሉ ዘርፍ የጥናትና ምርምር ተቋማት በተግባራዊ የጥናትና የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ተግባራዊነቱም የሚመራበት ዝርዝር ህጎች ይዘጋጃሉ።

5 ለመኖሪያ እና ለስራ ምቹ አካባቢ፡ ቤቶች እና ከተማ ልማት

ነባራዊ ሁኔታ

በአገራችን የከተማነት ትርጓሜ መሰረት የህዝብ ብዛቱ ከ2,000 በላይ የሆነና ከነዋሪው ከ50 በመቶ በላይ የሆነው ከግብርና ውጭ ባሉ የኢኮኖሚ ሴክተሮች የተሰማራ ከሆነ ይህ ሠፈራ ከተማ ተብሎ ይጠራል። ምንም እንኳን መስፈርቱ ክፍተት ያለበት እና በቀጣይ መሻሻል እንዳለበት የምናምን ቢሆንም በዚህ መስፈርት መሠረት በአገራችን 950 ከተሞች እንደሚገኙ በ1999 የተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ግን ከ2,500 በላይ ከተሞች እንደሚገኙ የክልሎች መረጃ ያመላክታል።

በኢትዮጵያ የከተሞች ዕድገት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት እንደሚያሳየው በ2008 በኢትዮጵያ ከተሞች የሚኖረው የህዝብ ብዛት 18 ሚሊዮን ወይም ከ20 በመቶ የማይበልጥ ነው። ይህም ቁጥር ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ ነው። ተመሳሳይ የህዝብ ቁጥር ካላቸው አገሮች አንጻርም በአገራችን በከተማ የሚኖረው የህዝብ ብዛት እጅግ አነስተኛ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ፡ ፡ በሌላ በኩል የአለም ባንክ ባካሄደው የከተሜነት ዳሰሳ ጥናት መሠረት የከተሞቻችን የዕድገት ምጣኔ 5.4 በመቶ መሆኑን አመላክቷል። በመሆኑም ከፍተኛ የከተሜነት እድገት በመኖሩ ምክንያት እ.ኢ.አ በ2037 የከተማ ህዝብ ብዛት እስከ 42.3 ሚሊዮን ወይም 37 በመቶ ሊደርስ እንደሚችል ተገምቷል።

ከተሞቻችን በአብዛኛው የከተማ ፕላንን ተከትለው የተመሠረቱ ባለመሆናቸው ለመኖሪያነትና ለሥራ ምቹ ካለመሆናቸውም በላይ ነዋሪዎቹም ለበርካታ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲዳረጉ ይስተዋላል። የአለም ባንክ እ.ኤ.አ በ 2015 ያደረገው ጥናት በከተሞቻችን ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ህብረተሰብ ከ26 በመቶ በላይ መሆኑ፣ የሥራ አጥነት ከ16.4 በመቶ በላይ መሆኑ፣ ለአገር ውስጥ ምርት (GDP) ከተሞች ያላቸው ድርሻ በአማካይ ከ38 በመቶ የማይበልጥ መሆኑ፣ በከተሞች ያለው የመሠረተ-ልማት እና የአገልግሎት አቅርቦት ሽፋኑ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፣ የመሠረተ-ልማት ጥራት ስታንዳርዱም ዝቅተኛና በቅንጅት የማይቀርብ መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩንና የዜጎችም የዕርካታ ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል ።

በአገራችን ያለው የመኖሪያ ቤት ብዛትና ጥራት ሁኔታ ከጎረቤት አገሮች ጋር እንኳን ሲነጻጸር በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በአለም ባንክ ጥናት መሠረት ከ70-80 በመቶ የከተማ ነዋሪዎች በጣም በአረጁና ከደረጃ በታች በሆኑ ቤቶች (Slum) ውስጥ እንዲሁም 80 በመቶ ከእንጨትና በጭቃ ከተሰሩ ቤቶች ይኖራሉ። እነዚህ ቤቶች በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት ላይ ከተደረሰው መስፈርቶች አንጻር በቂ ቦታ የሌላቸው፣ የአገልግሎቶች (ውሃ፣ መጸዳጃ፣ ንጽህና . . . ወዘተ) ያልተሟላላቸውና የባለቤትነት ማረጋገጫ የሌላቸው ናቸው።

በአጠቃላይ የአገራችን ከተሞች ከፍተኛ ድህንትና ሥራ አጥነት የሚስተዋልባቸው፣ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት ዕጥረት ያለባቸው፣ የመሠረተ-ልማት እና የአገልግሎት አቅርቦቱ ከከተማው ህዝብ ፍላጎት አንጻር የማይመጣጠን የሆነባቸው፣ ከተሞች ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ሊጫወቱ ከሚገባቸው ሚና አንጻር ብዙ የሚቀራቸው፣ በአጠቃላይ ከተሞቻችን ለኑሮም ሆነ ለሥራ ምቹ ያልሆኑ፣ ለኢንቨስትመንት ሳቢ ያልሆኑና የሁሉንም ዜጎች ዕርካታ ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ክፍተት ያለባቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ከተሞቻችን ላሉብት ዝቅተኛ እና አሳዛኝ ደረጃ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ቢችልም ያለፉት መንግስታት ለከተማ ልማት ዘርፍ የሰጡት ዝቅተኛ ትኩረት ዋነኛው ነው። የከተማ እና ቤቶች ልማት እስከ 1997 ድረስ የሚመራበት የፖሊሲ አቅጣጫ ባለመኖሩ ከተሞች በዘፈቀደ ሲመሩ ቆይተዋል። "ገጠርን ማዕከል ያደረገ" የልማት ስትራቴጂ እንደሚከተል ይገልጽ የነበረው ገዥው ፓርቲ ከተሞችን ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ በድን እዲሆኑ አድርጓቸዋል። በከተሞች የመኖሪያ ቤት ችግር እንዲባባስ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል በዋናነት የነዋሪው የገቢ መጠን አነስተኛ መሆን፣ በቂ የመሬት አቅርቦት አለመኖር እና የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ተጠቃሾች ናቸው።

ዋና ዋና ተግዳሮቶች

በአገራችን ለከተማ ልማት ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሳ የነበረ በመሆኑ ከተሞች ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና ሊጫወቱ አልቻሉም። የከተሞችን ችግር ለመፍታት የተደረገው ጥረት አናሳ በመሆኑ የከተሞች ችግር ውስብስብ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል። በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1997 ዓ.ም የከተማ ልማት ፖሊሲ ተቀርጾ በመተግበር ላይ የሚገኝ ቢሆንም በወቅቱ ገዢው ፓርቲ ሲከተለው በነበረው ርዕዮተ ዓለም የተነሳ ፖሊሲው በርካታ ክፍተቶች ነበሩበት። ላለፉት በርካታ ዘመናት ከከተማ ልማት ሴክተር አንጻር የሚስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች፦

01. የከተማ ልማት ሴክተር ሌሎች ሴክተሮችን የሚያስተሳስር ሳይሆን እንደ አንድ የኢኮኖሚ ሴክተር ብቻ አድርጎ የመውሰድ የዕይታ ክፍተት የነበረበት መሆኑ፣
02. ከተማን-ከከተማ እና ከተማን-ከገጠር አስተሳስሮ መምራት ባለመቻሉ በከተሞች የሚታዩትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍታት አለመቻሉ፣
03. የከተማ እና የገጠር መሬቶች በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እንዲመሩ መደረጉ፣ የመሬት ሊዝ ሥርዓት እና አተገባበር የነዋሪውን እና የከተሞቹን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑ፣
04. ለከተሞችን የተለያዩ ፕላኖች የተዘጋጀ ቢሆንም በፕላን ለመምራት በቂ የማስፈጸም አቅም እና የተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ እንዲሁም የከተማ ፕላን እና የልማት ዕቅዶች ትስስር በጣም የላላ በመሆኑ ሴክተሩ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ ዋነኛ ሞተር አድርጎ መጠቀም እና የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ማድረግ አለመቻሉ፣
05. የቤት ችግርን መፍታት ባለመቻሉ፣ የመሠረተ-ልማት አቅርቦት፣ የንጽህና ጉድለት፣ የአረንጓዴ ልማት ውስንነት በስፋት የሚስተዋል በመሆኑ ከተሞች ለመኖሪያና ለሥራ ምቹ አለመሆን፣
06. የአገራችንን የከተማ ልማት ሥራዎች ከአህጉር እና አለም አቀፍ ፕሮግራሞች ጋር በማስተሳሰር የከተሞችን ዕድገት ለማፋጠን እየተደረገ ያለው ጥረት አጥጋቢ አለመሆን የሚስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

ከአቅርቦቱ ጎን ለጎን ለእንክብካቤና ጥገና ትኩረት መስጠት፣ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አቅርቦት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን በማድረግ ማሻሻል፣ የከተማ ልማትን ከአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ጋር በማቆራኘት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎትን ማዘመን ይገባል።

የከተማ ልማት ዕድገትን በእውቀት ለመምራት ብቃት ያለው አመራር እና ባለሙያ በየደረጃው ሊፈጠር ይገባል። የተደራጀ እና ወቅታዊ የከተማ የመረጃ ሥርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ ሊገነባ ይገባል። የመረጃ ሥርዓቱ የመሬት አጠቃቀም እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃ ጨምሮ ዘርፈ ብዙ የሆኑ መረጃዎችን በማካተት አገር አቀፍ ዕይታ ያለው እንዲሆን ይደረጋል። በተጨማሪም የከተሞችን ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ዕድገትን፣ የኑሮ ጥራት ደረጃን (Life Quality) እና የድህነት ቅነሳ ደረጃን መለካት የሚያስችል መሆን ይጠበቅበታል።

በመጨረሻም በአገራችን ከፍተኛ የከተሞች ዕድገት እየተስተዋለ በመሆኑ ምክንያት ተጨማሪ የቤት፣ የመሠረተ-ልማትና የአገልግሎት ፍላጎት እያደገ የመጣ መሆኑ፣ አብዛኞቹ ከተሞች በፕላን ያልተመሰረቱ እና ተገቢውን ትኩረትም ያላገኙ በመሆናቸው የተጠራቀመ መጠነ ሰፊ የፍላጎት ክፍተት ይስተዋላል። ሆኖም እስከ አሁን አገራችን ስትከተለው ከነበረው የከተማ ልማት ሂደት ለየት ያለ አቅጣጫ መከተል የሚጠይቅ በመሆኑ በአገራችን የሚታየውን ይህን ከፍተኛ የከተሞቻችንን ዕድገት ታሳቢ ያደረገ እና የቤት ችግርን ጨምሮ በከተሞች የሚስተዋሉትን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል የፖሊሲ አቅጣጫዎች መቅረጽ ያስፈልጋል።

ስለሆነም ተገቢ የሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የፌዴራል መንግስት፣ የክልል መንግስታት፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ የግሉ ዘርፍ እንዲሁም ባለሚና እና ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ በማድረግ ከሁሉም በላይ ደግሞ የከተማ ነዋሪውን በስፋት በማሳተፍ የከተሞቻችን እድገት በማፋጠን ነጻነትና እኩልነት የሰፈነባቸው ከተሞች ተፈጥረው ለማየት አስፈላጊውን ሁሉ መፈጸም ይገባል።

የትኩረት አቅጣጫዎች

ክፍል ሶስት

ጠቅላላ ጉዳዮች
(Cross cutting Issues)

1. አካባቢ ጥበቃ 86
2. ስርአተ-ጾታ 87

1. አካባቢ ጥበቃ

‹አካባቢ› በዙሪያችን የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የሆኑ ሀብቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሁሉ መሠረት ነው። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች በከፍተኛ ፍጥነት እየተመናመኑ ይገኛሉ። ከሀገራችን የቆዳ ስፋት 15.1% የሚታረስ መሬት ሲሆን በደን የተሸፈነው መሬት እ.አ.አ. በ2015 15.5% ነበር። ሀገራችን በአብዛኛው ተራራማ የሆነ የመሬት ክፍል እና በርከት ያሉ ትላልቅ ወንዞች እንዲሁም ልዩልዩ የውሃማ አካላት አሏት። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአብዛኛው የተመሰረተው የተፈጥሮ ሀብቶችን መረት የሚያደርግ የልማት እንቅስቃሴ ሲሆን ይህም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እና ለውጭ ገበያ ይውላል።

ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ አገራችን በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መፈረሟ የሚታወቅ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የተባበሩት መንግስታት የዘላቂ ልማት ግቦችን እና እ.አ.አ. በ1992 የጸደቀው የሪዮ የምድር ጉባኤ (Rio Earth Summit) ይገኙበታል። በሀገር ውስጥም የተለያዩ የአካባቢ ህጎች በማውጣትና ከዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ጋር በማዛመድ ለመተግበር ጥረቶች ቢደረጉም በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ውስብስብ የአካባቢ ችግሮችን ለመቅረፍም ሆነ በዓለም አቀፍ የአካባቢ ህጎችን ተግባራዊ ለማድረግ አልተቻለም።

የአካባቢ ሀብቶች እና ስርዓተ ምህዳሮች በሚሰጡት አገልግሎት አይነት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ። እነርሱም ምርት መስጠት (provisioning)፣ የተፈጥሮ ሚዛን መጠበቅ (regulating)፣ መስህብነት (cultural) እና ድጋፍ ሰጪ (supporting) ናቸው። ይህም ማለት በአካባቢያችን የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችንም ሆነ የኑሮ ደረጃን ከሚወስኑ ነገሮች ዋነኞቹ ናቸው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በሁሉም አቅጣጫ እና ቦታዎች ያሉ ስርዓተ ምህዳሮች እና የተፈጥሮ ሀብቶች ተገቢ በሆነ ሁኔታ በማይደረጉ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎች የተነሳ በከፍተኛ ጫና ውስጥ ይገኛሉ።

ለዚህ በዋናነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ በእቅድ እና በመሬት አጠቃቀም ፕላን ያልተመራ ግብርና ወደ ተፈጥሮ ደኖች እና ረግረጋማ ቦታዎች እንዲሁም ወደ ከፍተኛ ተራራማ ስፍራዎች መስፋፋት፣ የደን መጨፍጨፍ እና መራቆት፣ የወንዞች እና ሌሎች የውሀ አካሎች ከከተማ እና ከኢንዱስትሪ በሚመነጩና ከውጭ ሀገር በሚገቡ ኬሚካሎች እና አደገኛ ቆሻሻዎች መበከል፣ በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ ምርት እና ምርታማነት መቀነስ፣ የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት፣ የመጤ ወራሪ ዝርያዎች በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት እና ነባር የብዝሀ ህይወት ዝርያዎች መጉዳትና የስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች መመናመን ወይም መጥፋት፣ ዘላቂ የማምረት እና የመመገብ መርህ ላይ ያልተመሰረተ የአመራረትና የአመጋገብ ሥርዓት፣ እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ እና ልማት የሚሰሩ ግለሰቦች የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተቋማት በቅንጅት ያለመስራት ከብዙዎቹ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሁሉን አቀፍ እና ሳይንሳዊ የአካባቢ ፖሊሲ፣ የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልት እንዲሁም ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ስርዓት አለመኖር ለሀገራችን የአካባቢ ችግሮች ዋነኛ ምክንያት ናቸው ብሎ ያምናል። ይህ የፖሊሲ እና ስትራቴጂ ክፍተት የአካባቢ ብክለትና ብክነት፣ ፍትሃዊ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም አለመኖር የሀገራችን የተፈጥሮ ሀብት በፍጥነት እንዲመናመን እና እንዲጎሳቆል አድርጓል። ሃላፊነት የማይወስዱ የግልና የመንግስት የልማት ድርጅት በተፈጥሮ ሀብቶቻችን ላይ በሚያስከትሉት ችግር የአካባቢ የልማት እንቅስቃሴ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የህዝብ ቅሬታ እና ቁጣ በመቀስቀስ በበርካታ የሀገራችን ክልሎች ያለመረጋጋት መንስኤ ሆነዋል።

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የዜጎችን በንፁህ እና በጤናማ አካባቢ የመኖር መብት እንዲከበር የሚደነግጉ አንቀጾች ቢኖሩትም ዜጎች የዚህ መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ ግን አልቻሉም። የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች ተከትሎ እ.ኤ.አ. በ1997 የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ወጥቶ እየተሰራበት የቆየ ቢሆንም ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም። ፖሊሲውን ለማስፈጸም በፌዴራል እና በክልል የተቋቋሙ ተቋማት ከፍተኛ የግንዛቤና የአቅም ውስንነት ይታይባቸዋል።

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ሲተገበሩ የነበሩ ፖሊሲዎችን እና አሰራሮችን በመፈተሽ የአካባቢ ጉዳይ ከእያንዳንዱ

ዜጋ ጋር የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ የዜጎች በነፃነት እና በእኩልነት የአካባቢውን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ የግድ የሚልበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። ኢትዮጵያ ባሏት የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ የአካባቢ ሀብቶች በዘላቂ ልማት መርህ በየአካባቢው የሚገኘው ህብረተሰብ እና መላው የሀገራችን ህዝቦችን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል የአካባቢ ፖሊሲ እና የመተግበሪያ ስልት በመንደፍ እንዲሁም ጠንካራ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት ይደር የማይባል አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አካባቢን ለመጠበቅ የሚከተለው ፖሊሲ ዋና አላማ መላው የሀገራችን ህዝቦች ንፁህ እና ለኑሮ ተስማሚ በሆነ አካባቢ እንዲኖሩ፣ ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩ ዜጎች እንዲሁም ቀጣዩ ትውልድ ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ለዚህም

- የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ተፈጥሯዊ ሂደታቸውን እንዲቀጥሉ በማስቻል የብዝሀ ህይወት ሀብቶች እንዲጠበቁና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- የደን ሀብቶቻችንን ጨምሮ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሀብቶቻችን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተባበር፣
- የአካባቢ ብክለትና ብክነትን በመንግስት፣ በህብረተሰብ፣ በአልሚ ባለሀብቶች፣ በሲቭክ ማህበራትና በልማት አጋሮች የጋራ ተሳትፎ በኃላፊነት እንዲሰራ በማስተባበር እንዲወገድ ማስቻል፣
- የአደገኛ ኬሚካሎችና የኢንዱስትሪ ዝቃጮች አጠቃቀም፣ አወጋገድ፣ አያያዝና ዝውውር በሰው፣ በእንስሳት ብሎም በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ማስተዳደር፣
- የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የሚገኙበት አካባቢ ህብረተሰቡ ብሎም ሀገሪቱን ተጠቃሚ በሚያደርጉ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎትና የካርቦን ግብይት የክፍያ ስርዓት በመዘርጋት በሀገር አቀፍም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የግብይት ስርዓቶች ዜጎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የአካባቢ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች የሚሰጡት አገልግሎት በምጣኔ ሀብት ስሌት ዋጋው ተተምኖ የውሳኔ እና የልማት እቅድና ትግበራ ምንጭ እንዲሆኑ እና የተጠያቂነት ስርዓት ውስጥ እንዲገባ ማስቻል፣ ልማዳዊ አሰራሮችና በአካባቢ ጉዳይ የሚሰጡ የውሳኔ አሰጣጦችን በዘመናዊ አሰራር መተካት፣
- በተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና ልማት ላይ ህብረተሰቡን በእያንዳንዱ የውሳኔ አሰጣጥም ሆነ የልማት እቅድ እና ትግበራ በሁሉም ደረጃ ማሳተፍ፣
- የአካባቢ ተቆርቋሪዎች፣ የሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች የአካባቢ ባለድርሻ አካላት በእቅድ እና ትግበራ የማሳተፊያ አሰራሮችን በመዘርጋት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፣
- የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃ እና ልማትም ሆነ ሌሎች የልማት እቅዶችና ትግበራዎች በመሬት ሀብት አጠቃቀም ፕላን መሰረት እንዲሆን ማስቻል፣
- የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራችን ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ በጥናት እንዲለይ በማድረግ ሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ ትብብር ላይ በጎ አስተዋፅኦ ማበርከት ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል፡፡

2.ስርአተ-ጾታ

በዓለማችን በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ እንደተቀመጠው ኢትዮጵያ እንደሌሎች ሀገራት ሁሉ ግብ አምስት የሆነውን የስርዓት-ጾታ እኩልነት ከማረጋገጥ አንጻር የደረሰችበትን ደረጃ፣ ስኬት፣ ድክመትና፣ ተሞክሮ መሰረት ያደረገ የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል እንድሚያስፈልግ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል።

የስርዓት-ጾታ አለመመጣጠን በማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ መዋቅሮች ውስጥ ተንሰራፍቶ ያለ ችግር ነው። የስርአተ-ጾታ ጉዳይ እንደ ድህነት ቅነሳ እና የሰላምና የዲሞክራሲ ስርአት ማጎልበት ያሉ ግዙፍ ሀገራዊ አጀንዳዎች ጋር ተሰናስሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

የሀገራችን ሴቶች መሰረታዊ ችግሮች ዛሬም ድረስ ተቀርፈዋል ማለት አይቻልም። በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ግልጽ የሆነ የሴቶች ፖሊሲ ባይኖርም አንዳንዶች በግል ጥረታቸው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ሚና የነበራቸው በዚህ ጥረታቸውም ፓርላማ ድረስ የተወከሉ ጠንካራ ሴቶች ሆነዋል። ጥቂት ሴት ልሂቃን ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በመዝለቅ አንዳንዶቹ በወቅቱ የንጉሳዊ ስርአቱን በጽኑ

ይቃወም በነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ንቁ ተሳታፊ እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል።

በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ህዝባዊ አስተዳደር እና በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ከ1966-1983) ድረስ ጠንካራ የስርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ተግባራዊ ባለመሆኑ ሴቶችን በተመለከተ ይህ ነው የሚባል ለውጥ ሊመጣ አልቻለም። ምንም እንኳን በፖሊሲ ደረጃ ተጨባጭ ለውጥ ባይመጣም በዘመኑ በርካታ ዘመቻዎች ማለትም **'የራዛ ዘመቻ'፣ 'አረንጓዴ ዘመቻ'፣ 'የእድገት በህብረት የእውቀትና የትምህርት ዘመቻ'** ወዘተ ሴቶች ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ እነዚህ ዘመቻዎች ስርዓተ-ጾታ ስሱ ስለመሆናቸው በቂ ማስረጃ የለም።

በ1983 የተደረገውን የመንግስት ለውጥ ተከትሎ በ1985 በሽግግር መንግስቱ ወቅት ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ ተረቅቆ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ፖሊሲው ለቀጣይ 10 ዓመታት የሴቶች ጉዳይ በፌደራል እና በክልሎች ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። ይህን የማደራጀት ስራ በወቅቱ በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ስር የተደራጀው የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በኃላፊነት ሲያስተባብር የቆየ ሲሆን አላማው በየልማት ሴክተሩ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት እንዲኖር ማድረግ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በወቅቱ በአለም ባንክ ይደገፉ የነበሩ በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች የተተገበሩ ሲሆን፣ ፕሮጀክቶቹ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአመለካከት እና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። የሴቶች ጉዳይ በሂደት የበለጠ ትኩረት እያገኘ የመጣ ሲሆን የሴቶች ጉዳይ በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ እንዲቋቋም ተደርጓል። ሚንስትር መ/ቤቱ በ1998 የሴቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅ በማዘጋጀት ወደ ተግባር የገባ ሲሆን ይኸው ፓኬጅ በ2009 ተሻሽሎ እስከ አሁን በስራ ላይ ይገኛል።

እ.አ.አ. በ2014 በተሰራ የተ.መ.ድ. የልማት ፕሮግራም ጥናት መሰረት ከስርዓተ-ጾታ ግቦች አንጻር ኢትዮጵያ ከ187 ሀገራት 173ኛ ደረጃ የያዘች መሆኑን ሪፖርቱ ጠቅሷል። ይሄው ጥናት የስርዓተ-ጾታ ልዩነትን በ3 ደርዝ ለክቶ የሚያሳይ ሲሆን በእናቶች ላይ የሚስተዋለውን የስነ-ተዋልዶ ጤና፣ ሴቶች በአንጻራዊነት በፓርላማ ያላቸው መቀመጫ/ውክልና እንዲሁም ሴቶች በስራ ገበታ ላይ ያላቸው ተሳትፎ እንደ መለኪያ ተወስደዋል (UNDP, 2014)።

የኢትዮጵያ ሴቶችን አጠቃላይ ሁኔታ በተለይም ባለፉት 27 ዓመታት የተከናወኑ ስራዎችን ስናስተውል የሚከተሉትን መሰረታዊ ችግሮች እናገኛለን፣

- **ሴቶችን ከማብቃት ይልቅ የልማት መሳሪያ አድርጎ መውሰድ፡** በተለያየ ጊዜ ተግባራዊ የተደረጉ የመንግስት ፕሮግራሞች፣ ለምሳሌ የ2009 **'የሴቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅ'** የስርዓተ-ጾታ እኩልነትና ሴቶችን ማብቃት ላይ ከማተኮር ይልቅ ሴቶች ልማትን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ የልማት መሳሪያ አድርጎ ይመለከታል። ይህም በርካታ አስርተ-አመታት ያስቆጠረውንና ጊዜው ያለፈበትን **'ሴቶች በልማት ውስጥ'** /Women in Development' በሚል አስተሳሰብ የተቀረጸ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ አስተሳሰብ የሴቶችን ሁለንተናዊ አቅም ለመገንባት እና ሴቶችን በልማት ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ሴቶችን እንደ አንድ የልማት መሳሪያ የሚመለከት ጎዶሎ የልማት አቅጣጫ ሆኖ እናገኘዋለን።
- **ነጻ ማህበራትን ማሳደግ አለመቻል፡** የዚህ ችግር እንደ አብዛኞቹ ኢ-ዴሞክራሲያዊ እና አምባገነን መንግስታት ለገዢው ፓርቲ እና ላለው ስርዓት የቆሙ የሴቶች ማህበራት እንዲፈጠሩ አድርጓል። የዚህ አይነት ማህበራት ህልውና ለገዢው ፓርቲ ባላቸው ጥቅም እና አገልግሎት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የሀገራችንን ሴቶች ጥቅም እና መብት ሊያስከብሩ የሚችሉ ጠንካራ አቅም ያላቸው ማህበራት እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ እንቅፋት ፈጥሯል። በተለያዩ ጊዜአት ሴቶች ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲሟገቱ በርካታ ሀገር አቀፍ እቅዶች የተዘጋጁ ቢሆንም የሴቶችን መብት እና ማህበራዊ ጫና ለመቀነስ መሬት ላይ ጠብ ያለ ስራ አልተሰራም። በመሆኑም የሴቶች ጉዳይ ከፖለቲካ ፍጆታ እና ከሚዲያ ፍጆታ ሳያልፍ የኢትዮጵያ ሴቶች በገጠር እና በከተማ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫና ወገባቸው ጎብጦ ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

ከላይ በጥቂቱ የተጠቀሰውን የሀገራችን ሴቶች የመብት ጥያቄ እና የፖሊሲ ማእቀፍ ክፍተት ውስጥ በማስገባት **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከስርአተ ጾታ አንጻር ሰፊ የማሻሻያ ስራዎች እና የፖሊሲ አቅጣጫ የሚከተል ሲሆን ዓላማውም ፍትህ በነገሰበት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ስርዓት ውስጥ የሴቶችን ፍትሀዊ ተጠቃሚነት

ማረጋገጥ ነው፡፡ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተሉትን ግቦች ለማሳካት ይሰራል፡፡

- በዘላቂ ልማት ግብ 5 (SDG-5) መሰረት የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን እና የሴቶችን እና ልጃገረዶችን አቅም ማጎልበት፣
- ሴቶችን በማጎልበት ህገ-መንግስታዊ መብቶቻቸውን ማቀዳጀት፣
- ለስርዓተ-ጾታ ስሱ የሆነ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መስተጋብር መፍጠር፣
- የሴታዊነት ንቅናቄ በማድረግ የተዛቡ የስርዓተ-ጾታ ግንኙነቶችን ማስታረቅ

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከላይ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፣

አግባብ ያለው የስርዓተ-ጾታ ተቋማዊ ግንባታ

ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ እና ስያሜ (የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የወጣቶች የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር) ሲደራጅ የቆየው መንግስታዊ ተቋም የሴቶችን ተፈጥሯዊ እና ህገ መንግስታዊ መብት ማስከበር እና ፍትሀዊ ተጠቃሚ ማድረግ አልቻለም፡፡

ይህንን ታሳቢ በማድረግ በፌደራል እና በክልል የሚቋቋሙ ተቋማት **'የስርዓተ-ጾታ ሚኒስቴር' እና 'የስርዓተ-ጾታ ቢሮ'** በሚል ስያሜ እንዲደራጁ የሚደረግ ሲሆን ተቋማቱ ሴቶችን በተመለከተ ስር ነቀል የአስተሳሰብ እና የአሰራር ለውጥ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

ከዚሁ የአደረጃጀት ለውጥ ጋር በተያያዘ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሚቋቋሙት የስርዓተ-ጾታ ቢሮዎች በሙሉ በባለሙያዎች እንዲመሩ በማድረግ እስከ አሁን የነበረው ደካማ የፖለቲካ እና የፓርቲ አደረጃጀት ሙሉ ለሙሉ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ **'የስርዓተ-ጾታ'** ተቋማቱ የወንዶችን አጋርነት እና ተሳትፎ በማሳደግ በህብረተሰቡ ውስጥ ሴቶችን በተመለከተ ስር የሰደዱ ወግ እና ልማዶችን እንዲሁም የተሳሳቱ አመለካከቶችን በጋራ ለማስወገድ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ የመንግስት ተቋማት የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ይካሄዳል እንዲሁም የልማት እቅዶች ስርዓተ-ጾታ ስሱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደንብ እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡ የፍትህ ስርዓቱን (በተለይ ፍርድ ቤቶች) ስርዓተ-ጾታ ስሱ እንዲሆኑ፣ በስዓተ ጾታ ላይ የሚሰሩ ጠንካራ የሲቪክ ማህበራት እንዲፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በፐብሊክ ሰርቪስ ውስጥ ሴቶች ተፈጥሯዊ ግዴታዎቻቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ አገልግሎት ማግኘት ይችሉ ዘንድ **ሴቶች ወሊድ ላይ** በሚሆኑበት ወቅት እና በወር አበባ ጊዜያቸው በቂ የሆነ ከስራ ገበታ ላይ እረፍት የሚያገኙበት የፍቃድ አገልግሎት ይመቻቻል፡፡ በተመሳሳይ በቂ የአባትነት የስራ ፍቃድ /Paternity leave/ ተግባራዊ በማድረግ በሴቶች ላይ የተከመረው የወላጅነት ሸክም እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡

ክፍል አራት

የእቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶች እና መለኪያዎች

1 የማስፈጸሚያ ስልቶች እና መሳሪያዎች 91
2 የስኬት መለኪያዎች 92

1 የማስፈጸሚያ ስልቶች እና መሳሪያዎች

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በዚህ የምርጫ ማኒፌስቶ ያስቀመጣቸውን ግቦች ለመተግበር እና ለማሳካት ልዩ ልዩ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎችን ይጠቀማል። ፓርቲው በምርጫው በሚያገኘው ድምጽ ላይ ተመስርቶ በህዝብ ተወካዮች እና በክልል ምክር ቤቶች በሚኖረው የህግ አውጪነት አቅም እንዲሁም በተለያዩ የአስፈጻሚ አካላት ውስጥ በሚኖረው ተሳትፎ በዚህ ሰነድ የተቀመጡት እቅዶች፣ ግቦች እና ስትራቴጂዎች በክልሎች እና በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲካተቱ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን፣ አፈጻጸማቸውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ይከታተላል። ከዚህ ቀጥሎ ፓርቲው የሚጠቀምባቸው የእቅድ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች (instruments) ተመልክተዋል።

1.1 ጠንካራና ዘመናዊ የህዝብ አስተዳደር መገንባት

በህዝብ አገልግሎት ላይ የሚታየውን ስር የሰደደ ብልሹ አሰራር ከስር መሰረቱ በመቀየር ጠንካራና ዘመናዊ የህዝብ አስተዳደር በመገንባት እንዲሁም ከማንኛውም ወገንተኝነት የፀዳ፣ በሙያው እንዲሁም በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነ ሲቪል ሰርቫንት በማብቃት ግባችንን እናሳካለን። ከሚተገበሩ ዝርዝር ስራዎች በከፊል E-Governance፣ የፖለቲካና የህዝብ አስተዳደር (Public Adminstration) መለያየት፣ ሲቪል ሰርቫንቱን ጥሩ ተከፋይ በማድረግ የመንግስት የስራ ቅጥር ብቁ ባለሙያዎችን እንዲስብ ማድረግ ይገኙበታል።

1.2 እውነተኛ የህዝብ ተሳትፎ ማሳደግ

ህዝብ የሁሉም ነገር ባለቤት እንደመሆኑ በእቅድም፣ በትግበራም ይሁን በግምገማ ጊዜ ማህበረሰባችንና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ንቁና እውነተኛ ተሳትፎ በማሳደግ ግባችንን እናሳካለን። የህዝብን ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ ትኩረት ተሰጥቶ ከሚሰራባቸው ጉዳዮች ውስጥ የሲቪክ ማህበራትን፣ የማህበረሰብ አደረጃጀቶችን (እንደ እድር፣ እቁብ ...) እንዲሁም የሙያ ማህበራትን አቅም ማጎልበትና ተሳትፏቸውን ማሳደግ ተጠቃሽ ናቸው።

1.3 የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ መጨመር

ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገት የግሉ ዘርፍ ሚና ቀዳሚ ቦታ የሚሰጠው ነው። ነገር ግን የግሉ ዘርፍ በተለያዩ ማነቆዎች ምክኒያት ሚናው አነስተኛ እንደሆነ ይታወቃል፤ እነዚህን ማነቆዎች በማስወገድ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ብሎም በማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ተሳትፎውን በማሳደግ ግባችንን እናሳካለን።

1.4 የ ሀገር ውስጥ የገቢ ምንጭ አቅምን አሟጦ መጠቀም

ለልማትና ለተለያዩ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሀገር ውስጥ የገቢ ምንጭ አቅምን አሟጦ በመጠቀም የውጭ ብድርን እና የበጀት ጉድለት ፋይናንሲንግ በመቀነስና የሀብት አጠቃቀምን ውጤታማ በማድረግ ግባችንን እናሳካለን።
የሀገር ውስጥ የገቢ ምንጭን ከማሳደግ ጎን ለጎን የግብር ፍትሃዊነትና ታማኝነት ላይ ሰፊ ስራዎች ይሰራሉ። የባለቤትነት ስሜትን ከመፍጠር አንጻር ግብር ከፋዮች የከፈሉት ገንዘብ ምን ላይ እንደዋለ የሚያረጋግጡበት ስርዓት የሚዘረጋ ይሆናል።

1.5 የህግ ማእቀፎችን ማሻሻል

ማነቆ የሆኑ የህግ ማእቀፎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ በማሻሻልና አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ማእቀፎችን በማስተዋወቅ ምቹና ኢጋዥ ከባቢን በመፍጠር ግባችንን እናሳካለን።

1.6 ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

ስራዎችን ማስጀመር ብቻ ሳይሆን በቂ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ በማድረግ፣ ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት፣ የመረጃ አያያዝን በማሻሻል፣ እውቅና በመስጠትና አስፈላጊ እርምት በመውሰድ ግባችንን እናሳካለን።

1.7 ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን

ማህበረሰባችን የተሟላና ወቅታዊ መረጃዎች እንዲደርሱት በማድረግ በሁሉም ስራዎች ላይ ግልጽነት እንዲሁም ተጠያቂነትን በማስፈን ግባችንን እናሳካለን።

2 የስኬት መለኪያዎች

የስኬት መለኪያዎችና ፓርቲያችን በ 2025 ለማሳካት ያቀዳቸው ግቦች በሰንጠረዥ 2.1 በአሀዝ ቀርበዋል። እነዚህ የስኬት መለኪያዎች በዋናነት የኢኮኖሚ፣ ትምህርትና ጤና ዘርፍን ሁኔታና እድገት ማሳያዎች የተካተቱበት ሲሆን ፓርቲው ስልጣን ይዞ አገር ሲያስተዳድር በ 2025 (እ.ኤ.አ) ለማሣካት ያለማቸው ግቦች ከመነሻ አመት (base year) እና ከ 2030 ዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals) ጋር በንፅፅር ቀርቧል። የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት መጠን፣ ከ 5 አመት በታቸ ልጆች ሞት መጠን፣ የመጀመሪያ ትምህርት ተሳትፎ እና መሰል የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እድገት መለኪያዎች የ 2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተሰልተዋል። በስኬት መለኪያዎች ሂሣባዊ ስሌት ውስጥ አገሪቱ የምትገኝበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተጨባጮችና ተግዳሮቶች ከግምት ተወስደዋል። በተጨማሪም ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገሪቱ ላይ ያስከተለው እና በቀጣይ አመታት ሊያስከትል የሚችለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅእኖዎች ታሳቢ ተደርገዋል።

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ስኬትና አሁናዊ ደረጃ እንዲሁም ያላትን የማደግ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት እስከ 2025 ድረስ ያለው የኢትዮጵያ አመታዊ አማካይ የኢኮኖሚ እድገት 8.1 % እንደሚሆን ታቅዷል። ይህም ግምታዊ ስሌት ሀገሪቱ ባለፉት 10 አመታት ያስመዘገበችውን የ 9.62 % አመታዊ አማካይ የኢኮኖሚ እድገት፣ የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን (International Monetary Fund) ከ 2020 እስከ 2025 በኢትዮጳያ ይመዘገባል ብሎ የተነበየውን የ 6 % አማካይ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት፣ የ 2030 ዘላቂ የልማት ግቦች ውስጥ የተካተተው ታዳጊ ኢኮኖሚዎች እንዲያሳኩት የታለመው የ 7 % አማካይ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት እና የኮቪድ -19 ወረርሺኝ ያደረሰውንና በቀጣይ አመታት የሚያደርሰውን ተፅእኖ ታሳቢ አድርጓል። በግብርና ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና ኢኮኖሚውን ወደ ኢንዱስትሪ ማሸጋገር ተገቢ መሆኑ እሙን ነው። በመሆኑም የኢንዱስትሪ ሽግግርን ለማሣካት ለዘርፉ የሚሠጠው ትኩረት እንዲጨምር እና ዘርፉ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 2019 ላይ ካለው 24.8 % በ 2025 ወደ 35.3 % እንዲያድግ ይደረጋል። በሚደረጉት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባሮችና በሚፈፀሙ ስትራቴጂዎች የኑሮ ውድነትን አሁን ካለበት ሁኔታ በግማሽ ለመቀነስም ታቅዷል።

ፓርቲው ከሚከተለው ትምህርት-መር የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አንፃር ለትምህርት ዘርፍ እና የሠው ሃይል አቅም ግንባታ የሚሠጠው ትኩረት ላቅ ያለ እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም የትምህርት እና ጤና ዘርፎች ውስጥ የሚገኙትን ተግዳሮቶች ለማቃለል እና የታለሙትን የየዘርፉ የስኬት ግቦች ለመምታት ያስችል ዘንድ የትምህርት እና ጤና ዘርፍ ወጪዎችን ከአጠቃላይ የመንግስት ወጪዎች ውስጥ ያላቸው ድርሻ በየአመቱ እንዲጨምር ተደርጎ የ 2025 አሀዝ 2019 ላይ ከነበረበት በ 25 % እንዲያድግ ያደርጋል። ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከ 2030 የትምህርት ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ውስጥ በ 2030 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን ሙሉ በሙሉ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን እና ማንበብ እና መጻፍ የሚችል ዜጋ መጠንን 75 በመቶ በምናሳካበት መልኩ የ 2025 ግቦች ተቀምጠዋል። በተጨማሪም ከ 5 አመት በታች ልጆች ሞት መጠንን እና የአራስ ልጆች ሞት መጠንን ከ 2030 የጤና ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች አንፃር ሙሉ በሙሉ እንዲሁም የእናቶች ወሊድ ሞት መጠንን 75 በመቶ ስኬት የሚመዘገብ ሆኖ የ 2025 ግቦች ተቀምጠዋል።

ተ.ቁ	አመልካቾች	መለኪያዎች	መነሻ አመት፣ 2019	2025	ዘላቂ የልማት ግቦች ፣ 2030	አስተያየቶች
	ኢኮኖሚ					
1.	የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት መጠን	%	8.36	8.1	7	
2.	የነፍስ ወከፍ ገቢ	የአሜሪካ ዶላር	602.6	895.5		
3.	የግብርና ድርሻ	የመቶኛ ድርሻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት	33.5	27.1		የባለፉት 10 ዓመታት ለውጥን ከግምት በማስገባት
4.	የኢንዱስትሪ ድርሻ	የመቶኛ ድርሻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት	24.8	35.3		
5.	የአገልግሎት ድርሻ	የመቶኛ ድርሻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት	37.1	33		
6.	የሥራ አጥነት መጠን	%	2.082[1]	1.88	0	የባለፉት 10 ዓመታት ለውጥን ከግምት በማስገባት
7.	የዋጋ ግሽበት መጠን	%	15.84	7.92		በግማሽ እየቀነሰ
8.	ድህነት	በቀን ከ 1.90 ዶላር በታች በሆነ ገቢ የሚኖሩ ሰዎች መቶኛ	32.6[2]	10.87 (18.6)	0 (11.6)	ከዘላቂ ልማት ግብ 75 በመቶውን በ 2030 ለማሳካት
9.	ኢንቬስትመንት	ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የመቶኛ ድርሻ	35.2[*]	41.8		የባለፉት 10 ዓመታት ለውጥን ከግምት በማስገባት
10.	የወጪ ንግድ	በቢሊዮኖች የአሜሪካ ዶላር	2.666[*]	3.962		የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ትንበያን ከግምት በማስገባት
	ትምህርት					
11.	የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (ከ1-8 ክፍል) የተጣራ ምዝገባ መጠን	%	94.7[*]	97.6	100	
12.	የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (ከ 9-12 ክፍል) አጠቃላይ የምዝገባ መጠን	%	48.5[*]	76.6 (63)	100 (75)	ከዘላቂ ልማት ግብ 75 በመቶውን በ 2030 ለማሳካት
13.	ማንበብ እና መጻፍ የሚችል ዜጋ መጠን	%	51.8[3]	81.5 (66)	100 (75)	ከዘላቂ ልማት ግብ 75 በመቶውን በ 2030

14.	የተማሪ-መምህር ጥምርታ (የመጀመሪያ ደረጃ)	የተማሪ ብዛት በአንድ አስተማሪ	39*	31.2		የባለፉት 5 ዓመታት ለውጥ እና የታለመውን የትምህርት ወጪን ጭማሪ ከግምት በማስገባት
15.	የተማሪ-መምህር ጥምርታ (9-12 ክፍል)	የተማሪ ብዛት በአንድ አስተማሪ	22.5*	18		የባለፉት 5 ዓመታት ለውጥ እና የታለመውን የትምህርት ወጪን ጭማሪ ከግምት በማስገባት
16.	የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (ከ1-8 ክፍል)	በአንድ ክፍል የተማሪዎች ብዛት	53*	47.7		የባለፉት 5 ዓመታት ለውጥ እና የታለመውን የትምህርት ወጪን ጭማሪ ከግምት በማስገባት
17.	የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (ከ 9-12 ክፍል)	በአንድ ክፍል የተማሪዎች ብዛት	49.7*	42.25		የባለፉት 5 ዓመታት ለውጥ እና የታለመውን የትምህርት ወጪን ጭማሪ ከግምት በማስገባት
18.	በትምህርት ዘርፍ የመንግስት ወጪ	ከመንግስት ወጪ የመቶኛ ድርሻ	24.9*	31.125		
	ጤና					
19.	ከ 5 አመች በታች ልጆች ሞት መጠን	ቁጥር ከ 1000 ሰዎች	59	40	25	
20.	የአራስ ልጆች ሞት መጠን	ቁጥር ከ 1000 ሰዎች	33	22	12	
21.	የወሊድ ሞት መጠን	ቁጥር ከ 100,000 ሰዎች	401[4]	248	70	ከዘላቂ ልማት ግብ 75 በመቶውን በ 2030 ለማሳካት
22.	የሰዎች-ሆስፒታል አልጋዎች ጥምርታ	በአንድ አልጋ የሰዎች ብዛት	3150*	1733		የባለፉት 10 ዓመታት ለውጥን ከግምት በማስገባት
23.	የሰዎች-ሐኪም ጥምርታ	ለአንድ ሐኪም የሰዎች ብዛት	26635[5]	21308		የባለፉት 10 ዓመታት ለውጥን ከግምት በማስገባት
24.	ንጹህ የውሃ አቅርቦት	የውሃ አቅርቦት ያላቸው ሰዎች በመቶኛ	75.9*	89	100	
25.	በጤና ዘርፍ የመንግስት ወጪ	ከመንግስት ወጪ በመቶኛ ድርሻ	12[6]	15		

[1]የ 2020 አሀዝ፣ [2]የ 2015 አሀዝ፣ [3]የ 2017 አሀዝ፣ [4]የ 2017 አሀዝ፣ [5]የ 2010 የኢትዮጵያ በጀት አመት አሀዝ፣ [6]የ 2012 የኢትዮጵያ በጀት አመት አሀዝ፣ *የ 2011 የኢትዮጵያ በጀት አመት አሀዝ

ምንጭ፡

World Bank (2020), World Development Indicators; Imf (2020), World Economic Outlook; National Bank Of Ethiopia (2020), National Bank Annual Report (2018/2019); United Nations (2015), Transforming Our World: The 2030 Agenda for Sustainable Development; WHO (2020), World Health Statistics 2020 Monitoring Health for SDGs; Ethiopian Ministry of Health (2020), Annual Performance Report (2019/2020); UNESCO Institute For Statistics (2020)

“እኩልነት በተግባር”

ብዕርነ
ፅምረሙ

‹‹እኩልነት በተግባር!››

የማስፈጸሚያ ስልቶችና የፓርቲውን ፕሮግራም
ለማግኘት እንዲሁም ለተጨማሪ መረጃ
በዊብሳይት: www.fepethiopia.com
እና ስልክ ቁጥር; +251953440303
ላይ ያግኙን!